ማንኛውም የወንጀል ክስ ***ወንጀሉ በተፈፀመበት ኣካባቢ*** በሚገኘው የሥረነገር ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ቀርቦ እንደሚታይ የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ 99 ይደነግጋል፡፡ ለምሳሌ የወንጀሉ ዓይነት በወረዳ ወይም በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሚታይ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ የወረዳ ፍርድቤት የትም የሚገኝ ወረዳ ፍርድቤት ሳይሆን ነገሩ የተከሰተበት ወረዳ ዉስጥ የሚገኝ የወረዳ ፍርድቤት ብቻ ነዉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ወንጀሉ የተፈፀመበትና የወንጀሉ ወጤት የታየበት ኣከባቢ የተለያየ የሚሆንበት ኣጋጣሚ ሊኖር ይችላል፡፡ ይህም ማለት ወንጀሉ የተፈፀመው በኣንድ ወረዳ ወይም ዞን ሲሆን የወንጀሉ ውጤት የታየበት ደግሞ በሌላ ወረዳ ወይም ዞን ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ ሁለቱ ፍ/ቤቶች ማለትም ወንጀሉ በተፈፀመበት ኣከባቢ የሚገኝ የወረዳ ወይም የዞን (ከፍተኛ) ፍ/ቤት ወይም የወንጀሉ ውጤት በታየበት ኣካባቢ የሚገኝ የወረዳ /ዞን (ከፍተኛ) ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ አካባቢያዊ ስልጣን ኣላቸው ማለት ነው፡፡

ኣንዳንድ ተግባሮች ደግሞ ከወንጀል ስራዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት ምክንያት ወንጀል ይሆናሉ፡፡

***መለማመጃ* 14**

በደቡብ ወሎ ዞን በሚታይ የወንጀል ጉዳይ አንድን ሰዉ በሃሰት እንዲመሰክር ሌላዉ ሰዉ በሰሜን ሸዋ ዞን ዉስጥ አግባባዉ፡፡ በዚህ መሰረት በደቡብ ወሎ ዞን ፍርድቤት ቀርቦ እንደታቀደዉ የሃሰት ምስክርነት ሰጠ፡፡ ዐቃቤህግ ይህን የሃሰት ምስክር ተግባሩን እንዲፈጽም የገፋፋዉን ሰዉ በወ/ህ/ቁ/ 455 መሰረት ለመክሰስ ፈለገ፡፡

*ዐቃቤህጉ እርስዎ ቢሆኑ የትኛዉ ፍርድቤት ይከስሱታል? ትክክለኛዉን የፍርድቤት አድራሻ የሚያሳይ ክስ ያዘጋጁ፡፡ ዝርዝሩን እንደተመቸዎት ይገምቱ፡፡ ባለሥልጣኑን ፍርድቤት የመረጡበትን የሥነሥርዓት ህግ ምክንያት ይግለጹ፡፡*

እርስዎ የሰሜን ሸዋ ዞን ፍርድቤት ዳኛ እንደሆኑ ያስቡ፡፡ ዐቃቤህግ ክሱን እርሶ በሚያስችሉበት ፍርድቤት አቀረበዉ፡፡ ተከሳሽ ፍርድቤቱ ሥልጣን የለዉም የሚል ክርክር አቀረበ፡፡

*ባልደረባዎን እንደዐቃቤህግ አስተያየት እንዲያቀርብ አድርገዉ ብይን ይስጡ፣ ይጻፉት፡፡*

ክሱ የቀረበበት ፍርድቤት የደቡብ ወሎ ዞን ፍርድቤት ነዉ፡፡ ተከሳሹ ቀርቦ የመገፋፋት ወንጀሉ የተፈጸመዉ በሰሜን ሸዋ ዞን ስለሆነ ፍርድቤቱ ሥልጣን የለዉም የሚለዉን ክርክሩን አቀረበ፡፡

*ብይንዎ የተለየ ይሆናል?*

ቀጥሎ የሚነሳዉ ጉዳይ ደግሞ ወንጀሉ ከበርካታ ቦታዎች በየትኛዉ እንደተፈፀመ ለማወቅ የማይቻል ሲሆን፣ በበርካታ ቦታዎች የተፈጸመ ሲሆን ክስ መሰማት ያለበት የት ነው የሚለውን ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄም የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ. 102 ያስቀመጠው መፍትሄ አለ፡፡ በአንቀፁ እንደተመለከተው ወንጀሉ ከበርካታ ቦታዎች መካከል የት እንደተፈፀመ ለማወቅ የማይቻል ሲሆን፣ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ቦታዎች የተፈጸመ ሲሆን ክሱ ከነዚህ ቦታዎች በአንዱ ስፍራ በሚገኝ የሥረነገር ሥልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት ሊቀርብ ይችላል፡፡

ለምሳሌ ተከሳሹ በምስራቅ ሸዋ ዞን ሆኖ በምዕራብ ሸዋ ዞን ላለ ሰው የያዝከው ግመል የእኔ ነዉ በማለት የሐሰት ደብዳቤ ይፅፍለታል፡፡ ቀጥሎም ወደ ምዕራብ ሸዋ ዞን ሄዶ በማታለል ግመሉን ይረከባል፡፡ የሰራውም ወንጀል የወንጀል ሕግ ቁ 692ን ይጥሳል፡፡ ወንጀሉ ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን ኣንደኛው የሐሰት ደብዳቤ መፃፉ ሁለተኛው ደግም ግመሉን በዚሁ በማጭበርበሪያ ደብዳቤ መሰረት መረከቡ ናቸው፡፡ ደብዳቤው የተፃፈው በምስራቅ ሸዋ ዞን ስለሆነ ክሱ በምስራቅ ሸዋ ወይም በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊሰማ ይቻላል፡፡

በሌላ ምሳሌ ተከሳሹ ያለኣግባብ ኣንዱን ሰው በኣላማጣ ወረዳ ቢይዘውና መሆኒ ወረዳ ወደ ሚገኘው ፖሊስ ጣቢያ ቢወስደው የወንጀል ሕግ ቁ 584ን የመጣስ ወንጀል ስለሚሆንና ይህ ሰውየውን ከሕግ ዉጪ በግድ የመያዙ የወንጀል ስራ ያለማቋረጥ ስለቀጠለ ክሱ በኣላማጣ ወይም በመሆኒ ወረዳ ፍርድ ቤት ሊታይ ይችላል፡፡

በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 103 መሰረት ወንጀሉ የተፈፀመው ተጠርጣሪው በጉዞ ላይ ሳለ ቢሆን ተጠርጣሪው ወይም ወንጀሉ የተፈፀመበት ሰው ወይም ነገር በጉዞው በሚያልፍበት ስፍራ ውስጥ ክሱን ለመስማት የሥረነገር ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ክሱ ይታያል፡፡ ተጠርጣሪው ወንጀል የፈፀመበት ሰው ወይም ሌላ ነገር (ንብረት) በስፍራው ካለፈ ወንጀሉ በዛው ስፍራ ባይፈፀምም ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት በነገሩ ሊፈርድ ይችላል፡፡

**መለማመጃ 15**

በኢትዮ-ጂቡቲ የምድር ባቡር ተሳፍሮ ከጂቡቲ ወደኢትዮጵያ ይገባ የነበረን አንድ ሰዉ የኮንትራባንድ ዕቃችንን ጠቁመህ አስይዘሃል በሚል ምክንያት ሦስት ኮንትራባንድ ነጋዴዎች ባቡሩ በሶማሌ ክልል የሚገኘዉን የደወሌ የፍተሻ ጣቢያ አለፍ እንዳለ ይደበድቡት ጀመር፡፡ ድብደባዉ ለረዢም ደቂቃዎች ሲፈጸም ቆይቶ ተደብዳቢዉ ሲደክም ይቋረጣል፡፡ ከዚያም ባቡሩ ጉዞዉን ቀጥሎ ድሬዳዋ ቆሞ ፍተሻ ከተደረገና የሚሳፈረዉ ተሳፍሮ የሚጫነዉ ተጭኖ ጉዞዉ ቀጥሎ አዳማ ሊገባ ሲል ተደብዳቢዉ በደረሰበት ድብደባ ምክንያት ህይወቱ አለፈ፡፡

*- ዐቃቤህግ እንደሆኑ በማሰብ አድራሻዉን ለባለሥልጣኑ ፍርድቤት በማድረግ ክስዎን ያዘጋጁ፤ አንዳንድ ዝርዝር ሁኔታዎችን በራስዎ መገመት ይችላሉ*

………

በድሬዳዋ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድቤት ዳኛ እንደሆኑ ያስቡ፡፡ ዐቃቤህግ ይህን ክስ በርስዎ ችሎት አቀረበዉ፡፡

*ክሱን ያስተናግዳሉ ወይስ ሥልጣን የለኝም ብለዉ ያሰናብቱታል?*

*ዳኝነትዎ በሶማሌ ክልል ወይም በኦሮሚያ ክልል እንደሆነ አስበዉ ክሱ ቢቀርብልዎ ምን እንደሚዉስኑ ይግለጹ፣ ይጻፉት*

*አዲስ አበባ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድቤት ዳኝነት በተቀመጡበት ይህ ክስ ቢቀርብልዎ ምን ይወስናሉ? ክሱን ያያሉ ወይስ ያሰናብቱታል?*

***ከዚህ በላይ ላሉት ዉሳኔዎችዎ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 99-107፣ የፌዴራል ፍርድቤቶች አዋጅ ቁ 25/1988 ቁ 4/11/፣ የወ/ህ/ቁ 25/2/የሚደነግጉትን ይመርምሩ፡፡

**አንድ ወንጀል ከኢትዮጵያ ግዛት ውጭ በኢትዮጵያ መርከብ ላይ ወይም ኤሮፕላን ውስጥ ቢፈፀም ኢትዮጵያ ውስጥ እንደተፈፀመ ይቆጠራል (የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ ቁ.104)፡፡ ይህ ቁጥር ክሱ በየትኛው የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት መታየት እንደሚገባው አይገልፅም፡፡**

***መለማመጃ 16***

*ከአዲስ አበባ ተነስቶ ወደኻርቱም ይበር በነበረ የኢትዮጵያ አየር መንገድ አዉሮፕላን ዉስጥ ተሳፋሪ ከነበሩት አንዱ ሌላዉን ተሳፋሪ አዉሮፕላኑ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ክልል ላይ በመብረር ላይ በነበረበት ጊዜ በፈጠሩት አለመግባባት ሲደባደቡ በቡጢ ጆሮግንዱ ላይ ስለመታዉ ወዲያዉ ህይወቱ አለፈ፡፡ ገዳዩ በአዉሮፕላኑ የደኅንነት ሠራተኞች ተይዞ ወደኢትዮጵያ እንዲመለስ ከተደረገ በኋላ የወንጀል ምርመራ ተደርጎበት ዉጤቱ ለአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ ተልኮ የተራ ነፍስ ግድያ ወንጀል ክስ ተመሰረተ፡፡ ተከሳሹም ክሱን ከሰማ በኋላ ይህ ፍርድቤት በዚህ ጉዳይ ላይ ሥልጣን የለዉም በማለት ተቃወመ፡፡*

*ዐቃቤህግ ቢሆኑ ለዚህ መቃወሚያ ምን ክርክር ያቀርባሉ? ይጻፉት*

*ዳኛዉ እርስዎ እንደሆኑ በማሰብ ከባልደረባዎ የዐቃቤህግ ሃሳብ ይቀበሉና በመቃወሚያዉ ላይ ይወስኑ፣ ይጻፉት*

**ከአካባቢያዊ ስልጣን ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ሌላ ነገር አንድ ክስ ካንድ ነገሩን ለማየት ስልጣን ካለው ፍርድ ቤት ወደ ሌላው ፍርድ ቤት የመዛወሩ ጉዳይ ነው፡፡**

***መለማመጃ* 17**

***በአንድ የክልል ጠቅላይ ፍርድቤት በመታየት ላይ ባለ የብሄረሰብ ግጭት ጋር የተያያዘ ወንጀል ጉዳይ ተከሳሹ ዳኞቹ ጉዳት ደረሰበት የተባለዉ ብሄረሰብ አባላት ስለሆኑ ነጻ የሆነ ዳኝነት ስለማላገኝ ጉዳዩ በሌላ ክልል ጠቅላይ ፍርድቤት ወይም በፌዴራል ከፍተኛ ወይም ጠቅላይ ፍርድቤት ይታይልኝ ሲል ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤት አመለከተ፡፡***

*እርስዎ በዚህ ጠቅላይ ፍርድቤት ዳኛ እንደሆኑ በማሰብ ለዚህ ማመልከቻ የሚሰጡትን ዉሳኔ ይጻፉ*

***ጉዳዩ የሃሰት ገንዘብ ማዘዋወርን ወንጀል የሚመለከት በመሆኑ ጉዳዩ በክልል ከፍተኛ ፍርድቤት በመታየት ላይ እያለ ተከሳሹ ዳኞቹ ጉዳዩ ከመወሰኑ በፊት በችሎት ላይ ከተማችንን የወንበዴ ጎሬ አደረግከዉ ብለዉ በችሎት የተናገሩኝ በመሆኑ ነጻ ዳኝነት እንደማላገኝ ማስረጃ ነዉ፣ ለዚህም ምስክሮች አሉኝ በማለት ዘርዝሮ ጉዳዩ በሌላ ሥልጣን ባለዉ ፍርድቤት ወይም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድቤት እንዲታይለት ማመልከቻዉን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድቤት አቀረበ፡፡***

*ማመልከቻዉ የቀረበለት ዳኛ እርስዎ እንደሆኑ ያስቡና በማመልከቻዉ ላይ ይወስኑ፣ ይጻፉትም*

******* ***ለዉሳኔዎ እንዲረዳዎ ህገመንግሥት ቁ*** 78/2/፣ 80፣ ***የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ*** 106፣ ***የፌዴራል ፍርድቤቶች አዋጅ ቁ*** 25/1988 ***ከቁ*** 8-15 /***በአዋጅ ቁ*** 138/1991 ***እና*** 321/1995 ***እንደተሻሻለ/ የሚደነግጉትን ይመርምሩ***

*የሚመለከተው ፍርድ ቤት ኣንድ ክስ ከአንድ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ ለማስተላለፍ የቀረበለትን ማመልከቻ የሚቀበልበት ኣራት ሁኔታዎች እንዳሉ ቁጥር* 106 *ያመለክታል፡፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡፡*

***ሀ) የበታች ፍርድ ቤት በልዩ ልዩ ምክንያቶች ኣድልዎ የሌለበት ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት እንደማይችል ግልፅ ሲሆን ፣***

***ለ) ክሱ በጣም ኣስቸጋሪና ከባድ የሆነ ለውሳኔ የሚያዳግት የሕግ ጉዳይ ሲኖርበት ፣***

***ሐ) የክሱ መዛወር ለባለጉዳዮችና ለምስክሮች በቦታው ቅርበትም ሆነ በሌላ ምክንያት ምቹ ወይም ተፈላጊ ሲሆን ፣ እና***

***መ) በአጭር ጊዜ ትክክለኛ ፍርድ የሚገኘው በክሱ መዛወር ብቻ ሲሆን ወይም የክሱ መዛወር በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ- ስርዓት የተፈቀደ ሲሆን ነው፡፡***

ምሳሌ 1፡- በአንድ ስፍራ ኣንድ ጢሪ የሌላቸዉ የ70 ዓመት ኣዛውንት (ሽማግሌ) ከኣከባቢው ነዋሪ ህዝብ በእርዳታ ያገኙትን እህል ሰርቀሃል ተብሎ የተከሰሰ ሰው ስርቆቱ በተፈፀመበት ቀን በሌላ ቦታ ነበርኩ ፤ ነገር ግን የአከባቢው ህዝብ በሽማግሌው መሰረቅ በጣም ስለተቆጣ በሌላ ቦታ እንደነበርኩ የሚያውቁልኝ ምስክሮች የማስፈራሪያ መልእክት ስለደረሳቸው እዚህ ሊመሰክሩልኝ ኣይችሉምና ወደ ሌላ ፍርድ ቤት ይዛወርልኝ ሲል ለዞን ፍርድ ቤት ቢያመለክት ፍርድ ቤቱ ምክንያቱን ከተቀበለ ነገሩን ለማየት የሥረነገር ሥልጣን ወዳለዉ ወደ ሌላ ፍርድ ቤት ሊያዛውርለት ይችላል፡፡ ከዚህም ሌላ ራሱ የዞን ፍርድቤቱ ምንም እንኳ ነገሩን የማየት የሥረነገር ሥልጣን ባይኖረዉም ነገሩን ወደራሱ አዛዉሮ ሊያየዉ ይችላል፡፡

ምሳሌ 2፡- አንድ ሰው የወንጀል ሕግ ዓንቀፅ 644 በመተላለፍ ለአካለመጠን ያልደረሱ ልጆችን የግብረ ስጋ ተፈጥሮአዊ ዝንባሌ ከልክ በላይ የሚቀሰቅሱ፤ የሚያበላሹ ወይም የሚያነሳሱ ፅሑሮችን ኣሳይቷል ተብሎ ቢከሰስ ፤ የዚህ ዓይነት ክስ የሚታየው በወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ተከሳሹ ለህዝብ ያሳየሁት ፅሑፍ በዓንቀፅ 644 ኣተረጓጎም "የግብረ ስጋ የተፈጥሮአዊ ዝንባሌ ከመጠን በላይ አላነሳሳም" ብሎ ቢከራከር "የግብረ ስጋ ተፈጥሮአዊ ዝንባሌ ከመጠን በላይ ማነሳሳት" የሚለው ከባድ የሆነ የሕግ ክርክር ለመፍጠር ስለሚችል ተከሳሹ ቢያመለክት የዞን ፍርድ ቤት ክሱን ራሱ ለማየት ሊወስን ይችላል፡፡

ክሱ ሥልጣን ባለዉ ፍርድቤት ከቀረበ ወይም በተገቢዉ ሁኔታ ወደሌላ ፍርድቤት ከተዛወረ በኂላ ክሱን ለመስማት የሚያስችሉ ርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡

# 2 ምዕራፍ ሁለት

## ክስ ስለመስማት

የክስ ማመልከቻ የቀረበለት ፍርድቤት ነገሩን ለመዳኘት ሥልጣን እንዳለዉ ከወሰነ ወደክስ መስማት ይገባል፡፡ ይህ ሂደት የተከሰሰዉ ሰዉ አጥፊነት ወይም ንጽህና የሚወሰንበትን ዋናዉ የጠቅላላዉ ሂደት ደረጃ ስለሆነ የሚመለከታቸዉ ባለሙያዎች በዚህ ጊዜ የሚያከናዉኗቸዉ ተግባራት ከፍተኛ ጥንቃቄን እንደሚጠይቅ አይካድም፡፡ ይህን ሂደት ለማከናወን ደግሞ ፍርድቤቱ ተከራካሪዎችንና ምስክሮቻቸዉን በግንባር ማግኘት ይኖርበታል፡፡ ይህን የሚያስፈጽምባቸዉ ህግጋት ተደንግገዉ ይገኛሉ፡፡

ባለጉዳዮች ከቀረቡ በኂላም የክስ መስማቱ ሂደት እንዴት እንደሚከናወን የሚመሩት የሥነሥርዓት ህግጋት እንዲሁ ተደንግገዉ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የግራቀኙን መብቶችና ጥቅሞች ለማመዛዘን ወይም ለማቻቻል በሚያስችል ሁኔታ የተደነገጉ ስለሆነ ይህ እንዴት እንደሆነ መመርመርና ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ ከባለሙያዎች የሚጠበቅ ነዉ፡፡ ለዚህም ይህ የሥልጠናዉ ክፍል ለሠልጣኞች ቀርቧል፡፡ ስለዚህ በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ሠልጣኞች

- የክስ መሰማት ሂደትን የሚገዙትን ህግጋት ይተነትናሉ
- ህግጋቱ በአተገባበር ጊዜ የሚያስነሱትን ችግር ይመረምራሉ
- እነዚህን ችግሮች ማስወገድ የሚያስችል አሰራር መለማመድ እንዲችሉ የተለያዩ ጭብጦች ላይ ክርክሮች ያቀርባሉ፣ ዉሳኔ ይሰጣሉ

## 2.1 <u>ክስ ለመስማት የሚደረጉ ዝግጅቶች</u>

### 2.1.1 <u>ቀን መቁረጥና ተከራካሪዎችን ከነምስክሮቻቸዉ ስለመጥራት</u>

ፍርድቤቱ ክስ ከቀረበለት በኋላ ነገሩን ለማየት ሥልጣን ያለዉ ከሆነ ክሱን የሚሰማበትን ቀን በመወሰን ለመዝገቡ ቀጠሮ ይሰጠዋል፡፡ በዚህ ቀን ተከሳሽ ክሱን ለመከላከል እንዲችል መቅረብ ስላለበት /የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 127/ እንዲቀርብና መልስ እንዲሰጥ መጥሪያ ይላክለታል፡፡ ከዚህ መጥሪ ጋር ተያይዞም የክሱ ቅጂ ከነሰነድ ማስረጃዉ ይላክለታል፡፡ ዓቃቤ ሕጉም ክሱን ለመስማት በተቀጠረበት ቀን እንዲቀርብ መጥሪያ ይላክለታል፡፡ ክሱ የሚሰማበት ቀን ለመወሰን ሌላ ቀጠሮ ሳያስፈልገው ፋይሉ እንደተከፈተና ፍርድቤቱ ሥልጣን እንዳለዉ እንዳረጋገጠ ወድያው ቀነ ቀጠሮ ተለይቶ ሊቀመጥ ይገባል፡፡ ፍርድ ቤቱ ክሱ የሚሰማበትን ቀን ሲወስን እንዲሁ በግምት ሳይሆን ተከሳሹ የሚገኝበት ቦታ ቅርበትና ርቀት፣ ምስክሮች የሚገኙበትና ለመቅረብ የሚወስድባቸው ጊዜ፣ የፍርድ ቤቱ የመዝገብ ብዛት ወዘተ ግምት ውስጥ በማስገባት መሆን አለበት፡፡ የቀጠሮ ቀን ስለመወሰንና ስለመጥሪያ አላላክ የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.123 ይመለከቷል፡፡

ከዚህ የተለየ የሚሆነዉ በአሁኑ ጊዜ አር. ቲ. ዲ. በተባለዉ አሰራር መሰረት የሚካሄደዉ የክስ መስማት ሂደት ነዉ፡፡ በዚህ አሰራር መሰረት ተከሳሹና ዐቃቤህግ ከዐቃቤህግ ምስክሮች ጋር ክሱ ሲቀርብ አብረዉ ይቀርባሉ፡፡ ስለዚህ ቀጠሮ መስጠት ሳያስፈልግ ክሱ መሰማቱ ይጀምራል፡፡ ምናልባት ነገሩ ቀጠሮ የሚሰጠዉ ተከሳሽ እንዲከላከል ተወስኖ መከላከያ ማስረጃዉን ለማቅረብ ጊዜ ሲያስፈልገዉ ነዉ፡፡

ክሱ የሚሰማበት ቀን እንደተወሰነ ሌላ መደረግ ያለበት ዓ/ሕጉና ተከሳሹ የምስክሮቻቸውን ዝርዝር ለፍርድ ቤቱ ሬጂስትራር ማቅረብ ነው (የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.124)፡፡ የማስረጃው ዓይነት የክሱ ፍሬ ነገር በቀጥታ ሆነ ቀጥታ ባልሆነ መንገድ የሚያውቁ ምስክሮች እና/ ወይም ልዩ እውቀት ያላቸው ሰዎች (ኤክስፐርቶች) ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ምስክሮች ነገሩ በሚሰማበት ቀን ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን መስጠት እንዲችሉ በፍርድ ቤቱ ሬጂስትራር በኩል መጥሪያ ይላክላቸዋል፡፡

የተለመደዉ አሰራር ክሱ የሚሰማበት ቀን ሲቆረጥ ዐቃቤህግና ተከሳሽ እንዲቀርቡ መጥሪያ መላክ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ደግሞ በአንዳንድ ፍርድቤቶች ግራ ቀኙ ምስክሮቻቸዉን ይዘዉ እንዲቀርቡ ይታዘዛል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ተፈላጊ ሰዎች ተሟልተዉ ላይቀርቡ ስለሚችሉ ምስክሮች ቀርበዉ ተከሳሽ ባይቀርብ ምስክሮች ሊጉላሉ ነዉ፡፡ የተከሳሽ ምስክሮች ቀርበዉ የዐቃቤህግ ምስክሮች ባይቀርቡ ዐቃቤህግ ማስረጃዉን ሳያቀርብ ተከሳሽ ሊያቀርብ ስለማይገባ የተከሳሽ ምስክሮች አላግባብ ሊደክሙ ነዉ፡፡ ስለዚህ ክሱ የሚሰማበት ቀን ከተቆረጠ በኋላ ስለተፈላጊ ሰዎች አቀራረብ የሚሰጠዉ ትዕዛዝ ለዚህ ችግር መፍትሄ የሚሰጥ ሊሆን ይገባል፡፡

**መለማመጃ 18**

*በርስዎ ችሎት አንድ የወንጀል ክስ ቀረበ፡፡ በማመልከቻዉ መጨረሻ ላይ ተከሳሹ በማረፊያቤት ይገኛል የሚል ማስታወሻ ይገኛል፡፡ የምስክሮች ዝርዝር ከማመልከቻዉ ጋር ተያይዟል፡፡ ክሱን አንብበዉ ፍርድቤቱ ሥልጣን እንዳለዉ አረጋገጡ፡፡ ከዚያ በኋላ ጉዳዩን ለመስማት ቀን ወስነዉ በአጀንዳዎ ላይ መዘገቡት፡፡ በዚህ ቀን ነገሩን ለመስማት የሚያስችሉትን አስፈላጊ ትዕዛዞች ሁሉ በሥነሥርዓት ህጉ መሰረት ይስጡ፡፡*

*በዚህ ረገድ የምስክሮችን አቀራረብ በተመለከተ የሚሰጡት ትዕዛዝ ምን ይመስላል? ይጻፉት*

*ይህ የርስዎ ትዕዛዝ ምስክሮችን ሁሉ በቀረቡበት ቀን ሰምቶ ከማሰናበት አስፈላጊነት አኳያ ምን ያህል የሚያዋጣ ወይም ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ትዕዛዝ ነዉ ይላሉ?*

*ተከሳሹ በዋስ ያለ ቢሆን የሚሰጡት ትዕዛዝ የተለየ ሊሆን ይችላል? ምክንያትዎን ይዘርዝሩ*

## 2.1.2 ክስን ለተከሳሽ ስለማድረስ

ፍርድ ቤት የቀረበለትን ክስ ለማየት ስልጣን ያለው መሆኑን ያረጋገጠ እንደሆነ የክሱ ግልባጭ ክሱ ከሚሰማበት ቀን በእጅጉ ቀደም ብሎ እንዲደርሰዉ ለተከሳሹ ሊልክለት እንደሚገባም የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.109 (4) እና 94/2/ሰ/ ይደነግጋሉ፡፡ ይህ የክስ ግልባጭ የማግኘት መብት በኤፌዴሪ ሕገ መንግስት እውቅና አግኝቷል፡፡ ይህ ድንጋጌ በሕገ መንግስቱ ዓንቀፅ 20 (2) የተመለከተ ሲሆን፤ የተከሰሱ ሰዎች ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገራቸው እና ክሱን በፅሑፍ የማግኘት መብት እንዳላቸው በግልፅ ሁኔታ ተቀምጧል፡፡ ከሕገ መንግስቱ ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለው የተከሰሱ ሰዎች የክሱ ግልባጭ (በፅሑፍ) ሊደርሳቸው ይገባል ብቻ ሳይሆን የክሱ ማመልከቻ በበቂ ሁኔታ ዝርዝር ነገሮችን መያዝ እንዳለበትና ተከሳሾች የተከሰሱበት ጉዳይ በሚገባ እንዲረዱ የሚያስችላቸው መሆን እንደአለበት ነው፡፡

ክስ ከማድረስ ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚገባዉ ተግባር ማስረጃን የማግኘትና የማየት መብትን የሚመለከት ነዉ፡፡ በተለይም ይህ ማስረጃን የማየት ወይም የማግኘት መብት ተፈጻሚ የሚሆነዉ መቼ ነዉ የሚለዉ ጭብጥ ትኩረት የሚሻ ነዉ፡፡

**መለማመጃ 19**

ለችሎትዎ የቀረበዉ ክስ በማስረጃ ዝርዝሩ ዉስጥ የተለያዩ ሰነዶች ተጠቅሰዋል፡፡ ሆኖም የተያያዘ ሰነድ የለም፣ ሰነዶቹ ካሉበት ቦታ እንዲቀርቡ የሚጠይቅም ማመልከቻ ተያይዞ አልቀረበም፡፡

*ስለክሱ አደራረስ የሚሰጡትን ትዕዛዝ ይጻፉ፡፡*

ለተከሳሽ የክስ ማመልከቻዉ ቅጂ ከቀጠሮዉ ቀን እጅግ ቀደም ብሎ እንዲደርሰዉ ሲላክለት ከምን ጋር እንደሚላክለት በሥነሥርዓት ህጉ የተደነገገ ነገር የለም፡፡ የዚህ አይነት ሥነሥርዓት ምናልባት በሙስና ወንጀሎች ሥነሥርዓት ህግ መሰረት የቅድመክስ ሂደት የሚከናወን ከሆነ ዐቃቤህግ መግለጫ ሲሰጥ አብሮ ማስረጃዎቹን አያይዞ እንዲሰጥ በሚደረግበት አጋጣሚ ጊዜ ሊያጋጥም ይችላል፡፡ ቀደም ሲል በነበረዉ የፍርድቤቶች አሰራር ልማድ መሰረት የክስ ቅጂ ለተከሳሽ የሚላከዉ ብቻዉን እንዲያዉም የማስረጃ ዝርዝር እንኳ የሌለዉ ቅጂ ነበር፡፡ የሰነድ ማስረጃ ካለ እንዲደርሰዉ ይደረግ የነበረዉ ተከሳሽ ቀርቦ ክሱ ተሰምቶ የዐቃቤህግ ምስክሮች ተሰምተዉ ሲያበቁ ነበር፡፡

ስለሰነድ ማስረጃዎች አቀራረብ ግልጽ የሆነ ድንጋጌ ባለመኖሩ ከላይ የተገለጸዉ አሰራር ተስፋፍቶ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ዐቃቤህግ ከክስ ማመልከቻዉ ጋር የሰነድ ማስረጃዎቹን ቅጂ አያይዞ እንዲያቀርብ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ስለዚህ በአሰራር በዳበረዉ የአሁኑ ጊዜ ልማድ ተከሳሽ ከክስ ማመልከቻዉ ቅጂ ጋር የሰነድ ማስረጃዎች እንዲደርሰዉ ይደረጋል፡፡

የማስረጃው ግልባጭ ከክሱ ቅጂ ጋር ለተከሳሹ እንዲደርሰው ማድረግ ያለው ፋይዳ ተከሳሹ የተመሰረተበት ክስና ክሱን ለማስረዳት የቀረበበት ማስረጃ በቂ ጊዜ አግኝቶ እንዲያየውና እንዲመረምረው ያስችለዋል፤ ለክሱ የሚሰጠዉ መልስ ወይም የሚያቀርበዉ ክርክር በደፈናዉ ሳይሆን በተሟላ መረጃ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ያደርጋል፣ የመከላከል ዓቅሙ እንዲጎለብት ያስችለዋል፡፡

**መለማመጃ 20**

*ለተከሰሰበት ጉዳይ በችሎትም እንዲቀርብ መጥሪያና የክስ ቅጂ ከነሰነድ ማስረጃዉ የላኩለት ተከሳሽ ቀረበ፡፡ ለክሱ ያለዉን መልስ ሲጠየቅ ክሱ ላይ የሚቀርብ መቃወሚያ እንደሌለዉ፣ ነገር ግን የወንጀሉን የተግባር ክፍል የፈጸመዉ ቢሆንም ጥፋተኛ እንዳልሆነ በመግለጽ ተከራከረ፡፡ በዚህ ጊዜ ዐቃቤህጉ እንደተለመደዉ ምስክሮቹን አቀርባለሁ የሚል ማመልከቻ አላቀረበም፡፡ ይልቁንም ተከሳሹ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 33/2/ መሰረት መብቱን ጠብቆ ላቀረበዉ ክርክር ያሉትን ማስረጃዎች እንዲደርሰን ያድርግ፣ የዕኩልነት መብት ዐቃቤህግ እንዲያሟላ የሚጠየቀዉን ተከሳሽም እንዲያሟላ ማድረግን ያስገድዳል፣ የተከሳሹን ማስረጃ ካየን በኋላ በክሱ አሰማም ላይ ያለንን ሃሳብ እናቀርባለን በማለት አመለከተ፡፡*

*በዚህ ክርክር ላይ የሚሰጡትን ዉሳኔ ይጻፉ*

****ለዉሳኔዎ እንዲረዳዎ በአሁኑ ጊዜ የህግ ሥርዓቱ አካል የሆነዉን የጸረሙስና ጉዳዮች የቅድመክስ ሂደትን የሚመለከተዉን ህግና አሰራር ከግንዛቤ ያስገቡ፡፡*

ክሱ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን እንዲቀርቡ የተጠሩ ወገኖች ሊቀርቡ ወይም ላይቀርቡ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ እነዚህ ወገኖች ሳይቀርቡ ሲቀሩ ወይም ሲቀርቡ ስለሚፈጸሙ ሥነሥርዓቶች በሚከተሉት ሁለት ክፍሎች እናያለን፡፡

## 2.2 በቀጠሮ አለመገኘትና ዉጤቱ

### 2.2.1 ተከሳሽ ባለመቅረቡ የሚወሰድ ርምጃ

ዓ/ሕግ የክስ ማመልከቻ ካቀረበ በኋላ ፍ/ቤቱ ክሱን ለመስማት ቀነ ቀጠሮ ሰጥቶ ዓ/ሕግና ተከሳሽ እንዲቀርቡ መጥሪያ እንደሚልክላቸውና ተከሳሽ በአካል ቀርቦ መከራከሩ አስፈላጊ መሆኑ ከላይ ተመልክቷል፡፡ ተከሳሽ መጥሪያ ደርሶት እያለ በቀጠሮው ዕለት ያልቀረበ እንደሆነ ፖሊስ በእስር እንዲያቀርበው ፍ/ቤቱ ትዝዛዝ ይሰጣል (ቁ.125 እና 160 (2)፡፡ በእስር እንዲቀርብ በተሰጠው ትእዛዝ መሰረት የቀረበ እንደሆነ የክሱ መሰማት ሂደት ይቀጥላል፡፡

በሌላ በኩል ተከሳሽ መጥሪያ የተላከለት ቢሆንም ተፈልጎ ሊገኝ ባለመቻሉ መጥሪያዉ ሳይደርሰዉ ይቀራል፡፡ በዚህም ጊዜ ፖሊስ ተከሳሹን አለማግኘቱን በመግለጽ በተለዋጪ ቀጠሮ እንዳቀርበዉ ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጠኝ የሚል መልሰ ወይም ተከሳሹ ሊገኝ ስለማይችል ማቅረብ እንደማይችል በመግለጽ መልስ ይሰጣል፡፡ በዚህ ጊዜ ፍርድቤት እና ዐቃቤህግ ምን ሊያደርጉ ይገባል የሚለዉ አከራካሪ እየሆነ ይገኛል፡፡

ሌላዉ ጥያቄ ፖሊስ ተከሳሽን ይዞ እንዲያቀርብ የተሰጠው ትእዛዝ አፈጻጸም ሳይሳካለት ቢቀርስ (ለመያዝ ፈልጎ ቢያጣውስ) የሚወሰድ እርምጃ ምንድን ነው የሚል ይሆናል፡፡ ይህ ጥያቄ በሁለት መንገድ ሊመለስ የሚችል ነው፡፡ ይኸውም ተከሳሽ በቂ ባልሆነ ምክንያት ክስ እንዲሰማ በተቀጠረበት ቀን ያልቀረበ እንደሆነ ተከሳሹ በሌለበት ክሱ እንዲሰማ ፍ/ቤቱ ሊያዝዝ ይችላል (ቁ.160-163) ፡፡ ይህ ዓይነት ትእዛዝ ሊሰጥ የሚቻለው ለሁሉም የወንጀል ዓይነቶች ሳይሆን በቁ.161 (2) እንደተመለከተው፤ ከአስራ ሁለት ዓመት በማያንስ ፅኑ እስራት የሚያሳስር ወንጀል የሰራ ወይም በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ከቁ.354 እስከ 365 (በአዲሱ ወንጀል ሕግ ከቁ 343 እስከ 354) ድረስ ያሉትን ወንጀሎች ፈፅሞ ፅኑ እስራት ወይም ከአምስት ሺህ ብር በላይ መቀጫ በሚያስቀጣ ወንጀል የተከሰሰ ሲሆን ነው፡፡ በሌሎች የወንጀል ዓይነቶች የተከሰሱትን ተከሳሾች በሚመለከት ግን መጥሪያ ደርሶአቸው ባይቀርቡም እንኳ በተገኙበት ጊዜ የክሱ መሰማት ሂደት እንዲቀጥል ለማድረግ መዝገቡ ተዘግቶ እንዲቆይ ከማዘዝ በስተቀር ተከሳሾቹ በሌሉበት ክሱ ሊሰማ አይችልም፡፡ ከዚህ በተያያዘ ተከሳሽ በሌለበት ክስን ስለመስማት በሚናገረዉ የዚህ ማሰልጠኛ ጽሁፍ ክፍል የሰፈረዉን ይመለከቷል፡፡

**መለማመጃ 21**

*በችሎትዎ በቀረበ የወንጀል ክስ ተፈላጊ የሆነዉ ሰዉ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጡ፡፡ ትዕዛዙን ሊያደርስ የወሰደዉ የፖሊስ ክፍል ተከሳሹን ሊያገኘዉ አለመቻሉን በመግለጽ የተላከዉን መጥሪያ መለሰዉ፡፡ ክሱ የነፍስ ግድያ ወንጀልን ይመለከታል፡፡ ተጎጂዉ በህክምና ይረዳ በነበረበት ጊዜ የሞት ስጋት ስላልነበረ ተፈላጊዉ በመጀመሪያ በዋስ የተለቀቀ ሲሆን ከሦስት ቀናት ህክምና በኋላ የተጎጂዉ ሁኔታ እየተበላሸ መጥቶ ስለሞተ የነፍስ ግድያ ክስ የቀረበ መሆኑን ከመዝገቡ ተረድተዋል፡፡ ዐቃቤህግ ባቀረበዉ ማመልከቻ ተከሳሹ በጋዜጣ ይጠራልኝና ካልቀረበ በሌለበት ክሱ እንዲሰማ ይታዘዝልኝ በማለት ጠየቀ፡፡*

*በዚህ ላይ ትዕዛዝ ይስጡ፣ ትዕዛዙን ይጻፉ፡፡*

*በሌላ በኩል በክሱ ዉስጥ ሦስት ሰዎች መከሰሳቸዉን ያስቡ፡፡ ሁለቱ የሚቀርቡት ተከሳሾች የዐቃቤህጉን ጥያቄ በመቃወም ያልቀረበዉ ተከሳሽ ያልተገኘ በመሆኑ ነገሩ በሌለበት ሊታይ ስለማይችል እርሱን ለመጥራት የጋዜጣ መዉጣትና በዚህ መሰረት መቅረብ አለመቅረቡን ማረጋገጥ የሚወስደዉ ጊዜ በፍጥነት ፍርድ የማግኘት መብታችንን ስለሚቀንስ ጥያቄዉ ዉድቅ ሆኖ በኛ ላይ የቀረበዉ ክስ ብቻ መታየቱ እንዲቀጥል ይደረግልን በማለት አመለከቱ፡፡*

*የሚሰጡትን ዉሳኔ ይጻፉ፡፡*

ተከሳሽ ከፍርድቤት የሚቀረዉ በመጀመሪያዉ ጥሪ ጊዜ ብቻ አይደለም፡፡ ተከሳሽ ከተጠራ በኂላ መቅረብ ጀምሮ ሊቀር ይችላል፡፡ የዐቃቤህግ ማስረጃዎች ከመሰማታቸዉ በፊት እንዲህ ያለዉ መቅረት ክሱ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 161/2/ የተመከቱትን ወንጀሎች የተመረኮዘ እስከሆነ ድረስ ተከሳሹ በሌለበት ይታያል፡፡ እንዲህ አይነት ወንጀሎችን የሚመለከት ክስ ከሌለ ግን ክሱ ሊቋረጥ ይገባል፡፡ በሌላ አጋጣሚ ተከሳሽ የዐቃቤህግ ምስክሮች ከተሰሙ በኂላ ፍርድቤቱ በነገሩ ላይ ብይን ለመስጠት ቀጠሮ ከያዘበት ቀን አንስቶ ከዚህ በኂላ በሚኖሩ ቀጠሮዎች ከፍርድቤት ሊቀር ይችላል፡፡

**መለማመጃ 22**

በአንድ ክስ ጉዳይ የዐቃቤህግ ምስክሮች ተሰምተዉ ካበቁ በኂላ ተከሳሹ ስለተመሰከረበት ይከላከል ተብሎ ቀጠሮ ተያዘ፡፡ ተከሳሽ በዚህ ቀጠሮ አልቀረበም ምስክሮቹም አልቀረቡም፡፡

*ዐቃቤህጉ እርስዎ ቢሆኑ በዚህ ጉዳይ ላይ ምን ያመለክታሉ?*

*ዳኛዉ እርስዎ እንደሆኑ አስበዉ ባልደረባዎን እንደዐቃቤህግ ክርክር እንዲያቀርቡ ካደረጉ በኂላ በክርክሩ ላይ ይወስኑ፡፡ ይጻፉት*

### 2.2.2 <u>ዐቃቤ ህግ ባለመቅረቡ የሚወሰድ ርምጃ</u>

ክሱ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን ዐቃቤህግ ሳይቀርብ ቢቀር ምን ሊደረግ እንደሚገባዉ በሚነሳዉ ጥያቄ ላይ የሚሰጡት መፍትሄዎች ከቦታ ቦታ ከባለሙያ ባለሙያ ይለያያሉ፡፡ አንዳንድ ቦታ በአንዳንድ ዳኞች የሚሰጠዉ መፍትሄ መዝገቡን መዝጋት ነዉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ዐቃቤህግ ሲቀርብ ክሱን መስማት ለመቀጠል ቀጠሮ ይለዉጣሉ፡፡

የመጀመሪያዉ መፍትሄ ከተከሳሹ በተገቢዉ ፍጥነት ፍርድ የማግኘት መብት አኳያ መዝገቡ የሚዘጋበት ምክንያት ሳይገለጽ ለነገሩ መቋጫ ሳይደረግ ማለትም በጉዳዩ ላይ ሳይወሰን መዝገቡን መዝጋት ይህን የተከሳሹን መብት አንጠልጥሎ የሚተዉ ነዉ፡፡ በህግ የሚደገፍ መሆኑም ያጠራጥራል፡፡ ወደሁለተኛዉ መፍትሄ ስንመጣ በተመሳሳይ ሁኔታ የተከሳሹን መብት የሚጎዳ ሆኖ ይገኛል፡፡ ይህን በፍጥነት ፍርድ የማግኘት መብት ለመንከባከብ ሲባል የተደነገገዉን የቀጠሮ ድንጋጌ /የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 94/2//ህ/ ስር የተደነገገዉን የሚያፈርስ ነዉ፡፡ በዐቃቤህግ አለመቅረብ ምክንያት ቀጠሮ ሊለወጥ

የሚችለዉ በምን ሁኔታ እንደሆነ ተደንግጎ ስለሚገኝ ሁልጊዜ ዐቃቤህግ እንዲቀርብ ለመጠበቅ ቀጠሮ መለወጥ ይህን ድንጋጌ ያልተከተለ አሰራር ይሆናል፡፡

**መለማመጃ 23**

በችሎትዎ በቀረበ ክስ ጉዳይ ተከሳሽንና ዐቃቤህግን እንዲሁም ምስክሮች እንዲቀርቡ አዘዙ፡፡ በቀጠሮዉ ቀን ተከሳሽና የግራቀኙ ምስክሮች ቀርበዋል፡፡ መዝገቡ ሲጠራ ዐቃቤህግ አለመቅረቡን ተገነዘቡ፡፡ ተከሳሽን ጠርተዉ ስለማንነቱ ካጣሩ በኋላ ተከሳሹ የሚያመለክተዉ ነገር እንዳለ ጠየቁ፡፡ ተከሳሹ በጠበቃ በኩል ዐቃቤህግ ክሱን እንደተወዉ ተቆጥሮ ከክሱ በነጻ እንዲሰናበት ጠየቀ፡፡ ዐቃቤህግ የቀረበትን በቂ ምክንያት ለማወቅ በተደረገዉ ማጣራት ይህን ሊያስረዳ የቀረበ ማንም አለመኖሩን፣ ከዐቃቤህጉ ጽ/ቤትም ሲጠየቅ ዐቃቤህጉ ለምን እንዳልቀረበ የሚታወቅ ነገር አለመኖሩን ተገነዘቡ፡፡

*በዚህ ጉዳይ ላይ ተገቢዉን ትዕዛዝ በጽሁፍ ይስጡ*

/ትዕዛዙን ሲሰጡ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥቁ 94/2//ሀ/ የተደነገገዉን ከግንዛቤ ያስገቡ፡፡/

በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 94/2//ሀ/ መሰረት ዐቃቤህግ ሲቀር በዚህ ዕለት ቀጠሮ ለመለወጥ ከቀጠሮ የቀረዉ በበቂ ምክንያት መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ይህም ቀጠሮ ከመለወጡ በፊት መከናወን አለበት፡፡ ይህን ምክንያት ለማጣራት ቀጠሮ መለወጥ ይህን የቀጠሮ ድንጋጌ የሚከተል አይሆንም፡፡ በቂ ምክንያት መኖሩ በዚሁ ቀን ለፍርድቤት ቀርቦ መረጋገጥ አለበት፡፡

## 2.2.3 ምስክር ባለመቅረቡ የሚወሰድ ርምጃ

እንደተከራካሪዎቹ ሁሉ ምስክሮችም የማይቀርቡበት አጋጣሚ አለ፡፡ ልክ እንደተከሳሹ ሁሉ ምስክርም በሁለት ሁኔታዎች ሳይቀርብ ሊቀር ይችላል፡፡ አንድኛዉ ሳይገኝ በመቅረቱ መጥሪያ ስላልደረሰዉ ማለትም መጠራቱን ባለማወቁ ሲሆን ሌላኛዉ ከተጠራ በኋላ ለመቅረብ ባለመፈለጉ ወይም ቢፈልግም ከአቅም በላይ የሆነ እክል ስላጋጠመዉ ሊሆን ይችላል፡፡

በምስክር አለመቅረብ ምክንያት በፍርድቤቶች የሚወሰደዉ የተለመደዉ ርምጃ በቅድሚያ ቀጠሮ መለወጥ፣ ከበርካታ ወይም ከመጠነኛ ተደጋጋሚ የቀጠሮ ለዉጥ በኋላ ምስክር አሁንም ሊቀርብ ካልቻለ የተለመደዉ አሰራር የክሱን መሰማት ምስክር እስኪገኝ አቋርጦ

መቆየት ወይም ምስክሩ በምርመራ ጊዜ የሰጠዉ ነዉ የተባለዉን ቃል በጽሁፍ የተቀመጠዉን በማስረጃነት እንዲቀርብ ማድረግ ነዉ፡፡

በርግጥም ምስክር ባልቀረበ ጊዜ ይኸዉ ቀጠሮ ለመለወጥ ምክንያት እንደሆነ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 94/2//ለ/ ስር ተደንግጓል፡፡ ሆኖም ይህ ቀጠሮ የመለወጥ ነገር ከላይ በታዩት ሁሉም ምስክር የሚቀርባቸዉ ሁኔታዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆን እንደሁ መወሰን ያስፈልጋል፡፡ እንደሚታየዉ ድንጋጌዉ ሁኔታዎቹን በመለየት የሚደነግግ አይደለም፡፡ ሆኖም በምስክር አለመቅረብ ምክንያት ቀጠሮ ሲለወጥ ሊሰጡ የሚገባቸዉን ትዕዛዞች በተመለከተ የተደነገገዉን የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 96 ከግንዛቤ በማስገባት ነገሩን መወሰን ያስፈልጋል፡፡ ይህ ድንጋጌ በዚህ ጊዜ እንዲሰጡ የሚደነግጋቸዉ ትዕዛዞች ቀጠሮ ሊለወጥ የሚችልባቸዉን ምክንያቶች ባህሪ የሚጠቁሙ ናቸዉ፡፡

**መለማመጃ 24**

በከፍተኛዉ ፍርድቤት በቀረበ አንድ የወንጀል ክስ ጉዳይ ለምስክርነት የተጠሩ ሰዎች የተላከላቸዉን መጥሪያ እንዲያደርስ ዐቃቤህግ ለፖሊስ ልኳል፡፡ ፖሊስ ከቀጠሮዉ ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ ምስክሮቹ በአድራሻቸዉ ሊገኙ አለመቻላቸዉን በመጥቀስ እንደማያቀርባቸዉ ለዐቃቤህግ መልስ ጻፈ፡፡ በቀጠሮዉ ቀን ምስክሮች በችሎት ሲጠሩ አልቀረቡም፡፡ ዐቃቤህግ ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጥቶኝ ፍለጋ በማድረግ እንዲቀርቡ አስደርጋለሁ በማለት አመለከተ፡፡ ተከሳሹ በጠበቃዉ አማካኝነት ምስክሮች በአድራሻቸዉ ሊገኙ ካልቻሉ ከየት ተፈልገዉ እንደሚገኙ ግልጽ አይደለም፡፡ ምስክሮች ሊገኙ ያልቻሉ በመሆኑ ዐቃቤህግ በቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍርድቤት የተመዘገበ ምስክርነት ካለዉ እርሱን ያቅርብ ከሌለዉ ደግሞ የት እንዳሉ የማይታወቁ ምስክሮች እንዲቀርቡ ቀጠሮ ሊሰወጥ አይገባም፣ ዐቃቤህግ ማስረጃ ስለሌለዉ ከክሱ በነጻ ልሰናበት በማለት ተከራከረ፡፡

*ዳኛዉ እርስዎ ነዎት፡፡ በዚህ ክርክር ላይ በጽሁፍ ትዕዛዝ ይስጡ፡፡*

በሌላ አጋጣሚ የተጠሩት ምስክሮች መጥሪያ የደረሳቸዉ ለመሆኑ ማረጋገጫ ነዉ የተባለ የተፈረመበት ወረቀት ከፖሊስ መልስ ጋር ለዐቃቤህግ ስለደረሰዉ ይህንኑ ዐቃቤህግ ለፍርድቤት አቀረበ፡፡ እርስዎም ምስክሮች ተይዘዉ እንዲቀርቡ ፖሊስን አዘዙ፡፡ ለዚህም መጠባበቂያ ቀጠሮ ያዙ፡፡ በቀጠሮዉ ቀን ፖሊስ ምስክሮቹን ይዞ ለማቅረብ በአድራሻቸዉ ሊያገኛቸዉ አለመቻሉን በመግለጽ መልስ አቀረበ፡፡ ዐቃቤህግ ምስክሮች የፍትህ ሥራን ላለመርዳት መሰወራቸዉን ስለሚያሳይ ተይዘዉ እንዲቀርቡ በድጋሚ ይታዘዝልኝ በማለት አመለከተ፡፡ በዚሁ መሰረት ቀጠሮ ይዘዉ ትዕዛዙ በድጋሚ እንዲፈጸም አዘዙ፡፡ በድጋሚ በተያዘዉ ቀጠሮ ፖሊስ ምስክሮችን አለማግኘቱን በመግለጽ መልስ ሰጠ፡፡ ምስክሮችም አልቀረቡም፡፡ ዐቃቤህግ በድጋሚ ትዕዛዙ እንዲፈጸም ይታዘዝልኝ በማለት አመለከተ፡፡ በዚህ ጊዜ ተከሳሹ በጠበቃዉ አማካኝነት ተከሳሽ በተገቢዉ ፍጥነት ፍርድ የማግኘት መብት አለዉ፣ የማይገኙ ምስክሮች እየተፈለጉ ተከሳሽ በካደዉ ወንጀል ላልተወሰነ ጊዜ ተከሳሽ ሆኖ መቆየት የለበትም፣ ስለዚህ ዐቃቤህግ ምስክሮቹን በዚህ ሁሉ ጊዜ ማቅረብ ካቃተዉ በቀዳሚ ምርምራ ፍርድቤት የተሰጠ ምስክርነታቸዉን እንዲያቀርብ፣ ይህ ከሌለ ማስረጃ እንደሌለዉ ስለሚያሳይ ክሱን የማያነሳ ከሆነ ተከሳሽ ከክሱ በነጻ እንዲሰናበት ሊታዘዝ ይገባል እንጂ ቀጠሮ ሊለወጥ አይገባም በማለት ተከራከረ፡፡

*እርስዎ ዳኛዉ በዚህ ክርክር ላይ ተገቢ ነዉ የሚሉትን ትዕዛዝ በጽሁፍ ይስጡ፡፡*

መጠራታቸዉን አዉቀዉ ያልቀረቡ ሰዎች በእስር እንዲቀርቡ ፓሊስን ማዘዝ ብቻ ሳይሆን ለፍትህ እርዳታ የመስጠት ግዴታቸውን ባለመወጣቸው ወይም እንዲቀርቡ ትእዛዝ ደርሶኣቸው እያለ እምቢ በማለታቸው ምክንያት ሊቀጡ እንደሚችሉ በወንጀል ሕግ ዓንቀፅ 448 ተመልክቷል፡፡ ስለዚህ ይህ ህግ ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ ለዚህም ከመጀመሪያዉ ጥሪ ጋር ይህን የቅጣት ማስጠንቀቂያ ጨምሮ ማዘዝ ተገቢ ይሆናል፡፡

## 2.3 ተከሳሽ ሲቀርብ የሚፈጸም ሂደት

### 2.3.1 ክስ ስለማሰማት

አንድ ሰዉ በቀረበበት ክስ ምስክንያት ተጠርቶ ፍርድቤት ሲቀርብ ከክሱ ጋር በተያያዘ ሊደረግለት የሚገባዉ የመጀመሪያዉ ትልቅ ነገር የተከሰሰበትን ወንጀል በችሎት እንዲሰማዉና እንዲረዳዉ ማድረግ ነዉ፡፡ ሆኖም ይህ ከመሆኑ በፊት በዚህ ክስ የሚፈለገዉ ሰዉ እርሱ ስለመሆኑ ማጣራት ሊደረግ ይገባል፡፡ የተከሳሹን በሳጥን ውስጥ መግባት ተከትሎ መከናወን ያለበት ነገር ቢኖር የተከሳሹን ማንነት ማረጋገጥ ነው፡፡ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ 128 እንደተመለከተው "ተከሳሹ በሳጥን ውስጥ ገብቶ ከቆመ በኋላ ማንነቱ፤ ዕድሜውና ስራዉ መረጋገጥ አለበት" ይላል፡፡ እዚህ ላይ ማንነት የሚል ቃል በሰፊው ካልተተረጎመ በስተቀር ስምን ብቻ ለማመልከት የተቀመጠ ነው የሚመስለው፡፡ ይሁን እንጂ ኣንድ ተከሳሽ ለፍ/ቤት መግለፅ ያለበት ስሙን፤ ዕድሜውና ስራውን ብቻ ሳይሆን፤ ዖታውን፤ ኣድራሻውን፤ የትምህርት ደረጃውንና የቤተሰቡን ሁኔታ (ያገባ ወይም ያላገባ መሆኑን፤ ልጆች ያሉት ወይም የሌሉት መሆኑን ወዘተ) ጭምር ነው፡፡ እነዚህ መረጃዎች ወደፊት ለሚሰጡ ዉሳኔዎች ጠቃሚ ናቸዉ፡፡

**መለማመጃ 25**

*ተከሳሽ፣ ዐቃቤህግ፣ ምስክሮች በአንድ ላይ እንዲቀርቡ በሚደረግበት አሰራር የተከሳሹ ማንነት በችሎት በሚረጋገጥበት ጊዜ ተከሳሹን ከሃሰተኛ ምስክሮች ለመከላከል ምን ሊደረግ ይገባል? እርስዎ የተከሳሽን ማንነት በሚያረጋግጡበት ጊዜ ወይም ከዚያ በፊት ምን ተግባራትን ያከናዉናሉ?*

በችሎትዎ ከቀረቡት ተከሳሾች በርከት ያሉት ላይ ምስክር ሊሰሙ ቀጠሮ ይዘዋል፡፡ ከተከሳሾቹ የአንዱ ጠበቃ ገና እርስዎ በችሎት እንደተሰየሙ ተነስቶ በዛሬዉ ዕለት ለምስክርነት የመጡ ሰዎች በችሎቱ አዳራሽ ካሉ ተከሳሹ ደንበኛዬ ከመጠራቱ በፊት እንዲወጡ ይታዘዝልኝ በማለት ጠየቀ፡፡ ምክንያቱን ሲጠየቅ ደንበኛዉ /ተሰካሽ/ ሲጠራና ማንነቱ ሲረጋገጥ ሊያዩ አይገባም፣ ተከሳሹን ስለማያዉቁት በምስክርነት ጊዜ እንዲለዩት ለማድረግ አሁን እንዳያዩት ማድረግ ይገባል ብሎ አስረዳ፡፡

*ዐቃቤህግ ቢሆኑ ይህን ጥያቄ ይቃወማሉን? በዝርዝር ይጻፉት*

*እርስዎ ዳኛዉ ከዐቃቤህግ የሚቀርበዉን ሃሰብ ሰምተዉ በጠበቃዉ ማመልከቻ ላይ ትዕዛዝ ይስጡ፣ ይጻፉት*

- ተከሳሽ ነዉ የተባለ ሰዉ በችሎትዎ አዳራሽ ተገኝቷል፡፡ እርሱ የተከሰሰበት መዝገብ ነዉ የተባለዉን ሲጠሩ የቀረበ የለም፣ ተከሳሹን አጅቦ የመጣዉ ህግ አስከባሪ ይህን ተከሳሽ ተነስ ብሎ አስነሳዉ፡፡ እርስዎም ይህን ሰዉ ለምን ሲጠሩት ዝም እንዳለ፣ ስለማንነቱ ወዘተ ሲጠይቁት ዝም አለ፡፡ በተለያየ መንገድ ሊያናግሩት ሞክረዉ አልተሳካልዎትም፡፡

*ስለግለሰቡም ሆነ ስለክሱ አሰማም የሚሰጡትን ዉሳኔ ይጻፉት*

በሌላ አጋጣሚ ተከሶ የቀረበዉ ሰዉ ማንነቱን ሲጣራ በክስ ማመልከቻዉ ዉስጥ የተጠቀሰዉ ተከሳሽ ስምና የቀረበዉ ሰዉ የሚገልጸዉ ስም የተለያየ ሆኖ ተገኘ፡፡ ዐቃቤህግ የምርመራ መዝገቡን አይቶ በክሱ የተመለከተዉ የተከሳሽ ስም በምርመራ መዝገቡ ከተመለከተዉ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን አረጋገጠ፡፡

*ዐቃቤህጉ እርስዎ ቢሆኑ ምን ያመለክታሉ*

*ዳኛዉ እርስዎ እንደሆኑ ያስቡ፡፡ ባልደረባዎን እንደዐቃቤህግ እንዲያመለክቱ አድርገዉ ዉሳኔ ይጻፉ*

*ነገሩን በግልጽ ችሎት ስለማየት፡-*

**ክሱን ለመስማት በተቀጠረበት ቀንና ሰዓት ክሱን ለመስማት ፍርድ ቤቱ ማስቻል አለበት፡፡ የተከሳሹን ወይም የተበዳዩን የግል ህይወትና ሞራል፣ የህዝቡን የሞራልና የፀጥታ ሁኔታ እንዲሁም የአገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ ሲል ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በዝግ ችሎት እንዲታይ ካልወሰነ በቀር ክሱ በግልፅ ችሎት መታየት ይኖርበታል (የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት ቁ** 20 (1) **፡፡**

ይህም እንዲሆን ያስፈለገበት ምክንያት የአሰራረ ግልፅነት ግዴታ በመንግሥት የሥልጣን አካላት ላይ የተጣለ ስለሆነና ይህ ግዴታ መፈጸሙ ለፍትሕ ዋስትና በመሆኑ ነው፡፡ የግልፅ ችሎት አስፈላጊነት ለዳኛውም በራስ የመተማመን ሁኔታ ይፈጥርለታል፡፡ ፍትህ ፍለጋ ለሚመጣና ለኅብረተሰቡ በአጠቃላይ በፍትሕ ተቋሙ /ፍርድ ቤት/ ላይ ያለውን እምነት እየጠነከረ እንዲሄድ ያደርገዋል፡፡

የክስ መሰማት ሂደት በግልፅ ችሎት እንዲካሄድ መደረጉ ችሎቱን የሚከታተሉ ወገኖች ዳኞች ገለልተኛነታቸውን ጠብቀው ባለጉዳዩችን በእኩልነት እያዩ ሂደቱን እየመሩ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ፣ የግራና ቀኝ ተከራካሪ ወገኖች ማስረጃና የሚሰጠውን ፍርድ ይዘት ለመገምገም ያስችላቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ዳኞች ነፃነታቸውን ጠብቀው ሕግንና ህሊናቸውን መሰረት አድርገው ምን ያህል የዳኝነት ስራቸውን እያከናወኑ እንዳሉ ኅብረተሰብ እንዲገነዘብ ያስችለዋል፡፡ ፍርድ ቤቶች የህዝብ (የተገልጋይ) አመኔታ እንዲያተርፉ ከሚያደርጉዋቸው ነገሮች አንዱ ስራቸውን በግልፅ ችሎት ሲያካሂዱ ስለሆነ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡

ከተከሳሽ መብት አኳያ እንዲሁ ጠቀሜታዉ የሚናቅ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ችሎቶች ግልጽ እና ባደባባይ መሆናቸዉ ተከሳሹ ያሉትን መብቶች በተገቢዉ መንገድ ሲገለገልባቸዉ ሊደርሱበት የሚችሉ መጋፋቶችን ያስቀራል፡፡ የታዛቢ የተመልካች መኖር ፍርድቤቶች ወይም ሌሎች ወገኖች ተከሳሹ መብቱን እንዳይሰራበት የሚያሰናክሉ ተግባራትን ከመፈጸም እንዲቆጠቡ ግፊት ስለሚያደርግ ከዚህ አኳያ የችሎት ሂደቶች ግልጽ መሆን ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለዉ፡፡

**መለማመጃ 26**

*በአንድ ዕለት ከሰዓት በኋላ የአንድ የወንጀል ይግባኝ ክርክር በቃል ለመስማት ቀጠሮ ይዘዉ ይገኛሉ፡፡ ተከሳሹ በሌላ አካባቢ ማረሚያቤት ተይዞ የሚገኝ በመሆኑ በቀጠሮዉ ዕለት የተከሳሹ ቤተሰብና ዘመድ የሆኑ ሰዎች እና ጠበቃዉ ብቻ በፍርድቤት ተገኝተዉ ነበር፡፡ ሆኖም በዚህ ጊዜ የነበረዎ መዝገብ ይኸዉ ብቻ በመሆኑ በጽ/ቤትዎ ለመስማት ፈልገዉ ጠበቃዉን ሲያስጠሩ የተከሳሹ ዘመዶችም ተከትለዉ ወደጽ/ቤቱ መጡ፡፡ ቁጥራቸዉ በዛ ያለ ሲሆን ጽ/ቤቱ ጠባብ ነበር፡፡ የችሎትዎ አስተናጋጅ ከጠበቃዉ በቀር ሌቹን ወደጽ/ቤቱ አላስገባችሁም ተመለሱ በማለት ሲመልሳቸዉ እርሰዎ አይተዋል ከቤተሰቦቹ አንዱ ሂደቱን ማየት አለብኝ ልታባርረኝ አትችልም በማለት ከአስተናጋጁ ጋር ዉዝግብ ዉስጥ ገቡ፡፡*

*በዚህ ጊዜ ምን ያደርጋሉ? አስተናጋጁን ይገስጻሉ ወይስ የባለጉዳዩን ዘመድ? ለምን?*

## *በጠበቃ ስለመከራከር፡-*

*ክስን የመስማት ጉዳይ ሲነሳ አብሮ የሚነሳው በጠበቃ የመታገዝ አስፈላጊነት ነው፡፡ የጠበቃ አስፈላጊነት በአጠቃላይ ሲታይ አንድ ተከሳሽ በሕግ የተቀመጠለት መብት በአግባቡና በተገቢ ሁኔታ እንዲጠቀምበት ለማስቻል ነው፡፡ ያለጠበቃ መከራከር የሚያስከትለው ጉዳት፤*

- *የተማረ ሰው ቢሆንም እንኳ ሕግ የማያውቅ ከሆነ እራሱን ለመከላከል ያዳግተዋል፣*
- ***የክስ ይዘትና ፎርም ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን ላያውቅ ስለሚችል በተገቢው ሰዓት ተገቢውን ተቃውሞ ለማቅረበ አይችልም፣***
- *የማሰረጃ አቀራረብ ደንቦችን ስለማያውቅ ታማኝነትና አግባብነት የሌላቸው የዓቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ተቀባይነት እንዳይኖራቸው ለማድረግ ጥረት አያደርግም፣*
- *ወንጀል የፈፀመ መሆኑ ቢረጋገጥ እንኳ በሕግ መሰረት ይቅርታ ሊያደርግለት ወይም ቅጣቱ ሊቀልለት የሚገባ መሆኑን ለማስረዳት አይችልም፡፡*

*ስለዚህ እነዚህን ችግሮች ለመቀነስ ወይም ለማስወገድ ተከሳሹ ጠበቃ ያለው እንደሆነ ከጠበቃው ጋር የመቅረብ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ በጠበቃ የመታገዝ ጉዳይ ተከሳሹ ዓቅም*

ካለው በራሱ ወጪ የመረጠውን ጠበቃ ማቆም የሚችል ሲሆን፤ ጠበቃ ለማቆም ዓቅም ያጣ እንደሆነ ግን ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ ያለ ጠበቃ ቢከራከር ፍትሕ ሊጓደልበት ይችላል የሚል እምነት ሲኖረው ከመንግስት ጠበቃ እንዲያገኝ ሊያዝዝ ይችላል፡፡ ተከሳሹም ዓቅም ከሌለው ከመንግስት ጠበቃ የማግኘት መብት እንዳለው ከኢፌዴሪ ሕገ መንግስት ቁ 20(5) መረዳት ይቻላል፡፡

ተከሳሹ ጠበቃ እንደሌለው ገልፆ መንግስት እንዲመድብለት ከጠየቀ ጉዳዩን የያዘዉ ፍርድ ቤት በበኩሉ በመንግስት ወጪ ጠበቃ ሊመድብለት የሚገባ መሆን አለመሆኑን መመርመር ኣለብን፡፡ በዚህ ረገድ በተለይም ያለጠበቃ መከራከር የፍትህ መጓደል ሊያስከትል የማይችልበት አጋጣሚ አለ ብሎ መከራከር ይቻላል ወይ የሚለዉ ጥያቄ መነሳቱ የማይታለፍ ነዉ፡፡

**መለማመጃ 27**

በችሎትዎ የቀረበዉ ተከሳሽ አነስተኛ የጨርቃጨርቅ ሱቅ ያለዉ ነጋዴ ነዉ፡፡ የተከሰሰዉ በቼክ በማጭበርበር ወንጀል ሲሆን አምስት መቶ ብር የያዘና በቂ ስንቅ የሌለዉ ቼክ ሰጥቷል ተብሎ ነዉ፡፡ ተከሳሽ ክሱን ከሰማ በኋላ መልስ ከመስጠቱ በፊት የህግ ባለሙያ ሊያማክር እንደሚገባዉና ለዚህም ፍርድቤቱ ተከላካይ ጠበቃ ሊመድብለት እንደሚገባ አመለከተ፡፡

*ይህን ጥያቄዉን በተመለከተ የሚወስኑት ምንድን ነዉ? ከነምክንያቱ ይጻፉት*

*ተከሳሹ ከሁለት ሳምንታት በፊት ስለመክሰሩ የተሰጠ የፍርድቤት ዉሳኔ ቢያቀርብና በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ትልቅ ቪላ ቤት ያለዉ መሆኑ ቢታወቅ ዉሳኔዎ የተለየ ይሆናልን? ምክንያቱስ?*

በሌላ በኩል ተከሳሹ ምንም ሥራ የሌለዉ ሆኖ የተከሰሰበት ወንጀል ደግሞ የስርቆት ወንጀል ነዉ፡፡ ክሱን ከሰማ በኋላ በጠበቃ መከራከር እንዲችል ፍርድቤቱ ጠበቃ በመንግሥት ወጪ እንዲሰጠዉ አመለከተ፡፡

*የሚሰጡት ዉሳኔ ምንድን ይሆናል? ከላይ ከሰጧቸዉ ዉሳኔዎች ምን ያህል እንደሚለይ ለማወዳደር ዉሳኔዎን ይጻፉት*

ከላይ ከተመለከቱት ሁኔታዎች በተለየ አንድ ተከሳሽ እጅግ ከባድ በሆነ ወንጀል ተከስሶ ጠበቃ ለመቅጠር አቅም እያለዉ አልቀጥርም፣ በመንግሥት ወጪም እንዲሰጠኝ አልፈልግም ራሴ እከራከራለሁ ብሎ ለፍርድቤቱ አመለከተ እንበል፡፡

*በዚህ የተከሳሽ አቋም ላይ የሚወስኑትን ዉሳኔ ይጻፉት*

ተከሳሹ ጠበቃ የተመደበለት እንደሆነ ከጠበቃው ጋር ተመካክሮ ለመቅረብ የሚያስችለው በቂ ጊዜ ሊሰጠው ይገባል፡፡ ከጠበቃው ጋር ለመመካከር ቀጠሮ እንዲሰጠው ከጠየቀም የጉዳዩ ክብደትና ውስብስብነት ግምት ውስጥ በማስገባት ክሱን ወድያው መቀጠል የተከሳሹን የመከላከል መብት የሚነካ መሆኑን ፍ/ቤቱ በሚገባ ካመነበት ቀጠሮ መስጠት ይችላል፡፡ የተከሳሹን የመከላከል መብት የማይነካ ከሆነ ግን ሌላ ቀጠሮ መስጠት ሳያስፈልግ ለመመካከር የሚበቃ የተወሰነ ጊዜ ብቻ መስጠት በቂ ሊሆን ይችላል፡፡

## *በአስተርጓሚ ስለመታገዝ፡-*

የክስ መስማት ሂደት ሲጀመር ሌላ ትኩረት የሚሻ ነጥብ ኣስተርጓሚ የመመደብ ጉዳይ ነው፡፡ ችሎቱ የሚካሄደው ተከሳሹ በማያዉቀው ቋንቋ ከሆነ ፍ/ቤቱ በመንግስት ወጪ ኣስተርጓሚ ሊመድብለት ይገባል (ሕገ መንግስት ዓንቀፅ 20 (7) እና የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ ቁ.126 (2) ይመለከቷል)፡፡ ኣስተርጓሚ የሚመደበው ተከሳሹ ሲያመለክት ወይም ተከሳሹ ባያመለክትም የችሎቱን ቋንቋ የማይገባው መሆኑን ፍ/ቤቱ ሲረዳው ነው፡፡ ቋሚ የፍ/ቤት ኣስተርጓሚዎች ካሉ የተከሳሹን ቋንቋ የሚረዳ ኣስተርጓሚ ፍ/ቤቱ ይመድባል፡፡ ቋሚ ኣስተርጓሚ ከሌለ ወይም ያሉት ኣስተርጓሚዎች የተከሳሹን ቋንቋ የማይረዱ ከሆነ ፍ/ቤቶች ለተከሳሹ ወይም ለዓ/ሕጉ (ለግል ተበዳዩም ጭምር) ዘመድ (የስጋ ወይም የጋብቻ) ያልሆነ ችሎታ ያለው ሌላ ሰው መርጠዉ ሲመደቡ ይስተዋላል፡፡ ሕጉ በግልፅ ያስቀመጠው ነገር ባይኖርም በተለምዶ ኣስተርጓሚው ክርክሩን መተርጎም ከመጀመሩ በፊት በእውነት ለማስተርጎም እንዲምል ይደረጋል፡፡ የመሃላ ቃሉም “በዚህ ፍ/ቤት የቀረበውን ክርክር በእውነትና የችሎታዬን ያህል ላስተረጉም እምላለሁ” የሚል መሆን አለበት፡፡ ምናልባት “እምላለሁ” ማለትን ሃይማኖቱ የማይፈቅድለት ከሆነ ሌላ ኣባባል እንዲጠቀም (ለምሳሌ “አረጋግጣለሁ” እንዲል) ሊፈቀድለት ይገባል፡፡

*መለማመጃ* **28**

*በዐቃቤ ህግነትዎ በደረሰዎ የወንጀል ምርመራ መዝገብ ዉስጥ ወንጀሉን ፈጸመ የተባለዉ ሰዉ ፍርድቤቱ የሚሰራበትን ቋንቋ እንደማይሰማና እንደማይናገር የሚገልጽ ማስታወሻ ወይም ጠቋሚ የሆኑ ነገሮችን ለምሳሌ በአስተርጓሚ ቃሉን መስጠቱን አረጋገጡ፡፡ ክሱን አዘጋጅተዉ ለፍርድቤት ሲያቀርቡ ፍርድቤቱ ለተከሳሹ አስተርጓሚ በተገቢዉ ጊዜ እንዲያዘጋጅለት ለማድረግ የሚያስችል ክስ ማቅረብ ፈለጉ፡፡*

*የክሱ ማመልከቻ ምን ይመስላል? ክሱን ይጻፉት፣ ለዚህም አንዳንድ ፍሬ ነገሮችን በራስዎ መገመት ይችላሉ፡፡*

*በችሎትዎ በቀረበዉ ክስ ተከሳሽ የሆነዉ ሰዉ የዉጪ ሃገር ዜጋ ነዉ፡፡ ሆኖም ይህን ጉዳይ ተከሳሹ ችሎት ቀርቦ እስኪያዩት ድረስ ልብ አላሉም፡፡ ስሙም ቢሆን በኢትዮጵያ የተለመደ የአረብኛ ስም ነዉ፡፡ ክሱን ለማሰማት ማንነቱን ለማረጋገጥ ሲሞክሩ ተከሳሹ የታንዛኒያ ዜጋ መሆኑን የሚችለዉ ቋንቋ ደግሞ ስዋሂሊ ወይም እንግሊዝኛ ብቻ መሆኑን አረጋገጡ፡፡*

*ስለአስተርጓሚ አገልግሎት ተገቢዉን የተከሳሹን ህገመንግሥታዊ መብቶች የሚያስከብር ትዕዛዝ ይስጡ*

*በሌላ በኩል በቀረበልዎ የክስ ማመልከቻ ላይ ከማስረጃ ዝርዝር ቀጥሎ አንድ ማስታወሻ ተጽፎ አዩ፡፡ ይህም ማስታወሻ ተከሳሹ በማረፊያቤት እንደሚገኝ፣ የናይጀሪያ ዜጋ በመሆኑ ጠያቂ የሌለዉ ስለሆነ ነገሩ በአስቸኳይ ቅድሚያ ተሰጥቶት እንዲታይለት ዐቃቤህግ እንደሚፈልግ የሚገልጽ ነዉ፡፡*

*ስለጉዳዩ አሰማም በጠቅላላዉ ነገሩ በሚሰማበት ቀን የተከሳሹን መብቶች በሚያስከብር መልኩ ትዕዛዝ ይስጡ*

## **2.3.2** *ክስን ስለመቃወምና በመቃወሚያዉ ላይ ስለመወሰን*

*ተከሳሽ ፍርድቤት ሲቀርብ ማንነቱ ተረጋግጦ ክሱ ተነቦለትና እንዲረዳዉ ተደርጎ ሲያበቃ ለክሱ ያለዉን መልስ እንዲያቀርብ ይጠየቃል፡፡ ለዚህም ከሁሉ አስቀድሞ የሚጠየቀዉ ክሱን ይቃወም እንደሆነ ነዉ፡፡ ክሱ ግልፅ ስለመሆኑና ሌሎች የክስ መቃወሚያዎች ይኖሩት እንደሆነ ፍርድቤቱ ይጠይቀዋል፡፡ መቃወሚያ ያለው መሆኑን አለመሆኑን ሳያረጋግጥ ፍ/ቤቱ የእምነት ክህደት ቃል ወደ መቀበል መሄድ የለበትም፡፡ የክስ መቃወሚያ አቀራረብና አወሳሰን በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ* 130 *እና ተከታዮቹ መሰረት የሚገዛ ነዉ፡፡*

*በተከሳሹ ሊቀርብ የሚችል መቃወሚያ በሁለት መልኩ ሊታይ ይችላል፡፡ አንደኛ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ* 130 (1) *እንደተመለከተው ተከሳሹ በክሱ ማመልከቻ ፎርም ወይም ይዘት ላይ መቃወሚያ ሲኖረው የሚቀርብ ነው፡፡ይህ ዓይነቱ መቃወሚያ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ*.111 *እና* 112 *የተዘረዘሩትን ነገሮች የሚመለከት ነው፡፡*

(1) በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 111 ላይ የተመለከቱት ነገሮች ስናይ፤ ማንኛውም የክስ ማመልከቻ፡-

- ቀንና ዓመት ምህረት የተፃፈበትና የተፈረመበት ፣
- የተከሳሹን ስም የያዘ ፣
- ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል መሰረታዊ ነገር ያካተተ ፣
- ወንጀሉ የተፈፀመበትን ጊዜና ስፍራ የሚያሳይ ፣
- የተበደለውን ሰው ስም ወይም ወንጀሉ የተፈፀመበትን ንብረት (ተገቢ በሆነ ጊዜ) የሚያመለክት፣
- ተከሳሹ ወንጀሉን ሲፈጽም ተላልፏል የተባለዉን የሕግ ዓንቀፅ የያዘ መሆን አለበት፡፡

(2) በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 112 የተመለከተው ደግሞ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል ለይቶ ኣውቆ መልስ ለመስጠት እንዲችል እያንዳንዱ ክስ ወንጀሉንና ሆኔታውን በዝርዝር መግለፅ እንዳለበት ነው፡፡ በተለይም የተከሰሰበት ህግ አነጋገርና የክሱ ዝርዝር አነጋገር በጣም ሊመሳሰል ይገባል፡፡ የተለያየ ከሆነ ክሱ ሁለት ይሆናል ማለት ነዉ፤ አንዱ በተጠቀሰዉ ህግ የተመለከተዉን ወንጀል ሌላዉ ደግሞ በዝርዝሩ የተመለከተዉን ወንጀል የሚመለከት ክስ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ የቱን ወንጀል እንደሚከላከል ግራ ሊጋባ ስለሚችል ይህ ድንጋጌ በጥብቅ ሊሰራበት ይገባል፡፡

ስለዚህ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 111 ወይም 112 ላይ ከተመለከቱት ሁኔታዎች (ነገሮች) ኣንዳንዶቹ በክሱ ማመልከቻ ላይ ያልተካተቱ ሆነው ያገኛቸው እንደሆነ ተከሳሹ በመቃወሚያ መልክ ሊያነሳቸው ይችላል፡፡

ሁለተኛው አይነት መቃወሚያ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 130(2) ላይ የተደነገገው ነው፡፡ በዚህ ንኡስ ቁጥር ስር በመቃወሚያነት ሊነሱ የሚችሉ በርከት ያሉ ምክንያቶች ተዘርዝረው የሚገኙ ሲሆን፤ ኣብዛኛዎቹ የመቃወሚያ ነጥቦች በተከሳሹ ወይም በጠበቃው ብቻ ሊነሱ የሚችሉ ናቸው፡፡ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 130(2)(ሐ) መሰረት የይርጋ ጊዜን ኣስመልክቶ የሚቀርብ ተቃውሞ ግን ተከሳሹ ባያነሳውም ዓቃቤ ሕጉ

ሊያነሳው ይችላል ወይም ፍ/ቤቱ በራሱ ውሳኔ ክሱን መዝጋት አለበት (የወ/ሕግ ቁ 216(2))፡፡ ፍ/ቤቱ ሌላ ማድረግ ያለበት የተከሳሹ ፍፁም ወይም ከፊል ሃላፊነት አጠራጣሪ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ሁሉ ተከሳሹ ተቃውሞ ባያቀርብም ስለዚሁ ነገር ልዩ እውቀት ያለውን የአዋቂ አሳብ መጠየቅ ነው፡፡ ቢያስፈልግም በተከሳሹ ጠባይ፣ ባለፈ ህይወት ታሪኩና በሁኔታዎቹ ላይ ምርመራ እንዲደረግ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል /የወ/ህ/ቁ 51/፡፡

በተለይ ተከሳሹ የአእምሮ በሽታ ያለበት ወይም በሚጥል በሽታ የሚታወክ ለመሆኑ፤ ወይም መስማትና መናገር የሚሳነው ለመሆኑ ወይም አእምሮን በሚያደነዝዝ ነገር ወይም በመጠጥ አዘውታሪነት በሽታ የተለከፈ ለመሆኑ የሚያመለክቱ ሁኔታዎች በተገኙ ጊዜ ፍ/ቤቱ ለዚሁ ልዩ እውቀት ያለውን ሰው አሳብ የመጠየቅ ግዴታ አለበት (የወ/ሕግ ቁ 51)፡፡

በመቃወሚያነት መቅረብ የሚችል ምን እንደሆነና መቃወሚያው ማንሳት ያለበት ማን እንደሆነ ካየን ዘንድ የሚቀርብበት ጊዜ መቼ ነው? የአቀራረቡስ ፎርም ምን መሆን አለበት የሚለውን ማየት አስፈላጊነቱ አጠያያቂ አይደለም፡፡

ተከሳሹ መቃወሚያ ካለው ማቅረብ ያለበት ክሱ ከተነበበለት በኋላ መሆኑ ከላይ ተገልጿል፡፡ ክሱ ከተነበበለት በኋላ መቃወሚያ ካለው ወድያው ማቅረብ አለበት፡፡ ክሱን ወዲያው ካልተቃወመ መቃወሚያውን በኋላ ማንሳት እንደማይችልም በመርህ ደረጃ ተደንግጓል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 130(3))፡፡ ሆኖም ይህ ድንጋጌ መርህ ብቻ ሳይሆን የመርሁን ልዩ ሁኔታም ደንግጓል፡፡ ይኸዉም፤

> "… ፍርድ ቤቱ ሲጠይቀው ተከሳሹ የክሱን ማመልከቻ ወድያው ካልተቃወመ በቀር ቆይቶ እንዲህ ያለውን መቃወሚያ ነገሩ በሚሰማበት በሌላ ጊዜ ሊያነሳ አይችልም፡፡ ስለሆነም መቃወም የሚችለው መቃወሚያው የሚፀና ፍርድ ከመስጠት የሚያግድ በሆነ ጊዜ ብቻ ነው፡፡"

የሚል ነው፡፡

እዚህ ላይ መነሳት የሚገባው ጥያቄ "የሚፀና ፍርድ ከመስጠት የሚያግድ" እና ዘግይቶም ቢሆን ሊቀርብ የሚችል መቃወሚያ የትኛዉ ነው? የሚል ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ መልስ ሊሆኑ የሚችሉ ሶስት ምሳሌዎች መጥቀስ ይቻላል፡፡

1) ቁ.130 (2) (ለ) ተከሳሹ በዚሁ ክስ ከዚህ ቀደም ተከሶ ነፃ የወጣ ወይም የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠበት መሆኑ ወይም
2) ቁ.130 (2) (ሐ) ክስ የቀረበበት ወንጀል በይርጋ ሕግ የታገደ ወይም ምሕረት ወይም የኣዋጅ ምሕረት (ይቅርታ) የተደረገለት መሆኑን ወይም
3) ቁ.130 (2) (ሰ) ለፈፀማቸው ተግባሮች ሃላፊ ያለመሆኑን ባመለከተ ጊዜ ነው፡፡

የመጀመሪያው ምሳሌ ብንመለከት በስነ ስርዓት ሕጉ ብቻ የተቀመጠ ሳይሆን በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት ዓንቀፅ 23 ላይም "ማንኛዉም ሰው በወንጀል ሕግና ስነ ስርዓት መሰረት ተከሶ የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኛነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና ኣይከሰስም ወይም ኣይቀጣም" በሚል መልኩ ተገልፆ ይገኛል፡፡ በሁለተኛው ምሳሌ የተጠቀሰ ይቅርታን በተመለከተም ሕገ መንግስተዊ እውቅና ያገኘ ነው (ዓንቀፅ 71 (7)) ፡፡ እንዲሁም የይርጋ ጉዳይ በፍርድ ቤት ሳይቀር መነሳት ያለበት መቃወሚያ በመሆኑና ለተግባሩ ሃላፊ ያለመሆን ጥያቄም ኣስገዳጅ ድንጋጌ ሆኖ በወንጀል ሕግ የሰፈረ በመሆኑ ክሱ እንደተነበበ ወድያው ባይቀርቡም የሚፀና ፍርድ ከመስጠት የሚያግዱ በመሆናቸው በማንኛውም ጊዜ ሊነሱ የሚችሉ መቃወሚያዎች ናቸው፡፡

**መለማመጃ 29**

በበታች ፍርድቤት በታየ የወንጀል ክስ ጉዳይ ተከሳሹ ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት ከተወሰነበት በኋላ ይግባኝ አቀረበ፡፡ ከይግባኝ ቅሬታዎቹ መሃል አንዱ ነገሩ የይርጋ ጊዜ ያለፈበት ሆኖ እያለ የበታች ፍርድቤት ክሱን በይርጋ ታግዷል ብሎ ማሰናበት ሲገባዉ አይቶ ፍርድ መስጠቱ ተገቢ አይደለም፣ ስለዚህ የበታች ፍርድቤት ዉሳኔ ይሻርልኝ የሚል ነዉ፡፡ ይግባኝ ሰሚዉ ዳኛ እርስዎ ስለሆኑ ዐቃቤህግ ለዚህ ቅሬታ መልስ እንዲሰጥ አደረጉ፡፡ ዐቃቤህግም ይህ ክርክር በበታች ፍርድቤት ክሱ በተሰማ ጊዜ ሊቀርብ የሚገባዉ መቃወሚያ ነዉ፣ በይግባኝ ጊዜ ሊቀርብ አይገባም፣ ዉድቅ ይደረግልኝ ብሎ ተከራከረ፡፡

*በዚህ የቅሬታ ነጥብ ላይ የሚሰጡት ዉሳኔ ምንድን ነዉ?ይጻፉት*

በሌላ አጋጣሚ በርስዎ ችሎት በይግባኝ እየተከራከሩ ያሉት ወገኖች ይህን ነጥብ አላነሱም እንበል፡፡ ሆኖም እርስዎ ይግባኝ ሰሚዉ ዳኛ ይግባኙን ሲመረምሩ ክሱ በቀረበ ጊዜ በህግ የተፈቀደዉ የክስ ማቅርቢያ ጊዜ አልፎ የነበረ መሆኑን አስተዋሉ፡፡

*በዚህ ጊዜ የሚሰጡት ዉሳኔ ከላይኛዉ ይለያልን? ይጻፉት*

*የመቃወሚያ ኣቀራረቡ ዘዴ ሲታይ ደግሞ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 130 (1) ወይም (2) መሰረት የሚቀርበው መቃወሚያም ሆነ ዓቃቤ ሕጉ ለመቃወሚያው የሚሰጠው መልስ ሁሉ በቃል መቅረብ እንዳለበት ከወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 131 (1) መረዳት ይቻላል፡፡ ተደጋጋሚ ስልጠናዎች እየተሰጡ ኣሁን ኣሁን እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም በተግባር ሲሰራበት የነበረና ኣሁንም ሙሉ በሙሉ ተቀርፏል ብሎ በኣስተማማኝ መናገር የማይቻለው፤ መቃወሚያ ለማቅረብ ጊዜ መስጠት፣ መቃወሚያው በፅሑፍ ማቅረብ፣ ዓ/ሕግ የመቃወሚያው ግልባጭ እንዲደርሰው ማድረግ፣ ዓ/ሕግ በሚሰጠው ቀነ ቀጠሮ መልሱን በፅሑፍ ማቅረብ፣ ተከሳሹ በበኩሉ የመልስ መልስ በፅሑፍ ለማቅረብ ጊዜ መዉሰድ፣ በመጨረሻ ፍ/ቤቱ የተከሳሽን መቃወሚያና የዓ/ሕግን መልስ ከሕጉ ጋር ኣገናዝቦ ብይን ለመስጠት ቀጠሮ መያዝ፤ ምናልባት ምርመራው ያላለቀ ከሆነ ተለዋጭ ቀጠሮ መስጠት፣ ወዘተ የመሰለዉን ሂደት ተከትሎ መስራት ነዉ፡፡ ይህ የተንዛዛ ኣካሄድ ሕጉ ከሚያዘው ውጭ መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡*

**መለማመጃ 30**

*በችሎት ዐቃቤህግነት በቀረቡበት አንድ ክስ ላይ ተከሳሹ የክሱን ፎርምና ይዘት አስመልክቶ መቃወሚያ አቀረበ፡፡ እርስዎም በዚህ ላይ መልስ ለመስጠት ጠየቁ፣ ፍርድቤቱ በንዲህ አይነት መቃወሚያ ላይ ዐቃቤህግ መልስ እንዲሰጥ አይጠበቅም በማለት መቃወሚያዉን መርምሮ ዐቃቤህግ ክሱን ያሻሽል ብሎ ትዕዛዝ ሰጠ፡፡ በትዕዛዙ አሰጣጥ ቅሬታ ስላለዎት በቀጠሮዉ ቀን ቀርበዉ በዚህ ትዕዛዝ መሰረት ከመፈጸማችን በፊት ለመቃወሚያዉ መልስ እንድንሰጥ ይደረግልን በማለት አመለከቱ፡፡ ፍርድቤቱም ትዕዛዙ ያልተፈጸመበት ምክንያት በቂ አይደለም በማለት ዐቃቤህግ ክሱን አስተካክሎ ባቀረበ ጊዜ ክሱ ይቀጥላል እስከዚያዉ ተከሳሽ ከክሱ ተሰናብቷል ዋስትና ተከልክሎ ከታሰረበት እንዲፈታ የሚል ትዕዛዝ ሰጠ፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ይግባኝ እንበል የሚል ሃሳብ ለሥራ ባልደረባዎ አቀረቡ፡፡ የሥራ ባልደረባዎ ስለመቃወሚያ አቀራረብና አወሳሰን በሥነሥርዓት ህጉ የተደነገጉትን በመጥቀስ ፍርድቤት የክስን ፎርምና ይዘት በተመለከተ በሚነሱ መቃወሚያዎች ላይ ዐቃቤህግ መልስ እንዲሰጥ የመጋበዝ/የመጠየቅ ግዴታ የለበትም፣ ስለዚህ ክሱን አሻሽሎ በማቅርብ እንዲቀጥል ማድረግ የተሻለ ነዉ የሚል ሃሳብ አቀረቡ፡፡*

*እርስዎ በሃሳብዎ ጸንተዉ ይግባኝ ያቀርባሉ ወይስ ከባልደረባዎ ሃሳብ ጋር ይስማማሉ? ምክንያቶችዎን ወይም ክርክሮችዎን በዝርዝር ይጻፉ*

*በዚህ ጉዳይ ይግባኝ ቀረበ እንበል፡፡ ይግባኙ የቀረበልዎ ይግባኝ ሰሚ ዳኛ እንደሆኑ ያስቡ፡፡*

*በዚህ ቅሬታ ላይ የሚሰጡትን ዉሳኔ ይጻፉ*

*ከመቃወሚያ ጋር ተያይዞ ሌላ መታየት ያለበት ነጥብ በመቃወሚያነት መቅረብ ያለበት በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.130 ላይ ከተዘተዘሩት ምክንያቶች ሲገኝ ብቻ ነው ወይስ ከዚያ ውጭ የሆኑ ምክንያቶች ሲገኙም ማቅረብ ይፈቀዳል የሚለው ነው፡፡ በዚህ ዙርያ ሁለት ኣስተሳሰቦች ይራመዳሉ፡፡ በአንድ በኩል በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.130 ላይ ባይሸፈንም የክሱ መሰማት ሂደት እንዳይቀጥል የሚያደርጉ ሌሎቸ ምክንያቶች በተገኙ ጊዜም ተከሳሽ እንዲያነሳ ሊፈቀድለት ይገባል የሚሉ ኣሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.130 ሌላ የመቃወሚያ ነጥብ በማይጨምር ሁኔታ ዘርዝሮ ያስቀመጠ በመሆኑ ከዚያ ውጭ የሚቀርብ ተቃውሞ ተቀባይነት ሊያገኝ ኣይገባም የሚል ሓሳብ የሚያራምዱ አሉ*

**መለማመጃ 31**

በእርስዎ ችሎት ከቀረቡት የወንጀል ክሶች በአንዱ ላይ ተከሳሹ ቀርቦ ክሱን ከሰማ በኋላ ፍርድቤቱ ነገሩን ለማየት ሥልጣን የለዉም ምክንያቱም የነፍስ ግድያ ወንጀል በመሆኑና ፍርድቤቱ የወረዳ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት ስለሆነ የሚል መቃወሚያ አቀረበ፡፡

ዐቃቤህግ ይህ በሥነሥርዓት ህጉ ዉስጥ ለክስ መቃወሚያነት ተብሎ ያልተመለከተ በመሆኑ መቃወሚያዉ ዉድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራከረ፡፡

*በዚህ ክርክር ላይ ይወስኑ፣ ዉሳኔዉን ይጻፉ*

*በመቃወሚያ ላይ የመወሰን ሂደት፦*

በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 130(2) መሰረት የሚቀርበውን ማንኛውንም መቃወሚያ ፍርድ ቤቱ በመዝገቡ ከፃፈ በኋላ ዓ/ሕጉ መልስ እንዳለው ይጠይቃል፡፡ የቀረበውን መቃወሚያ ሕግን በመጥቀስ ለመወሰን የሚቻል ከሆነ ወይም ዓ/ሕጉ መቃወሚያውን ካልተቃወመ ፍ/ቤቱ ወድያው ይወስናል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 131(1))፡፡ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማጣራት ማስረጃ መቅረቡ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘውና ማስረጃ ሳይቀርብ ወድያው ውሳኔ (ብይን) መስጠት የማይቻል በሆነ ጊዜ አስፈላጊው ማስረጃ እንዲቀርብ ማዘዝ ይችላል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 131(3))፡፡ የተፈለገው ማስረጃ አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ ፍ/ቤቱ ወዲያው ውሳኔ መስጠት እንዳለበት የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 131 (4) ይደነግጋል፡፡

ፍርድ ቤቱ በመቃወሚያው ላይ የሚሰጠው ውሳኔ /ብይን/ እንደየመቃወሚያው ዓይነት ሊለያይ ይችላል፡፡ ይኸዉም፡-

ሀ) የቀረበው መቃወሚያ የሕግ ድጋፍ የሌለው ከሆነ ወይም በማስረጃ ካልተደገፈ መቃወሚያውን ውድቅ ያደርጋል ፣

ለ) በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 130/2/ለ/፣ /ሐ/ መሰረት የቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት ካገኘ ክሱን ዘግቶ ተከሳሹን ያሰናብታል ፣

ሐ) በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.130/2/ሀ/ መሰረት የቀረበ መቃወሚያ ከሆነ ጉዳዩ በተጀመረበት ፍ/ቤት እንዲቀጥል በማዘዝ መዝገቡን ይዘጋል ፣

መ) በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 130(2) (መ) መሰረት የቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት ካገኘ ክሱ ተነጥሎ እንዲታይ ያዝዛል ፣

ሠ) በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 130 /2/ሠ/ የቀረበ መቃወሚያ ከሆነ ኣስፈላጊው ፈቃድ እስኪሰጥ መዝገቡን ለጊዜው ይዘጋዋል ፣

ረ) በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 130/2/ረ/ የቀረበ ከሆነ ደግሞ ኣስቀድሞ መፈፀም ያለበት ስርዓት እስኪፈፀም መዝገቡን ለጊዜው ይዘጋዋል፡፡

ሸ/ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 130/2/ሰ/ የተመለከተዉ መቃወሚያ በማስረጃ ከተረጋገጠ ተከሳሹ ተገቢዉን ህክምና ወይም ጥበቃ በሚያገኝበት ቦታ እንዲቆይ በማድረግ የክሱ መሰማት ይቋረጣል /የወ/ሕግ ዓንቀፅ 48፣ 49፣ 129 እስከ 132/፡፡

**መለማመጃ 32**

በአንድ የወንጀል ክስ ተከሳሹ ክሱን በችሎት ከሰማ በኋላ በጠበቃዉ አማካኝነት ለፈጸማቸዉ ተግባሮች ኃላፊነት የሌለዉ ሰዉ መሆኑን ተከራክሮ ፍርድቤቱ በሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረት የአዋቂ ምርመራ ተደርጎለት ከባድ የአዕምሮ ህመም ያለበት ስለዚህም ስለሚያደርገዉ ነገር ምንም ግንዛቤ የሌለዉ ሰዉ መሆኑ ስለተረጋገጠ ፍርድቤቱ ‹‹መዝገቡ ተዘግቷል፣ ተከሳሹ ህክምና እንዲያገኝ በአማኑኤል ሆስፒታልና በቃሊቲ ማረሚያ ቤት ተይዞ ይቆይ›› የሚል ትዕዛዝ ሰጠ፡፡ ለበርካታ ወራት ሲታከም የቆየዉ ተከሳሽ ከሞላ ጎደል ወደ መልካም ጤንነት ተመለሰ፡፡ ዐቃቤህጉም ተከሳሹ የዳነ ስለሆነ የተዘጋዉ መዝገብ ተከፍቶ ክሱ መሰማቱ ይቀጥልልኝ በማለት አመለከተ፡፡ ሆኖም ፍርድቤቱ ተከሳሹ ኃላፊነት የሌለዉ ሰዉ በመሆኑ ክሱ የተዘጋ ስለሆነ አሁን ቢድንም ክሱ እንደገና አይታይም በማለት ማመልከቻዉን ሳይቀበለዉ ቀረ፡፡ ዐቃቤህጉም ይግባኝ አቀረበ፡፡ ዋና ይዘቱም የተከሳሹ ህመምተኛ መሆን የተረጋገጠዉ በመቃወሚያ ጊዜ ነዉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ክሱ ሊቀጥል ስለማይችል መዘጋቱ ተገቢ ነበር አሁን ግን ተከሳሹ ስለዳነ ክሱ ሊሰማ ይችላል፡፡ ከክሱ ነጻ ሊወጣ የሚችለዉ ማስረጃዎች ቀርበዉ ክሱን በመከላከያ ማስረጃ አስተባብሎ መሆን አለበት እንጂ ለመቃወሚያዉ መሰረት የነበረዉ ሁኔታ ከተወገደ በኋላ ክሱ የማይቀጥልበት ምክንያ የለም የሚል ነዉ፡፡

*ዳኛዉ እርስዎ ነዎት፡፡ ይግባኙ ላይ ዉሳኔ ይስጡ፣ ይጻፉት*

## 2.3.3 ክስን ማሻሻል እና ክስን ማንሳት

ኣአንድ ክስ ፍርድ /ውሳኔ/ ከመሰጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ፍ/ቤቱ በራሱ ኣስተያየት ወይም በባለጉዳዩች ማመልከቻ በቀረበለት ጊዜ ተሻሽሎ እንዲቀርብ ሊያዝዝ እንደሚችል በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ. 119 ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ይህ ሕግ እንደሚያመለክተው በተከሳሹ ላይ በቀረበው ክስ ዋና ስህተት የተገኘ ሲሆን ወይም ያልተጠቀሰ ነገር ሲገኝና ይኸውም ተከሳሹን የሚያሳስት ወይም ያሳሳተ በመሰለ ጊዜ እንደ ነገሩ ሁኔታ ክሱ እንዲለወጥ ወይም እንዲጨመር ወይም ኣዲስ ክስ እንዲዘጋጅ ፍ/ቤቱ ማዘዝ ይችላል፡፡ ስለዚህ የክስ ማሻሻል ውጤት በክሱ ላይ ለውጥ ማድረግ ወይም መጨመር ወይም ኣዲስ ክስ ማዘጋጀት ነው፡፡

በዚህ የሕግ ቁጥር ዙርያ ሲያከራክር የነበረና ኣሁንም እያከራከረ ያለው ነጥብ ክስን የማሻሻል ዓላማ በሚመለከት ነው፡፡ ክስን የማሻሻል ዓላማ ተከሳሹን ሊያሳስትና ሊጎዳ የሚችል ስሕተት ያለበት ሆኖ ሲገኝ (ለተከሳሹ ጥቅም ሲባል የሚደረግ) ነው የሚሉ እንዳሉ ሁሉ፣ ለተከሳሹ ጥቅም ብቻ ተብሎ ሳይሆን ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት የማያስችል ስህተት ሲገኝም ክስ መሻሻል አለበት ብለው የሚከራከሩ አሉ፡፡ የመጀመርያው ሓሳብ የሚደግፉ ሰዎች ለክርክራቸው መሰረት አድርገው የሚወስዱት ዓንቀፅ 119 ብቻ ሲሆን፣ ሁለተኛውን አማራጭ የሚደግፉ ደግሞ የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.119 ከቁ.118 በማጣመር ሊታይ ይገባል ይላሉ፡፡ የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.118 እንደሚያመለክተው "… ስህተቱ ወይም ሳይጠቀስ የቀረው ኣስፈላጊ ነገር ካልሆነ ወይም ስህተቱ ወይም ሳይጠቀስ የቀረው ተከሳሹን ያሳሰተው ካልሆነ ወይም ***በዚህ ምክንያት ትክክለኛ ፍርድ መስጠት የማይቻል*** ካልሆነ በቀር እንዲህ ያለ ስህተት ወይም ሳይጠቀስ የቀረው ነገር ክሱን ዋጋ ኣያሳጣውም፡፡" ይላል፡፡ ስለዚህ ከሁለቱ ቁጥሮች አገላለፅ ክስን የማሻሻል ዓላማ በአንድ በኩል ተከሳሹን እንዳያሳስትና እንዳይጎዳ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ክስ የማሻሻል ውጤቱ ተከሳሽን ሊጎዳ የሚችል ቢሆንም ትክክለኛውን ፍርድ ለመስጠት ክሱን ማሻሻል ኣስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜም ሊሻሻል እንደሚገባ የሚያንፀባርቅ ነው፡፡

ስለዚህ የወንጀል ፍትሕ ስርዓት ዓላማ የመንግስትና የህዝብ ጥቅም ፣ በወንጀሉ የተጎዳ ሰውን እና የተከሳሹን መብት ለማስጠበቅ በመሆኑ በክስ ማሻሻል ሂደትም

የተከሳሹን መብት ለማስጠበቅ /ለመጠበቅ/ ብቻ ሳይሆን በኣጠቃላይ የፍትሕ ስርዓቱን ለማሳካት ሲባልም ሊደረግና ግምት ውስጥ ሊገባ የሚገባው ነው፡፡ ለዚህም የወ/መ/ሥ/ሥ/ቁ 118 – 3 መመልከት በቂ ይሆናል

**መለማመጃ 33**

አንድ ተከሳሽ ተራ ግድያ ፈጽሟል ተብሎ ክስ ቀርቦበታል፡፡ ይህን ክስ ከሰማ በኋላ ተከሳሹ በክሱ ላይ መቃወሚያ የለኝም፣ ክሱ ግልጽ ነዉ፣ ወንጀሉን አልፈጸምኩም፣ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት በመከራከሩ ዐቃቤህግ ክሱን አስረዳለሁ ብሎ ማስረጃ ለማቅረብ ቀጠሮ ባስያዘበት ቀን ምስክሮች ከመቅረባቸዉ በፊት አግኝቷቸዉ ሲያነጋግራቸዉ ተከሳሹ ከተከሰሰበት ወንጀል የከፋ ወንጀል መፈጸሙን ሊያስረዱ እንደሚችሉ ስለተረዳ ክሱን ለማሻሻል እንዲፈቀድለት ሊያመለክት ወሰነ፡፡ በዚህ መሰረት በቀጠሮዉ ቀን ቀርቦ ማስረጃ ከማሰማቱ በፊት ክሱን ለማሻሻል ጠየቀ፡፡ ፍርድቤቱ የሚፈቅድ ከሆነም የተስተካከለ የክስ ማመልከቻ ይዞ መቅረቡንና ለፍርድቤቱ እና ለተከሳሽ በችሎት ማድረስ የሚችል መሆኑን ገለጸ፡፡

*የተከሳሹ ተከላካይ ጠበቃ ቢሆኑ ምን ክርክር ሊያቀርቡ ይችላሉ?*

*እንደዐቃቤህግ ሆነዉ ክርክርዎን በየትኛዉ ህግ ያሳምናሉ?*

*የችሎቱ ዳኛ ቢሆኑ በዚህ ክርክር ላይ ምን ትዕዛዝ ይሰጣሉ? ይጻፉት*

**መለማመጃ 34**

በችሎትዎ በቀረበ የወንጀል ክስ የወንጀሉ ጊዜ በዝርዝር ስላልተገለጸ ተከሳሹ ጊዜዉ ተለይቶ ይገለጽ፣ ለመከላከል ያስቸግረኛል፣ ዓመቱ ብቻ ሳይሆን ወር፣ ቀንና ሰዓት ሊገለጽ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ሆኖም ዐቃቤህግ ጊዜዉ በበቂ ሁኔታ የተገለጸ ስለሆነ መቃወሚያዉ ዉድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሮ ችሎትዎም በዚህ ነገር አምኖ መቃወሚያዉ ዉድቅ ከተደረገ በኋላ ክሱ በሚሰማበት ጊዜ ምስክሮች ወንጀል የተፈጸመበትን ጊዜ በክሱ ከተገለጸዉ ዓመት የተለየ አድርገዉ መመስከር ሲጀምሩ ዐቃቤህግ ክሱ የጊዜ አገላለጹ ተከሳሹን የሚያሳስት በመሆኑ ላሻሽል የሚል ጥያቄ አቀረበ፡፡ ተከሳሹም ይህ ጥያቄ ቀደም ሲል ተነስቶ ዐቃቤህግ የጊዜ አገላለጹን ተገቢ ነዉ ብሎ ተከራክሮ ፍርድቤቱም አምኖበት ቀሪ የተደረገ ከመሆኑም በላይ ክሱ በአሁኑ ደረጃ የሚያሳስተኝ አይደለም ግልጽ ነዉ፣ በዚሁ ታይቶ ሊወሰን ይገባል በማለት ተቃወመ፡፡

*የሚሰጡትን ትዕዛዝ ይጻፉት*

**መለማመጃ 35**

*በሌላ አጋጣሚ በቀረበልዎት ክስ ማመልከቻዉ የተጣሰዉን ህግ በተሟላ ሁኔታ የማይጠቅስ ሆኖ አገኙት - ለምሳሌ «የወ/ህ/ቁ/407 የሚደነግገዉን በመተላለፍ» የሚል ነዉ፡፡*

*ዐቃቤህግ ክሱን ላሻሽል በማለት ጠየቀ፡፡ ተከሳሹ ግን ሊሻሻል አይገባዉም በዚሁ ሊቀጥል ይገባል በማለት ተከራከረ፡፡*

*የርስዎ ዉሳኔ ምን እንደሚሆን በህግ የተደገፈ ምክንያት በመግለጽ ይጻፉ፡፡*

ሌላ ሊነሳ የሚገባው ነጥብ ክስን የማሻሻል ጥያቄ መቅረብ ያለበት "…ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ…" መሆኑን የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁጥር 119 ስለሚያመለክት ይህ ድንጋጌ የተፋጠነ ፍትሕ እንዳይሰጥ ሂደቱ የተጓተተ እንዲሆን ምክንያት አይሆንም ወይ? የሚል ነው፡፡

ለምሳሌ አንድ የወንጀል ጉዳይ የተከሳሹ መከላከያ ማስረጃ እስከተሰማበት ጊዜ አንድ ዓመት ፈጅቷል እንበል፡፡ ከዚያ በኋላ የክስ መሻሻል ጥያቄ ቢቀርብና ቢፈቀድ የክርክሩ ሂደት አንድ ብሎ ስለሚጀምር ተጨማሪ አንድ ዓመት ሊወስድ ይችላል ማለት ነው፡፡

**መለማመጃ 36**

*ክሱ የመከላከያ ማስረጃ እስከመስማት ከተካሄደ በኋላ ዐቃቤህግ ክሱ በከባዱ ወንጀል ሊሆን ስለሚገባዉ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ክሴን ላሻሽል ብሎ አመለከተ፡፡ በርግጥም ሲቀርብ የነበረዉ የዐቃቤህግ ማስረጃ በከባዱ ወንጀል ሊከሰስ የሚገባዉ እንደነበረ ያመለክታል፡፡ ሆኖም ተከሳሹ ባቀረበዉ ተቃዉሞ ነገሩ ከዚህ በኋላ አዲስ ሊደረግ አይገባም ከዚህ በኋላ ማስረጃዎቼን እንደገና ፈልጌ ማግኘት አልችልም በዚሁ ፍርድ ሊሰጥ ይገባል በማለት ቢቃወምም በቀረበዉ መከላከያ ማስረጃ መሰረት ተከላክሏል አልተከላከለም የሚለዉ ሳይወሰን በፊት ፍርድቤቱ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ በሚል ምክንያት ክሱ አስቀድሞ እንዲሻሻል አዘዘ፡፡ በዚሁ መሰረት ክሱ ቀርቦ የዐቃቤህግ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ ተከሳሹ እንዲከላከል ታዘዘ፡፡ በዚህ ጊዜ የተከሳሹ ምስክሮች ሊገኙ አልቻሉም፡፡ በዚህ ምክንያት ክሱን አልተከላከለም ጥፋተኛ ነዉ ተብሎ ቅጣት ተወሰነበት፡፡ በዚህ ፍርድ ላይ ይግባኝ ሲል የክስ መሻሻሉን ሂደት በተመለከተ ቅሬታ አቀረበ፡፡*

*ይግባኝ በሚሰማዉ ፍርድቤት ዳኛ እንደሆኑ በማሰብ በዚህ ቅሬታ ላይ የሚሰጡትን ዉሳኔ ይጻፉ፡፡*

ክስን የማሻሻል ውጤት ምን እንደሆነ ወይም ክስ እንዲሻሻል ከተፈቀደ በኋላ መደረግ ያለበት ነገር ምን እንደሆነ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ 120 እና 121 ተደንግጓል፡፡ ቁጥሮቹ እንደሚያመለክቱት፤ ኣንዱ ውጤት ዓ/ሕግ ያቀረበው የተሻሻለ ክስ ግልባጭ ለተከሳሹ እንዲደርሰው ይደረግና የክስ መሰማቱ ሂደት እንደ ኣዲስ ይጀምራል፡፡ ቀጥሎ፡ ዓ/ሕግ ማስረጃውን ያሰማል፤ ተከሳሽም የመከላከያ ማስረጃ ካለው ያቀርባል፡፡

## *ክስ ስለማንሳት፡-*

ከክስ ማንሳት ጋር በተያያዘ የተለያዩ ህግጋት ክስን ለማንሳት ዐቃቤህግ ሥልጣን ያለዉ መሆኑን ይደነግጋሉ፤ ለምሳሌ የፌዴራል አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣዉ አዋጅ ቁ 691/2003 የፍትህ ሚኒስቴርን ሥልጣንና ተግባር በሚወስነዉ ክፍሉ ይህን ሥልጣን ይሰጠዋል፡፡ ይህንም በህግ መሰረት እንደሚፈጽመዉ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ህግ የሚለዉ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 122 ሲሆን ይህ ህግ የተሻረ በመሆኑ በምን ህግ መሰረት ክስ ይነሳል የሚል ጭብጥ የክርክር መነሻ ሲሆን አዘዉትሮ ይስተዋላል፡፡ በሌላዉ ወገን ደግሞ ይህ ድንጋጌ በሙሉ ስላልተሻረ ህግ አለ ማለት ነዉ፣ ስለዚ በዚህ መሰረት ክስ ማንሳት ይቻላል የሚል ክርክር ይነሳል። ስለዚህ ጥያቄዉ ይህ ህግ ተፈጻሚነት አለዉ ወይ የሚለዉ ነዉ፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ክስ ማንሳት የሚቻለዉ በሂደቱ የትኛዉ ደረጃ ላይ ነዉ የሚለዉም ጥያቄ መልስ የሚሻ ነዉ፡፡

**መለማመጃ 37**

ዐቃቤህግ ባቀረበዉ ክስ ምስክሮቹን አቅርቦ አሰምቶ ሲያበቃ ችሎትዎ ዐቃቤህግ ክሱን አስረድቶ እንደሆነ ለመበየን ቀጠሮ ይዘዉ ባሉበት ጊዜ ዐቃቤህግ ክሱን ለማንሳት ማመልከቻ በጽ/ቤትዎ አቀረበ፡፡ የቀረበዉን ማስረጃ በሰሙበት ጊዜ እንደሚያስታዉሱት እና በመሃሉ አንድ ጊዜ እንደመረመሩት ክሱን ሊያስረዳ የሚችል አይደለም፡፡ በዚህ ምክንያት ተከሳሹን መከላከል ሳያስፈልገዉ ከክሱ በነጻ ይሰናበት የሚል ብይን እያዘጋጁ ይገኛሉ፡፡

*በዚህ የዐቃቤህግ ጥያቄ ላይ የሚሰጡትን ዉሳኔ ይጻፉ፡፡*

በሌላ በኩል ብይኑን አዘጋጅተዋል፡፡ ይህንንም በችሎት ለማሰማት ጉዳዩን ሲጠሩ ዐቃቤህግ ብይኑ ከመነገሩ በፊት ክሴን አንስቻለሁ የሚል ማመልከቻ በጽሁፍ አድርጎ አቀረበ፡፡

*ምን እንደሚወስኑ ይጻፉ፡፡*

ከዚህ በተለየ ሁኔታ ችሎትዎ ተከሳሽን ተከላከል ብሎ የተከሳሽን መከላከያ ማስረጃ ሰምቶ አብቅቶ ለፍርድ ቀጥሮታል ብለዉ ያስቡ፡፡ መከላከያ ማስረጃዉን በችሎት እንደሰሙትም ሆነ በቀጠሮዉ መሰረት እንደመረመሩት ክሱን በግልጽ የሚያስተባብል ነዉ፡፡ ዐቃቤህግ ምናልባትም ይህን ስለሚያዉቅ ይሆናል ክሴን አንስቻለሁ የሚል ማመልክቻ በጽ/ቤት አቀረበ፡፡

*በቀጠሮዉ ዕለት የሚሰጡትንና የሚያሰሙትን ዉሳኔ ይጻፉ፡፡*

ወይም መከላከያዉን በሰሙበትም ሆነ በመረመሩበት ጊዜ በነበረዉ አቋምዎ መሰረት ፍርዱን አዘጋጅተዉ ተከሳሹ ክሱን የተከላከለ መሆኑን የሚገልጽ ፍርድ አዘጋጅተዋል፡፡ ይህንኑ ለመንገር በችሎት በተሰየሙበት ጊዜ ዐቃቤህግ ማመልከቻ አለኝ ብሎ ክሴን አንስቻለሁ የሚል ማመልከቻ አቀረበ፡፡

*የተለየ ዉሳኔ ይሰጣሉ? ዉሳኔዎን ይጻፉ*

*መለማመጃ* **38**

*በአንድ የነፍስ ግድያ ወንጀል ክስ ጉዳይ ዐቃቤህግ ምስክሮቹን ማግኘት ስላልቻለ ከተደጋጋሚ ቀጠሮ በኋላ ምስክሮች እስኪገኙ ክሱ ይቋረጥ ቢባል ተከሳሹ በተከሳሽነት ሳይፈረድበትና ክሱ ሳይታይ ያላግባብ ስለሚያቆየዉ ምስክሮቹን ባገኘ ጊዜ ክሱን ለመቀጠል እስከዚያዉ ክሱን በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.* 122 *መሰረት አነሳለሁ በማለት አመለከተ። ፍርድቤቱ ተከሳሽን ሃሳቡን በመጠየቅ በዚህ ነገር እንደሚስማማ ካረጋገጠ በኋላ ዐቃቤህግ ክሱን ለማንሳት የጠቀሰዉ ህግ የተሻረ ስለሆነ እና ወንጀሉም ከባድ ወንጀል በመሆኑ ክሱን ማንሳት አይችልም፣ ምስክሮቹን ካሉበት ፈልጎና አስፈልጎ ያቅርብ በማለት ለዚሁ እንዲሆን የሰባት ወር ቀጠሮ በመስጠት ወሰነ።*

*ዐቃቤህጉ እርስዎ ቢሆኑ በዚህ ትዕዛዝ ላይ የሚወስዱት ርምጃ ምንድን ነዉ? ክሱን ትቶ በቀጠሮ ዕለት መቅረት ወይስ ይግባኝ ብሎ ማስቀየር?*

*ዐቃቤህግ በዚህ ጉዳይ ላይ ይግባኝ እንዳቀረበ እና ይግባኝ ሰሚዉ ዳኛ እርስዎ እንደሆኑ በማሰብ በዚህ ነገር ላይ ዉሳኔ ይስጡ ይጻፉት*

ክስ ማንሳት በአሁኑ ጊዜ ገደብ ያልተደረገበት በመሆኑ ወይም የነበሩበት ገደቦች የተሻሩለት ሂደት በመሆኑ የክስ ማንሳት ጥያቄ በዐቃቤህግ ሲቀርብ ፍርድቤቶች ሊቀበሉት የሚገባ ይመስላል፡፡ ሆኖም በዚህ ጊዜ የክስ ማንሳቱ ተግባር በተከሰሰዉ ሰዉ ላይ የሚያስከትላቸዉን የመብት ጉዳቶች ይኖሩ እንደሆን ፍርድቤቶች ሊመረምሩ የሚገባ መሆኑን በዚህም ክስ ማንሳትን ይከለክሉ እንደሆነ በዉይይት ሊዳብር የሚገባዉ የተግባር መመሪያ ነዉ፡፡

## 2.3.4 ዕምነት ክህደት ስለመስጠት

***ስለዕምነት ቃል፦***

በአጠቃላይ ስለ እምነት ቃል ሲወሳ ሁለት ነገሮች ወደ ኣእምሮኣችን ይመጣሉ፡፡ እነሱም ዓ/ሕግ እና ተከሳሽ በሚያደርጉት ስምምነት (Plea bargaining) በተከሳሹ የሚሰጥ እምነት ቃል ኣንዱ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ተከሳሹ ክሱን በሚሰማዉ ፍርድ ቤት ፊት ቀርቦ ክሱን ከተነበበለት በኋላ የሚሰጠው የእምነት ቃል (Plea of guilty) ነው$

የእምነት ቃል ለመስጠት መስማማትን በዋነኝነት በኮመን ሎው የሕግ ስርዓት ተከታይ ኣገሮች የሚታወቅ ሆኖ ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች (ዓ/ሕግና ተከሳሽ) የሚስማሙት፤ ተከሳሽ የእምነት ቃል እንዲሰጥና በአንፃሩ ደግሞ ዓቃቤ ሕግ በተከሳሹ ላይ የሚያቀርበው ክስ

እንዲቀንስ ወይም ተመስርቶ የነበረ ክስ ቀንሶ እንዲያነሳ ወይም ቅጣት እንዲቀልለት ለፍርድ ቤት ሓሳብ ማቅረብ ነው$ በእነዚህ አገሮች አብዛኛዎቹ የወንጀል ጉዳዮች ውሳኔ የሚያገኙት በእምነት ቃል መሰረት ነው$ ለዚህ ኣሰራር መምጣት ምክንያት የሆኑት ደግሞ በየጊዜው የሚጨምረውን የፍ/ቤት ጉዳዮች ብዛት የማቃለል ፍላጎትና የክርክር ስርዓት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተወሳሰበ መምጣት ነው ይባላል$

በኢትዮጵያ የሕግ ስርዓት መጀመሪያ የተከሳሹ እምነት ክህደት ቃል ከመጠየቁ በፊት ተከሳሹ የቀረበበትን ክስ በሚገባ እንዲረዳው ፍ/ቤቱ የክሱን ዝርዝር ለተከሳሹ ማስረዳት አለበት (የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ132(1) እና ሕገ መንግስት ቁ 20(2)) $ በመሆኑም ፍ/ቤቱ ለተከሳሹ መግለፅ ያለበት ነገር፤ የወንጀሉን ዝርዝር፣ ወንጀሉን የሚያቋቁሙ የሕግ፣ የሞራል እና የግዙፍ ተግባር ጠባዮች ሁሉ (የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ 111(1)(ለ) እና የወ/ሕግ ቁ 23))፣ ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ሊወሰንበት የሚችለውን የቅጣት ዓይነትና የቅጣቱ መነሻና ጣሪያ፣ የተከሳሹን ሕገ መንግስታዊ መብቶች ማለትም፣ ያለመናገር መብቱን፣ ክሱን ለማመን ወይም ለመካድ ሙሉ መብት እንዳለው እና ጥፋተኛነቱን ማረጋገጥ የዓ/ሕግ ግዴታ መሆኑንና ጥፋተኛነቱ በማስረጃ እስኪረጋገጥ ንፁህ ሆኖ የመገመት መብት ያለው መሆኑን ነው$ ኣስፈላጊው ገለፃ ከተደረገለት በኂላ ተከሳሹ የቀረበለትን ክስ መፈፀሙንና ጥፋተኛ  መሆኑን የሚያምን ወይም የሚክድ መሆኑን ፍ/ቤቱ ይጠይgል$

ተከሳሹ በክሱ ማመልከቻ ላይ የተዘረዘረውን ወንጀል መፈፀሙን ያመነ እንደሆነ ፍ/ቤቱ የእምነት ቃሉን ወድያው መቀበል የለበትም $ ቃሉን ከመቀበሉ በፊት ተከሳሹ ሙሉ በሙሉ ያመነ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት $ ኣንድ ተከሳሽ ለቀረበበት ክስ ሙሉ በሙሉ ኣምኗል የሚባለው መቼ ነው? የሚል ጥያቄ በዚህ አጋጣሚ ማንሳት ተገቢነት አለው $ ተከሳሹ ወንጀሉን ፈፅሜያለሁ ብሎ ማመኑ ብቻ ሙሉ በሙሉ ማመኑን ኣያረጋግጥም $ ሙሉ በሙሉ ኣምኗል ለማለት የሚከተሉትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ሀ) ተከሳሹ የወንጀሉን ዝርዝር በትክክል መረዳቱን ጠይቆ ማረጋገጥ ፣

ለ) የተከሳሹን የእምነት ቃል ፍ/ቤቱ ከተቀበለው ወድያው የጥፋተኛነት ውሳኔ እንደሚሰጥና ተከሳሹ የመከላከል ዕድል እና ጥፋተኛነቱን አስመልክቶ በይግባኝ የማስለወጥ መብት እንደማይኖረው መረዳቱን ማረጋገጥ፣

ሐ) ወንጀሉን መፈፀሙን ያለምንም ተጽዕኖ እያመነ እንደሆነ ይህንኑ ከተከሳሹ ጠይቆ ማረጋገጥ ፣

መ) ተፅዕኖ ደርሶበት እንደሆነ ያለ ፈቃዱ እንዲያምን መገደድ እንደሌለበት መረዳቱን ማረጋገጥ፣

ሠ) በክስ ማመልከቻው ላይ የተዘረዘረውን የወንጀሉን አፈፃፀም ዝርዝር ተከሳሹ ፈፀምኩ ከሚለው አገላለፅ (አነጋገር) ጋር በማስተያየት እንዲሁም ተከሳሹ ቢክድ ኖሮ ዓ/ሕግ ሊያቀርብ ያዘጋጀውን ማስረጃ በአጭሩ በመጠየቅ ተከሳሹ ወንጀሉን ለመፈፀሙ የሚያሳዩ መሰረታዊ እውነታዎች (Factual basis) መኖራቸውን ማረጋገጥ አለበት $

ይህን ሁሉ ማጣሪያ ካደረገ በኂላ ፍ/ቤቱ ሁለት ኣማራጮች ይኖሩታል፡፡ ይኸውም በተከሳሹ እምነት ቃል ላይ ጥርጣሬ ካደረበት ዓ/ሕግ ማስረጃውን አቅርቦ እንዲያሰማ ለማዘዝና ተከሳሹም የመከላከያ ማስረጃውን እንዲያቀርብ ለመፍቀድ ይችላል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 134(2)) $ ባደረገው ማጣሪያ የተከሳሹን የእምነት ቃል ከተቀበለው ግን ተከሳሹ ጥፋተኛ ነኝ ብሏል በማለት ከመዘገበ በኋላ በተከሳሹ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ይሰጣል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 134/1/)፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚገባው ነጥብ የስነ ስርዓት ሕጉ በተከሳሹ እምነት ቃል ብቻ ውሳኔ ሊሰጥባቸው የሚችሉና የእምነት ቃል ቢኖርም ከወንጀሉ ከባድነት ኣንፃር ታይቶ ማስረጃ ሊሰማባቸው የሚገባ የወንጀል ዓይነቶች ለይቶ ኣለማስቀመጡ ነው $ በልምድ እንደሚሰራበት ግን በዕድሜ ልክ ወይም በሞት ሊያስቀጣ በሚችል ወንጀል /ወይም ሌሎች ከባድ የሚባሉ ወንጀሎች/ የተከሰሰ ሰው ወንጀሉን ስለመፈፀሙ ቢያምንም ፍ/ቤቱ ማስረጃ እንዲቀርብ ሲያዝዝ ይስተዋላል$

በተግባር በተደጋጋሚ እንደሚታየው ተከሳሹ የተከሰስኩበትን ወንጀል ፈፅሜያለሁ፣ ጥፋተኛ ነኝ በማለት የእምነት ቃሉን ሲሰጥ ወንጀሉን ለምንና እንዴት እንደፈፀመው የሚያመለክት ዝርዝር ሁኔታ ሲገልፅ አይታይም ፣ ፍ/ቤቱም ይህን ዝርዝር ነገር

እንዲገልፅ አያደርግም /ለምሳሌ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤት በይግባኝ ባይ እነአፈወርቅ ዘዉዴ እና ዐቃቤህግ መካከል በመዝገብ ቁ 17709 ታኅሳስ 28/97፣ በፈቃደ ደገፋ እና ዐቃቤህግ መካከል በመዝ/ቁ 14845 የወሰነዉ ክርክር ይመለከቷል/$ በሌላ መልኩ ደግሞ ተከሳሽ የሰጠው መልስ የክህደት ቃል መሆኑ በግልፅ የሚያሳይ ሆኖ እያለ የእምነት ቃል ሰጥቷል እየተባለ የጥፋተኝነት ፍርድ ሲሰጥ ይታያል $

የእምነት ቃል መስጠት የተለያየ ፋይዳ ይኖረዋል$ ይህ ጥያቄ በሶስት መንገድ ማየት ይቻላል $ ኣንደኛ፡- ተከሳሹ ለተከሰሰበት ወንጀል ያመነ እንደሆነ በማመኑ ብቻ ለቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሊኖረው ይችላል $ ከኣንዳንድ ተጨማሪ ወጪዎች (ለኣንዳንድ ነገሮች ማስፃፊያና ለመከላከያ ምስክሮች ከሚከፈል ወጪ) ሊድን ይችላል$ ሁለተኛ፡- ለፍርድ ቤቱ የስራ ጫና ይቀንስለታል፤ጊዜና ወጪ ይቆጥብለታል$ ሶስተኛ፡- በአጠቃላይ ለፍትሕ ስርዓቱ የሚኖረው ጠቀሜታ ሲታይም ወንጀለኞች ቶሎ በአፋጣኝ ሲወሰንባቸው ኅብረተሰቡ ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን እርግጠኛ ይሆናል (እፎይታ ይሰማዋል) ፤ ዋስትና ኣለኝ ይላል$ የወንጀሉ ሰለባ የሆኑ ሰዎችም ወንጀል የፈፀሙባቸው ሰዎች ቶሎ ሲቀጡ በመንግስትና በሕግ ስርዓቱ ትልቅ ኣመኔታ ያሳድራሉ፡፡

***መለማመጃ* 39**

*ተከሳሹ ተበዳይዋን እንዳትከላከል በኃይል በማስወገድ በእጇ ይዛ እየተነጋገረችበት የነበረዉን ተንቀሳቃሽ ስልክ ታግሎ በመንጠቅ ወስዶ የዉንብድና ወንጀል ፈጽሟል የሚል ክስ ቀርቧል፡፡ የተከሰሰዉ ሰዉ በችሎት ቀርቦ ክሱን ከሰማ በኋላ ተበዳይዋ በስልክ እየተነጋገረች እያለ ከኋላዋ ሳታየኝ በመምጣት ቀስ ብዬ ስልኩን በመያዝ ስስበዉ ለቀቀችዉ ይዤ ሮጥኩ በማለት ቃሉን ሰጠ፡፡*

*የችሎቱ ዐቃቤህግ እርስዎ ነዎት፡፡ ለፍርድቤቱ ማስረጃ አቅርቤ የዉንብድና ተግባር መፈጸሙን አስረዳለሁ ይላሉ ወይስ በሰጠዉ እምነት መሰረት ጥፋተኛ ይባልልኝ ይችላሉ? የሚያቀርቡትን የቃል ማመልከቻ ከዝርዝር ክርክሮቹ/ምክንያቶቹ ጋር ይጻፉት*

*በዚህ ጉዳይ ነገሩን የሚያዩት ዳኛ እርስዎ ነዎት እንበልና ዐቃቤህጉ ተከሳሹ ባመነዉ መሰረት ጥፋተኛ ይባልልኝ የሚል ማመልከቻ ቢያቀርብ የሚወስኑት ምን ይሆናል? ይጻፉት*

***ስለክህደት ቃል፡-***

***አንድ ተከሳሽ የቀረበበትን ክስ በሚመለከት መልሱን እንዲሰጥ ጥያቄ ሲቀርብለት የሚኖረዉ ሁለተኛ አማራጭ የክህደት ቃል መስጠት ነው$ ተከሳሹ ለቀረበበት ክስ ክዷል የሚባለው ምን ዓይነት ቃል ሲሰጥ ነው የሚል ጥያቄ የሚመልስልን የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ*** 133 ***ነው$ እንደ ቁ***.133 (1) ***አነጋገር ተከሳሹ ለክሱ የክህደት መልስ ሰጥቷል የሚባለው፤ ለክሱ መልስ ያልሰጠ እንደሆነ /በሕገ መንግስት ዓንቀፅ*** 19 (2) ***መሰረት የተያዙ ሰዎች*** (***ለተከሰሱ ሰዎችም ተፈፃሚነት አለው***) ***ላለመናገር መብት ስላላቸው/፣ ወይም ወንጀሉን ኣልፈፀምኩትም ጥፋተኛ ኣይደለሁም ብሎ የካደ እንደሆነ፤ ወይም በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ***.133 (2) ***እንደተመለከተው ተከሳሹ የወንጀል ድርጊቱን አምኖ ስለኣፈፃፀሙ ምክንያት ያቀረበ እንደሆነ ፤ ጥፋተኛ ኣይደለሁም ብሏል ሲል ፍ/ቤ በመዝገብ መፃፍ አለበት$ በተግባር እንደሚታየው ተከሳሹ ሙሉ በሙሉ የክህደት ቃሉን በሚሰጥበት ጊዜ*** (***ቁ***.133(1)) ***በፍርድ ቤት በኩል የሚፈፀም ስህተት ባይኖርም ወይም ግምት ውስጥ የሚገባ ባይሆንም፤ ተከሳሹ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ***.133(2) ***መሰረት የሰጠው ቃል በሚኖርበት ጊዜ ግን በስህተት ወይም ሆን ተብሎ ስራን ከእጅ ፈጥኖ ለማዉጣት ሲባል እንደ እምነት ቃል እየተወሰደ ማስረጃ ሳይሰማ ውሳኔ እንዳይሰጥ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፣ የጥፋተኝነት ቃል ስላልሆነ፡፡***

| ***መለማመጃ* 40** |
|---|
| በችሎትዎ በቀረበ የወንጀል ክስ ተከሳሹ ተጠርቶ ቀርቧል፡፡ እርስዎም ክሱን አንብበዉለት ስለክሱ በዝርዝር ካስረዱት በኂላ ክሱ ገብቶኛል፣ ነገር ግን ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት መልስ ሰጠ፡፡ ዐቃቤህጉ ግን እኛ ከክሳችን ጋር በምን እንደፈለግነዉና ይህንንም የምናስረዳበትን ማስረጃ ዝርዝርና የሰነድ ማስረጃ አያይዘን ያቀረብንለት ስለሆነ ተከሳሽ ጥፋተኛ አይደለሁም ሲል ለምን እንደሆነ ዝርዝር ክርክሩን እንዲሰጥ ይደረግልን፣ በደፈናዉ ጥፋተኛ አይደለሁም ማለት የተከሳሽን ክርክር አያሳይም፣ አንድ ሰዉ በአንድ ወንጀል ጥፋተኛ የማይሆነዉ በበርካታ ምክንያቶች ስለሆነ ከነዚህ በየትኛዉ ምክንያት እንደሆነ ሊገለጽ ይገባል፣ ይህ ካልሆነ የዐቃቤህግ ማስረጃ ከቀረበ በኂላ በዚያዉ ልክ ማስረጃ በማዘጋጀት የመከላከል ነገር ይፈጥራል፣ ወዘተ የሚል ክርክር አቀረበ፡፡<br><br>*እንደችሎቱ ዳኛ በዚህ ክርክር ላይ ይወስኑ፣ ይጻፉት* |

***<u>ስለዕምነት ክህደት መለወጥ</u>፡-***

በእኛ አገር የሕግ ስርዓት የእምነት ቃል ማሻሻልን በተመለከተ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕጉ ቁ.135 ተደንግጎ ይገኛል ፡፡ በንኡስ ቁጥር (1) እንደተመለከተው “የተሰጠው ቃል የእምነት በሆነ ጊዜ እና ፍርድ ቤቱ ክሱን መስማት በሚቀጥልበት ጊዜ ጥፋተኛ ኣይደለሁም የማለት ቃል መመዝገብ የሚገባው ሆኖ ያገኘው እንደሆነ ጥፋተኛ አይደለሁም የሚለው ቃል ይመዘግባል” ይላል$

ተሰጥቶ የነበረ እምነት ቃል እንዲሻሻል ሓሳቡን የሚያመነጨው ማን ነው? የሚል ጥያቄ መቼውም ቢሆን መነሳቱ ኣይቀርም$ ከሕጉ ኣነጋገር ኣንፃር ሲታይ ሓሳቡ የሚያመነጨው ፍርድ ቤት ብቻ ወይም ተከሳሽ ብቻ ነው ብሎ ማስቀመጥ ኣይቻልም፡፡ ተከሳሽ ራሱ ሰጥቶት የነበረ የእምነት ቃል ተሽሮ ወይም ተሻሽሎ ጥፋተኛ እንዳልሆንኩ ይመዝገብልኝ ሊል ይችላል፡፡ ፍርድ ቤትም ከተከሳሹ ኣነጋገርና ከሌላ ሁኔታ በመነሳት ጥፋተኛ ነኝ ብሏል ብሎ መዝግቦት የነበረዉን በመሰረዝ የክሕደት ቃሉን እንደሰጠ ኣድርጎ ጥፋተኛ ኣይደለሁም ብሏል ብሎ ሊመዘግብለት ይገባል$ የእምነት ቃል ማሻሻል ጥያቄ እንዲነሳ የሚያደርጉ ሁኔታዎች ወይም ምክንያቶች በሕጉ የሰፈሩ ኣይደሉም $ ስለዚህ በዋነኛነት ለፍርድ ቤቱ የተተው ይመስላሉ፡፡

**መለማመጃ 41**

**እየተሰማ ባለ ክስ ጉዳይ ተከሳሹ ክሱን እንደማይቃወም ገልጾ ወንጀሉን አልፈጸምኩም በማለት ስለተከራከረ የዐቃቤህግ ማስረጃዎች እንዲቀርቡ ከታዘዘ በኋላ ምስክሮች በክፊል ቀርበዉ ባለበት የዕምነት ክህደት ቃሌን ላስተካክል ጥፋተኛ ነኝ ይኸዉ ተመዝግቦ በዚሁ የጥፋተኛነት ዉሳኔ ይሰጠኝ ሲል አመለከተ፡፡**

*ዐቃቤህጉ እርስዎ ነዎት፡፡ በዚህ ላይ የሚያመለክቱትን ይጻፉ*

*በሌላ በኩል ዐቃቤህግ በዚሁ የዕምነት ቃል መሰረት ጥፋተኛ ይባልልኝ ብሎ ቢያመለክትና ዳኛዉ እርስዎ ቢሆኑ በዚህ ጥያቄ ላይ የሚሰጡትን ብይን ይጻፉት*

*ማስታወሻ፡- ብይንዎ በኢትዮጵያ የህግ ሥርዓት ጥፋተኛ ነኝ ተብሎ በግልጽ መልስ በተሰጠበት አጋጣሚ እንኳ ማስረጃ ተሰምቶ ሊወሰን የሚችልበት መሆኑን ከግንዛቤ ያስገባ ቢሆን ይመረጣል፡፡*

**ከእምነት ቃል ማሻሻል ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት የመጨረሻ ነጥብ ፣ እምነት ቃልን የማሻሻል ጥያቄ መቼ መቅረብ** (*መነሳት*) **እንዳለበት ነው$ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ** 135(1) **እንደተደነገገው የእምነት ቃል እንዲሻሻል ሓሳብ የሚቀርበው** “*... ፍርድ ቤቱ ክሱን መስማት በሚቀጥልበት ጊዜ ...*” **ነው** $ **የዚህን ድንጋጌ ይዘት ስንመለከት ፣ የንኡስ ቁ** (1) **ብቻ ብናይ “ፍ/ቤቱ ክሱን መስማት በሚቀጥልበት ጊዜ” የሚለውን ሓረግ የእምነት ክህደት ቃል ከተሰጠ እና የጥፋተኛነት ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ባለው ጊዜ ውስጥ እንደሚደረግ የሚያመለክት ይመስላል$ ይሁን እንጂ በንዑስ ቁ** (2) “*በተከሳሹ ላይ የተሰጠው የጥፋተኛነት ውሳኔ ውድቅ ይሆናል*” **ይላል$ ስለዚህ በድምር ሲታይ የእምነት ክሕደት ቃል እንዲሻሻል ሓሳብ ማቅረብ የሚቻለው ወይም ፍርድ ቤቱ ማንሳት የሚችለው ተከሳሹ የእምነት ክሕደት ቃሉን ካስመዘገበ ጀምሮ የጥፋተኛነት ውሳኔ እስከ ተሰጠበት ባለው ጊዜ ውስጥ መሆኑን ከሕጉ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡**

**መለማመጃ 42**

በችሎትዎ የቀረበዉ ተከሳሽ የተከሰሰበትን ከባድ የዉንብድና ወንጀል ህጉ እንደሚፈልገዉ አምኖ በዚሁ መሰረት ጥፋተኛ ነዉ ብለዉ ወስነዋል፡፡ ቅጣት ለመወሰን በአዳሪ ቀጠሮ ይዘዉ ቅጣቱን ወስነዉ በችሎት አሰምተዉ ሲጨርሱ ተከሳሹ በቀደመዉ ቀጠሮ ጥፋተኛ ነኝ ያልኩት ተበዳዩና ቤተሰቡ ወንጀሉን የፈጸምከዉ አንተ እንደሆንክ ስለምናምን አምነህ ካልተቀጣህ እኛ እንቀጣሃለን ብለዉ ስላስፍራሩኝ እንጂ ወንጀሉን አልፈጸምኩም በማለት በችሎት ተናገረ፡፡ ክሱም በማስረጃ እንዲወሰንልኝ በማለት አመለከተ፡፡

*ዐቃቤህጉ እርስዎ እንደሆኑ ያስቡና ለዚህ ክርክር ተገቢ ነዉ የሚሉትን መልስ ያመልክቱ /በጽሁፍ/*

*ዳኛዉ እርስዎ እንደሆኑ በማሰብና ዐቃቤህግ ተከሳሽ በግልጽ ወንጀሉን ለመፈጸሙ ሙሉበሙሉ አምኖ የተሰጠ ዉሳኔ ነዉ፡፡ የዕምነት ቃል መለወጥ መብት አይደለም፡፡ ስለሆነም ዉሳኔዉ በዚሁ ሊጸና ይገባል የሚል ክርክር እንዳቀረበ በመገመት የሚሰጡትን ዉሳኔ ይግለጹ /በጽሁፍ/*

## 2.4 <u>ስለማስረጃ አቀራረብ እና ስለቀጠሮ</u>

**መለማመጃ 43**

በርስዎ ችሎት የተለያዩ አስቀድመዉ የተዘጋጁ የትዕዛዝ ፎርሞችን ይጠቀማሉ፡፡ ከነዚህ ዉስጥ አንዱ በወንጀል የተከሰሰ ሰዉ እና ከሳሽ ዐቃቤህግ እንዲቀርብ ትዕዛዝ የሚሰጥበት ነዉ፡፡ በዚህ ፎርም መሰረት የከሳሽና የተከሳሽ ምስክሮችና ሌሎች ማስረጃዎች በቀጠሮዉ ቀን እንዲቀርቡ የሚያስገድድ ዐረፍተነገር አለዉ እንበል፡፡

*በዚህ መሰረት ትዕዛዝ በሚሰጡበት ጊዜ ይህን የፎርሙን አካል እንዳለ ሞልተዉ ይፈርማሉ ወይስ ይህን ክፍል በመሰረዝ ትዕዛዙን ይፈርማሉ? ከነምክንያትዎ ዘርዝረዉ ይጻፉ፣ ከባልደረባዎ ጋር ይወያዩበት፡፡*

ፎርሙን እንዳለ በመቀበል ትዕዛዙን ሞልተዉ ፈረሙ ብለን እናስብ፡፡ በዚህ መሰረት ለምስክሮች የሚደርሱት መጥሪያዎች ተዘጋጅተዉ በግራ ቀኙ በኩል ተወስደዉ ለምስክሮቻቸዉ ስለተሰጡ የግራ ቀኙ ምስክሮች ቀረቡ፡፡ ሆኖም በድንገተኛ እክል ምክንያት ተከሳሹ ሳይቀርብ ቀረ፡፡

*ምስክሮቹን በተመለከተ የሚሰጡትን ትዕዛዝ ይጻፉ*

በሌላ ሁኔታ ተከሳሽና ምስክሮቹ ሲቀርቡ የዐቃቤህግ ምስክሮች አልቀረቡም፡፡

*የተከሳሽን ምስክሮች አስመልክቶ የሚጡት ትዕዛዝ ምንድን ይሆናል? ይጻፉት*

ከላይ በተመለከቱት ሁኔታዎች ምስክሮች በተከታዩ ቀጠሮ እንዲቀርቡ ትዕዛዝ ሰጥተዋል ብለን እናስብ፡፡ በዚህ መሰረት ምስክሮች ቀረቡ፡፡ ሆኖም በመጀመሪያዉ ሁኔታ ተከሳሹ አሁንም አልቀረበም፣ በሁለተኛዉ ሁኔታ ደግሞ የዐቃቤህግ ምስክሮች አሁንም አልቀረቡም፡፡

*ስለቀረቡት ምስክሮች ትዕዛዝ ይጻፉ*

## 2.4.1 ምስክሮች ሳይቀርቡ ወይም ሳይሟሉ ሲቀሩ የሚፈጸም ሥነሥርዓት

አንድ ክስ በሚሰማበት ቀን የዐቃቤህግም ሆነ የተከሳሽ ምስክሮች ሳይቀርቡ ሲቀሩ ቀጠሮ መለወጥ ከሚቻልባቸዉ ምክንያቶች አንዱ ተደርጎ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 94/2/ለ// ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ምስክሮች በንዲህ ያለ ቀጠሮ ሳይቀርቡ የሚቀሩት አንድም ተፈልገዉ ሊገኙ ባለመቻላቸዉ መጠራታቸዉን የሚያዉቁበትን መጥሪያ ማድረስ ባለመቻሉ ነዉ፣ አለያም መጠራታቸዉን አዉቀዉ ሊቀርቡ ባለመፈለግ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መቅረብ ባለመቻላቸዉ ነዉ፡፡ ከላይ የተገለጸዉ ቀጠሮ የመለወጥ ነገር ከነዚህ ሁኔታዎች በአንዱ ወይም በሌላዉ ብቻ ወይም በሁሉም ሁኔታዎች ተፈጻሚ ይሆን እንደሆነ በህጉ ዉስጥ በግልጽ የተመለከተ ነገር የለም፡፡ ሆኖም ምስክሮች ባለመቅረባቸዉ ምክንያት ቀጠሮ ሲለወጥ ቀጠሮ የተሰጠበትን ጉዳይ ለማስፈጸም በፍርድቤት የሚሰጡ ትዕዛዞችን ባህሪ የሚደነግገዉን ህግ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 96/1/ ስንመለከት ያልቀረበዉ ምስክር ተይዞ እንዲቀርብ የሚያደርግ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ይዞ የማቅረብ ትዕዛዞችን የሚመለከተዉን የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 125 ስንመለከት ተይዘዉ የሚቀርቡ ሰዎች ምን አይነት ሰዎች እንደሆኑ ይደነግጋል፡፡

**መለማመጃ 44**

ችሎት በተሰየሙበት አንድ ዕለት ከቀረቡ ጉዳዮች አንዱ ምስክር ለመስማት ቀጠሮ የተያዘበት ነዉ፡፡ ለዚህም ምስክሮች እንዲቀርቡ ትዕዛዝ የተሰጠ መሆን መዝገቡ ያሳያል፡፡ መዝገቡ ሲጠራ ተከሳሽና ዐቃቤህግ ቀረቡ፤ የተፈለጉት የዐቃቤህግ ምስክሮች ግን አልቀረቡም፡፡ ዐቃቤህግም ፖሊስ ምስክሮቹ አድራሻቸዉን ለቀዉ የት እንደሄዱ እንደማይታወቅ የገለጸልኝ ስለሆነ ቀጠሮ ተለዉጦ ምስክሮች እንዲቀርቡ ድጋሚ መጥሪያ ይሰጥልኝ በማለት አመለከተ፡፡

ተከሳሽ በበኩሉ መጥሪያ ደርሶት ሳይቀርብ ለቀረ ምስክር እንጂ ላልተገኘ ምስክር ቀጠሮ አይለወጥም፣ ለዚህም የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 94/2/ለ/ እና 96 የሚደነግጉትን አጣምሮ ማየት ይበቃል፣ ስለዚህ ዐቃቤህግ በቀዳሚ ምርመራ ጊዜ ያስመዘገበዉ የምስክሮች ቃል ካለዉ ያቅርብ እንጂ ምስክሮቹ የት እንደሚገኙ እንኳ ሳይታወቅ እንዲቀርቡ መታዘዝ የለበትም፣ በአማራጩ ዐቃቤህግ ክሱን የማያነሳ ከሆነ ክሱ ማስረጃ የለዉም ተብሎ ብይን ይሰጥልኝ በማለት አመለከተ፡፡

*በዚህ ክርክር ላይ ተገቢ ነዉ የሚሉትን ትዕዛዝ በጽሁፍ ይስጡ*

ምስክር ባለመገኘቱ ሳይቀርብ ሲቀር ቀጠሮ መለወጥ በፍርድቤቶች አካባቢ የተለመደ ነዉ፡፡ ከህጋዊነቱ አኳያ የሚያከራክር ቢሆንም ይህ አይነቱ አሰራር የምንታገሰዉ ሆኖ ተቀብለነዉ ስንሰራበት ይስተዋላል፡፡ ሆኖም በድጋሚ በሰጠነዉ ቀጠሮ መሰረት ምስክሩ ሳይገኝና ሳይቀርብ ቢቀር የምንሰጠዉ ትዕዛዝ ቀደም ሲል ከሰጠነዉ የተለየ ሊሆን ይችል እንደሆነ እንዲሁ የሚያከራክር ይሆናል፡፡ አንድ ጊዜ ቀጠሮ መለወጥ ከጀመርን ምክንያቱ እስካልተለወጠ ድረስ ቀጠሮ የማንሰጥበት ምክንያት አይኖርም፡፡

**መለማመጃ 45**

በዳኝነት በሚሠሩበት ችሎት በዕለቱ ከተያዙት ቀጠሮዎች አንዱ የአንድ ተከሳሽን መከላከያ ምስክሮች ለመስማት የተያዘ ነዉ፡፡ ለዚህ እንዲረዳ ተከሳሽ ምስክሮቹን እንዲያቀርብ መጥሪያ ተሰጥቶት ከወሰደ በኋላ ሊያገኛቸዉ ስላልቻለ የፍርድቤቱን መጥሪያ እንዳልሰጣቸዉ በመግለጽ ቀጠሮ እንዲለወጥለት አመለከተ፡፡ ዐቃቤህግ ስላልተቃወመ፣ ሆኖም ለመጨረሻ ጊዜ እንዲታዘዝ ስለጠየቀ ቀጠሮ ለዉጠዉ መጥሪያ በድጋሚ አዘዙ፡፡ ሆኖም አሁንም ተከሳሹ ምስክሮቹን ሊያገኛቸዉ እንዳልቻለ፣ ስለዚህ ምስክሮቹ በጣም የሚያስፈልጉት ስለሆነ ሳይሰሙ ፍርድ ቢሰጥ የመከላከል መብቱን አንደሚጎዳዉ በመግለጽ በድጋሚ መጥሪያ እንዲሰጠዉ አመለከተ፣ አያይዞም የዐቃቤህግ ምስክሮች በተደጋጋሚ ፍለጋ የቀረቡና የተሰሙ ከመሆኑም በላይ በተለያየ ጊዜ ተከፋፍለዉ እየተንጠባጠቡ ቀርበዉ ስለተሰሙ በተመሳሳይ የኔንም ምስክሮች አቀራረብ ፍርድቤቱ ታግሶ ሊጠብቅ ይገባል በማለት አመለከተ፡፡ ዐቃቤህግ ግን ከዚህ በኋላ ምስክር እንዲቀርብ ሊታዘዝ አይገባም፣ እኛ ክሳችንን ያስረዳን ስለሆነ ተከሳሽ ፈጥኖ ካልተከላከለ ባቀረብነዉ ማስረጃ መሰረት ፍርድ ሊሰጥ ይገባል እንጂ የመከላያ ምስክር ለማቅረብ ቀጠሮ ሊለወጥ አይገባም በማለት በጽኑ ተከራከረ፡፡

*ተገቢ ነዉ የሚሉትን ትዕዛዝ ይጻፉ*

በምስክሮች አቀራረብ ዙሪያ የሚታይ ሌላዉ ችግር የምስክሮች ተንጠባጥቦ መቅረብን የሚመለከት ነዉ፡፡ ቀደም ባለዉ ጊዜ በቀጥታ ለፖሊስ፣ አሁን አሁን ደግሞ ለዐቃቤህግ ፍርድቤት በሚሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረት ምስክሮች እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡ ነገር ግን ይህን ትዕዛዝ ሁልጊዜ አሟልቶ መፈጸም ማስቸገሩ አይቀርም፡፡ ስለዚህ በከፊል ምስክሮች በርከት በሚሉባቸዉ ጉዳዮች ሁሉም ምስክሮች በአንድ ጊዜ እንዲቀርቡ ማድረግ ሲያዳግት ይስተዋላል፡፡ በዚህ የተነሳ የምስክሮች አሰማም የተዘበራረቀ ሆኖ ይታያል፡፡ አንዳንድ ችሎቶች ምስክሮች ካልተሟሉ አንሰማም በማለት ቀጠሮ ሲለዉጡ ሌሎች

ደግሞ ይህ ምክንያት ቀጠሮ ለመለወጥ በቂ አይደለም፣ የቀረበ ምስክር ሊመለስ አይገባም በሚል የቀረበን ምስክር መስማት እስከቻሉ ድረስ መስማትን ይመርጣሉ፡፡

**መለማመጃ 46**

በአንድ ችሎት በአንድ ዕለት ከቀረቡት መዝገቦች ዉስጥ በአንዱ ምስክሮች እንዲቀርቡ ቀጠሮ ተይዟል፡፡ በዚህ መሰረት መዝገቡ ተጠርቶ ምስክሮች ቀርበዉ እንደሁ ሲጠየቅ ሁለት ምስክሮች መቅረባቸዉን አሳወቁ፡፡ በዚህ ጉዳይ እንዲቀርቡ ታዝዞ የነበረዉ አምስት ምስክሮችን ነዉ፡፡ በዚህ ጊዜ ፍርድቤቱ በተለምዶ እንደሚደረገዉ ዐቃቤህግ ምን እንደሚያመለክት ጠየቀ፡፡

*የችሎቱ ዐቃቤህግ እርስዎ ቢሆኑ ለፍርድቤቱ ምን ያመለክታሉ? ይጻፉት*

*የችሎቱ ዳኛ እንደሆኑ ያስቡ፣ ባልደረባዎን እንደዐቃቤህግ ሃሳባቸዉን ይቀበሉ፣ በጉዳዩ ላይ ተገቢዉን ትዕዛዝ በጽሁፍ ይስጡ*

በተመሳሳይ ሁኔታ የዐቃቤህግ ምስክሮችና ኤግዚቢት እንዲቀርቡ በሚታዘዝበት ጊዜ የማስረጃ መንጠባጠብ ይከሰታል፡፡ በዚህ ጊዜ የምስክሮች ተሟልቶ አለመቅረብ እንዳለ ሆኖ ምስክሮች ቀርበዉ ኤግዚቢት የማይቀርብበት አጋጣሚ የበዛ ነዉ፡፡ ከኤግዚቢት ማስረጃ ባህሪ አኳያ የማስረጃ አሰማም ላይ ከፍተኛ ችግር ይፈጥራል፡፡ ኤግዚቢት በምስክር አማካኝነት ካልሆነ በራሱ ለፈራጁ ወገን የሚናገረዉ ነገር ብዙም አይደለም፣ ምስክሮች ይህን ማስረጃ እንዴት፣ የት፣ መቼ፣ ለምን፣ ከማን፣ በማን እንደተያዘ ካልገለጹ በቀር ማስረጃዉ ግዑዝ ነገር ነዉ፡፡

በዚህ አይነት ማስረጃዉ ተንጠባጥቦ ሲቀርብ ምስክሮች /ኤግዚቢት ባይቀርብም/ የሚሰሙበት አጋጣሚ በርካታ ነዉ፡፡ በተለይ የኤግዚቢት አለመቅረብ ብዙም ትኩረት ሲሰጠዉ አይስተዋልም፡፡ አንዳንዴ ኤግዚቢት ቢኖርም እንዲቀርብ ሳይታዘዝ ሲዘነጋ ይታያል፡፡ በዚህ ጊዜ ኤግዚቢት አይቀርብም፣ እንዲሁም እንዲቀርብ ታዝዞ ሳይቀርብ ይቀራል፡፡ በዚህ ጊዜ ምስክሮች ከቀረቡ ይሰማሉ፡፡ ከዚህ ሁሉ በኋላ ማለትም ምስክር ከተሰማ፣ ነገሩ ካለቀ በኋላ ፖሊስ ወይም ዐቃቤህግ ኤግዚቢት የተባለዉን ነገር ለፍርድቤቱ ይዘዉ በመቅረብ ይመዝገብልን የሚል ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡

**መለማመጃ 47**

በአንድ ክስ ጉዳይ ኤግዚቢትና ምስክሮች እንዲቀርቡ ታዝዞ በተቀጠረበት ዕለት መዝገቡ ተጠርቶ ምስክሮች በከፊል መቅረባቸዉ ተረጋገጠ፡፡ ኤግዚቢትና ከፊሉ ምስክሮች አልቀረቡም፡፡ ችሎቱ ዐቃቤህግን ምን እንደሚያመለክት ጠየቀ፡፡

*ዐቃቤህጉ እርስዎ እንደሆኑ በማሰብ በዚህ ጉዳይ ላይ ያመልክቱ፣ ይጻፉት*

በዚህ ጉዳይ ዐቃቤህግ ምስክሮች ያልተሟሉ ስለሆነና ኤግዚቢት ባልቀረበበት ሊመሰክሩ ስለማይገባ ዛሬ የቀረቡት ምስክሮች በሚቀጥለዉ ቀጠሮ ያለመጥሪያ እንዲቀርቡ ተነግሯቸዉ ኤግዚቢቱን ፖሊስ ዛሬ ያላቀረበበትን ምክንያት ከመግለጽ ጋር እንዲያቀርብ ታዝዞ ሌላ ቀጠሮ ይሰጠን በማለት አመለከተ፡፡ ተከሳሹና ጠበቃዉ ግን ይህን በጽኑ ተቃወሙ፣ ምስክር ቀርቦ እያለ ያልቀረበ ምስክር እስኪቀርብ ተብሎ እንዲመለሱ ማድረግ በሚቀጥለዉ ቀጠሮ ሳይቀርቡ ቢቀሩ ለሌላ ቀጠሮ ስለሚዳርግ አሁን እንደቀረቡ ምስክሮቹ ይሰሙልን፣ አለበለዚያ በተገቢዉ ፍጥነት ፍርድ የማግኘት መብቴን ይጎዳል የሚል ክርክር አቀረቡ፡፡

*ዳኛዉ እርስዎ እንደሆኑ አስበዉ በዚህ ክርክር ላይ ይወስኑ፣ ይጻፉት*

በችሎትዎ ከታዩት ጉዳዮች በአንዱ የመከላከያ ማስረጃ ከሰሙ በኋላ መዝገቡን ለፍርድ ሊቀጥሩ ሲዘጋጁ በችሎቱ የተገኘዉ ዐቃቤህግና ፖሊስ አንድ ነገር አመለከቱ፡፡ ይኸዉም ለክሱ የተጠቀሰ ኤግዚቢት በምስክሮች ሲጠቀስ የነበረዉ ዕቃ ዛሬ ይዘነዉ ስለቀረብን በፍርድቤቱ መዝገብ ላይ በማስረጃነት ይመዝገብልን የሚል ማመልከቻ ነዉ፡፡ በዚህ ጊዜ ተከሳሹ በጠበቃዉ አማካኝነት ምስክሮች ይህን የተባለዉን ዕቃ አይተዉ ስላልመሰከሩ ሲጠቅሱት የነበረዉ ይህ ዕቃ ይሁን ሌላ ማረጋገጥ በማይቻልበት ሁኔታ ይህ ኤግዚቢት ሊቀርብ አይገባም፣ ምስክሮች ዕቃዉን እያዩ ስለዚህ ዕቃ የሚመሰክሩትን ዕቃዉን እያየን በመስቀለኛ ጥያቄ ሳንመረምር ማስረጃ ተብሎ ሊመዘገብ አይገባም በማለት ተቃወመ፡፡

*ዳኛዉ እርስዎ ቢሆኑ የሚወስኑትን ይጻፉ*

## 2.4.2 ምስክሮች ስለመስማት

### 2.4.2.1 የዐቃቤህግ ማስረጃ አሰማም እና በማስረጃዉ ላይ የሚሰጥ ዉሳኔ

#### *ሀ) የዓ/ሕግ ምስክር መስማት*

*በተከሳሹ ላይ የቀረበው ክስ መሰረት ባለው ፍሬ ነገር ላይ የተመሰረተ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ የግድ መሰማት ይኖርበታል፡፡ ይህ አስፈላጊ የሆነበት ምክንያትም በዘመናዊው የዳኝነት አሰራር ሓቁን አንጥሮ ለማውጣት ብቸኛው መንገድ ክስን መስማት* /Trial/ *በመሆኑ ነው፡፡*

ተከሳሹ ለቀረበበት ክስ መልስ ካልሰጠ ወይም የተከሰሰበትን ድርጊት አልፈፀምኩም ብሎ የካደ እንደሆነ፣ ከሳሹ ወገን /አብዛኛው ጊዜ ዓቃቤ ሕግ/ ያቀረበውን ክስ ያስረዱልኛል የሚላቸውን ማስረጃዎች አቅርቦ በማሰማት ማስረዳት አለበት፡፡ በመሆኑም ዓ/ሕግ አንድን የወንጀል ክስ ከመመስረቱ በፊት፡

ሀ/ ተፈፀመ የተባለው ድርጊት በሕግ የሚያስጠይቅ መሆኑን እና

ለ/ የሚያስጠይቅ ነው ቢባል እንኳ ማስረዳት የሚቻል መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

ከሳሽ ወገን እንደ ክሱ በሚገባ ማስረዳት የሚጠበቅበት ምክንያት፡

- የትኛዉም ሰዉ እስኪፈረድበት ድረስ ንጹህ ሆኖ እንዲታሰብ መብት ስላለዉ
- ንፁህ ሰው ባልሰራው ወንጀል እንዳይቀጣና እንዳይበደል ለመጠንቀቅ፣
- የወንጀል ቅጣት አንዴ ከተፈፀመ የደረሰውን ጉዳት ወደኋላ ተመልሶ ማስተካከል ስለማይቻል ከመቅጣት በፊት አጥፊነትን አስቀድሞ በሚገባ ማረጋገጥ አስፈላጊ ስለሆነ፣
- ተከሳሹ አንዴ ጥፋተኛ ነው ተብሎ ከተቀጣ በህዝብ ዘንድ ስሙና ታሪኩ ስለሚጎድፍ ፣ የወደፊት ዕድሉ ስለሚበላሽና የቀደሞ ስሙን ለመመለስ ከባድ በመሆኑ ከፍተኛ ጥንቃቄ ለማድረግ

ተብሎ ነው፡፡

ዓ/ሕጉ ምስክሮቹን ከማሰማቱ በፊት ያቀረበውን ክስና የሚያቀርበውን ማስረጃ ዓይነት በአጭሩና ያለ አድልዎ በመግለፅ ክሱን መክፈት አለበት (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.136(1)፡፡ ይህም በተለምዶ ጭብጥ እየተባለ የሚጠራውና በክሱ የተዘረዘሩ ፍሬ ነገሮችን የሚያረጋግጥለት ማስረጃ የቱ መሆኑን ዓ/ሕጉ የሚገልፅበት ነው፡፡ በዓ/ሕግ የቀረቡ ምስክሮች በክሱ ፍሬ ነገር ላይ ያላቸው እውቀት ሊለያይ ይችላል፤ የሰነድ ማስረጃ ካለውም ምስክሮች የማያውቁትን ፍሬ ነገር የሚያስረዳለት ሊሆን ይችላል፣ ሌላ የማስረጃ ዓይነት ካለም እንዲሁ፡፡ ይህ ሁኔታ ሲኖር ዓ/ሕጉ ማን ምን እንደሚያስረዳለት በሚገባ ዘርዝሮ ማስቀመጥ አለበት፤ ፍ/ቤቱም ይህን ሳያስደርግ ማለፍ የለበትም፡፡

በልምድ እንደሚሰራበት ግን ዓ/ሕግ ስለጭብጡ ሓሳቡን እንዲያቀርብ (እንዲገልፅ) ሲጠየቅ ምስክሮቹ የሚያስረዱልኝ እንደ ክሱ ነው በማለት በጣም ኣጠቃላይ በሆነ መልኩ ሲያስቀምጥ ይታያል፡፡ ይሁን እንጂ ከላይ እንደተገለፀው ምስክሮቹ በተፈፀመው ወንጀል ያላቸውን እውቀት የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡

የዓ/ሕግ ማስረጃ የሰነድ በሚሆንበት ጊዜም የሚሰተዋል ችግር አለ፡፡ የሰነድ ማስረጃው ኣስቀድሞ ከፍርድ ቤቱ መዝገብ እንደሚያያዝ ግልፅ ነው፡፡ ሆኖም ማስረጃ በሚሰማበት ቀን ዓ/ሕግ ስለሰነድ ማስረጃው ዋና ይዘትና ሊያስረዳው የሚችል ነገር ምን እንደሆነ ለፍ/ቤቱ መግለፅ ሲገባው ይህን ሳያደርግ የሚቀርበት ሁኔታ በተደጋጋሚ ይታይል፡፡ ፍ/ቤቱም ትኩረት ሳይሰጠው ይቀራል፡፡

**መለማመጃ 48**

*በችሎትዎ የቀረበዉን ክስ ከነሰነድ ማስረጃዉና የምስክሮች ዝርዝር ለተከሳሹ እንዲደርስ ትዕዛዝ ሰጥተዉ ለተከሳሹ ስለደረሰ ተከሳሹ በቀጠሮዉ ቀን ቀረበ፡፡ ክሱ ከተነበበለት በኋላ ለክሱ መልስ ለመስጠት እንዲችልና መከላከያዉን ማዘጋጀት እንዲችል የዐቃቤህግ የማስረጃ ዝርዝር ብቻ ሳይሆን ማስረጃዉ ምን ለማስረዳት እንደቀረበ መግለጫ ጭምር ሊኖረዉ ይገባል በማለት ተከራከረ፡፡*

*ዐቃቤህግ እንደሆኑ በማሰብ ለዚህ ክርክር የሚሰጡት የመልስ ክርክር ምንድን ነዉ? ይጻፉት*

*ዳኛ እንደሆኑ ያስቡና፣ ዐቃቤህግ ተከሳሹ ያቀረበዉን ጥያቄ ዉድቅ ይሁን በማለት ቢከራከር ምን ይወስናሉ? ይጻፉት*

እንግዲህ ዓ/ሕግ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ 136(1) መሰረት ስለ ክሱና ምስክሮቹ ሓሳቡን ከገለፀ በኋላ ምስክሮቹንና በምስክርነት የሚቀርቡ ልዩ እውቀት ያላቸው ሰዎች (ኤክስተርቶች) እንዳሉ ይጠራል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.136(2))፡፡ በመሰረቱ ዓ/ሕግ ማቅረብ የሚችለው በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.124 መሰረት ባቀረበው ዝርዝር ላይ የተጠቀሱትን ምስክሮች ነው፡፡ ሆኖም ግን በዝርዝሩ ላይ ያልተጠቀሱ ምስክሮች እንዲቀርቡለት ዓ/ሕግ ከጠየቀና ፍ/ቤቱም ምስክርነታቸው ለነገሩ ኣስፈላጊ መሆኑን ካመነበት እንዲሰሙ መፍቀድ ይችላል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.143(2)) ፡፡ ይህም የሚሆነዉ በተለምዶ በዝርዝሩ ዉስጥ ያሉት ምስክሮች ተሰምተዉ ካበቁ፣ ወይም የሚፈለጉት ያህል ከተሰሙ በኋላ ነዉ፡፡

እንዲሁም ክሱ በከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲታይ የቀረበ በሆነ ጊዜ በቀዳሚ ምርመራ ፍርድ ቤት ያልተሰሙ ምስክሮችንም ቢሆን ዓ/ሕጉ የፈለገውን ምስክር ስምና የሚሰጠውን ምስክርነት ዓይነት ለተከሳሹ በፅሑፍ ገልፆ መጥራት እንደሚችል በሕጉ ተመልክቷል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.143(3)) ፡፡ የሚጠሩትን ምስክሮች ዝርዝርና የሚያስረዱትን ነገር ለተከሳሹ እንዲገልፅ የሚገደድበት ምክንያት ደግሞ ተከሳሹ ለመከላከል እንዲችል ሁኔታው እንዲመቻችለት ለማድረግ ነው፡፡ በተጨማሪም የነገሩ መሰማት ከተጀመረ በኋላ ክስ የተሻሻለ ወይም የተለወጠ እንደሆነ ለክሱ ከተሰሙት ምስክሮች ውስጥ ማንኛውንም እንደገና አስጠርቶ እንዲሰማ የማድረግ መብት አለው (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.121)፡፡

ምስክሮች የምስክርነት ቃላቸውን ከመስጠታቸው በፊት መማል ወይም እውነትን ለመናገር ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ ይህ ስነ ስርዓት ተደረገ ለማለት ብቻ የሚደረግ ሳይሆን ተከሳሽን ጥፋተኛ ወይም ነፃ የማስደረግ ውጤት ስላለው ትልቅ ግምት ሊሰጠው የሚገባ ነው፡፡ ምስክሩ "እምላለሁ" ማለትን ሃይማኖቱ የማይፈቅድለት ወይም ምናልባት ሃይማኖት የሌለው ከሆነ "እምላለሁ" በማለት ፋንታ "አረጋግጣለሁ" ካለ በቂ እንደሆነ ተደርጎ መወሰድ ኣለበት፡፡ ልምዱ እንደሚያሳየን ምስክሩ ክርስትያን ከሆነ መፅሓፍ ቅዱስ ይዞ ፣ ሙስሊም ከሆነ ደግሞ ጣቱን ወደ ላይ ከፍ ኣድርጎ ወይም ቁርዓን ይዞ ይምላል፡፡ የስነ ስርዓት ሕጉ ግን ምስክሩ ምን ይዞ ወይም እንዴት መማል እንዳለበት የሚለው ነገር የለም፡፡ ስለዚህ መፅሓፍ ቅዱስ ወይም ቁርዓን ይዞ ወይም ጣቱን ወደ ላይ ከፍ አድርጎ እንዲምል ማስገደድ ኣስፈላጊ ኣይደለም፡፡ በሌላ በኩል ግን እውነቱን ኣለመመስከር ወይም በሓሰት መመስከር በወንጀል ሕግ እንደሚያስጠይቅ እንዲያውቁት መንገር ተገቢ ነዉ፡፡ የወንጀል ሕጋችን በቁ 453 እንዳመለከተው ፤

> "(1) *የዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ያለው ስርዓት በሚካሄድበት ጊዜ ምስክር ሆኖ የቀረበ ማንም ሰው ማንኛውንም ተከራካሪ ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት አስቦ ሓሰተኛ ምስክርነት ወይም የልዩ ኣዋቂነት ኣስተያየት የሰጠ እንደሆነ ወይም እውነቱን የደበቀ እንደሆነ፤*

*(2) ምስክሩ እውነቱን ለመናገር ምሎ ወይም ማረጋገጫ ሰጥቶ እንደሆነ ... ቅጣቱ ከአስር ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እስራት ነው፡፡..."*

ስለዚህ እውነቱን ካልተናገረ የሚያስከትልበት ቅጣት ከባድ መሆኑን ኣውቆ እንዲመሰክር ሊነገረው ይገባል፡፡ በተለይ በአሁኑ ጊዜ መለኮታዊ ሃይልን አለመፍራት እየሰፋ በመሄዱ በመለኮታዊ ኃይል ስም የሚደረግ የዕዉነት ማረጋገጫ የሚያስጨንቅና ዕዉነትን ብቻ ለመናገር የሚገፋፋ መሆኑ እየቀነሰ ስለመጣ የቀረዉ አማራጭ ለመሃላ ፈጻሚዉ ቅርብ የሆነዉን የመንግሥትን ኃይልና ኃላፊነት ማስታወስ ነዉ፡፡

ሌላ መፈፀም ያለበት ስነ ስርዓት፣ ፍ/ቤቱ የያንዳንዱን ምስክርነት ሲቀበል መጀመሪያ የምስክሩን ስም፣ አድራሻውን፣ ስራውንና ዕድሜውን እንዲሁም መሐላ ማድረጉን ወይም እውነት ለመናገር ማረጋገጡን መጥቀስ አለበት (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 147(1)) ፡፡ እንዲሁም ምስክሩ ከተከሳሹ ወይም ከተበዳዩ ጋር ያለው ዝምድና ወይም ቅርበት ወይም ፀብ (ጥላቻ) መጠየቁ ጠቃሚ ነው፡፡ ጠቃሚ የሆነበት ምክንያትም በማስረጃ ምዘና ጊዜ የማስረጃን ክብደት ለመወሰን ስለሚረዳ ነዉ፡፡

እያንዳንዱ የዐቃቤ ህግ ምስክር ማንነቱ ከተረጋገጠ በኋላ መጀመሪያ ዓ/ሕጉ ዋና ጥያቄ፣ ከዚያም ተከሳሹ ወይም ጠበቃው መስቀለኛ ጥያቄ፣ ቀጥሎም ዓ/ሕጉ ድጋሚ ጥያቄ ይጠይቁታል፡፡ በመጨረሻም በተለምዶ ፍርድቤት ማጣሪያ ጥያቄ ይጠይቃል፡፡

ዋና ጥያቄ የሚባለው ምስክሩን ያቀረበው ወገን በመጀመሪያ የሚያቀርበው ጥያቄ ሲሆን ኣላማውም ምስክሩን የጠራው ወገን በክርክሩ ያለውን ኣቋም እንዲደግፍለት ለማድረግ ሲሆን ምስክሩም በጭብጥ ስለተያዘው ፍሬ ነገር በቀጥታም ሆነ ቀጥታ ባልሆነ መንገድ የሚያውቀውን እንዲያስረዳ ለማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም በዋናው ጥያቄ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ስለ ክርክሩ ፍሬ ነገር ተገቢ የሆኑትንና ምስክሩ በቀጥታ ወይም ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ስለሚያውቃቸው ፍሬ ነገሮች ብቻ ነው፡፡ በዋና ጥያቄ ጊዜ ተከሳሹ ወይም ጠበቃው ካልፈቀደ ዓ/ሕጉ መሪ ጥያቄ መጠየቅ እንደማይችል ተደንግጓል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 137(1)(2))፡፡ መሪ ጥያቄ የተከለከለበት ምክንያትም ምስክር ኣቅራቢው ወገን እንዲመለስለት የሚፈልገውን ፍሬ ነገር በጥያቄ መልክ

ለምስክሩ ማቀበል ስለሌለበትና ምስክሩ ያላረጋገጠውን ፍሬ ነገር እንደተረጋገጠ በማስመሰል በማለፍ ወሳኝ የሆነ ፍሬ ነገር መኖር አለመኖሩ ሳይታወቅ መታለፍና ስህተት መፍጠር ስለሌለበት ነው፡፡

መስቀለኛ ጥያቄ የሚባለው ምስክሩን ያቀረበው ወገን ዋና ጥያቄ ጠይቆት እንዳበቃ ሌላኛው ወገን የሚያቀርበው ጥያቄ ነው፡፡ የመስቀለኛ ጥያቄ ዓላማ በዋናው ጥያቄ በተሰጠው መልስ ውስጥ ያለውን የስህተት ቃል፣ የሚያጠራጥር ወይም እውነት ያልሆነውን ቃል ለፍ/ቤቱ ለመግለፅና ለማስተባበል ነው (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.137 (3))፡፡ ስለሆነም በዋና ጥያቄ ከተነሳው ነጥብ ጋር የማይገናኝ ወይም ወደዚያ የማያመራ አዲስ ነገር በመስቀለኛ ጥያቄ መጠየቅ አይቻልም፡፡ ሆኖም በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ መሪ ጥያቄ መጠየቅ ይቻላል፡፡

ድጋሚ ጥያቄ ምስክሩ መስቀለኛ ጥያቄ ተጠይቆ ካበቃ በኋላ ምስክሩን ያቀረበው ወገን የራሱን ምስክር ለሁለተኛ ጊዜ የሚጠይቀው ጥያቄ ነው፡፡ የድጋሚ ጥያቄ ዓላማም ተከሳሹ ወይም ጠበቃው በመስቀለኛ ጥያቄ ያነሳውን ነገር ለማጣራት ብቻ የሚቀርብ ጥያቄ ነው (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.139) ፡፡ ስለዚህ በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ ከተነሳው ጉዳይ ጋር ግንኙነት የሌለው ወይም አዲስ ነገር በድጋሚ ጥያቄ ጊዜ ማንሳት አይቻልም፡፡

**መለማመጃ 49**

ምስክር እየተሰማበት ባለ አንድ ጉዳይ ዐቃቤህግ ያቀረበዉን ምስክር ተከሳሽ/ጠበቃዉ መስቀለኛ ጥያቄ ከጠየቀዉ በኋላ ዐቃቤህግ ድጋሚ ጥያቄ እንዲያቀርብ ተፈቀደለት፡፡ ዐቃቤህጉም በአንዳንድ በምስክሩ አሰማም ጊዜ በተነሱ ነጥቦች ላይ መጠየቅ እንደጀመረ መሪ ጥያቄ አነሳ፡፡ በዚህ ጊዜ ተከሳሽ/ጠበቃዉ በፍጥነት ተቃወመ፡፡ ዐቃቤህጉም ተከሳሽ/ጠበቃዉ በመሪ ጥያቄ ባስመሰከሩበት ነጥብ ላይ እየጠየቅኩ ስለሆነ መሪ ጥያቄ ሊፈቀድልኝ ይገባል ብሎ ተከራከረ፡፡

*ዳኛዉ እርስዎ ቢሆኑ ምን ይበይናሉ? በጽሁፍ ይግለጹ*

ሌላዉ ጉዳይ በሕግ በግልፅ ካልተፈቀደ በቀር የተከሳሽ የጥፋተኝነት ታሪክ (ሪኮርድ) ከፍርድ በፊት ስለማይገለፅ ይህን የሚያመለክቱ ጥያቄዎች ለምስክሩ መቅረብ የለባቸውም፡፡ ለምን ቢባል ተከሳሹ በተያዘው ክስ ጥፋተኛ ሳይባል ፍ/ቤቱ አስቀድሞ ስለተከሳሹ የጥፋተኝነት ሪኮርድ ያወቀ እንደሆነ ዳኞች በነፃ ህሊናቸው ውሳኔ እንዳይሰጡ ሊያደርጋቸው ይችላል የሚል ስጋት አለ፡፡

ምስክሮች የሚቀርብላቸውን ጥያቄ በነፃና በመሰላቸው መንገድ ሊመልሱት ይገባል፡፡ ዓ/ሕግ ያቀረበው ምስክር ክሱን በሚጎዳ ሁኔታ ቢመሰክር ዓ/ሕጉ ይህ ቃል እንዳይመዘገብ ምስክሩም ቃሉን መስጠት እንዲያቆም ፍ/ቤቱን መጠየቅ የለበትም፡፡ ጥያቄው ቢቀርብም ፍ/ቤቱ ጥያቄውን ሳይቀበል የምስክሩን ቃል መመዝገብ አለበት፡፡ ዓ/ሕጉ ጥያቄውን ቢያቆምም ፍ/ቤቱ ኣስፈላጊ መስሎ ከታየው ምስክሩን መመርመር መቀጠል ይችላል፡፡

የምስክሮች ቃል ሲመዘገብም ቅደም ተከተሉን ጠብቆ ለዋና ጥያቄ የተሰጠዉ ምስክርነት ዋና ጥያቄ ወይም ‹‹ለዐቃቤህግ ዋና ጥያቄ የምስክር መልስ›› የሚል ርዕስ ይሰጠዋል፣ መስቀለኛ ጥያቄም እንዲሁ፣ እና ድጋሚ ጥያቄና የፍርድቤት ማጣሪያ ጥያቄ በተመሳሳይ የየራሳቸዉ ርዕስ እየተሰጣቸዉ እያንዳንዱ የጥያቄ ዓይነት የሚጀምርበትና የሚያልቅበትን ቦታ በሚያሳይ መልኩ መመዝገብ አለበት፡፡ የአመዘጋገቡ ስርዓትም በዋነኛነት በሓተታ መልክ መሆን አለበት፤ እያንዳንዱ ቃል በምስክሩ ኣገላለፅ መመዝገብ ይገባዋል (ቁ.147(3)(4))፡፡ በዚህ አይነት የሚመዘገበዉም የምስክር ቃል እንጂ ጥያቄዉ አይደለም፡፡ ሆኖም በድምጽ መቅጃ በመጠቀም የሚከናወን ክስ መስማት የሚነገረዉን ሁሉ ስለሚመዘግብ ጥያቄና መልሱ ጭምር ተገልብጦ መቅረቡ አይቀርም፡፡

ስለማስረጃ ሊባል የሚገባዉና የሚቻለዉ ይህን ያህል ብቻ እንዳልሆነ ይታወቃል፡፡ ሆኖም የማስረጃ ህግን በተመለከተ ራሱን የቻለ ስልጠና ስለሚሰጥ ይህን ያህል አጠቃላይ ነገር ስለዐቃቤህግ ማስረጃ አሰማም በዚህ ስልጠና ከተነሳ በቂ እንደሆነ ይታሰባል፡፡

***ለ) <u>የዓ/ሕግ ማስረጃ እንደ ክሱ ባለስረዳ ጊዜ የሚፈፀም ስነ ስርዓት</u>***

ዓ/ሕጉ ማስረጃውን ኣሰምቶ ከጨረሰ በኋላ ፍ/ቤቱ መዝገቡን መመርመር ያለበት ሲሆን ይህ ማስረጃ መከላከያ ማስረጃ ባይቀርብ ተከሳሹን ጥፋተኛ ሊያደርገዉ የማይችል ከሆነ ተከሳሹ በነፃ እንዲለቀቅ ፍ/ቤቱ ያዝዛል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.141)፡፡ ይህ ትእዛዝ (ብይን) ክርክሩ የመጨረሻ ዕልባት እንዲያገኝ የሚያደርገው በመሆኑ ትዕዛዙ ሲሰጥ መዝገቡን በጥንቃቄ መመርመር ይጠይቃል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በወ/መዝ/ቁ 450/88 የሚከተለውን ትእዛዝ ሰጥቶ ነበር:: የስር ተከሳሽ የወ/መ/ሕግ ቁ. 637/1/ሐ ተላልፎ ከባድ የውንብድና ወንጀል ፈፅሚል የሚል ክስ ይቀርብበታል:: ክሱን ክዶ ስለተከራከረ ዓ/ሕግ ማስረጃውን እንዲያቀርብ ይታዘዛል:: ሆኖም ዓ/ሕግ ማስረጃውን እንዲያቀርብ በተደጋጋሚ ታዝዞ ሊያቀርብ ስላልቻለ፣ በተከሳሽ ላይ የመሰረተውን ክስ በማስረጃ አስደግፎ ማስረዳት አልቻለም በማለት ተከሳሹ መከላከል ሳያስፈልገው በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.141 መሰረት በነፃ ይሰናበት ሲል ብይን ሰጥቷል::

ዐቃቤ ህግ የከፍተኛ ፍ/ቤትን ትእዛዝ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያለ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም በመዝ/ቁ 8803 የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥቷል::

> "… በመሰረቱ አንድ ተከሳሽ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.141 መሰረት በነፃ ሊሰናበት የሚችለው ዓ/ሕግ ማስረጃውን አሰምቶ ከጨረሰ በኋላ ማስረጃው ተከሳሹን ጥፋተኛ የሚያደርገው ሆኖ ባልተገኘ ጊዜ እና ማስረጃው በቂ ሆኖ ሳያገኘው ሲቀር ነው::
>
> በዚህ በተያዘው ጉዳይ ላይ ግን የዓ/ሕግ ማስረጃዎች አልተገኙም ተባለ እንጂ ቀርበው ተሰምተው ምስክርነታቸው በቂ አይደለም ባልተባለበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት ከፍ ሲል የተመለከተውን የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.141 መሰረት አድርጎ መልስ ሰጭውን በነፃ ማሰናበቱ የሕጉን ትርጉም የሳተ ነው::
>
> ስለሆነም የስር ፍ/ቤት… የሰጠውን ብይን… ሽረን ዓ/ሕግ ምስክሮቹን ባገኘ ጊዜ ክሱን የማንቀሳቀስ መብቱን ጠብቀናል…"

ሲል ወስኗል::

**መለማመጃ 50**

በችሎትዎ እየተስተናገደ በነበረ የወንጀል ክስ የዐቃቤህግ ማስረጃ ተሰምቶ ተከሳሽ እንዲከላከል ታዝዞ ባለበት ደረጃ ተከሳሹ ምስክሮቹን ፈልጎ ሊያገኛቸዉ አልቻለም፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ጉዳዩ መታየት ከጀመረ በኋላ የዐቃቤህግ ምስክሮች ባለመገኘታቸዉ ክሱ ሳይሰማ ምስክሮች እስኪገኙ ለሰባት ዓመታት ተቋርጦ ቆይቶ እንደገና ስለተጀመረና በመሃሉ የተከሳሽ ምስክር ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎች በሞትና ከሃገር በመዉጣት ሊገኙ ባለመቻላቸዉ ነዉ፡፡ ስለዚህ ተከሳሹ ከሃገር የወጡት ምስክሮች እስኪገኙ ድረስ ክሱ ተቋርጦ ይቆይልኝ በማለት አመለከተ፡፡

*የችሎቱ ዐቃቤህግ ቢሆኑ ለዚህ ክርክር የሚያቀርቡትን በመርህ ላይ የተመሰረተ የመልስ ክርክር ይጻፉ*

*እንደችሎቱ ዳኛ ባልደረባዎን እንደዐቃቤህግ ሆነዉ የመልስ ክርክር እንዲያቀርቡ ካደረጉ በኋላ በዚህ ክርክር ላይ የሚሰጡትን ትዕዛዝ ይጻፉ*

በሌላ በኩል ቀደም ሲል በምሳሌነት የተመለከተዉን ዉሳኔ በመዝገብ ቁ 8803 የሰጠዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤት ዳኛ እንደሆኑ ያስቡ፡፡ ተከሳሹ ይግባኝ ብሎ የቀረበበት ጉዳይ ቀረበልዎ፡፡ የይግባኙም ቅሬታ በስር ፍርድቤት ተከላከል ተብዬ ምስክሮቼ ሲፈለጉ ሊገኙ አልቻሉም፡፡ እኔም ምስክሮቼ እስኪገኙ እንደዐቃቤህግ ሁሉ ክሱ ተቋርጦ ይቆይልኝ ብዬ ያመለከትኩትን ባለመቀበል መከላከል እንዳልፈለግክ ይቆጠራል በማለት ጥፋተኛ በማለት ወስኖብኛል፡፡ ሆኖም ፍርድ የሚሰጠዉ የመጨረሻዉ የክርክር ማቆሚያ ንግግር /የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 149/ ከተደረገ በኋላ በመሆኑና ይህም ንግግር የሚቀርበዉ የመከላከያ ማስረጃ መሰማት ሲጠናቀቅ ስለሆነ /የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 148/ መከላከያ ምስክሮቼ ተገኝተዉ ከመሰማታቸዉ በፊት ፍርድ ሊሰጥ አይችልም፡፡ ስለዚህ ይህ ፍርድ ዉድቅ ተደርጎ ምስክሮቼ ሲቀርቡ የማሰማት መብቴ ተጠብቆ እስከዚያዉ እንዲቋረጥ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

*ዉሳኔዎ ምን ይሆናል? ይጻፉት*

*በዉሳኔዎ ዉስጥ ፍርድቤት የዐቃቤህግ ማስረጃ ሲጠፉ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 141 መሰረት መወሰን አይችልም የሚለዉ የጠቅላይ ፍርድቤት ዉሳኔ ምን ያህል ተገቢ እንደሆነ ይተቹ፡፡*

## *ሐ) <u>የዓ/ሕግ ምስክሮች እንደ ክሱ ባስረዱ ጊዜ የሚፈፀም ስነ ስርዓት</u>*

የዓ/ሕግ ምስክሮች እንደ ክሱ ባላስረዱ ጊዜ ተከሳሹ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.141 መሰረት በነፃ እንደሚሰናበትና የክርክሩ መቋጫ እንደሚሆን ከላይ ተመልክተናል:: አሁን ደግሞ የዓ/ሕግ ምስክሮች እንደ ክሱ ኣስረድተዋል የሚል እምነት ሲኖረው ፍ/ቤቱ ምን ዓይነት ትእዛዝ መስጠት እንዳለበት እናያለን::

ከወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ 142(1) መገንዘብ እንደሚቻለው የዓ/ሕግ ምስክሮች እንደ ክሱ ያስረዱ እንደሆነ ተከሳሹ የመከላከያ ማስረጃውን እንዲያሰማ ሊነገረው እንደሚገባ ነው::

ተከሳሹ እንዲከላከል በማለት ፍ/ቤቱ የሚሰጠው ትእዛዝ (የሚነግረው ነገር) ይዘት ምን መሆን አለበት የሚል ነጥብ ከሕጉ እና ካለው ልምድ አንፃር ማየቱ ተገቢነት አለው:: የሕጉ ይዘት ሲታይ ተከሳሹ በቀረበበት ማስረጃ መሰረት የተመሰከረበት ከሆነ መከላከያውን እንዲጀምርና ለክሱ መልስ ቃሉን መስጠትና የመከላከያ ምስክሮቹን ማቅረብ የሚችል መሆኑን ፍ/ቤቱ ለተከሳሹ ሊነግረው እንደሚገባ ይገልጻል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 142(1))::

**መለማመጃ 51**

አንድ ተከሳሽ ተከሶበት በነበረ የዉንብድና ወንጀል የዐቃቤህግ ማስረጃ ሲቀርብ ቆይቶ ሲመረመር ተከሳሹ ከተበዳይ ላይ ንብረት መዉሰዱን፣ ሆኖም ይህን ተግባር በፈጸመበት ጊዜ በተበዳይ ላይ የፈጸመዉ የኃይል ተግባር እንዳልነበረ የሚያሳይ ሆኖ ተገኘ፡፡ ስለዚህ ተከላከል የሚል ብይን ሊሰጡ ፈለጉ፡፡ ነገር ግን እንዴት ተከላከል እንደሚሉት ሲያስቡ ማስረጃዉ ክስ የቀረበበትን ወንጀል እንዳላስረዳ ተገነዘቡ፡፡

*በዚህ ነገር ላይ የሚሰጡት ብይን እንዲሁ በደፈናዉ ተከላከል የሚል ወይም ከዚህ በበለጠ ዝርዝር ይኖረዉ እንደሁ ብይኑን በመጻፍ ያሳዩ፡፡*

ተከሳሽ መከላከያ ማስረጃውን እንዲያሰማ የሚነገረው የዓ/ሕግ ምስክር በቂ ባይሆንም ነገሩን የበለጠ ለማጣራት በሚል ሳይሆን የዓ/ሕግ ማስረጃ በቂ ሲሆንና የማፍረሻ ማስረጃ ካልቀረበ በቀር ተከሳሹን ጥፋተኛ የሚያደርግ መሆኑን ፍ/ቤቱ ሲያምን ብቻ መሆን ይገባዋል:: በተግባር እንደሚታየው ግን ፍ/ቤቱ በዓ/ሕግ ማስረጃ ብቃት ላይ ጥርጣሬ እያለውም የመከላከያ ማስረጃ እንዲቀርብ ወይም ተከሳሽ እንዲከላከል የሚያዝዝበት አጋጣሚ አለ::

**መለማመጃ 52**

*እየተሰማ ባለ አንድ የወንጀል ክስ ተከሳሹ ተከላከል ተብሎ በተለያየ ምክንያት የመከላከያ ምስክሮቹ ሳይቀርቡ ወይም ሳይሰሙ ቆይተዉ ይህ ጉዳይ በሚታይበት ችሎት እርስዎ ዳኛ ሆነዉ መስራት ጀመሩ፡፡ በቀጠሮዉ እለት የተከሳሹ መከላከያ ምስክሮች ተሟልተዉ ቀርበዉ ተሰሙ፡፡ ከዚያ በኋላ በያዙት ቀጠሮ መዝገቡን መርምረዉ ሲጨርሱ መጀመሪያም ተከሳሹ እንዲከላከል ሲታዘዝ የዐቃቤህግ ማስረጃ ምን እንዳስረዳ ሳይተነተን መሆኑን፣ እርስዎ እንደመረመሩትም ይህ ማስረጃ ተከሳሽ በመከላከያ ማስረጃ ክሱን ባያስተባብል ሊያስፈርድበት በሚችል መጠን የሚያስረዳበት እንዳልሆነና ስለዚህም ቀድሞዉንም ተከላከል ሊባል የሚገባዉ እንዳልነበረ፣ የመከላከያ ማስረጃዉም ስለተከሰሰበት ጉዳይ ሳይሆን ስለሌላ ጉዳይ የሚያስረዳ መሆኑን ተገነዘቡ፡፡*

*በዚህ ደረጃ ምን ይወስናሉ? ወንጀል መፈጸሙ አልተረጋገጠም ከክሱ በነጻ ይሰናበት ይላሉ ወይስ የመከላከያ ማስረጃዉ ክሱን ስለማያስተባብል ጥፋተኛ ነዉ ብለዉ ይደመድማሉ? ለምን?*

*ፍ/ቤቱ ተከሳሽን መከላከያ ማስረጃ ኣቅርቦ እንዲያሰማ ሲነግረው አንዳንድ ጊዜ ተከሳሹ መከላከያ የለኝም የሚል መልስ ያቀርባል:: ተከሳሹ መከላከያ የለኝም ወይም ማቅረብ ኣልፈልግም ካለ ይህንን በፅሑፍ እንዲያረጋግጥ የሚያስገድድ ሕግ ስለሌለ ቃሉን ብቻ በመመዝገብ ወደ ውሳኔ መሻገር ይቻላል፡፡ ነገር ግን ተከሳሽ በይግባኝ ጊዜ መከላከያ ማስረጃዬን እንዳላቀርብ ተደርጌ ተፈረደብኝ እንጂ መከላከያ የለኝም አላልኩም የሚል ክርክር ቢያቀርብ ማስረጃ ያስፈልጋል፡፡ እንዲህ አይነት ማስረጃ አያስፈልግም ፍርድቤቱ መታመን አለበት ከተባለ በሌላዉ ጽንፍ ክፉ ልቡና ያላቸዉ ዳኞች ተከሳሽን ለመጉዳት ማለትም የመከላከል መብቱን ለማስቀረት ሲሉ ተከሳሽ መከላከያ የለኝም ብሏል ብሎ በመመዝገብ እንዲፈርዱበት በር ይከፍታል፡፡*

**መለማመጃ 53**

*በበታች ፍርድቤት ሲታይ በነበረ አንድ የወንጀል ክስ ጉዳይ ፍርድቤቱ ማስረጃ ከሰማ በኋላ ተከሳሹን ልትከላከል ይገባል በማለት ብይን ስለሰጠ ተከሳሹ ቅሬታ አድሮበታል፡፡ በዚህም የተነሳ በዚህ ብይን ላይ ይግባኝ አቀርባለሁ በማለት የብይኑን ግልባጭ ጠየቀ፡፡ ይህን መሰረት አድርጎ ያዘጋጀዉ የይግባኝ ቅሬታ ለይግባኝ ሰሚ ፍርድቤት ቀረበ፡፡*

*በዐቃቤህግነት በዚህ ይግባኝ ላይ የሚያቀርቡትን ክርክር ይጻፉ*

*ዐቃቤህጉ ይህን ይግባኝ ሊስተናገድ አይገባም በማለት ተቃወመ ብለን እናስብ፡፡ እንደይግባኝ ሰሚ ዳኛ በዚህ ክርክር ላይ የሚሰጡትን ዉሳኔ ይጻፉ*

*ክርክርዎ ወይም ዉሳኔዎ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 184 እና 185 የተደነገገዉን ታሳቢ ያደረገ ቢሆን ይመረጣል*

2.4.2.2 <u>ስለመከላከያ ማስረጃ</u>

*<u>የመከላከያ ምስክሮችን መስማት፡-</u>*

*የተከሳሽ የመከላከል መብት ሕገ መንግስታዊ መሰረት ያገኘ በመሆኑ መሰረታዊ መብት ነው*:: *በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት ዓንቀፅ* 20(4) *እንደተመለከተው የተከሰሱ ሰዎች* "… *ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቻቸው ቀርበው እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት ኣላቸው*…" *ይላል*:: *ይህ መሰረታዊ መብት በስነ ስርዓት ሕጉም ቢሆን ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም የስነ ስርዓት ሕጉ በሚያዘው መሰረት መብቱን መጠቀም ይችላል*::

*በመሰረቱ የመከላከያ ምስክሮች የመስማት ስነ ስርዓት ኣፈፃፀም ከዓ/ሕጉ የምስክሮች ኣሰማም ስነ ስርዓት የተለየ ኣይደለም*:: *በዚህ መሰረት ተከሳሹ ወይም ጠበቃው በመከላከያ ሊያስረዳ ያቀረበውን ማስረጃ በአጭሩ በመግለፅ መከላከያውን የማሰማት ሂደት ይከፍታል* (*የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ*.142(2)):: *እዚህ ላይ ተከሳሹ መግለፅ የሚጠበቅበት ነገር ያቀረባቸው ምስክሮች ወይም ሌላ ማስረጃ ምን እንደሚከላከሉለት እንደየእውቀታቸው* (*በጉዳዩ ላይ ያላቸውን እውቀት*) *ለያይቶ ማስመዝገብ ነው*:: *ምስክሮቹ በየተራ እየተጠሩ እንዲመሰክሩ የሚደረግ ሲሆን ከዛ በፊት ግን ስለ ዓ/ሕግ ምስክሮች የተገለፀውን የመሃላ ፎርምና ይዘት መሰረት ኣድርገው መማል አለባቸው*::

**መለማመጃ 54**

*ጉዳዩ እየተሰማ ያለ አንድ የወንጀል ተከሳሽ እንዲከላከል ስለታዘዘ የመከላከያ ምስክሮቹን አቅርቧል፡፡ ነገር ግን ፍርድቤቱ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/* 142/1/ *በተደነገገዉ መሰረት ስለክሱ መልስ ቃልህን መስጠት ትችላለህ ባለዉ መሰረት ተከሳሹ ምስክሮቹን ከማሰማቱ በፊት ቃሉን መስጠት እንደሚፈልግ በማስታወቁ ቃሉን እንዲሰጥ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/* 142/3/ *ተፈቀደለት፡፡ ሆኖም ቃሉን ከመስጠቱ በፊት በዕዉነት ቃሉን ስለመስጠቱ መሃላ እንዲፈጽም የችሎቱ አስተናጋጅ ጠየቀዉ፡፡ ተከሳሹ መሃላ መፈጸም አልፈቅድም፣ ይህ ግዴታ በምስክሮች ላይ ብቻ የተጣለ ነዉ፣ እንዲሁ ልሰማ ብሎ አመለከተ፡፡*

*በዐቃቤህግነትዎ በዚህ የተከሳሹ ማመልከቻ ላይ የሚያቀርቡት ክርክር ምንድን ነዉ? ይጻፉት*

*ዳኛዉ እርስዎ ቢሆኑ ምን ይወስናሉ? ትዕዛዝዎን ይጻፉት*

ከላይ የተመለከተዉን ቃል ተከሳሹ በመሃላ/ያለመሃላ ሰጠ ብለን እናስብ፡፡ በሥነሥርዓት ህጉ መሰረት ከእርሱ ቀጥለዉ የመከላከያ ምስክሮች የምስክርነት ቃላቸዉን ሰጡ፡፡ ነገሩን ለፍርድ ቀጠሩት፡፡ በዚህ መሰረት የምስክሮቹን ቃል ሲመረምሩት ከጉዳዩ ጋር ብዙም የተገናኘና ክሱን ሃሰት ሊያስብል የሚችል ሆኖ አላገኙትም፡፡ ሆኖም ተከሳሹ ከምስክሮቹ ቀድሞ የሰጠዉ ቃል ሲታይ ከክሱ ጋር ተቃራኒ፣ ስለዚህም በክሱ የተመለከተዉን ወንጀል ተከሳሽ እንዳልፈጸመዉ የሚያሳይ እንደሆነ አስተዋሉ፡፡

*በዚህ መሰረት የሚሰጡት ፍርድ ምን ይሆናል? ተከሳሽ ክሱን ተከላክሏል በነጻ ይሰናበት የሚል ነዉ ወይስ አልተከላከለም ጥፋተኛ ነዉ የሚል ነዉ? ለምን? ፍርዱን በአጭሩ ይጻፉ*

ተከሳሹ ማሰማት የሚችለው ማስረጃ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.124 መሰረት ባቀረበው ዝርዝር ላይ ያሉትን ምስክሮች ነው:: ሆኖም ግን በዓ/ሕግ ምስክር ጉዳይ እንዳየነው በዝርዝሩ ላይ ያልተጠቀሰ ምስክር እንዲቀርብለት ተከሳሹ ከጠየቀና ፍ/ቤቱም ጥያቄውን ከተቀበለው ምስክሩ እንዲቀርብለት ሊያዝዝ ይችላል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.143 (2):: በተጨማሪም የነገሩ መሰማት ከተጀመረ በኋላ ክሱ የተሻሻለ ወይም አዲስ ክስ የተዘጋጀ ከሆነ በማንኛውም ጊዜ ተከሳሹ ከተሰሙት ምስክሮች ውስጥ ማንኛውም እንደገና ኣስጠርቶ እንዲያሰማ የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ነው (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.121) ::

ከዚህ በተጨማሪ ተከሳሹ ቃሉን መስጠት የፈቀደ (የፈለገ) እንደሆነ በመጀመሪያ ቃሉን መስጠት ኣለበት:: ሆኖም በሚሰጠው ቃል ላይ መስቀለኛ ጥያቄ ሊጠየቅ እንደማይችልና ነገር ግን ፍ/ቤቱ ነገሩን ለማብራራት መጠየቅ እንደሚችል ሕጉ ኣስቀምጧል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.143(3)):: ይሁን እንጂ ተከሳሹ የሚሰጠው ቃል የተመሰከረበትን ነገር ከመከላከል ኣንፃር ምን ፋይዳ እንዳለው ሕጉ በግልፅ ያለው ነገር የለም፡፡

የተከሳሹ መከላከያ ምስክሮች አጠያየቅ፣ የጥያቄዎቹ ዓይነትና የምስክርነት ቃል አመዘጋገብ ከላይ ስለ ዓ/ሕግ ምስክሮች በተገለፀው አይነት ይሆናል፡፡

ይህ ማስረጃ ከተሰማ በኂላ ፍርድቤቱ ክሱ ተስተባብሎ እንደሁ ይመረምራል፡፡ በዚህ መሰረትም በጉዳዩ ላይ ፍርድ ይሰጣል፡፡ ፍርዱም ተከሳሹ ***ክሱን*** አስተባብሏል ከክሱ በነጻ ይሰናበት ወይም ***ክሱን*** ኣላስተባበለም ለወንጀሉ ጥፋተኛ ነዉ የሚል ይሆናል፡፡

### 2.4.3 በማስረጃ መስማት ጊዜ የፍርድቤት ሚና

በማስረጃ ረገድ ፍርድ ቤቶች (ዳኞች) ያላቸው ሚና ስንመለከት በዓለማችን በሚገኙ ሁለት ዋና ዋና የሕግ ስርዓቶች ልዩነት ይታያል:: በኮመን ሎዉ የሕግ ስርዓት አገሮች የክርክሩ አድማስ የሚወስኑት (ጥፋተኛ ነኝ በማለትና ለማመን በመስማማት ኣማካኝነት) ፣ የክርክሩን ስትራተጂ የሚቀይሱት ፣ ማስረጃን የማቅረብና የመጠየቅ ሚና የሚወጡት በዋነኛነት ባለጉዳዮች ናቸዉ፡፡ ስለዚህ የዳኘው ሚና በጣም ውሱን ነው::

በኮንቲኔንታል የሕግ ስርዓት ያለው ኣሰራር ስናይ ግን የክርክሩን ስትራተጂ የሚቀይሰው፣ የክርክሩን አድማስ የሚወስነው፣ የትኛው ማስረጃ መቅረብ እንደለበትና እንደሌለበት ከመወሰን ኣኳያ ከፍተኛ ሚና የሚጫወተዉ፣ በዋነኝነት ለምስክሮች ጥያቄ የሚያቀርበዉ፣ ወዘተ ዳኛ ነው::

በእኛ ኣገር የሕግ ስርዓት በመሰረቱ ማስረጃ ማቅረብና ምስክሮችን መመርመር የዓ/ሕጉና የተከሳሹ ሃላፊነት ቢሆንም ፍ/ቤቱም ሰፋ ያለ ሚና እንዳለዉ ማየት ይቻላል:: ፍ/ቤቱ በምስክር ኣቀራረብና ምርመራ ያለው ሚና ሰፊ ነዉ፡፡ ሆኖም ይህን ሚናዉን ሲጫወት ገለልተኛነቱን በማይነካና በጥንቃቄ ሊሆን እንደሚገባ መርሳት የለብንም:: ስለዚህ ይህንን እንደመነሻ በመያዝ የፍ/ቤቱ  ሚናዎች ምን እንደሆኑ እናያለን::

ሀ) ምስክሮችን መመርመር (መጠየቅ) በዋነኛነት የባለጉዳዮች ሃላፊነት ቢሆንም ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት ኣስፈላጊ መስሎ ከታየው ፍ/ቤቱ በማንኛውም ጊዜ ምስክሮቹን ማናቸውንም ጥያቄ ለመጠየቅ ይችላል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.136 (4)):: በተለምዶም የፍርድ ቤት ማጣሪያ ጥያቄ እየተባለ ይጠራል:: ከሕጉ ኣነጋገር ተነስተን ዳኞች ምን ዓይነት ጥያቄ ማንሳት ኣለባቸው ብለን እናስባለን፡፡ ሕጉ የሚለው “ማናቸውንም” ጥያቄ ነው:: በተግባር ያለው ኣካሄድ በተለይ ያለጠበቃ የሚከራከሩ ተከሳሾች የዋና ጥያቄ ምንነትና እንዴት እንደሚቀርብ ባለማወቃቸው ወደ ማዘበራረቅ ስለሚገቡ ዳኞች ራሳቸው ዋና ጥያቄ ሳይቀር ሲጠይቁላቸው ይታያል::

**መለማመጃ 55**

ምስክር እየተሰማ ባለበት በአንድ የወንጀል ክስ ጉዳይ ዐቃቤህጉ ዋና ጥያቄ እየጠየቀ ባለበት ጊዜ ፍርድቤቱ ጣልቃ እየገባ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መመርመር ስለጀመረ ዐቃቤህግ በፈለገዉ አይነት ማስረጃዉን ማሰማት አልቻለም፡፡ ስለዚህ ዐቃቤህግ ፍርድቤቱ የማጣሪያ ጥያቄ የሚጠይቅበት የራሱ ጊዜ መጨረሻ ላይ ስላለዉ ምስክሬን በተዘጋጀሁበትና በምፍልገዉ መንገድ እንዳሰማ በተለያዩ ጥያቄዎች አያቋርጥብኝ ብሎ አመለከተ፡፡

*ዳኛዉ እርስዎ ቢሆኑ በዚህ ጥያቄ ላይ የሚሰጡት ትዕዛዝ ምንድን ይሆናል?*

*ፍርድቤቱ ጥያቄዎችን የሚጠይቀዉ ወይም መጠየቅ የሚችለዉ የተከራካሪዎቹ ጥያቄዎች ካበቁ በኋላ ነዉ ብለዉ መጠየቀዎን ያቋርጣሉ ወይስ መጠየቀዎን ይቀጥላሉ? ለምን? ትዕዛዝዎን ይጻፉት*

*ይህን ጥያቄ ያነሳዉ ተከሳሹ ቢሆንና እርስዎ ዐቃቤህግ ሆነዉ ፍርድቤቱ በአጋጣሚ ሃሳብዎን በዚህ ጉዳይ ላይ ቢጠይቅዎ ምን ሃሳብ ያቀርባሉ? ተከሳሽ ልክ ነዉ ይላሉ ወይስ ፍርድቤቱ ጥያቄዎችን በማንኛዉም ጊዜ ሊጠይቅ ይችላል ብለዉ የተከሳሹን ጥያቄ ይቃወማሉ? ለምን?*

ጥያቄ ከመጠየቅ ጋር በተያያዘ ፍርድቤት ለተከራካሪ ወገኖች ያልተፈቀደ ሥልጣን አለዉ፡፡ ይኸዉም በምስክር መስማት ሂደት ተከሳሽ ቃሉን ለመስጠት በፈቀደ ጊዜ ቃሉን ሲሰጥ ከፍርድቤት በቀር በሚሰጠዉ ቃል ላይ ሊጠይቀዉ የሚችል ወገን የለም /የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 142/3//፡፡ በዚህ ጊዜ ዐቃቤህግ ይቅርና ተከሳሹ ጠበቃ ያለዉ ቢሆን ጠበቃዉ እንኳ ጥያቄ እየጠየቀ ሊያስመሰክረዉ አይችልም፡፡

**ለ) <u>ዳኞች ተጨማሪ ምስክር እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላሉ:: በዚህም መሰረት</u>፤**

1. ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት ምስክርነቱ ኣስፈላጊ መስሎ ከታየው ፍርድ ቤቱ ፍርድ ከመስጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ማንኛውንም ምስክር መጥራት ይችላል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.143(1)):: ማንኛውንም ምስክር ሲል ኣስቀድሞ ቃሉን ያልሰጠ ሆኖም የቀረቡ ምስክሮች ቃላቸውን ሲሰጡ ስሙን የጠሩትና ስለጉዳዩ የሚያውቅ ሰው፣ ወይም ሌላ ዓይነት ማስረጃ ሊኖር ይችላል:: በፍ/ቤቱ ጥያቄ ኣማካኝነት ባለጉዳዮች በሚሰጡት ጥቆማ ወይም በሌላ መንገድ የተገኝ ሊሆን ይችላል::

2. ዓ/ሕጉና ተከሳሹ በምስክር ዝርዝር ላይ ያልተጠቀሱ ምስክሮች እንዲቀርቡላቸው በጠየቁ ጊዜ ምስክሮቹ ነገሩን ለማዘግየት ሳይሆን ለትክክለኛ ፍትሕ ኣስፈላጊ መስሎ ከታየው ምስክሮቹ እንዲጠሩ ፍ/ቤቱ ለማዘዝ ይችላል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.143 (2)) ::
3. ተከሳሹ ለቀረበበት ክስ የእምነት ቃል የሰጠ ቢሆንም ፍ/ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ዓ/ሕጉ ለክሱ የሚደግፈውን ማስረጃ እንዲያቀርብ ለማዘዝና ተከሳሹም መከላከያውን እንዲያቀርብ ለመፍቀድ ይችላል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.134 /2/ ይመለከቷል)::
4. እንዲሁም በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 194 እንደተደነገገዉ በይግባኝ መስማት ጊዜም ቢሆን ፍርድቤት ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ሊያዝዝ ይችላል፡፡

**መለማመጃ 56**

በአንድ የወንጀል ክስ ጉዳይ የተቆጠሩ ምስክሮች ተሰምተዉ አብቅተዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ለፍርድ ቀጠሮ ከመያዙ በፊት ተከሳሹ አንድ የሰነድ ማስረጃ በማስረጃ ዝርዝሩ ዉስጥ ያልተጠቀሰ በተጨማሪ ማስረጃነት እንዳቀርብ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 143 መሰረት ይፈቀድልኝ በማለት አመለከተ፡፡ እንዳጋጣሚ ሆኖ ተከሳሹ በዋስ የሚገኝ ነዉ፡፡ ይህ ሰነድ ደግሞ ከኢትዮጵያ ዉጭ የሚገኝ ነዉ፡፡ ሆኖም በጉዳዩ ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት የሚረዳ ሰነድ ነዉ፡፡ ዐቃቤህግ ምን እንደሚል ተጠየቀ፡፡ እርሱም እንዲህ አይነት ማስረጃዎችን በተጨማሪነት ለማቅረብ ይህ ህግ አግባብነት የለዉም፣ ህጉ ምስክሮችን የሚመለከት ስለሆነ ሰነዶችን አስቀድሞ ማቅረብ ይገባል እንጂ በዚህ ህግ መሰረት በተጨማሪ ማስረጃነት ማቅረብ አይቻልም ጥያቄዉ ዉድቅ ሆኖ መዝገቡ ለፍርድ ይቀጠርልኝ በማለት ተከራከረ፡፡

*ዳኛዉ እርስዎ ቢሆኑ በዚህ ክርክር ላይ የሚሰጡትን ዉሳኔ ይጻፉ*

ከዚህ በተያያዘ የፍርድቤት ኃላፊነት በሥነሥርዓት ህጉ የተመለከቱትን ከላይ የተገለጹትን ብቻ በማከናወን ይወሰናል ወይ የሚለዉ ጥያቄ አግባብ ያለዉ ጥያቄ ነዉ፡፡ ፍርድቤት ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ ከነዚህ ያለፈ፣ ነገር ግን ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸዉን ተግባሮች እንዳያከናዉን ሊከለከል ይገባ እንደሁ መልስ ሊያገኝ ይገባዋል፡፡

**መለማመጃ 57**

*በችሎትዎ በሚታይ የወንጀል ክስ ማስረጃዎች በሚቀርቡበት ጊዜ ከተነሱት ክርክሮች አንዱ ወንጀሉ የተፈጸመበትን ቦታ የአካባቢ ሁኔታ የሚመለከት በመሆኑ የዐቃቤህግ ምስክሮች የመሰከሩትን ነገር ዕዉነትነት ፍርድቤቱ በቦታዉ ተገኝቶ ይመርምርልኝ፣ በቦታዉ ያለዉ ሁኔታ ከተመሰከረዉ ፈጽሞ የማይገናኝ ነዉ፣ ወዘተ. በማለት አመለከተ፡፡ ዐቃቤህግም በወንጀል ጉዳይ ፍርድቤት እንዲህ አይነት የማስረጃ ስብሰባ ተግባር ለመፈጸም ሥልጣን አልተሰጠዉም፣ ተጨማሪ ምስክሮችን ለመጥራት፣ የቀረቡ ምስክሮችን ማጣሪያ ጥያቄ መጠየቅ እንጂ ወንጀል የተፈጸመበት ቦታ ተገኝቶ ማስረጃ መሰብሰብ በሥነሥርዓት ህጉ አልተፈቀደም፣ ስለዚህ ችሎቱ ጥያቄዉን ዉድቅ ያድርግልኝ በማለት ተከራከረ፡፡*

*በዚህ ክርክር ላይ የሚሰጡትን ትዕዛዝ ይጻፉ*

## 2.5 <u>*የክርክር ማቆሚያ ንግግር /የመፋረጃ ሃሳብ/*</u>

*የክርክር ማቆሚያ ንግግር የሁለቱም ተከራካሪዎች ወገን ምስክሮች ተሰምተው ካለቁ በኋላ፣ ተጨማሪ ምስክሮች ቀርበው ከሆነም ከተሰሙና ሌሎች የሰነድ ማስረጃዎችም ካሉ ተጠቃልለው ከቀረቡ በኋላ ዓ/ሕጉና ተከሳሹ ወይም ጠበቃው የሚያቀርቡት ነው። የመፋረጃ ሓሳቡ የሚቀርበውም በቃል እንጂ በፅሑፍ እንዳልሆነ ከሕጉ የቋንቋ ኣጠቃቀም (ይናገራል ስለሚል) መረዳት ይቻላል። ሆኖም ሲሰራበት የነበረና አሁንም ሙሉ በሙሉ ቀርቷል ለማለት የማያስደፍረው ተከራካሪዎች የመፋረጃ ሓሳባቸውን ለማቅረብ ቀጠሮ እንዲሰጣቸው ሲጠየቁ ፍ/ቤትም የሚፈቅድላቸው መሆኑ ነው። የመፋረጃ ሓሳብ እየተባለ ሲቀርብ የነበረውም በቃል ሳይሆን ብዙ ሓተታ በያዘ ፅሑፍ ነበር።*

**መለማመጃ 58**

*አንድን የወንጀል ክስ በችሎትዎ ሰምተዉ ማስረጃዎች ከተጠናቀቁ በኋላ ዐቃቤህግ የመፋረጃ ሃሳብ እንዳቀርብ አጠር ያለ ቀጠሮ ይሰጠኝ ብሎ ስለጠየቀና በችሎቱ የተለመደ አሰራር በመሆኑ በጽሁፍ መፋረጃ ሃሳቡን በሬጂስትራር በኩል እንዲያቀርብ ፈቀዱ፡፡ ተከሳሹ ግን ዐቃቤህግ የሚያቀርበዉን ሃሳብ ማወቅ ስላለብኝና ለዚህም የራሴን የመልስ ሃሳብ ማቅረብ መብት ስላለኝ ይህ የዐቃቤህግ ሃሳብ ሊደርሰኝ እንዲችል በሬጂስትራር በኩል ሳይሆን ወይ እዚሁ አሁን በቃል ያቅርብ፣ ካልሆነም ቀጠሮ ተይዞ እዚሁ ችሎት ላይ ደርሶኝ በተራዬ ቀጠሮ ተይዞልኝ መልሴን እንዳቀርብ ሊታዘዝ ይገባል፣ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.* 148 *ይህን ይደነግጋል፡፡ በማለት ተከራከረ፡፡*

*ምን ይወስናሉ? ይጻፉት*

ዓ/ሕግ ንግግሩን ካቆመ በኋላ ቀጥሎም ተከሳሹ ወይም ጠበቃው ስለ ሕጉና ስለማስረጃው ሁኔታ ይናገራል:: የዓ/ሕግ ማስረጃን በመከላከያው ያፈረሰው መሆኑን፣ በነፃ ሊለቀቅ እንደሚገባ ወይም ወደ ቀላል ዓንቀፅ መለወጥ የሚገባው መሆኑ አለመሆኑን ወዘተ ይገልፃል:: ተከሳሾቹ ብዙ ከሆኑ ተከሳሹ ወይም ጠበቃው ንግግር የሚያደርግበትን ተራ ፍ/ቤቱ ይወስናል::

በሁሉም ሁኔታ ግን ተከሳሽ የመጨረሻዉ ንግግር አድራጊ ነዉ፡፡ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 148 መጀመሪያ ዐቃቤህግ ቀጥሎ ተከሳሽ እንደሚናገሩ ደንግጎ ከዚህ በማስከተል ሁልጊዜም ተከሳሽ በመጨረሻ እንደሚናገር መደንገጉ ዐቃቤህግ ለተከሳሽ ንግግር መልስ ሊሰጥ እንደሚችል ወይም ከተከሳሽ ቀጥሎ ሊናገር እንደሚችል መጠቆሙ ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በተቻለ መጠን ንግግሩ በችሎት ሆኖ አንዱ የሌላዉን ንግግር እየሰማ እንዲነጋገሩ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለዚህ ግራ ቀኙ በየፊናዉ ሳይሰማማ ንግግሩን በጽሁፍ አድርጎ ነገሩን በማይወስን ወገን ማለትም በሬጅስትራር አማካኝነት መለዋወጡ ተገቢ እንዳልሆነ ያሳያል፡፡

የመዝጊያ ንግግር ማድረግ ግዴታ ባለመሆኑ ሁለቱ ተከራካሪዎች ከፈለጉ የሚያደርጉት ነው:: ንግግር እንዲያደርጉ ተጠይቀው ፈቃደኞች ካልሆኑ ካላቀረባችሁ ብሎ ፍ/ቤቱ የሚያስገድድበት ሁኔታ መኖር የለበትም::

# 3 ምዕራፍ ሦስት

## ስለፍርድ

በወንጀል ክስ ጉዳይ የክስ መስማቱ ሂደት ሲገባደድ ፍርድቤት ይህን ሂደት የሚያሳርገዉ በዚህ ሂደት የደረሰበትን ግኝት በመግለጽ ነዉ፡፡ ይህ ግኝት ተከሳሹን ከክሱ ነጻ የሚያደርግ ወይም ጥፋተኛ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ሁሉ በጽሁፍ ሊሰናዳ ይገባል፡፡

በዚህ መሰረት ተከሳሹ ጥፋተኛ ነዉ የሚል ግኝት ላይ የተደረሰ እንደሆነ ከዚህ የሚቀጥል ሌላ የፍርድ ሂደት ይኖራል፡፡ ይህም የቅጣት አወሳሰን ሂደት ሲሆን የፍርድ አሰጣጥ አካል ነዉ፡፡

ፍርድ የክርክሩ ሂደት ግኝት መግለጫ እንደመሆኑ መጠን ይህን ዓላማዉን የሚያሳካ ሊሆን ስለሚገባዉ ይህን ጉዳይ በሚገዙት ህግጋትና አሰራሮች ላይ የሚከተለዉ ሥልጠና ቀርቧል፡፡

የፍርድ አጻጻፍና የቅጣት አወሳሰን ጉዳዮች ራሳቸዉን የቻሉ ሥልጠናዎች የሚሰጥባቸዉ ስለሆነ በዚህ ክፍል የሚቀርበዉ ሥልጠና ከሥነሥርዓት ህጉ ጋር የተያያዙ ነጥቦች ላይ ብቻ ያተኩራል፡፡ ስለዚህ በዚህ ምዕራፍ ማለቂያ ላይ ሠልጣኞች

- ስለፍርድ አጻጻፍ እና ስለቅጣት አወሳሰን መንደርደሪያ የሚሆን ዕዉቀት ያገኛሉ

## 3.1 ስለፍርድ አሰጣጥና አጻጻፍ

ስለፍርድ አጻጻፍ ራሱን የቻለ ሥልጠና የሚሰጥበት ስለሆነ በዚህ የሥልጠናዉ ክፍል ብዙ የሚባል ነገር አይኖርም፡፡ ከዚህ የሚከተለዉን ብቻ እናያለን፡፡

ፍርድ ማለት ምን ማለት እንደሆነ የወ/መ/ሕ/ስ/ስ ያስቀመጠው ትርጉም ባይኖርም ከስነ ስርዓቱ ኣጠቃላይ ይዘት አንፃር ሲታይ፣ ፍርድ ማለት በከሳሽ ወገን የተመሰረተ ክስ እና በሁለቱ ወገኖች የቀረበ ማስረጃ ይዘት ኣግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ ተከሳሽን ነፃ ወይም ጥፋተኛ ማድረግ ማለት ነው በሚል መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል::

የፍርድ ዓላማ በዓ/ሕግ ወይም በግል ከሳሽ እና በተከሳሽ መካከል ሲካሄድ የቆየው ክርክር በተቻለ መጠን አጭር፣ ግልፅ፣ በምክንያት ላይ የተመሰረተ፣ ቅደም ተከተሉን የጠበቀ አድርጎ ከነክርክሩ መፍትሄ ለባለጉዳዮችና ለህዝቡ ለመግለፅ (ለመንገር) ነው:: ይህን ዓላማ ለማሳካት ዳኞች ውሳኔ በሚፅፉበት ጊዜ የክስ (ፍሬ ነገር)፣ የማስረጃና የሕግ ተጠየቃዊ ትስስር (logical interrelation) በሚያሳይና በምክንያት ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት::

ፍርድ የሚሰጠው ዓ/ሕጉና ተከሳሹ ወይም ጠበቃው የመዝጊያ ሓሳባቸውን ካሰሙ በኋላ ነው (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.149(1)):: ክሱ ከአንድ በላይ በሆኑ ዳኞች የሚታይ ከሆነ ዳኞቹ በሕግ ጉዳይና በማስረጃው ላይ ሙያዊ ውይይት ያደርጋሉ:: በዚህ መሰረት ውሳኔ ማግኘት ያለባቸው ነጥቦች (ጭብጦች) ለይተው ያወጣሉ$ ፍርዱም በሙሉ ድምፅ ወይም በድምፅ ብልጫ ሊሰጥ ይችላል:: በድምፅ ብልጫ የተወሰነ እንደሆነ በሓሳብ የተለየው ዳኛ የተለየበትን ምክንያት በመግለፅ የራሱን ሓሳብ በፅሑፍ ማስፈር አለበት$ በድምፅ የተለየው ዳኛ ሓሳቡን በፅሑፍ ሲያስቀምጥ በአብላጫ ድምፅ ውሳኔ የሰጡትን ዳኞች መዝለፍና ማንቋሸሽ የለበትም$ ከእነሱ የተለየበትን የፍሬ ነገር ኣስተያየት ወይም የሕግ ኣተረጓጎም ብቻ ማስቀመጥ አለበት$

የሚሰጠው ፍርድ የቀረበውን ክስና በግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ቀርቦ የተሰማውን ማስረጃ ኣጭር መግለጫ (Summary) ፍ/ቤቱ ማስረጃውን የተቀበለበትን ወይም ያልተቀበለበትን ምክንያቶች፣ ፍርዱ የተመሰረተበትን ሕግ መጥቀስና ጥፋተኛም ሆኖ በተገኘ ጊዜ ጥፋተኛ የተባለበትን የሕግ ዓንቀፅ መጥቀስ አለበት$ ፍርዱም ቀን ተፅፎበት ፍርዱን በሰጠው ዳኛ ወይም ዳኞች መፈረም አለበት (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.149(1)) $

በአጭሩ በወንጀል ጉዳይ የሚሰጥና የሚፃፍ ፍርድ በአጠቃለይ የኅብረተሰቡን፣ በተለይ ደግሞ የተከሳሹና የወንጀሉ ሰለባ የሆኑትን ሰዎች መብት የሚነካ በመሆኑ ዳኞች በእነዚህ ባለመብቶች በተለይ ደግሞ በተከሳሹና በተበዳዩ እግር ቆመው ነገሮችን በጥልቀትና ኣስተዋይነት በተሞላበት መንገድ መዝገቡን በመመርመር ፍርድ ሊሰጡና ሊፅፉ ይገባል$

በግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የቀረቡትን ማስረጃዎች (በፍ/ቤት በተጨማሪነት የቀረቡትንም ጭምር) ፍ/ቤቱ ከመረመረ በኋላ ተከሳሹን ጥፋተኛ የማያደርግ ሆኖ ካገኘው በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ. 149(2) መሰረት ነፃ እንዲሆንና ታስሮ ከሆነም እንዲለቀቅ ትእዛዝ በመስጠት ይወስናል፡፡

ፍ/ቤቱ ማስረጃዎቹን ከመረመረ በኋላ ተከሳሹ በሚገባ የተመሰከረበትና በመከላከያው ያላስተባበለው ሆኖ ያገኘው እንደሆነ በተከሳሹ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ይሰጣል$ (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 149(1) ይመለከቷል)$ የጥፋተኛነት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የሚቀጥለው የቅጣት ስነ ስርዓት ሆኖ፣ የቅጣት ውሳኔውን ለመስጠት ቀጠሮ መስጠት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፡፡

**መለማመጃ 59**

ሲታይ በቆየ አንድ የወንጀል ክስ ማስረጃዎች ተሰምተዉ ክርክሩ ከተጠናቀቀ በኋላ ተመርምሮ ተከሳሽን ጥፋተኛ ነች የሚል ዉሳኔ ተሰጠ፡፡ ወንጀሉ በእስራት ወይም በገንዘብ መቀጮ ሊያስቀጣ የሚችል ነዉ፡፡ ተከሳሿ በዋስ ሆና ስትከራከር ቆይታለች፡፡ ችሎቱም በስራ ብዛት ምክንያት የቅጣት ዉሳኔዉን በሌላ ጊዜ ለመስጠት አሰበ፡፡ ስለዚህ ዳኛዉ ቀጠሮ ለመያዝ ሲዘጋጁ ተከሳሿ በዋስ የቆየሁ ስለሆነና ልቀጣ የምችለዉ ገንዘብ ብቻ ሊሆን ስለሚችል፣ ህጻናት ልጆች ለብቻዬ የማሳድግ በመሆኑ፣ ወዘተ. የሚሉትን ምክንያቶች በመግለጽ ለቅጣት ዉሳኔ በሚያዘዉ ቀጠሮ ለመቅረብ አሁን ባለችበት በዋስ ቆይታ ለመቅረብ እንድትችል አመለከተች፡፡

*ዐቃቤህግ ቢሆኑ የሚያቀርቡትን በመርህ ላይ የተመሰረተ ክርክር ይጻፉ*

ዳኛዉ እርስዎ ነዎት፡፡ ዐቃቤህግም ጥፋተኛ የተባለችዉ በእስራት ሊያስቀጣ በሚችል ወንጀል በመሆኑ ጥፋተኛ ከተባለች በኋላ በእስር ቆይታ ቅጣት ሊወሰን ይገባል እንጂ በዋስ ልትቆይ አትችልም በማለት ተከራከረ

*ምን ይወስናሉ? ይጻፉት*

ለክርክርዎ ወይም ለዉሳኔዎ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 206 የተደነገጉትን ሁኔታዎች ግምት ዉስጥ ያስገቡ፡፡

## 3.2 <u>የቅጣት አወሳሰን</u>

የቅጣት አወሳሰንን የሚመለከት ራሱን የቻለ ሥልጠናና ማሰልጠኛ ማንዋል ይኖራል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ስለዚህ እዚህ የሚቀርበዉ ከሥነሥርዓት ህጉ ጋር የተያያዘዉ አዝማሚያ ብቻ ነዉ

ቅጣት ጥፋተኛ ሆኖ ለተገኘ ሰው የሚሰጥና ጥፋተኛ የተደረገበት ዓንቀፅ የሚያዝዘውን የቅጣት ዓይነት መሰረት በማድረግ የሚወሰን ነው$ ፍ/ቤቱ ቅጣትን የሚወስነው የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.149 (3-7) በመከተል ነው$

የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.149(3) እና (4) እንደሚከተለው ይነበባል

> *... (3) ተከሳሹም ጥፋተኛ ነው በተባለ ጊዜ ስለቅጣት ማክበድ ወይም ማቅለል ዓቃቤ ሕጉ ያለውን አስተያየት እንዲሰጥ ፍርድ ቤቱ ይጠይቀዋል$ ዓቃቤ ሕጉም ስለተከሳሹ ጠባይ ለማስረዳት ምስክሮች ለመጥራት ይችላል$*
>
> *(4) ዓቃቤ ሕጉ ስለቅጣቱ አስተያየቱን ከሰጠ በኋላ ተከሳሽ ወይም ጠበቃው መልስ የመስጠት መብት ኣለው፣ ስለጠባዩም ለማስረዳት ምስክሮች ለመጥራት ይችላል$ ተከሳሹ ቀድሞ በጥፋተኝነት ኣልተፈረደብኝም ያለ እንደሆነ ዓቃቤ ሕጉ ከዚህ ቀደም በጥፋተኝነት የተፈረደበት ለመሆኑ ለፍርድ ቤቱ ማስረዳት አለበት*

ከእነዚህ ንኡስ ቁጥሮች መገንዘብ እንደሚቻለው፤

1. ከጥፋተኝነት ውሳኔ በኋላ ዓ/ሕጉ ስለ ቅጣት ማክበድ ወይም ማቅለል ኣስተያየት ካለው እንዲገልፅ ፍ/ቤት የሚጠይቀው ሲሆን ዓ/ሕጉም ስለተከሳሹ ጠባይ ለማስረዳት ምስክሮችን የመጥራት መብት አለው፡፡ ብዙዉን ጊዜ ዐቃቤህግ ስለቅጣት ማቅለያ ሃሳብ ሲያቀርብ አይስተዋልም፡፡ የቅጣት ማክበጃዉም እንደነገሩ የሚቀርብ እንጂ በደንብ ተጠንቶ ተመርምሮ የሚቀርብ አይደለም፡፡
2. ተከሳሹ ወይም ጠበቃው ስለ ቅጣቱ መልስ ይሰጣል$ መልሱም ስለቅጣት ማቅለያ ወይም ስለጠባዩ በዐቃቤህግ የቀረበዉን ክርክርና ማስረጃ የሚቃወም ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ ይህ መልስ ዐቃቤህግ ባለበት ኃላፊነት መሰረት ሳያቀርበዉ የቀረ የቅጣት ማቅለያ ካለ እርሱን ለማቅረብ ወይም ዐቃቤህግ

ባቀረባቸዉ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ያልተስማማ እንደሆነ የተለየ ነገር ስለመኖሩ ይሆናል ማለት ነዉ፡፡

3. ዓ/ሕግ ተከሳሹ የወንጀል ሪከርድ እንዳለው ሲገልጽ ተከሳሹ ግን ይህ ሁኔታ ከካደ ዓ/ሕጉ ማስረጃ አቅርቦ ማስረዳት አለበት፡፡ በተለምዶ ግን ዐቃቤህግ ይህን የጥፋተኛነት ታሪክ የሚያስረዳ ማስረጃ ተከሳሽ ከመቃወሙ በፊት ከቅጣት ሃሳቡ ጋ ሲያቀርበዉ ይስተዋላል፡፡ ይህም ተከሳሹ ባለማወቅ ሳይቃወም ቢቀር ፍርድቤት በነገሩ ላይ ለመወሰን የሚያስችለዉ ማስረጃ እንዳያጣ ያደርገዋል፡፡

የቅጣት ክርክሩ ከተጠናቀቀና ካስፈለገም ስለቅጣቱ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ ፍ/ቤቱ ቅጣቱን ይወስናል$ ለዚህ የቅጣት ዉሳኔ ተገቢዎቹን የቅጣት አወሳሰን ህግጋት መጥቀስ ይጠበቅበታል፡፡

ፍርድ ቤቶች በወንጀል ሕግ ቁ 88 በተደነገገዉ መሰረት የቅጣት ውሳኔ መጣል እንደሚገባቸው ተደንግጓል$ የማቅለያ (የወ/ህ/ቁ 82፣ 83፣ 179 እና 180) እና የማክበጃ (ዓንቀፅ 84፣ 85፣ 183 እና ተከታዮቹ የሚገልጿቸው) ምክንያቶች ሲኖሩም እነዚህኑ በመመርመር ዳኞች ቅጣትን ከፍ ወይም ዝቅ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ አሁን ደግሞ የፌዴል ጠቅላይ ፍርድቤት በወ/ህ/ቁ 88/4/ በተሰጠዉ ሥልጣን መሰረት ያወጣዉ የቅጣት አወሳሰንመመሪያ ስላለ ይህ መመሪያ የሚለዉን በመመርመር ዉሳኔ መስጠት ይገባል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸዉ ዓቃቤያነ ሕግ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 149 (3) የተሰጣቸውን ኃላፊነት ቢኖርም የሚያቀርቡዋቸውን አስተያየቶች ስንመለከትም ባብዘኛው የሚከተሉትን ይመስላሉ$

"ተከሳሹን የሚመለከት በፖሊስ የቀረበ ሪኮርድ ስለሌለ ፍርድ ቤቱ ተመጣጣኝ ቅጣት ይወስንልን$"

"ተከሳሹ ቀደም ሲል ሪኮርድ ስላለበት (የመዝገብ ቁጥር በመጥቀስ) ቅጣቱ ከብዶ ሊወሰንበት ይገባል$"

“የወንጀሉ አፈፃፀም ከባድ እና አደገኛ ስለሆነ ቅጣቱ ከብዶ እንዲወሰንልን እናመለክታለን$”

‹በተደራራቢ ወንጀሎች ጥፋተኛ ስለተባለ ቅጣቱ ይክበድበት›

ህጉ ዓቃቤ ሕጉን የሚጠይቀው ስለ ቅጣት ማክበጃ ብቻ ሳይሆን ስለ ቅጣት ማቅለያም ሃሳብ እንዲያቀርብ ነው$ ዓቃቤነ ሕግ ግን ብዙዉን ጊዜ ስለተከሳሹ የቅጣት ማቅለያ ሲያቀርቡ አይታዩም$ በአጠቃላይ በአሁኑ ጊዜ ፍርድ ቤቶች ዓቃቤያነ ሕግን ጠይቀው የሚያገኙት መረጃ ብዙዉን ጊዜ ለቅጣት ማክበጃነት የሚረዳ ብቻ ነዉ፡፡

ከተከሳሹ የሚቀርቡት አስተያየቶችም ቢሆኑ ባብዛኛው ዕድሜውን፣ የጤና ሁኔታዉን፣ የትምህርት ደረጃውንና የቤተሰብ ሃላፊ መሆኑን የሚገልፁ ናቸው$ እነዚህ መረጃዎች ብዙውን ጊዜ በተጨባጭ ማስረጃ የተደገፉ ኣይደሉም$ ዓቃቤ ሕግም ቢሆን ከተከሳሽ የሚቀርበውን ኣስተያየት ለመቋቋም ሙከራ ሲያደርግ ኣይታይም$ ፍርድ ቤቶቹም በሁለቱም ተከራካሪዎች የቀረበላቸዉን የቅጣት ሓሳብ በመቀበል ቅጣት ሲወስኑ ይታያሉ፡፡ በርግጥ አሁን አሁን ፍርድቤቶች አልፎ አልፎም ቢሆን የተከሳሽን የቅጣት ክርክሮች የሚመለከት ማስረጃ እንዲቀርብ ሲያዝዙ እየተስተዋለ ነዉ፡፡

ክሱ በሚሰማበት ጊዜ ስለ ወንጀሉ ክብደትና ስለአፈፃፀሙ የሚመለከቱ መረጃዎች ሊቀርቡ እንደሚችሉ ይታወቃል$ እነዚህ ብቻ ግን ዳኛው የሚጠበቅበትን ውስብስብ የሆነ የቅጣት ኣወሳሰን ግዴታውን እንዲወጣ የሚያስችሉት ኣይሆኑም$ በቅጣት ጊዜ ተጨማሪ ማስረጃዎች ማግኘት መቻል አለበት$ የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ ያሰፈራቸው ከላይ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች ሰፋ ብለውና ዓላማቸውን ለማስፈፀም በሚያስችል መንገድ ካልተተረጎሙ ፋይዳቸው እምብዛም ነው$

የስነ ስርዓት ሕጉ ሁለቱ ንኡስ ዓንቀፆች ፍርድ ቤቱ ቅጣትን በሚመለከት መረጃውን ከተከራካሪ ወገኖች ብቻ በሙግት መልክ እንዲያገኝ የሚደነግጉ ይመስላሉ፡፡ ነገር ግን ህጉ ፍርድ ቤቶች በክርክር ጊዜ ከሚገኘው መረጃ ብቻ በመነሳት ቅጣት እንዲወስኑ አልሞአል ማለት ያስቸግራል$ የስ/ስ/ሕጉ ዓንቀፆች ከዋናው ሕግ ጋር አጣጥሞ በመተርጎም ከሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች ከሚያገኘው ውጪ ተጨማሪ መረጃ መሰብሰብ መቻል ይጠበቅበታል$ ለምሳሌ በፖሊስ ምርመራ መዝገቦች የሚገኙት በጥቅም ላይ ያልዋሉ ሰነዶች በቅጣት ማቅለያነት ሊጠቅሙ የሚችሉ መረጃዎች ሊገኙባቸው

ይችላሉ$ ዓቃቤያነ ሕግ እነዚህን ለማቅረብ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቢቀሩ ፍርድ ቤቱ እየጠየቀ ሊያስመጣቸው ይገባል$

ይህ አሰራር ተገቢ የሚሆነዉ እንዲሁ ብንከተለዉ መልካም ስለሆነ ብቻ ሳይሆን ፍርድቤቶች በቅጣት አወሳሰን ጊዜ ቅጣት ከመወሰናቸዉ በፊት ምርመራ እንዲከናወን ሊያደርጉ እንደሚችሉ በህግ የተደነገገ ስለሆነም ጭምር ነዉ፡፡ የወ/ህ/ቁ/ 195 እንደሚደነግገዉ ቅጣት ከመወሰኑ በፊት ወይም ቅጣት ከመታገዱ በፊት ስለተከሳሹ በባለሙያ ማጣራት እንዲደረግ ፍርድቤት ሊያዝዝ ይችላል፡፡

## ግለ መመዘኛ እና መወያያ ጥያቄዎች

1. KSN ymS¥T £dT kmjm„ bðT yZGJT tGÆR bên¾nT mkÂwN ÃlbT b¥N nW)
2. xND sW bwLDÃ kt¥ bsW እJ mRZ qMî lሀKMÂ wd ÆHRÄR XNdÿd bçSp¬l# HYwt bÃLF¿ YH DRg!T yfim sW y¸kssW byት¾W øN F¼b@T nW)
3. xè "h´ bJJU kt¥ y/ሰT gNzB sRè DÊÄê xM_è b!Ãs‰=W mksS ÃlbT yT nW)
4. ±l!S tkú>N XNÄ!ÃqRB ¬Zø úÃqRB b!qR wYM MNM mLS ÆYs_ ›¼?g# MN ›YnT _Ãq lF¼b@t ÃqRÆL) F¼b@t!S l!wSdW y¸gÆW XRM© MNDnW) y±l!S dmwZ ¥gD nW wYS l@§ x¥‰+ xl) ?GN msrT xDRUc!h# twÃ†bTÝÝ
5. tkú> yKS ¥mLkÒ XNÄ!dRsW y¸drGbT MKNÃT lMNDnW) ?g mNGSt!Â Sn SR›T ?g# msrT b¥DrG twÃ†bTÝÝ
6. tkú¹# -b" úÃ¥KR ዩ¸s-Wን yXMnT "L tqÆYnT l!ñrW YgÆL wYS xYgÆM) lMN)
7. bwNjL tkሰî y?G -b" l¥öM xlmÒl# ytrUg-lTÂ -b" ÆÃg" FT? l!ÙdLbT mçn#N y¬mnbT sW mNGST bnÉ y¸ÃöMlT mçn# bx!ØÁ¶ ?g mNGST ›Nq} 20¼5¼ tdNGÙLÝÝ tkú¹# ›QM yl@lW mçn# y¸rUg-W XNÁT nW)
8. GL} Cl¿T ¥lT MN ¥lT nW) ›§¥WS) Ä¾WÂ ›"b! ?g#N½ tkú¹#NÂ ጠb"WN BÒ l!YZ b¸CL b!é WS_ b!ÃSCL¿ Ks# bGL} Cl¿T tsMaL l¥lT Yቻ§L)
9. yKS ¥ššL ›§¥ MNDnW) yKSN ¥ššL _Ãq y¸ÃqRbW ¥N nW) tkú¹#N b¸¯Ä h#n@¬ b!ššLS tqÆYnT ¥GßT xlbT ይላሉ) lMN)
10. ›¼?G Ks@N §Nú Bl¿ l¸ÃqRbW /úB F¼b@T mkLkL YC§L) lMN)
11. xND tkú> ltkssbT g#ÄY yXMnT K?dT "l#N kmS-t bðT bF¼b@t l!ngrW y¸gÆ MNDN nW) ›§¥WS)

12. xND tkú> ÆልሰራW ወንጀል yXMnT ”L y¸s_bT h#n@¬ l!U_M YC§L y¸L XMnT xlምት) bMN MKNÃT Blጦ ያስባሉ)

13. yXMnT ”L ¥ššL XNd¸ÒL ?g# bGL} xSqMጧLÝÝ የK?dT ”LS ¥ššL YÒ§L)

14. bq-éW qN MSKéC úYqRb# yq„ XNdçn F¼b@t! q-é lmS-T XNd¸CL bw¼m¼?¼ስ¼ስ¼q!(94¼2(l¼ tmLKaLÝÝ lmçn# XNÄ!H ›YnT h#n@¬ s!ÃU_M lSNT Gz@ nW mQ-R y¸ÒlW) y›¼?G MSKéC Ãl bq! MKNÃT úYqRb# yq„ XNdçn F¼b@t! MN ›YnT Wún@ mS-T YC§L) ytkú¹# mk§kÃ MSKéC úYqRb# b!q„S)

15. ›¼?G MSKécN qRbW yMSKRnT ”§cWN lF¼b@T kmS-¬cW bðT MN ›YnT ZGJT ¥DrG Y-bQb¬L ይላሉ)

16. y›¼?G MSKéCÂ ytkú¹# mk§kÃ xND§Y qRbW XNÄ!sÑ mdrg# MN _QM YñéêL) ጉዳቱስ?

17. y›¼?G MSKéC bÑl# wYM bkðL úYqRb# b!q„ bF¼b@t! mwsD ÃlbT XRM© MND nW)

18. yqDä y_Ít"nT ¶kRD b¥Sr©nT mQrB ÃlbT mc! nW) lMN YmስLዎታL)

19. yFRD b@t! ¥È¶Ã _Ãq! y¸qRbW mc! nW)

20. kw¼m¼?¼ስ¼ስ¼q!(137¼1¼ yMNgnzbW ngR MNDN nW)

21. Ks# b¸s¥bT g!z@ tkú> b-@Â m¬wK MKNÃT g#Ä†N mk¬tL ÆYCL MN mdrG xlbT)

## ሦስተኛ ጠቅላላ ክፍል

## ልዩ ሥነሥርዓቶች

የወንጀል ጉዳዮች ሁሉ እስካሁን ባየነዉ በመደበኛዉ ሥነሥርዓት ብቻ የሚመሩ አይደሉም፡፡ አንዳንድ ጉዳዮች የተከሳሹን ወይም የወንጀሉን ባህሪ መሰረት በማድረግ፣ ወይም ለህግ አስፈጻሚዉ የህግ ማስፈጸም አመቺነት ሲባል ወዘተ. የተለዩ ሥነሥርዓቶች በህግ እንዲታወቁ ተደርጓል፡፡ ስለዚህ ባለሙያዎች የዚህ አይነት ሥነሥርዓት የሚገዛቸዉን ጉዳዮች የሚያስተናግዱበት አጋጣሚ ስለሚኖር እነዚህን ሥነሥርዓቶች ማወቅና በነዚህ ሥነሥርዓቶች መስራትን መለማመድ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ይህን ለማሳካትም ከዚህ በኋላ ያለዉ በተለያዩ ልዩ የወንጀል ሥነሥርዓቶች ላይ የተመሰረተ ሥልጠና ቀርቧል፡፡ በዚህ ጠቅላላ ክፍል መጠናቀቂያ ላይ ሠልጣኞች

- ስለልዩ ሥነሥርዓቶች የተደነገጉ ህግጋትን ይለያሉ፣
- በነዚህ ሥነሥርዓቶች ላይ የተመሰረቱ ጭብጦች ላይ ክርክሮችን ያቀርባሉ፣ ዉሳኔ ይሰጣሉ

## 1. ምዕራፍ አንድ

## የጸረሙስና ሥነሥርዓት

የወንጀል ምርመራ፣ ክስ አመራር፣አካሄድና ዋስትናን በሚመለከት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርአት መጽሐፍ ከተመለከተው ውጭ አንዳንድ በባሕሪያቸውና አፈፃፀማቸው ለየት ይላሉ የሚባሉ ወንጀሎችን የምርመራ የማስረጃ አሰባሰበና ክስ አቀራረብን የሚደነግጉ የሥነ ሥርአት ድንግጌዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አንዱ በአዋጅ ቁጥር 434/1997 የወጣው የፀረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርአትና የማስረጃ ሕግ ነው፡፡ ይህን በዚህ ክፍል እንመለከተዋለን፡፡

በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 7 ላይ የሙስና ወንጀሎችን ለማየት ሥልጣን የተሰጣቸው የፌዴራል ጠቅላይና ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ሲሆኑ በክልሎች ደግሞ የክልል ጠቅላይና ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ናቸው እንዲሁም ከሙስና ወንጀል ጋር በተያየዘ የሚነሱ የመያዝ፣ የብርበራ፣ የቀነ ቀጠሮ፣ በማረፊያ ቤት የማቆየት፣ የዋስትና የእግድ እንዲሁም ከምርመራ ጋር የተያያዙ ሌሎች ተመሣሣይ ጉዳዮች የሚታዩትም በእነዚሁ ከላይ በተጠቀሱት ፍ/ቤቶች መሆኑ በዚሁ አንቀጽ 7/4/ ላይ ተመልክቷል፡፡ ይህን ህግ በተመለከተ የተለዩ የሆኑ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ነጥቦችን ብቻ እናነሳለን፡፡ ለዚህም አዘዉትሮ የሚሰራባቸዉን የተለዩ የሥነሥርዓት ሁኔታዎችን መርጠናል፡፡

### 1.1. የዋስትና ሥነሥርዓት

በሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰዉ እንደማንኛዉም ሰዉ በዋስ የመለቀቅ መብቱ የተከበረ ነዉ፡፡ ይህም ሂደት እንደማንኛዉም የወንጀል ጉዳይ በመደበኛዉ የሥነሥርዓት ህግ የሚመራ ቢሆንም የተለዩ ሂደቶች የተደነገጉለት ነዉ፡፡

#### 1.1.1 ዋስትና የሚከለከልበት ምክንያት

የፀረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርአትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁ. 434/97 አንቀጽ 4 በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት እንዳላቸው በመርሕ ደረጃ ያስቀምጣል፡፡ ነገር ግን በሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰው ወንጀሉ ከ10 ዓመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በዋስትና ሊለቀቅ እንደማይችል አንቀጽ 4/1/ ይደነግጋል፡፡

የአዋጁ አንቀጽ 4/2/ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 28 ከተመለከተው ጋር ተመሣሣይ ሲሆን መርማሪው አንድን በሙስና ወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘን ሰው የዋስትና ወረቀት አስፈርሞ ስለሚለቅበት ሁኔታ የሚዘረዝር ነው፡፡

**መለማመጃ 1**

በሚዉሉበት ችሎት ሊስተናገዱ ከቀረቡት ጉዳዮች አንዱ የሙስና ወንጀል ክስ ነዉ፡፡ ተከሳሹ ላይ በርከት ያሉ ክሶች ቀርበዋል፡፡ ሁሉም ክሶች እስከአስር ዓመት እና ከዚያ በታች በሆነ የእስራት ቅጣት በሚያስከትሉ ወንጀሎች ላይ የተመሰረቱ ናቸዉ፡፡ ክሱ ከተሰማ በኋላ ተከሳሹ ወንጀሎቹ ከአስር ዓመት በላይ ሊያሳስሩ ስለማይችሉ በዋስ ልለቀቅ ብሎ አመለከተ፡፡

*እርስዎ የችሎቱ ዐቃቤህግ ቢሆኑ ምን ክርክር ያነሳሉ? ይጻፉት*

*ዳኛዉ እርስዎ ቢሆኑና ዐቃቤህግ ጥያቄዉ ዉድቅ እንዲሆን ቢከራከር ምን ይወስናሉ? ይጻፉት*

በሌላ ሁኔታ በቀረበዉ አንድ የሙስና ወንጀል ክስ ስፋትና ዉስብስብነት፣ በተለይም የድርጊቶቹ መብዛት እና የተከሳሾቹ መብዛት ምክንያት ችሎቱ አንዱን ክስ ለአሰራር እንዲመች ሲባል ብቻ በተለያዩ መዝገቦች ተከፋፍሎ እንዲቀርብ ባዘዘዉ መሰረት በበርካታ መዝገቦች እንደገና ተዘጋጅቶ ቀረበ፡፡ ክሱ አንድ ቢሆንም ወንጀሉ የሙስና በመሆኑ የተነሳ ተከሳሾች በዋስ እንዳይለቀቁ ታዝዞ በማረፊያ ቤት ሆነዉ ሲከራሩ ቆይተዋል፡፡ ሆኖም በመሃሉ አዋጅ ቁ 434/1997 ሲወጣ ዋስትና የሚከለከለዉ በቅጣት መጠን መሆኑን ደነገገ፡፡ የ1996 ዓም የወንጀል ህግ በ1997 ዓም በግንቦት ወር ሥራ ላይ ሲዉል ተከሳሾች የተከሰሱበትን ወንጀል እስከአስር ዓመት ብቻ የሚያስቀጣ አድርጎ ደነገገዉ፡፡ ተከሳሾች በዚህ ህግ መሰረት በዋስ እንለቀቅ በማለት አመለከቱ፡፡

*እንደዐቃቤህግ የሚያቀርቡትን መከራከሪያ ይጻፉ*

*ዳኛዉ እርስዎ ቢሆኑ ምን ይወሰናሉ? ዉሳኔዎን ይጻፉ*

### 1.1.2 የዋስትና ዉሳኔ ላይ የይግባኝ ሥነ ሥርዓት

የአዋጁ አንቀጽ 5 የዋስትና መብትን በማክበር ወይም በመከልከል በሚሰጥ ውሣኔ ላይ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚቻል ይደነግጋል፡፡ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 75 ላይ በዋስትና ወረቀት ለመለቀቅ የሚቀርብን ማመልከቻ ፍ/ቤት ውድቅ ካደረገ ይግባኝ ማለት እንደሚቻል በመደንገጉና ዋስትና ከተፈቀደ የይግባኝ ማለት ስለመቻሉ በግልጽ ባለመደንገጉ አንዳንድ ጊዜ በፍ/ቤቶች እና በዐቃቤህግ መካከል ዉዝግብ የሚፈጥር ሆኖ ቆይቷል፡፡ ስለዚህ ይህ የአዋጁ ድንጋጌ የይግባኝ መብቱን በግልጽ ማስቀመጡ ይህን ዉዝግብ ቢያንስ በሙስና ጉዳዮች የሚያስቀር ይሆናል፡፡

ይህ የአዋጁ አንቀጽ 5/2/ ከወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች የተለየ አዲስ ሃሳብ የያዘ ነው፡፡ በመደበኛ ሁኔታ አንድ በዋስትና ለመለቀቅ አቤቱታ ያቀረበ ሰው ፍ/ቤቱ የዋስትና ጥያቄውን ከተቀበለው ከታሳሪዉ የሚጠበቅበት ፍ/ቤቱ ስለዋስትናው የሚጠይቀውን ግዴታ ብቻ ማሟላት ነው፡፡ ይህ ከተሟላ ወዲያውኑ ይለቀቃል ማለት ነው፡፡ በፀረሙስና ልዩ የሥነ-ሥርአት ሕግ ግን ፍ/ቤት ተከሳሽ ወይም ተጠርጣሪው በዋስ እንዲለቀቅ ቢወስንና ተጠርጣሪው ሊያሟላ የሚገባውን ግዴታ ቢያሟላ እንኳን በውሳኔው ላይ ይግባኝ ከተባለበት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኙን መርምሮ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት ተከሳሹ አይለቀቅም፣ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ተግባራዊ ሳይደረግ ይቆያል፡፡

ሆኖም ዓ/ሕጉ ወይም መርማሪው በፍ/ቤቱ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የጠየቀበት መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ከይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በዋስትና ጥያቄው ላይ ውሣኔ ለሰጠው ፍ/ቤት የማቅረብ ግዴታ ተጥሎበታል፡፡ ፍ/ቤቱም በውሣኔው ላይ ይህንኑ ግዴታ በመጥቀስ መርማሪው ወይም አቃቤ ሕጉ ይህን ግዴታውን ባይወጣ ተጠርጣሪው ግዴታዎቹን እንዳሟላ ወዲያዉ እንዲለቀቅ ትዕዛዝ ማስፈር እንዳለበት በአንቀጽ 5/3/ ሥር ተመልክቷል፡፡

**መለማመጃ 2**

*የሙስና ጉዳዮችን በሚያስተናግድ ችሎት ያስችላሉ ብለን እናስብ፡፡ በዚህ ምክንያት ዋጋ በሌለዉ የመሥሪያ ቤቱ ቼክ ተጠቅሞ የብር አርባ ሺ ዕቃዎች ከአንድ መደብር በመግዛት ለግል ጥቅሙ አዉሎ የሙስና ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ የተከሰሰ የአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የዕቃ ግዢ ሠራተኛ ጉዳይ የጊዜ ቀጠሮ ሲጠየቅበት ቆይቶ ምርመራዉ ስለተጠናቀቀ ክስ እስክናቀርብ ተጠርጣሪዉ እንዳይጠፋ በማረፊያ ቤት ይቆይልን ሲል መርማሪዉ ለችሎትዎ አመለከተ፡፡ ሆኖም ተጠርጣሪዉን በማረፊያ ቤት የሚያቆይ ምክንያት የለም ብለዉ በዋስ እንዲለቀቅ ወሰኑ፡፡ ሆኖም መርማሪዉ ይግባኝ እላለሁ ብሎ በችሎት አሳወቀ፡፡ ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ተፈጻሚ የሚሆነዉ ሥነሥርዓ ተጠርጣሪዉ ወዲያዉ እንዲለቀቅ የሚፈቅድ አይደለም፡፡*

*በዚህ መሰረት ስለዋስትናዉ ትዕዛዝ አፈጻጸም ተገቢዉን ትዕዛዝ ይስጡ፣ ይጻፉት*

*በዚህ ጉዳይ ነገሩ የተመራልዎ ዐቃቤህግ እንደሆኑ ያስቡ፡፡ በዋስትናዉ ጥያቄ ላይ የተሰጠዉን ዉሳኔ የሚቃወሙብትን ምክንያት ዘርዝረዉ በመግለጽ የይግባኝ ማመልከቻ ያዘጋጁ*

***የዋስትና ግዴታ ሁኔታዎች፦***

የአዋጁ አንቀጽ 6ም እንደዚሁ ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ ድንጋጌዎች ለየት ያለ ነው፡፡ በዚህ ሕግ መሰረት የዋስ መብቱ የተከበረለት ሰው የመንቀሳቀስ መብቱ በተወሰነ ደረጃ ሊገደብ ይችላል፡፡ ከተወሰኑ አካባቢዎች እንዳይወጣ፣ ከአንዳንድ ቦታዎች (ማስረጃ ሊያጠፋ በሚችልባቸው ቦታዎች) እንዳይደረስ፣ በተወሰነ የጊዜ ልዩነት ውስጥ የሙስና ወንጀልን ለሚያጣራ ወይም ክስ ለመመስረት ሥልጣን ለተሰጠው አካል ሪፖርት እንዲያደርግ እና ወይም ከአገር እንዳይወጣ ገደብ ሊደረግበት ይችላል፡፡

እነዚህ ድንጋጌዎች ከሙስና ወንጀሎች ከባድነትና ውስብስብነት አኳያ በአንድ በኩል የዋስትና መብት መሰረታዊነት እንዳለ ሆኖ በሌላ በኩል ግን ተጠርጣሪዎች ያላግባብ ከተጠያቂነት እንዳያመልጡ በተቻለ መጠን ለመከላከል እና ጥንቃቄ ለማድረግ ታስቦ የተደነገጉ ይመስላል፡፡

## 1.2 ንብረት ስለማገድ እና ስለማስተዳደር

ልዩ የሥነሥርዓትና የማስረጃ ህግ ወደህግ ሥርዓቱ ካስገባቸዉ የተለዩና አዲስ ነገሮች አንዱ በምርምራ ጊዜ ንብረትን ማገድ ይመለከታል፡፡

**መለማመጃ 3**

በጸረሙስና ዐቃቤህግ በተሰጠዉ ዉክልና መሰረት በችሎትዎ የጊዜ ቀጠሮ እየጠየቀ ተጠርጣሪዉን በመመርመር ላይ የሚገኝ የምርምራ ክፍል አለ፡፡ ከቀጠሮዎቹ በአንዱ የተጠርጣሪዉ እና የዘመዶቹ ንብረቶች ናቸዉ በማለት ከትላልቅ ቪላ ቤቶች እስከ ማብሰያ ዕቃዎች ዘርዝሮ በተጠረጠረበት የሙስና ወንጀል የተገኙ ናቸዉና ተቆጥረዉና ታሽገዉ እንዲሁም እንዳይሸጡና እንዳይተላለፉ ታግደዉ እንዲቆዩ ይታዘዝልኝ በማለት በቃለመሃላ አመለከተ፡፡ ተጠርጣሪዉ ግን ከሙስና ወንጀል ጋር ምንም ግንኙነት የላቸዉም፣ ሊታገዱ አይገባም በማለት ተከራከረ፡፡

*በዚህ ጊዜ ምን ይወስናሉ? ዉሳኔዎን ይጻፉ*

ንብረት ከታገደ በኋላ ከንብረቱ ስፋት አኳያ በፍርድቤቱ አስተዳዳሪ ሊሾምለት ይችላል፡፡ ንብረቱ አነስተኛ ሆኖ የተለየና የተመዘገበ ሲሆን እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ ታግዶ በተጠርጣሪዉ እጅ ሊቆይ ይችላል፡፡

## 1.3 የቅድመ ክስ ዝግጅት ሥነሥርዓት

በኢትዮጵያ ፍርድቤቶች ባህል ለረዥም ጊዜ ሳይታወቅ የቆየ ቢሆንም በአንዳንድ የሥነሥርዓት ህጉ ድንጋጌዎች በዉስጠታዋቂ ሊኖር ይችላል ብለን ልንከራከርበት የምንችለዉ የማስረጃ መገላለጥ ሥነሥርዓት በዚህ ልዩ የሥነሥርዓት ህግ ከተካተቱት ጉዳዮች አንዱ ነዉ፡፡ ይህም የቅድመክስ ዝግጅት ተብሎ የተደነገገዉ ሥነሥርዓት ነዉ፡፡

### 1.3.1 ዓላማዉና የሚከናወንበት ምክንያቶች /በተግባር/

ይህ ሥነሥርዓት ዓላማዉ ምን እንደሆነ በአዋጁ ተዘርዝሮ ይገኛል፡፡

ቁ. 36. የቅድመክስ ዝግጅት ዓላማና ሂደት

1/ የቅድመክስ ዝግጅት ዓላማ የሚከተሉት ናቸዉ

ሀ. ለክሱ አወሳሰን ሊረዱ የሚችሉ ጭብጦችን ለመለየት

ለ. ባለጉዳዮች ጭብጦቹን እንዲረዱ እገዛ ለማድረግ

ሐ. የክሱን ሂደት ለማፋጠን

መ. ፍርድቤት የክሱን አካሄድ ለመምራት እንዲያስችለዉ ለማገዝ

እነዚህ ዓላማዎች ያሉት ሥነሥርዓት ቀደም ሲል ስለሙስና ጉዳዮች ታዉጆ የነበረዉ ህግ በአስገዳጅነት በሁሉም የሙስና ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን ይደነግግ ነበር፡፡ ሆኖም ይህን ህግ ባሻሻለዉ በአዋጅ ቁ 434/1997 ይህ ሥነሥርዓት በፍርድቤት አስፈላጊነቱ ሲታመንበት ብቻ እንዲከናወን ተደንግጓል፡፡

በተግባር እንደሚታየዉ የቅድመክስ ዝግጅት ሥነሥርዓት ረዥም ጊዜ ሲወስድ ይታያል፡፡ ይህ የተወሰደዉም ጊዜ ቢሆን ዋናዉን የክሱን ሂደት እንዲያጥር የማድረግ ዉጤት የለዉም፡፡ ምክንያቱም ፍርድቤቶች የቅድመክስ ዝግጅት ሥነሥርዓት ሲያካሂዱ

ማጠቃለያዉ ላይ በዋናዉ የክሱ መስማት ሂደት የሚታዩ ጭብጦችን የመለየት ልማድ እየተዉ መጥተዋል፡፡

### 1.3.2 የቅድመ ክስ ዝግጅት የሚደረግበትና የማይደረግበት አጋጣሚዎች

የቅድመ ክስ ዝግጅት ማድረግ አለማድረግን በተመለከተ በአዋጁ በቁ 35 የተደነገገዉ መርህ ሲታይ ይህን ዝግጅት ማድረግ እንደማያስፈልግ፣ ሆኖም ፍርድቤቱ

> ‹‹የቀረበዉ ክስ ጭብጦችና የማስረጃዉ ዝርዝር ዉስብስብ በመሆኑ ምክንያት የፍርድ ሂደቱን የሚያራዝመዉና የሚያወሳስበዉ መስሎ ከታየዉና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 36 የተመለከቱትን ዓላማዎች ሊያሟላ ይችላል በሎ ካመነ የቅድመክስ ዝግጅት እንዲከናወን ሊወስን…››

እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡

በአሰራር ልማድ የማስረጃዉ ዝርዝር አነስተኛ ከሆነ የሙስና ወንጀሎችን የሚያዩ ችሎቶች የቅድመክስ ዝግጅትን ሥነሥርዓት ሲገድፉት ይስተዋላል፡፡

## 1.4 የማስረጃ ልዩ ሥነሥርዓቶች

በዚህ ልዩ የሥነሥርዓት ህግ ማስረጃን የሚመለከቱ ለየት ያሉ ሂደቶችን ተቀብለናል፡፡ እነዚህ ጉዳዮች ምንም እንኳ የማስረጃ ህግ ስለሌለን ከህጋችን አኳያ ያልተለመደ ነዉ ማለት ባይቻልም በተግባር ከታወቀዉ አቀራረብ ለየት የሚል ነገርን የያዙ ናቸዉ፡፡

### 1.4.1 የህግ ግምት ማስረጃ

አንዳንድ ነገሮችን ማስረዳት አስቸጋሪ በመሆኑ ለህግ ማስፈጸም ጉዳይ መሰናክል ሊሆን ስለሚችል ይህን የማስረዳት ሸክም በህግ ግምት የማዉረድ አሰራር በማስረጃ ህግ የተለመደ ነዉ፡፡ ስለዚህ የሙስና ወንጀልን በተሳካ መንገድ ለመዋጋት ለዚሁ ሲባል የወጡ ህጎችን ያለመሰናክል ማስፈፀም እንዲቻል በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ እንደተረጋገጡ እንዲቆጠር የህግ ግምት ተደንግጎ ይገኛል /የአዋጁ ቁ 57/2//፡፡ ይህ ድንጋጌ በ1996 ዓም በወጣዉና ተፈጻሚነቱ ከአዋጁ በኋላ እንዲሆን በተደረገዉ የወንጀል ህግ በቁ 403 እንደገና ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ይኸዉም

> ‹‹ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በቀር፣ የሙስና ወንጀሎቹ የተፈጸሙት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም ለመጉዳት መሆኑ በተደነገገ ጊዜ በአንቀጹ ዉስጥ

> የተመለከተዉ ግዙፋዊ ፍሬ ነገር /ድርጊት/ እንደተፈጸመ ከተረጋገጠ፣ ድርጊቱ የተፈጸመዉ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራስ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት ወይም የሦስተኛ ወገንን መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት እንደሆነ ይገመታል፡፡››

የሚል ነዉ፡፡ ስለዚህ ይህ አይነት የተለየ የሃሳብ ሁኔታ የተደነገገባቸዉ ወንጀሎችን መሰረት ያደረገ ክስ ከቀረበና የተግባር ክፍሉ በማስረጃ ከተረጋገጠ፣ ይህን የሃሳብ ሁኔታ ማስረዳት ሳያስፈልግ እንደተረጋገጠ ስለሚቆጠር ዐቃቤህግ የማስረዳት ኃላፊነቱን ተወጣ ይባላል፤ ተከሳሽም እንዲከላከል ይጠበቃል፡፡ ይህ የሃሳብ ሁኔታ ስለመኖሩ በህግ የተወሰደዉ ግምት ትክክል እንዳልሆነ የሚያሳይ ማስረጃ በመከላከያነት ከቀረበ ተቀባይነት ይኖረዋል፣ ለማስተባበል የተፈቀደ የህግ ግምት ስለሆነ፡፡

**መለማመጃ 4**

እርስዎ የሙስና ጉዳዮች በሚታዩበት ችሎት ዳኛ ነዎት፡፡ በዚህ ጊዜ የወ/ህ/ቁ/ 408 የሚደነግገዉን ተላልፎ ጉቦ የመቀበል ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ የተከሰሰ ሰዉ ጉዳይ ቀርቧል፡፡ ይህን ጉዳይ በተመለከተ የመንግሥት ሠራተኛ የሆነዉ ተከሳሹ ከአንድ ሰዉ ገንዘብ የተቀበለ መሆኑን ብቻ ዐቃቤህግ በምስክሮች አስረዳ፡፡ ለምን ይህን ገንዘብ እንደተቀበለ ግን አላስመሰከረም፡፡ ይልቁንም ምስክሮቹ ለምን ገንዘቡን እንደተቀበለ እንደማያዉቁ መሰከሩ፡፡ ዐቃቤህግ በዚሁ ብይን እንዲሰጥ ጠየቀ፡፡

*የሚሰጡትን ብይን በአጭሩ ይጻፉ*

ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ላይ የህግ ግምት መደንገግ ለኢትዮጵያ ህግ ሙሉ ለሙሉ አዲስ ነዉ ሊባል አይችልም፡፡ በሙስና ወይም በመንግሥት ሥራ ላይ በሚፈጸሙ ወንጀሎች የታወቀ ባይሆንም በንብረት ላይ በሚፈጸሙ ወንጀሎች ጉዳይ ይህ የህግ ግምት ታዉቆ ይገኝ ነበር፡፡ ይህም በእንግሊዝኛዉና በፈረንሳይኛዉ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቅጂዎች በግልጽ ተደንግጎ የነበረ ሲሆን በአማርኛዉ ግልጽ ሳይሆን ቆይቶ በ1996 ዓም በወጣዉ የወንጀል ህግ በቁ 663 በግልጽ ተደንግጓል፡፡

## 1.4.2 <u>የግብረ አበር ምስክርነት</u>

እንደ የህግ ግምት ሁሉ ህግ የማስፈጸም አቅምን ከፍ ለማድረግ ሲባል በአዋጁ ተቀባይነት ካገኙ አዳዲስ ሥነሥርዓቶች አንዱ ግብረአበርን ምስክር የማድረግ ነገር ነዉ፡፡ ይህም ያለመከሰስ መብት በልዋጩ በማግኘት የሚሰራበት ሥነሥርዓት ነዉ፡፡

በዚህ አይነት ምስክር የሆነ ሰዉ ምስክርነት እንደማንኛዉም ምስክር ምስክርነት እንዲወሰድ ወይም ክብደት እንዲሰጠዉ ተደንግጓል /የአዋጁ ቁ 43/5//፡፡

እንዲህ አይነት ሰዉ ምስክር ሊሆን የሚችለዉ ነገሩ ወደፍርድቤት ከመድረሱ በፊት ነዉ /የወ/ህ/ቁ/ 406/1//፡፡

| **መለማመጃ 5** |
| --- |
| *የሙስና ጉዳዮችን በሚያይ ችሎት ዳኛ ነዎት፡፡ በዚሁ መሰረት የቀረበልዎትን ክስ እያዩ ባለበት ጊዜ በመቃወሚያ በተደረገ ክርክር ከተከሳሾቹ አንዱ በተከሰሰበት ነገር ቀደም ብሎ ተከሶ የተቀጣ ስለሆነ ክሱ ቀሪ ተደርጓል በማለት አሰናበቱት፡፡ ዐቃቤህግም በሌሎቹ ተከሳሾች ላይ ምስክር እያሰማ ባለበት ወቅት የተሰናበተዉ ተከሳሽ ሰጥቶ የነበረዉን የተከሳሽነት ቃል ሲያይ ሌሎቹን ተከሳሾች ወንጀሉን ፈጽመዋል የሚል ይዘት ያለዉ ሆኖ ስላገኘዉ ይህን ሰዉ በምስክርነት ሊያቀርበዉ ጠየቀ፡፡ ሌሎቹ ተከሳሾች ይህ ምስክር አብሯቸዉ የተከሰሰ ስለሆነ ከዚህ በኋላ በምስክርነት ሊጠራ አይገባም በማለት ተከራከሩ፡፡* |
| *በዚህ የተጨማሪ ምስክር አቀራረብ ላይ የተነሳዉን ክርክር ይበይኑ፣ ብይኑን ይጻፉ* |

## 1.4.3 የአስጠቂ ምስክር ሥነሥርዓት

ይህ የልዩ ሥነሥርዓት አዋጅ ከመዉጣቱ በፊት በልማድ ይደረግ እንደነበረዉ አንድ ምስክር በምርምራ ጊዜ ከሰጠዉ ቃል የተለየ ምስክርነት በችሎት ከሰጠ የምርመራ ጊዜ ቃሉን ለፍርድቤቱ በማሳየት ዐቃቤህግ ምስክሩን መሪ ጥያቄ መጠየቅ ይፈቀድለት ነበር፡፡ ይህ ሥነሥርዓት በዚህ የልዩ ሥነሥርዓት ህግ ዕዉቅና አግኝቶ በህግነት ተደንግጓል /የአዋጁ ቁ 44/፡፡ ይኸዉም

> «1/ በዐቃቤህግ ወይም በመከላከያ ምስክርነት የቀረበ ማንኛዉም ሰዉ በምስክርነት በተጠራበት ጉዳይ እዉነቱን ለመናገር ባለመፈለግ ቀድሞ ከሰጠዉ የምስክርነት ቃል የሚቃረን የምስክርነት ቃል የሰጠ እንደሆነ ፍርድቤቱ ምስክሩን ያቀረበዉ ወገን መሪ ጥያቄ እንዲጠይቅ ሊፈቅድለት ይችላል
>
> 2/ ፍርድቤቱ መሪ ጥያቄ እንዲጠየቅ ከመፍቀዱ በፊት ተቃራኒ የምስክርነት ቃል የሰጠ መሆን አለመሆኑን ምስክሩን ይጠይቀዋል፡፡ ምስክሩ ተቃራኒ የምስክርነት ቃል መስጠቱን ከተቀበለ መሪ ጥያቄዉን ይፈቅዳል፡፡

3/ ምስክሩ ተቃራኒ የምስክርነት ቃል መስጠቱን የካደ እንደሆነ ፍርድቤቱ ምስክሩ ተቃራኒ ቃል መስጠት አለመስጠቱን ይወስናል

በማለት ተደንግጎ ይገኛል፡፡

## 2 ምዕራፍ ሁለት

## ስለወጣት አጥፊዎች ወንጀል ሥነሥርዓት

ህጻናት በወንጀል ነገር ገብተው ሲገኙ የሚስተናገዱበት ሂደት ከአዋቂዎች የተለየ ነው፡፡ የተለየ ጥበቃ የሚደረግላቸውን ህጻናት በመለየት ይህ ልዩ ሥነስርዓት ያስፈለገበት ምክንያትና ሂደቱ ምን እንደሚመስል ይዳሰሳል፡፡

የወጣት አጥፊነት የፍትህ ሂደት የሚባለው ህጻናት ወንጀል ፈጽመው ሲገኙ የምንከተለው ሥነስርዓት ነው፡፡ አዋቂዎች ወንጀል ፈጸሙ ሲባል ከምንከተለው መደበኛ አሰራር የተለየ ነው፡፡ ሆኖም ህጻን ማነው የሚለው በቅድሚያ መታወቅ አለበት፡፡

### 2.1 የወጣት አጥፊነት ፍቺ

ህጻን ማለት ኢትዮጵያ በአፀደቀቻቸው የህጻናት መብቶች ኮንቬንሽን /ህመኮ/ አንቀፅ 1፣ የአፍሪካ ህጻናት መብቶች እና ደህንነት ቻርተር /አህመደቻ/ አንቀፅ 2፣ እና በኢትዮጵያ የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 215 መሰረት እድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም ሰው ነው፡፡

ለወንጀል ተግባር ህጻን ማለት እና ለፍትሐብሔር ተግባር ህጻን ማለት የተለያየ ነው፡፡ ለወንጀል ጊዜ የተጠያቂነቱ እድሜ መነሻ እንደ ሃገሩ ሁኔታ ሊለያይ ይችላል፡፡ የወንጀል ተጠያቂነት እድሜ ከፍትሐብሔር ዝቅ ያለ ነው፡፡ በአገራችን ህጻናት ዝቅተኛ የወንጀል ተጠያቂነት እድሜ በወ/ህ/ቁ 53 መሰረት 9 ዓመት ነው፡፡ ወጣት አጥፊዎች ተብለው የተለየ ጥበቃ የሚያገኙት እድሜያቸው ከ9-15 ዓመት የሚሆኑ ህጻናት ናቸው፡፡ በዚህ ፅሑፍ ውስጥም ህጻናት ተብለው የሚጠቀሱትም እነዚሁ ክፍሎች ብቻ ናቸው፡፡ ህጻኑ 15ኛ ዓመት ልደቱን ካከበረ ለወንጀል ህግ ጉዳይ እንደ አዋቂ ይቆጠራል፡፡ በወ/ህ/ቁ 56 መሰረት እድሜያቸው 15-18 ለሆኑት ህጻናት ጥበቃ የሚደረገው ከጥፋተኝነት ውሣኔ በኋላ በቅጣት ጊዜ ብቻ ነው፡፡ የጥበቃው አድማስ

ጠባብ ነው፡፡ ሁሉም ህጻናት ሊካተቱ ይገባል የሚል ተቃውሞ በህጻናት ዙሪያ ከሚሰሩ ድርጅቶች ይደመጣል፡፡ የወጣት አጥፊነት ፍትህ ሂደትን የሚገዙት ድንጋጌዎች በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ 171-180 ያሉት ናቸው፡፡

## 2.2 በወጣት አጥፊዎች ጉዳይ የክስ አጀማመርና የወንጀል ምርመራ ሂደት

ህጻናት ገና በአካልም ሆነ በአእምሮ ያልበሰሉ በመሆናቸው ወደ ወንጀል ውስጥ ገብተው ከተገኙ መታየት ያለበት በዋነኛነት ለዚህ ችግር የዳረጋቸው ምክንያት ነው፡፡ አጥፍተው ሲገኙ አላማው እነሱን መቅጣት ሣይሆን በቀላሉ ሊታረሙ የሚችሉበት የእድሜ ሁኔታ ላይ ስለሚገኙ የወደፊት ህይወታቸው ፈር የሚይዝበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው፡፡ የፍትህ አካላት ሚና መሆን ያለበት እንደ ሐኪም ችግራቸውን ተረድተው መፍትሔ ማፈላለግ ነው፡፡ ለዚህም ተግባር ፍ/ቤቶች የህጻናቱን ችግር ለመገንዘብ የስነ ልቦና እና የማህበራዊ ሣይንስ ባለሙያ እርዳታ ያስፈልጋቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ በአዲስ አበባ ፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በህጻናት ጉዳይ ባለሞያዎችን የማሳተፍ አሰራር ይከተላል፡፡

ህጻናት በወንጀል ነገር ገብተው ከተገኙ ፖሊስ፣ ዓ/ህግ፣ ወላጅ፣ ሞግዚት ወይም የተበደለ ወገን ህጻኑን በጥበቃ ወደ ፍ/ቤት መውሰድ አለበት፡፡ በተበዳይ አቤቱታ የሚያስከስስ ጉዳይ ከሆነ ተበዳዩ አቤቱታ በቅድሚያ ማቅረብ አለበት፡፡ ፖሊስ ፍርድ ቤት የሚሰጠውን ትእዛዝ ሣይቀበል ምርመራውን ማከናወን አይችልም፡፡ ምርመራን ማጣራት የሚኖርበት ፍ/ቤቱ በሚሰጠው መመሪያ ላይ በመመስረት ነው፡፡

**መለማመጃ 6**

በችሎትዎ ከቀረቡት ጉዳዮች አንዱ በተጠራበት ጊዜ የቀረበዉ ተከሳሽ ስለማንነቱ ተጠይቆ ሲያስረዳ ዕድሜዉ 13 ዓመት መሆኑን ገለጸ። በዚህ ጊዜ በዚህ ተከሳሽ ላይ የተጣራዉ ምርመራ በማን ትዕዛዝ እንደሆነ ዐቃቤህጉን ጠየቁት። ዐቃቤህግም ስለዚህ የሚያዉቀዉ ነገር እንደሌለ፣ ነገር ግን ተከሳሹ በምርመራ ጊዜ የሰጠዉ ዕድሜ 16 ዓመት መሆኑን፣ ስለዚህ ምርመራዉን ለማጣራት የማንም ትዕዛዝ እንደማያስፈልግና ጉዳዩ መሰማቱ እንዲቀጥል አመለከተ። በዚህ ጊዜ ተከሳሹ በምርመራ ጊዜም ሆነ አሁን ዕድሜዩ 13 ዓመት መሆኑን ብቻ ነዉ የተናገርኩት፣ ዐቃቤህጉና መርማሪዉ ራሳቸዉ ናቸዉ ዕድሜዩን 16 ዓመት ብለዉ የመዘገቡት ብሎ ለፍርድቤቱ ተናገረ።

*ምን ትዕዛዝ ይሰጣሉ? ይጻፉት*

*ከዚህ ቀጠሮ በኋላ ተከሳሹ ዕድሜዉ ከ12 – 14 ዓመት እንደሚገመት ማረጋገጫ ቢቀርብልዎ /ለምሳሌ የተከሳሹ ወላጆች የተወለደበትን ቀን በመግለጽ ቢመሰክሩ ወይም የትዉልድ ምስክር ወረቀት፣ ወይም የክርስትና ማስረጃ ቢያቀርቡ/ ዉሳኔዎ ምን ይሆናል? ይጻፉት*

ህጻኑ ከ10 ዓመት በላይ በሆነ ፅኑ እሥራት ወይም በሞት በሚያስቀጣ ወንጀል ከተከሰሰ ዓ/ህግ ክስ አዘጋጅቶ ማቅረብ አለበት። በሌሎች ጉዳዩች ግን ዓ/ህግ ክስ ማቅረብ የሚችል መሆን አለመሆኑ አልተደነገገም።

## 2.3 <u>የወጣት አጥፊዎች የፍርድ ሂደት</u>

ዓ/ህግ ክሱን አዘጋጅቶ ካቀረበ በኋላ ጉዳዩን መከታተል ስለመቻል አለመቻሉ ህጉ ላይ የተቀመጠው በከፍተኛ ፍርድ ቤት በሚቀርቡ ጉዳዩች ላይ ብቻ ነው። በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 176 መሰረት ዐ/ህግ በከፍተኛ ፍ/ቤት በሚታዩ ጉዳዮች ላይ መገኘት አለበት። ዐ/ህግ ክሱን ካቀረበ በኋላ መከታተል ስለ መቻሉ ሁለት ዓይነት አተረጓጎም አለ። አንደኛው ዓ/ህግ ክሱን ካቀረበ በኋላ በችሎት ጉዳዩን የመከታተል መብት የለውም የሚለው ነው። ሌላኛው ዓ/ህግ ክሱን ካዘጋጀ ሊከታተል ይገባል፣ ካለዚያ የማይከታተለውን ክስ ማዘጋጀቱ ትርጉም የለውም የሚለው ነው።

የህጻን ወላጆች፣ ሞግዚት፣ አሣዳሪ ወይም ሌላ ቤተዘመድ ካልቀረበ ወይም ከ10 ዓመት በላይ ፅኑ እሥራት ወይም በሞት በሚያስቀጣ ወንጀል ህጻኑ ከተከሰሰ ፍ/ቤቱ የግድ ለህጻኑ ጠበቃ እንዲቆም ማድረግ አለበት።

ህጻኑ ፍ/ቤት ከቀረበ በኂላ መዝገቡ መቀጠር ካለበት ህጻኑን ሊረከብ ለሚችል ወላጅ ወይም ዘመድ ወይም ተቋም መሰጠት አለበት፡፡ ይህ አደራ የተሰጠዉ ወገን ህጻኑን ፍርድቤት የማቅረብ ኃላፊነት የተጣለበት ቢሆንም ለዚህ የሚሆን ዋስትና እንዲሰጥ ይገደድ እንደሆን በህጉ የተደነገገ ነገር የለም፡፡

የችሎቱ አካሄድ መደበኛ የፍ/ቤት ሒደትን የማይከተል መሆን አለበት፡፡  በሒደቱ  ላይ ህጻኑ ሊሰማው የማይገባዉ ነገር ካለ በችሎት እንዲወጣ መደረግ አለበት፡፡ በችሎቱ ውስጥ ዓ/ህግ ሊገኝ ከሚችልበት፣ ከላይ ከተገለፀው ልዩ አጋጣሚ ውጪ መገኘት የሚችሉት ምስክሮች፣ልዩ አዋቂዎች፣ወላጆች፣ሞግዚት ወይም የበጎ አድራጊዎች ድርጅቶች አባላት ናቸው፡፡  ጉዳዩ በዝግ ችሎት የሚስተናገድ ነው፡፡

ክሱ ሲሰማ ተከሳሹ ለክሱ መልስ እንዲሰጥ ስለሚጠየቅ በዚህ ረገድ መነሣት ያለበት ነጥብ ካለ መቃወሚያን ጨምሮ መቅረቡ ተገቢ ነው፡፡  ህጻናትን በተመለከተ የሚሰጥ ፍርድ የተለየ ባህሪ ተብሎ ሊጠቀስ የሚገባው ጉዳይ ታይቶ የተሰጠ የመጨረሻ የሚፈፀም ውሣኔ ወይም ትእዛዝ ቢኖርም ሊሻሻል መቻሉ ነው፡፡ ፍ/ቤቱ በራሱ አስተያየት ወይም የህጻኑ ሐላፊ ወይም አደራ የተቀበለ ሰው ወይም ድርጅት ጥያቄ የተሰጡ ውሣኔዎች እና ትእዛዞች እንደተፈለገ ሊሻሻሉ ወይም ሊለወጡ ይችላሉ፡፡ ይህም የሁኔታዎችን ተለዋዋጭነት ከግምት በማስገባት ለህጻኑ ሊጠቅም የሚችል ማንኛውም ክስተት እያገናዘቡ ለህጻኑ ጥቅም የሚያግዙ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችል ነው፡፡

የህጻናት የፍትህ ሥርዓት የተለየ የሚያደርገው ሌላው አሰራር በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ 160 የተደነገገዉ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት ህጻኑ በሌለበት ክሱ ሊስተናገድ አይችልም፡፡

የችሎት ሂደት በዝግ ሲሆን ክሱ በሚሰማበት ጊዜ ተከሳሹ ክሱን ካላመነ በክሱ ሊመሰክሩ የሚቀርቡትን ምስክሮች የሚመረምረዉ ፍርድቤቱ ነዉ፡፡ ከሳሽ ወገን ሊመረምር ይችል እንደሆነ አልተደነገገም፡፡ አቤቱታዉ ወይም የዐቃቤህግ ክስ ከቀረበ በኂላ ከከሳሽ ወገን ዐቃቤህግ ብቻ በከፍተኛ ፍርድቤት በሚታዩ ጉዳዮች ላይ መቅረብ የሚችል ከመሆኑ በቀር ከሳሽ በሌለበት ነገሩን ፍርድ ቤቱና ተከሳሽ በዝግ ችሎት የሚመረምሩ መሆኑ ተገቢዉ ሥነሥርዓት ነዉ /የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 176/፡፡

ተከሳሽ ክሱን ካመነ በዚሁ ጥፋተኛ ሊባል ይችላል፡፡ ተከሳሽ ክዶ ነገሩ በማስረጃ ከተመረመረ በኋላ የክርክር ማቆሚያ ንግግር ይደረጋል፡፡ ይህንም የሚያደርገዉ የተከሳሽ ወገን ብቻ ነዉ፡፡ ይህም ከሳሹ ወገን በሂደቱ እንደማይሳተፍ ጠቋሚ ነዉ፡፡ ከዚህ ንግግር በኋላ ፍርድቤቱ ፍርድ ይሰጣል፡፡

## 3 *ምዕራፍ ሦስት*

### ስለደንብ መተላለፍ

ydNB m t§lF g#Ä×Cም በt ly |n |R›T b?g# m \ r T mStÂgD xlÆcWÝÝ Xnz!H g#Ä×C MN ›YnT XNdçn#Â mktL y¸gÆN ytly x\‰R MN XNdçn q_lN XNmlk¬ለንÝÝ

ydNB m t§lF wNjL mfiM y¸ÃSkTlW t-ÃqnT q§L mçn#N kGMT b¥SgÆT y|n |R›T ?UCN g#Ä×ቹ y¸StÂgÇbTN xµÿD x+RÂ qLÈÍ XNÄ!çN y¸ÃdRG |R›T zRGaLÝÝ ydNB m t§lF wNjL |n |R›T y¸m‰W bw¼m¼|¼|¼ህ/q 167 XSk 17; Æl#T DNUg@ãC m \ r T nWÝÝ

k¸ÃSkTl#T ¥^b‰ê qWS KBdTÂ QlT xNÉR wNjlÖCN ydNB m t§lፍ yçn#Â ÃLçn# BlÖ mkÍfL bhgሮች ytlmd nWÝÝ y¦g‰CN ywNjL ?GM wNjlÖC k¸ÃSkTl#T xdU KBdTÂ QlT xNÉR wNjLÂ dNB m t§lF ብሎ bh#lT kFlÖ Ymlk¬cêLÝÝ **በደንብ መተላለፍ ተጠያቂነት የሚኖረው** g#Ä† bwNjL ?G y¥Y¹fN çñ s!g" BÒ XNdçn bw¼?¼ቁ 736¼2 SR tdNGÙLÝÝ wNjL y¸Æl#T kw¼?¼ቁ 1 XSk 733 SR ytdngg#T s!çn# kw¼?¼ቁ 734 XSk 865 ytdngg#T dGä dNB m t§lF ÂcWÝÝ

**ሆኖም በክስ ማቅረብ ጊዜ** ywNjLÂ ydNB m t§lF g#Ä×CN mlyT q§L xYdlMÝÝ bwNjL ?g# y¸gß#Â btnÉÉ¶nT bdNB m t§lF WS_ ytµttT kh#lt byT¾W WS_ XNd¸wDq y¸Ãw²Gቡ tGÆ‰TN y¸ÃSqM-# DNUg@ãC Yg¾l#ÝÝ

l**ምሳሌ** ÃKL y¸**ከተሉትን** mzRzR YÒ§LÝÝ XnRs#M yw¼?¼ቁ 481 XÂ bl@§ wgN yw¼?¼ቁ 8;8 XÂ 8;9 Xና ymúsl#T ÂcWÝÝ xND g#ÄY **በአንድ አንቀጽ**

ስር ብቻ ሊሸፈን ከቻለ bh#l t|M bwN j LÂ bdNB m t §l F bxND g!z@ xÃS- YQMÝÝ y¸ mሳሰl# DNUg@ãC s!ÃU_Ñ bQD¸Ã ywN j L ?g# b¸gÆ y¸¹FÂcW mçn# መrUg_ xl bTÝÝ êÂW ywN j L ?G y¥Y¹FÂcW kçn nW wd dNB m t §l F DNUg@ãC ¥M‰T Ãlብን ÝÝ y?UênT mRHN y¸dnGg#T bw¼?¼ቁ 2¼5 XÂ 736¼2 m \ r T xND DRጊT y¸ÃSqÈW bwN j L ?G wYM bdNB m t §l F ?G kh#l t| bxNd¾W BÒ XN©! bh#l t|M mçN yl bT MÝÝ ነገር ግን በሁለቱም የሚያስጠይቅ ጉዳይ ሲያጋጥም ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ክስ ማቅረብ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ በስለት ሰው የወጋ ግለሰብ አካል ላይ ጉዳት በማድረስና ለብቻው ደግሞ በደንብ መተላለፍ ወንጀል ስለት በመያዙ ብቻ ሊጠየቅ ይችላል፡፡

## 3.1 በደንብ መተላለፍ የወንጀል ምርመራ - የተጠርጣሪ መያዝ አስፈላጊነት

በደንብ መተላለፍ ወንጀል ጉዳይ በተከሳሹ ላይ ሊወሰን ከሚችለዉ ቅጣት ዝቅተኛነት የተነሳ ክሱ በሚሰማበት ጊዜ ተከሳሹ መቅረቡ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ተከሳሹ በተላከለት መጥሪያ ላይ መልሱን ማለትም ዕምነት ክህደቱን ጽፎ ፈርሞ ሊመልስ ይችላል /የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 168/፡፡

ከላይ እንደተገለጸዉ ተከሳሹ ክሱን ሲያምን X‰s# bxµL F¼b@T mQr B y¸gd dW y¥ r ðÃ b@T XSR½ yGÁ¬ |‰ wYM የ¥S-Nq q|Ã ወይም የmWqS ቅጣት ለመጣል F¼b@ t| k f l g nWÝÝ kgNzB m q ô W À Ãl# QÈèC µl# kmwsÂcW bðT t kœ¹# እንዲከላከል :DL l!s-W YgÆLÝÝ

ስለዚህ እንዲህ አይነቱን ወንጀል መነሻ በማድረግ ምርመራ ሲጣራ ተጠርጣሪዉን መያዝ ያስፈልግ እንደሆነ መወሰን ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ረገድ የመያዢያ ትዕዛዝ አሰጣጥን የሚደነግጉት የወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓቱን ህጎች መመርመር እና ከዚህ ጋር ያለዉን ግንኙነት መወሰን ያሻል፡፡ /«… ወንጀሉ የሚያስይዝ መሆኑ …» የሚለዉን ሃሳብ ያስታዉሷል/

**መለማመጃ 7**

**የምርምራ ክፍል ባልደረባ የሆነ ፖሊስ በችሎትዎ ቀርቦ የመያዢያ ትዕዛዝ ይሰጠኝ፣ ተጠርጣሪዉ የፈጸመዉን ተግባር እመረምራለሁ በማለት አመለከተ። ነገሩን ሲመረምሩ የደንብ መተላለፍ ነገር መሆኑን ተገነዘቡ።**

***በዚህ ጥያቄ ላይ የሚሰጡትን ትዕዛዝ ይጻፉ***

## 3.2 የተከሳሽ አቀራረብና የክሱ መሰማት

ydNB mt§lF wNjL s!fiM ;”b@ ?G wYM yGL kœ> bq_¬ lF¼b@T xb@t¦¬ b¥QrB tkœ¹#N ¥SqrB YC§LÝÝ **ተከሳሹን ለማስቀረብ** b¸§kW m_¶Ã ytkœ¹# SM½ bdNB mt§lF ytfimW tGÆR½ g!z@Â ï¬½ yt§lfW ?GÂ y?G xNq} t-Qî ltkœ¹# mDrS xlbTÝÝ bq-é qN ;”b@ ?GÂ tkœ>M MSKéCÂ l@lÕC ¥Sr©ãCM µ§ᶦcW XNÄ!ÃqRb# bm_¶Ã l!gl}§cW YgÆLÝÝ

**ቀደም ሲል እንድተገለጸዉ ተከሳሽ ክሱን ካመነ ፍርድቤት በግንባር መቅረብ ላያስፈልገዉ ይችላል። ሆኖም** kµd bq-é qN **በግንባር መቅረብ ያስፈልገዋል። በዚህ ጊዜ ተከሳሹና ዐቃቤህግ ምስክሮቻቸዉን ማቅረብ አለባቸዉ።**

**በደንብ መተላለፍ ወንጀል የ**tbdl wgNM ±l!SÂ ;”b@ ?G zND mÿD œÃSfLgW bq_¬ xb@t¦¬WN lF¼b@T ¥QrB YC§LÝÝ YH FT? bq§l# l^Brtsb# XNÄ!dRS ytzUj |R›T bmçn# **ሊተ**gbR YgÆLÝÝ lz!H xtgÆbR **ዳኛ** X‰s#N xzUJè m-bQ xlbTÝÝ

**የክሱ መሰማት በቃል ይከናወናል። የግራቀኙ ምስክሮች በዚህ አይነት ተሰምተዉ ከቃላቸዉ ዋና ዋናዉ ብቻ በመዝገቡ ይጻፋል።**

## 3.3 የፍርድ አሰጣጥና የቅጣት አወሳሰን

bdNB mt§lF wNjL ክስ F¼b@t| y:MnT ”L ¥rUgÅW kqrblT y;”b@ ?GN xStÃyT sMè በጽሁፍ QÈT ይወስናል ግልባጩንም ለተከሳሹ ይልካል/የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 169/። ይህ የሚሆነዉ የገንዘብ ቅጣት ሲወሰን መሆኑ ግልጽ ነዉ፣ ተከሳሹ ሳይቀርብ የሚወሰን ስለሆነ ግልባጩ ይላክለታል።

kgNzB WÀ yçn# QÈèC yሚwsn# kçn tkœ¹# bF¼b@T m_¶Ã t-Rè mQrB xlበTÝÝ bz!H g!z@ tkœ¹# yF¼b@t|N m_¶Ã xKBé y¥YqRB kçn ¬Sé XNÄ!qRB l!drG YC§LÝÝ

በሌላ በኩል ተከሳሹ ክሱን ካላመነ በግንባር ቀርቦ ማስረጃዎች ተሰምተዉ F¼b@t| wÄ!ÃW tfim ytÆlWN tGÆRÂ tÈs ytÆlWN ?G -Qî x+R y”L FRD ይሰጣል፡Ý h#l# ngR bxND q-é l!ÃLQ y¸CL nWÝÝ

ለደንብ መተላለፍ የሚጣለዉ የእስራት ቅጣት የማረፊያቤት እስራት ሲሆን kxND qN XSk ƒST wR l!rZM YC§L¿ ygNzB mqÅ dGä kBR xND XSk BR ƒST mè wYM bL† h#n@¬ XSk BR xMST mè BR DrS l!ÃDG YC§LÝÝ XNdng„ h#n@¬ y¥rðÃ b@T XS‰TÂ ygNzB mqô tÈMé l!wsN YC§LÝÝ በማረፊያ ቤት እስራት ytqÈ sW y¸¬\rW bmdb¾ XSR b@T œYçN lBÒW btzUj ¥rðÃ b@T nWÝÝ

## 4 ምዕራፍ አራት

## ተከሳሽ በሌለበት ክስ መስማት

### 4.1 መርህ

በመርህ ደረጃ ክስ መሠማት ያለበት ተከሳሽ ባለበት ነው፡፡ በወንጀል ተጠርጥሮ የተከሰሰ ሰው ፍርድ ቤት ቀርቦ ክሱ ደርሶትና ተረድቶት የመሰማት ሕገ መንግሥታዊ መብት እንዳለው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንሥግሥት አንቀጽ 20 ደንግጓል፡፡ ይህ ማለት ግን የወንጀል ክስ ሁሉ ተከሳሽ ፍርድ ቤት ካልቀረበ ታይቶ አይወሰንም ማለት አይደለም፡፡ በሕግ ተለይተው በተመለከቱ ሁኔታዎችና ወንጀሎች ላይ ተከሳሽ በሌለበትም ክሱን ሰምቶ መወሰን ይቻላል፡፡

## 4.2 ቅድመ ሁኔታዎች

የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ ቁጥር 160/2/ ነገሩ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን ተከሳሽ ካልቀረበ ወይም ለመቅረቱ በቂ ምክንያት የሚሰጥለት እንደራሴ ካልቀረበ እንዲያዝ ፍ/ቤት ትዕዛዝ እንደሚሰጥ ይደነግጋል፡፡ በዚህ ትዕዛዝ መሠረት መፈፀም ካልተቻለ ተከሳሹ በሌለበት ነገሩን ለመስማት ፍ/ቤቱ እንደሚያስብበት የዚሁ ህግ ቁ/ 160/3/ ያስቀምጣል፡፡ በዚህ ረገድ በህጉ በቁ 161 ስር የተመለከተዉ ድንጋጌ ተከሳሽ በሌለበት ክስ የመስማትና ያለመስማት ነገርን ለመወሰን አጋዥ ነዉ፡፡ በዚህ ድንጋጌ ተከሳሽ ***ያለበቂ ምክንያት በቀረ ጊዜ*** እርሱ በሌለበት ሊታዩ የሚችሉ ወንጀሎች ዝርዝር ተመልክቷል፡፡

***መለማመጃ 8***

በርስዎ ችሎት የቀረበን ክስ ለመስማት ቀጠሮ ይዘዉ ተከሳሹና ዐቃቤህግ እንዲቀርቡ አዘዙ፡፡ በቀጠሮዉ ዕለት መጥሪያዉን ለተከሳሽ እንዲያደርስ የወሰደዉ ፖሊስ ክፍል ተከሳሹን ማግኘቱንና መጥሪያዉን አስፈርሞ መስጠቱን በመግለጽ ተከሳሽ የፈረመበት ነዉ ያለዉን መተማመኛ በማያያዝ መልስ ሰጠ፡፡ ሆኖም ተከሳሹ ሲጠራ አልቀረበም፡፡ ዐቃቤህግ በበኩሉ ሲጠየቅ ክሱ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 161/2፣ለ/ ከተመለከቱት በአንዱ ወንጀል የቀረበ ስለሆነ ተከሳሽ በጋዜጣ ተጠርቶ ክሱ በሌለበት ይሰማልኝ በማለት አመለከተ፡፡

*በዚህ ክርክር ላይ የሚሰጡትን ትዕዛዝ ይጻፉ*

በሌላ አጋጣሚ ነገሩን ለመስማት በተያዘዉ ቀጠሮዉ ዕለት መጥሪያዉን ለተከሳሽ እንዲያደርስ የወሰደዉ ፖሊስ ክፍል ተከሳሹን ማግኘት አልቻልንም፣ ስለዚህ መጥሪያዉን ለመስጠት አልቻልንም፣ ባገኘነዉ ጊዜ እናቀርባለን በማለት መልስ ሰጠ ወይም አዘዉትሮ እንደሚደረገዉ ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጥቶን እናቅርብ በማለት መልስ ሰጠ፡፡

*ዐቃቤህጉ እርስዎ ቢሆኑ /ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጥ ከሚለዉ ክርክር ሌላ/ ምን ክርክር ያቀርባሉ? ይጻፉት*

*ዳኛዉ እርስዎ ቢሆኑና ዐቃቤህግ በበኩሉ ሲጠየቅ ክሱ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 161/2፣ለ/ ከተመለከቱት በአንዱ ወንጀል የቀረበ ስለሆነ ተከሳሽ በጋዜጣ ተጠርቶ ክሱ በሌለበት ይሰማልኝ በማለት ቢያመለክት የሚሰጡት ትዕዛዝ ምን ይመስላል? ይጻፉት*

አንድን የወንጀል ክስ ተከሳሽ በሌለበት መስማትና መወሰን የሚቻለው በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 161/2/ መሠረት ከ12 ዓመት በማያንስ ጽኑ እሥራት የሚያሳስር ወንጀል ሠርቷል ተብሎ ወይም በአዲሱ የወንጀል ሕግ ቁ/ 343 እስከ 354 ድረስ ያሉ ወንጀሎች ፈጽሟል ተብሎ በጽኑ እሥራት ወይም ከ5000 ብር በላይ በሚያስቀጣ ወንጀል የተከሰሰ ሰዉ ሲሆን ነው፡፡ ከነዚህ በአንዱ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ወንጀሎች ተከስሶ ያለበቂ ምክንያት በቀጠሮዉ ቀን ሳይቀርብ ከቀረ ፍርድቤቱ ተከሳሹ በሌለበት ክሱን ለመስማት ይችላል፡፡ በዚህ መሰረት ፍርድቤቱ ነገሩን ተከሳሽ በሌለበት ለማየት ከወሰነ ይህንኑ ወሳኔና ነገሩ ሊታይ ቀጠሮ በተሰጠበት ቀን ባይቀርብ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ በታዘዘው መሠረት ቀጥሎ እንደሚታይ ለተከሳሹ ለማስታወቅ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 162 መሠረት ፍ/ቤት በጋዜጣ ማስታወቂያ እንዲያወጣ ያዝዛል፡፡ ከጋዜጣ በተሻለ በሌላ መንገድ መጥሪያው ለተከሳሽ ሊደርስ ይችላል ከተባለም አማራጩ ለፍ/ቤት የተተወ ነው፡፡

**መለማመጃ 9**

በአንድ የወንጀል ክስ ከተከሰሱት ሰዎች አንዱ አልቀረበም፡፡ ፖሊስ ነገሩ ሊሰማ በተቀጠረበት ዕለት ተከሳሹን ማግኘት አልቻልንም፣ ስናገኘዉ እናቀርባለን በማለት መልስ ሰጠ፡፡ ሆኖም ይህ ተከሳሽ ከዚህ ቀጠሮ ሁለት ቀናት ቀደም ብሎ በነበረ አንድ ምሽት በፈረንሳይኛ ቋንቋ በሚተላለፍ አንድ የዉጭ ሃገር ሬዲዮ ፕሮግራም ላይ ስለተከሰሰበት ነገርና ስለክሱ መግለጫ በቃለመጠይቅ መልክ ሲሰጥ እንደነበር እርስዎ ዐቃቤህጉ ፈረንሳይኛ ስለሚችሉ ሰምተዋል፡፡ በቃለመጠይቁ ከተነሱት ነገሮች አንዱ ተከሳሹ ያለበት ሃገር መንግሥት ተከሳሹን አሳልፎ እንዲሰጥ በኢትዮጵያ መንግሥት የተጠየቀ ቢሆንም ስምምነት ላይ አለመደረሱን ይልቁንም የተሰጠዉ መልስ የእንቢታ መሆኑን የሚገልጽ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ወንጀሉ በዕድሜልክ ጽኑ እስራት ወይም በሞት የሚያስቀጣ ነዉ፡፡

*እንደዐቃቤህግ በዚህ መረጃ ላይ ተመስርተዉ ምን ክርክር ወይም ለሌሎች ተቋማት ጥያቄ ያቀርባሉ? ይጻፉት*

ከላይ የሚያቀርቡት ክርክር እንዳለ ሆኖ ወደቢሮዎ ሲመለሱ ከዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተላከ ደብዳቤ አገኙ እንበል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ተከሳሹ ተላልፎ እንዲሰጥ የተደረገዉ ጥረት አለመሳካቱንና ቀርቦ የነበረዉ ክስ ላይ በዚሁ መሰረት ተገቢዉ ዉሳኔ እንዲሰጥበት የሚጠይቅ ነዉ፡፡

*በዚህ ላይ ተመስርተዉ ለፍርድቤት የሚያቀርቡት የተለየ ክርክር ይኖራል? ይጻፉት*

*በሌላ በኩል ወንጀሉ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 161/2/ ስር የተመለከቱትን ወንጀሎች የሚመስል ባይሆን ከላይ በተመለከቱት ሁኔታዎች ላይ ተመስርተዉ የሚሰጡት ዉሳኔ ወይም የሚያቀርቡት ክርክር ወይም ጥያቄ ካለ ይጻፉት*

## 4.3 የክሱ መሰማትና ፍርድ አሰጣጥ

ነገሩ ተከሳሽ በሌለበት እንዲሰማ ፍርድቤቱ የወሰነ እንደሆነ ተከሳሽ ነገሩ ሊሰማ የተቀጠረበትን ጊዜና ይህን ዉሳኔዉን የሚያዉቅበትን የጋዜጣ ጥሪ ያደርጋል፡፡ ከዚህ በኋላ በዕለቱ ተከሳሽ መቅረብ አለመቅረቡን ያጣራል፡፡ ተከሳሹ በዚህ ዕለት ካልቀረበ ነገሩ ***እንደማንኛዉም ጉዳይ*** ተሰምቶ ይወሰናል፡፡

በተግባር እንደሚታየዉ ግን ፍርድቤቶች የዚህን የጋዜጣ ጥሪ ሥነሥርዓት የሚያከናዉኑት ተከሳሹ በሌለበት ነገሩ የሚሰማ መሆኑን ሳይወስኑ ነዉ፡፡ ተከሳሽ በሌለበት ነገሩን ለማየት የሚወስኑት እንዲያዉም ከዚህ የጋዜጣ ጥሪ በኋላ ነዉ፡፡ ይኸዉም የጋዜጣ ጥሪን እንደመጥሪያ ምትክ እየተገለገሉበት መሆኑን ያሳያል፡፡

**መለማመጃ 10**

በችሎትዎ በቀረበ የወንጀል ክስ በርካታ ተከሳሾች ተመልክተዋል፡፡ ከነዚህም ዉስጥ ከፊሉ በማረፊያ ቤት ቆይተዉ የቀረቡ ሲሆን ከፊሉ የተከሰሱበት ወንጀል በዋስ አያስለቅቅም ተብሎ በማረፊያ ቤት እንዲቆዩ ታዝዟል፡፡ ቀሪዎቹ ሁለቱ መጥሪያ ደርሷቸዉ ከፈረሙ በኋላ በመቅረታቸዉ ቀደም ባለዉ ቀጠሮ በተሰጠዉ ትዕዛዝ /ተይዘዉ እንዲቀርቡ በታዘዘዉ/ መሰረት ፖሊስ ሊፈጽም ስላልቻለ ዐቃቤህግ በጋዜጣ ተጠርተዉ የማይቀርቡ ቢሆን ነገሩ በሌሉበት ይሰማልኝ በማለት አመለከተ፡፡ ሆኖም በማረፊያ ቤት ሆነዉ የሚከራከሩት ተከሳሾች በዉጭ ያሉት ተከሳሾች መጥሪያ ደርሷቸዉ ያልቀረቡ ስለሆነ በጋዜጣ የሚጠሩበት ምክንያት የለም፣ ስለዚህ ነገሩ በሌሉበት እንዲሰማ ቀጠሮ ሊያዝ ይገባል እንጂ በጋዜጣ ተጠርተዉ መቅረባቸዉን ለመጠባበቅ ቀጠሮ ሊሰጥብን አይገባም በማለት ተከራከሩ፡፡

*በዚህ ነገር ላይ ትዕዛዝ በጽሁፍ ይስጡ*

# 5 ምዕራፍ አምስት

## የወንጀል ተጠቂዎች መብቶች

የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ ዓላማና ግብ በወ/ህ/ቁ 1 እንደተደነገገዉ

> "የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግሥት፣ የሕዝቦቹን፣ የነዋሪዎቹን ሰላም ደህንነት ሥርዓት መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው፡፡ የወንጀል ሕግ ግብ ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፣ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው በማድረግ ነው"

የወንጀል ሕጉ ዓላማና ግብ እንደሚያስረዳው ትኩረቱ ቅድመ ማስጠንቀቂያ መስጠት ሲሆን ፤ አጥፊም ሆነ ተጎጂ ከመኖራቸው በፊት ሊደረጉ የሚገባቸውን ወይም የማይገባቸውን ነገሮች አስቀድሞ በማሳወቅ ላይ ያተኮረ እንደመሆኑ ተደራሽነቱ (የሕግ መተላለፍ እስከሚፈፀም ድረስ) ለአጥፊም ሆነ ለተጎጂ እኩል ሆኖ ይስተዋላል፡፡

የወንጀል ሕጉ ወደሚፈፀምበት የሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች በምንመጣበት ጊዜ ዋናው ሕግ በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ሊያስቀጡ ይችላሉ ብሎ ለአጥፊም ለተጎጂም እኩል ያስቀመጣቸው ጉዳዮች ተጥሰው በሚገኙበት ወቅት የሚወሰደው ቀጣይ እርምጃ የሚመራበትን ሥርዓት የሚደነግግ እንደመሆኑ ለወንጀል ተጠርጣሪዎችም ሆነ ለወንጀል ተጠቂዎች ሊከበሩ የሚገቡ መብቶች ተካተውበት እናገኛለን፡፡

እስከአሁን በተሰጠዉ ሥልጠና በአብዛኛዉ የታየዉ የወንጀል ህግን በማስፈጸም ጊዜ የተከሳሽ ወይም የአጥፊዉን መብቶች ስለመጠበቅ ጉዳይ ምን ሊደረግ እንደሚገባ ነዉ፡፡ በርግጥ ወንጀል ፈጸመ ተብሎ የታሰበን ሰዉ ለፍርድ የማቅረቡ ሂደት በራሱ የወንጀል ተጎጂዎችን ጥቅም የማስከበር ተግባር ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ግለሰብ የወንጀል ተጠቂም ሆነ ኅብረተሰብ ወንጀል ሰርቷል የተባለን ሰዉ ለፍርድ እንዲቀርብ ማድረግ በከፍተኛ ሁኔታ የሚያገባቸዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ ከዚህ ባለፈ ደግሞ ሌሎች የተጎጂዎች መብቶችን የሚመለከት ሥልጠና ከዚህ በኋላ ይቀርባል፡፡

ስለ ወንጀል ተጠቂዎች በሚነሳበት ወቅት ጎልቶ የሚወጣ አንድ ጥያቄ አለ፡፡ ይኸውም የወንጀል ተጠቂ ማን ነው? የሚለው ነው፡፡ በዚህ ጥያቄ ዙሪያ በተለያዩ ምሁራንና የአመለካከት ዘርፎች ምላሽ ተሰጥቶበታል፡፡ በአጠቃላይ ለመረዳት እንደሚቻለውም እንደወንጀሉ ሁኔታ የወንጀል ተጠቂ የሚለው ፅንሰሃሳብ የተለያዩ አካላትን ሊያካትት የሚችል ነው፡፡ ለምሣሌ ያህል በወንጀል ጉዳዮች ላይ ዐቃቤ ሕግ በተሟጋችነት መቅረቡ በአንድ የወንጀል ድርጊት አጠቃላይ ተጠቂው ማህበረሰቡ በጠቅላላው መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ በተጨባጭም አንዳንድ የወንጀል ድርጊቶች አጠቃላይ የማህበረሰቡን ቁጣ ሲቀሰቅሱና አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ ህብረተሰቡ በሰላማዊ ሰልፍና በተለያዩ መንገዶች ስሜቱን ሲገልፅ የሚስተዋልባቸው አጋጣሚዎች አሉ፡፡ ይህም ከግል ተበዳይ ሌላ በአንድ የወንጀል ድርጊት የአጠቃላይ ህብረተሰቡ ሰላማዊ ሕይወት ሊናጋ እና አንድ ማህበረሰብ እንደማህበረሰብ የወንጀል ተጠቂ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችልባቸው አጋጣሚዎች እንዳሉ የሚያመለክት ነው፡፡

የወንጀል ተጠቂ የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ ጠበብ አድርገን ስንመለከተው ደግሞ በመጀመሪያ ረድፍ የምናገኘው በወንጀል ምክንያት ቀጥተኛ ሰለባ የሚሆኑትን የግል ተበዳዮች ወይንም ደግሞ የግል ተበዳዮችን ቤተሰቦች ነው፡፡ አንድ የሥርቆት ወንጀል ቢፈፀም ሥርቆት የተፈፀመበት አካባቢ ህብረተሰብን ሰላማዊ ኑሮ መደፈር ከማሰብ ባሻገር ንብረቱ የተሰረቀበት ግለሰብ ንብረቱን በማጣቱ የሚደርስበት ቁሳዊ ጉዳት የግል ህይወቱ በመደፈሩ የሚደርስበት ሞራላዊ ጥቃት ሊታሰብ የሚችል ነው፡፡ በተመሳሳይ አንድ የግድያ ወንጀል ቢፈፀም የሟች ቤተሰቦች ላይ የደረሰው ጥቃት በህብረተሰቡ ሰላማዊ ኑሮ ላይ ከሚደርሰው ጥቃትና ተፅእኖ ተለይቶ ሊታይ የሚችል ነው፡፡

ከላይ ለማየት እንደተሞከረዉ ሁሉም የወንጀል ተጠቂዎች ወንጀል ፈጽሟል የተባለዉን ሰዉ ለፍርድ እንዲቀርብ የማድረግ መብት አላቸዉ፡፡ በዚህ ረገድ ኅብረተሰቡ በጠቅላላ በዚህ ሂደት በዐቃቤህግ ተወክሎ ይሳተፋል፡፡ የግል ተጠቂዉ ግን በሂደቱ ዉስጥ የመሳተፉ ነገር በተግባር በጣም ዉስን ነዉ፡፡ ነገር ግን በህግ ዉስጥ ይህን ተሳትፎ የሚፈቅዱ አጋጣሚዎች የሉም ወይ የሚል ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ነዉ፡፡

በአሁኑ ጊዜ በዓለም አካባቢ የወንጀል ተጎጂዎችን መብት በተመለከተ የሚደረጉ ንቅናቄዎች የሚያነሷቸዉ የተለያዩ መብቶች አሉ፡፡ እነዚህ መብቶችን በጠቅላላዉ በክስ ሂደት የመሳተፍ መብት እና የካሳ መብት ብለን ከፋፍለን ማየት እንችላለን፡፡

በዚህ የሥልጠናዉ ክፍል መጠናቀቂያ ላይ ሠልጣኞች

- የወንጀል ተጠቂ ግለሰቦች በወንጀል ሥነሥርዓት ሂደቱ ዉስጥ እንዲሳተፉ መንገድ የሚከፍቱ የህግ ድንጋጌዎችን ይለያሉ
- እነዚህን ድንጋጌዎች በመከተል የወንጀል ተጠቂዎችን በሂደቱ ለማስተፍ ቢሰራ የሚያጋጥሙ ችግሮች ይኖሩ እንደሆን ይመረምራሉ
- የወንጀል ተጠቂዎችን በወንጀል ሥነሥርዓት ሂደት ዉስጥ ለማሳተፍ የሚችል አሰራርን ለመለማመድ በአንዳንድ ጭብጦች ላይ ክርክር ያቀርባሉ፣ ዉሳኔ ይሰጣሉ
- የወንጀል ተጎጂዎችን የካሳ መብት የሚመለከቱ ህግጋትን በመለየት ስለአፈጻጸማቸዉ በሚነሱ ችግሮች ላይ ክርክር ያቀርባሉ ዉሳኔ ይሰጣሉ

## 5.1 የወንጀል ተጠቂዎች በክስ ሂደት የመሳተፍ መብት

የወንጀል ተጠቂ የሆነ ሰዉ የመጀመሪያ ፍላጎቱ ይህን ጥቃት ያደረሰበትን ሰዉ ለፍርድ እንዲቀርብ ማድረግ ነዉ፡፡ ይህን ለማሳካት በሚከናወነዉ ሂደት እንዲሳተፍ ማድረግ ይህን ፍላጎቱን ወይም ጥቅሙን ማስከበር ነዉ፡፡ በተለይ ደግሞ ይህን ሂደት ለማሳካት የሦስተኛ ወገኖች /ለምሳሌ ሌሎች ምስክሮች/ ተሳትፎ ሁልጊዜና በቀላሉ ላይገኝ የሚችል ከመሆኑ አኳያ ለወንጀሉ ከማንም በላይ ከተከሳሹ እኩል ቅርበት ያለዉንና በሙሉ ፍላጎት ሊሳተፍ የሚችለዉን ተጠቂዉን ማሳተፍ የህግ ማስፈጸምን ችሎታ ከፍ ሊያደርግ የሚችል በመሆኑ ተመራጭ ነዉ፡፡ ስለዚህ ይህ የመሳተፍ ነገር ተጠቂዉ ሊጠይቅ እና ሊከበርለት የሚገባዉ መብት ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ይህ በተለይ የመደመጥ መብት የሚባለዉን መብት የሚመለከት ነዉ፡፡

በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ ዉስጥ ይህን ተሳትፎ የሚፈቅዱ መንገዶች ተደንግገዉ ይገኛሉ፡፡ ወንጀሉ ተፈጸመ ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ የተጠቂዉን ትብብርና ተሳትፎ የሚጠይቁ የተለያዩ የህግ ማስፈጸም ሂደቶች በነዚህ ህጎች ተመልክተዉ ይታያል፡፡

**መለማመጃ 11**

የወንጀል ተጠቂ የሆነ ሰዉ ወንጀሉን በተመለከተ በሚከናወኑት ሂደቶች ዉስጥ ተሳታፊ የሚሆንባቸዉን መንገዶች የሚገዙትን ወይም የሚደነግጉትን ህግጋት የተቻለዎትን ያህል ፈልገዉ ያግኙ፣ ይዘርዝሯቸዉም

ከነዚህ ዉስጥ የወንጀል ተጠቂዉ በፍርድቤት ፈቃድ ወይም አጋዥነት ይህን ተሳትፎ የሚያገኝባቸዉን መንገዶች የሚደነግጉትን ህግጋት ይለዩ፡፡

እንዲሁም በዐቃቤህግና በምርመራ ክፍሎች ፈቃድና ተቆጣጣሪነት የሚገኝን ተሳትፎ የሚገዙትን ህጎች ይለዩ

የወንጀል ተጠቂዎች መልስ የሚሹ ብዙ ጥያቄዎች ይኖሯቸዋል፡፡ ለምን ጥቃቱ በእኔ ላይ ደረሰ? ጥቃቱ በእኔ ላይ እንዳይደርስ ምን ማድረግ ነበረብኝ? ወደፊትስ ተመሳሳይ ጥቃት እንዳይደርስብኝ ምን ዋስትና አለኝ? ወዘተ. የሚሉት ጥያቄዎች በወንጀል ተጠቂዎች አእምሮ የሚመላለሱ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የደረሰባቸው የወንጀል ድርጊት ስላሳደረባቸው ማህበራዊና ስነልቦናዊ ጠባሳ ለመደመጥ ይሻሉ፡፡ ስለሆነም በሕግ ፊት ቀርበው መደመጥ ይፈልጋሉ፡፡

የወንጀል ተጠቂዉ ወንጀል የተፈፀመበት መሆኑን ራሱ ወይም ሌላ ሰዉ ለባለሥልጣን ሊያሳዉቁ መብት እና አንዳንዴም ግዴታ አለባቸዉ፡፡ በዚህ ጊዜ የምርመራ ክፍሎች ይህን የተጠቂዉን ተሳትፎ በሚገባ ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡ ምንም ያህል አጠራጣሪ ሁኔታ ቢሆን በሥነሥርዓት ህጉ እንደታዘዘዉ መርማሪዉ የወንጀል የተጠቂዉ የወንጀል ሪፖርት ሲደርሰዉ ምርመራ ማከናወን አለበት /የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 23/፡፡
ነገር ግን ምርምራ ክፍሉ ይህን ግዴታ ሳይወጣ ቢቀር ተጠቂዉ ምርመራዎች እንዲከናወኑ ለማዘዝ ለሚችለዉ ለዐቃቤህግ ተቋም ይህን አቤቱታ በማቅረብ ተሳትፎዉን ማሟላት ይችላል /የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 8 እና 16/፡፡ በዚህ በኩል መንገዱ ከተዘጋ ግን በሌላዉ ተቋም በፍርድቤት በኩል ተሳታፊ መሆን የሚችልበት መንገድ ይኖር እንደሆን ሊመረመር ይገባል፡፡ በርግጥ በዚህ ደረጃ ከምርመራ ጋር በተያያዘ የሚሰሩ ወገኖች የበለጠ ባለሥልጣን ስለሆኑ በፍርድቤት ፈቃድ ተሳታፊ የመሆኑ ነገር የጠበበ ይመስላል፡፡

**መለማመጃ 12**

በእርስዎ ችሎት አንድ ያልተለመደ አቤቱታ ቀርቧል፡፡ አቤቱታዉን ያቀረበዉ ሰዉ ወንጀል ተፈጽሞብኛል፣ ሆኖም የአካባቢዉ ፖሊስም ሆነ ዐቃቤህግ ተቋማት የወንጀሉን ሪፖርት በቃል ሰምተዉ ምስክሮችን እንሰማለን፣ ሌላ ማስረጃም እናሰባስባለን አንተን ግን የከሳሽነትም ሆነ የምስክርነት ቃል አንቀበልህም ስላሉኝ ከዚህ ወንጀል ጋር በተያያዘ ቃል ለመስጠት እፈልጋለሁ፣ ፍርድቤቱ ይመዝግብልኝ የሚል ነዉ፡፡

*ይህን አቤቱታ እንዴት ያስተናግዱታል፣ ትዕዛዝ በጽሁፍ ይስጡበት*

የምርምራዉ ተግባር በተጠቂዉ ተሳታፊነት መከናወኑ ሊቀጥል ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ግን ተጠርጣሪዉ በሚያቀርበዉ የዋስትና ጥያቄ ክርክር ተደርጎ ዉሳኔ በፍርድቤት ሊሰጥ ይችላል፡፡ ይህ ዉሳኔ ለተጠቂዉ ስጋት የሚፈጥር ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህ አኳያ ፍርድቤት ተጠቂዉን በማሳተፍ ረገድ ምን ሊያደርግ እንደሚችል ጥያቄ ይነሳል፡፡

**መለማመጃ 13**

ተጠርጣሪዉ በርስዎ ችሎት በሚታየዉ የጊዜ ቀጠሮ ጉዳይ በዋስትና ወረቀት ልለቀቅ በማለት አመለከተ፡፡ መርማሪዉ ምርመራዬን ጨርሻለሁ፣ ተጠርጣሪዉ በዋስትና ወረቀት ቢለቀቅ አልቃወምም አለ፡፡ በዚህ ጊዜ ተጠቂዉ በርስዎ ችሎት ተገኝቶ ነገሩን እየተከታተለ ስለነበር ማንነቱን አሳዉቆ ተጠርጣሪዉም ሆነ መርማሪዉ ያቀረቡትን ክርክር በመቃወም ለመናገር ፈቃድ ጠየቀ፡፡

*የዚህን ሰዉ ጥያቄ ይቀበሉታልን? ምክንያትዎን በመግለጽ ዉሳኔዎን ይጻፉ*

ተጠቂዉን እንዲናገር ፈቀዱለት እንበል፡፡ ተጠቂዉ ለፍርድቤቱ የተናገረዉ ፍሬነገር ተጠርጣሪዉ በእስር ላይ ባለበትና ምርመራዉ ሲከናወን በነበረበት ጊዜ ከጎበኙት ሰዎች እንዲሁም በምስክርንት በፖሊሰ ተፈልገዉ በምርመራ ክፍሉ ተገኝተዉ ከነበሩ ሰዎች ባገኘዉ መረጃ መሰረት ተጠርጣሪዉ ከእስር እስኪፈታ እንጂ ተጠቂን ለአሁኑ ጉዳት ሲገርመዉ ነፍሱን ሊያጠፋዉ እንዳቀደ ማወቁን የሚገልጽ ሆኖ በዚህ ምክንያት በዋስትና ወረቀት እንዳይለቀቅ የሚማጸን ነዉ፡፡

*ምን ይወስናሉ? ይጻፉት*

የዋስትና ጥያቄ ከሚከለከልባቸዉ ምክንያቶች አንዱ ሌላ ወንጀል በተጠርጣሪ ሊፈጸም ይችላል የሚለዉ እምነትና የማስረጃ መባከን ስጋት ነዉ፡፡ ይህም በተጠርጣሪዉ ተግባር የሚፈጠር ስጋት ነዉ፡፡ ተጠርጣሪዉ በተለያየ መንገድ ምስክሮች ወደፍርድቤት

እንዳይቀርቡና እንዳይመሰክሩ ሊያደርግ ይችላል፡፡ በዚህ ምክንያትና በምስክሮች መጥፋት ምክንያት ክስን ማስረዳት አለመቻል ስለሚከሰት ወንጀል የፈጸመዉን ሰዉ ለፍርድ አቅርቦ ፍርዱን እንዲያገኝ የማድረግ የኅብረተሰብና የግል ተጠቂዉን መብቶች ይጎዳሉ፡፡ ስለዚህ በዚህ ነገር ተጠቂዉ የሚያገባዉ መሆኑ ግልጽ ነዉ፡፡

**መለማመጃ 14**

*ፖሊስ ምርምራ የሚያደርግበት የከባድ ዉንብድና ጉዳይ በጊዜ ቀጠሮ መዝገብ እርስዎ እያዩት ይገኛል፡፡ የምስክሮች ቃል /የተጠቂና ቤተሰቡ ቃል/ በምርመራ ክፍሉ ተመዝግቦ አልቋል፡፡ ሆኖም ጥቂት የምርመራ ማጠናቀቂያ ተግባራት ስለሚቀሩ እነዚህን ለማከናወን የጊዜ ቀጠሮ ጠይቋል፡፡ ተጠርጣሪዉ አልተቃወመም፡፡ በጊዜዉ ተጠቂና ቤተሰቡ በችሎትዎ ተገኝተዉ ነበር፡፡ ስለዚህም ለመናገር ፈቃድ ጠየቁ፡፡ ፈቃድ ከሰጧቸዉ በኋላ የተናገሩት ፍሬነገር ሲታይ የዲቪ ዕጣ ስለወጣላቸዉ ከጥቂት ቀናት በኋላ በዉጭ ሃገር ለመኖር እንደሚሄዱ፣ ስለዚህ ክሱ በሚሰማበት ጊዜ ስለማይገኙ ክሱ በዚህ ምክንያት እንዳይመክን ስጋት እንዳላቸዉ የሚገልጽና ይህን ለማስቀረት የምስክርነት ቃላቸዉ በፍርድቤት ዋጋ ያለዉ ማስረጃ እንዲሆን በቀዳሚ ምርመራ እንዲመዘገብላቸዉ ይታዘዝ ዘንድ የሚጠይቅ ሆኖ አገኙት፡፡*

*በዚህ ጥያቄ ላይ የሚሰጡትን የተጠቂዉን ጥቅም የሚያስጠብቅ ዉሳኔ ይጻፉት*

በዚህ ጉዳይ ዐቃቤህግ እንደሆኑ ያስቡ፡፡ ፍርድቤቱም ከተጠቂዉ የቀረበዉን ጥያቄ አስመልክቶ ሃሳብ እንዲያቀርቡ ጋበዘዎት፡፡

*ይህን የተጠቂ ጥያቄ እንዴት ያስተናግዱታል? ዉሳኔዎን ይጻፉት፡፡*

በሌላ በኩል ወንጀሉ በአካል ላይ ጉዳት የማድረስ ወንጀል እንደሆነ ያስቡ፡፡

*እንደዳኛ የተበዳዮችን ጥያቄ እንዴት ያስተናግዱታል?*
*እንደዐቃቤህግ ምን ይወስናሉ?*

በሌላ ሁኔታ ደግሞ ተበዳዮች የቀረቡት ፍርድቤቱ ምስክርነታቸዉን በወ/መ/ሀ/ሥ/ሥ/ቁ 35 መሰረት እንዲመዘግብላቸዉ ነዉ ብለን እናስብ፡፡

*በዚህ ጥያቄ ላይ የሚሰጡትን ዉሳኔ በጽሁፍ ያቅርቡ*

ምርመራ ተከናዉኖ ; " b͒ ?G ከሚወስናቸዉ ዉሳኔዎች ከፊሎቹ ሂደቱ እንዲቋረጥ የሚያደርጉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ክስ አይቀርብም ወይም ምርመራዉ ይዘጋል የሚሉ ዉሳኔዎችን ሊሰጥ ይችላል፡፡ b¥ÂcWM MKNÃT ሂደቱ ሲቋረጥ lb§Y ; " b͒ ?G½ l ± l!SÂ l t bÄY ¥œwQ XNÄlbT bw¼m¼?¼|¼|¼q|. 39¼4 XÂ 43¼2 |R t dNGg͒ Sl ¸ g" h#Lg!z͒ m t GbR x l bTÝÝ YH GL}nትÂ t - ÃqነTN l ¥S f N wœ" x \ ‰R bm çn# l!¬ለፍ xYgÆMÝÝ

btlY ተበዳዩ በሂደቱ ዉስጥ እንዲሳተፍ ከማድረግ አኳያ ከፍ ያለ አስተዋጽዖ ይኖረዋል፡፡ ltbÄY ¥œwq QR ktsß lb§Y ;”b ?G xbt¬WN b¥QrB g‡Ä† XNdgÂ XNÄ!¬Yና ምናልባትም ሂደቱ እንዲቀጥል l!ÃSdRG የሚችልበትን መንገድ ይከፍታልÝÝ ስለዚህ በህግ የታወቀ ግዴታ እንደመሆኑ ይህን ዉሳኔ ytbdl sW qRï XSk!-ይQ ሳይጠብቅ X‰s‡ ዐቃቤህግ ሊያደርሰዉ ይገባልÝÝ

በግል አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጡ ወንጀሎችን በተመለከተ አቤቱታዉ ሳይቀርብ የትኛዉም ባለሥልጣን ጉዳዩን ማየትና መወሰን አይችልም፡፡ በዚህ ነገር ዋናዉ ባለሥልጣን ተጠቂዉ ነዉ፡፡

***መለማመጃ 15***

በግል አቤቱታ ብቻ በሚያስቀጣ ወንጀል በተከሰሰ ሰዉ ጉዳይ ላይ እያስቻሉ ባሉበት ሁኔታ ለምስክርነት የቀረበዉ ተበዳይ ከመመስከሩ በፊት ማመልከቻ አቀረበ፡፡ ይዘቱም በተከሳሽ ላይ የቀረበዉ ክስ ቀሪ እንዲሆን የሚጠይቅ ነዉ፡፡

*በዚህ ጥያቄ ላይ ተገቢዉን ትዕዛዝ ይጻፉ*

*በሌላ በኩል ያለግል አቤቱታ ለማስቀጣት በሚችል ወንጀል ጉዳይ ተበዳዩ ተመሳሳይ አቤቱታ ቢያቀርብ የሚሰጡት ዉሳኔ የተለየ ይሆናልን? ለምን?*

*ከላይ በተመከቱት ሁኔታዎች የችሎቱ ዐቃቤህግ እርስዎ ቢሆኑ ለተበዳዩ ጥያቄ የሚያቀርቡትን ክርክር በጽሁፍ ያስፍሩ*

ለወንጀል ክስ ከማንም የበለጠ ምስክር ሊሆን የሚችለዉ ለነገሩ እጅግ ቅርብ የሚሆነዉ ብዙዉን ጊዜ ተጠቂዉ ነዉ፡፡ ሆኖም አንዳንድ ጊዜ ባለማስተዋል ወይም በሌላ ምክንያት ተጠቂዉ በምስክርነት እንዳይቀርብ ስለሚፈለግ በምስክርነት ሳይቆጠር ሊቀር ይችላል፡፡ በዚህም የተነሳ በክስ ሂደቱ ዉስጥ እንዳይሳተፍ ይደረጋል፡፡

**መለማመጃ 16**

በችሎትዎ በመታየት ላይ ባለ አንድ የወንጀል ጉዳይ ምስክሮች እንዲቀርቡ ተብሎ በተቀጠረበት ዕለት ምስክሮች ሳይቀርቡ ቀርተዋል፡፡ በዚህ ጊዜ በችሎት የተገኘ አንድ ሰዉ ተነስቶ በዚህ ጉዳይ ተበዳይ ነኝ፣ በፖሊስ ምርመራ ጊዜ ቃሌን ስሰጥ በፍርድቤት ተጠርተህ ይህን ቃልህን ትስጣለህ ተብዬ ነበር፣ ነገር ግን አሁን በምስክርነት እየተጠሩ ያሉ ሰዎች በወንጀሉ ጊዜ በቦታዉ ያልነበሩ ቢሆንም ጎረቤቶቹ ናቸዉ፣ ዛሬ ወደዚህ ፍርድቤት ስመጣ አግኝቻቸዋለሁ፣ የትም ሄደዉ አያዉቁም፣ ያም ሆኖ በነገሩ የበለጠ የማዉቀዉ እኔ ስለሆንኩ ምስክርነቴ ሊሰማ ይገባል፣ ነገሩን ወደሌላ ቀን ከመቅጠር ፍርድቤቱ ምስክርነቴን ይስማኝ ብሎ ተናገረ፡፡

*ይህን ጥያቄ እንዴት ያስተናግዱታል? ይህን ሰዉ አርፎ እንዲቀመጥ ወይም ከችሎት እንዲወጣ ያዝዛሉ ወይስ ችሎት ደፍሯል ብለዉ ይቀጡታል ወይስ ለነገሩ ትኩረት ሰጥተዉ በጥያቄዉ ላይ ለመወሰን ይመረምራሉ? ዉሳኔዎን ይጻፉት*

ለነገሩ ትኩረት በመስጠት ለመመርመር ስለወሰኑ ይህ ሰዉ ባቀረበዉ ጥያቄ ላይ ተከሳሹን ምን እንደሚል ጠየቁ፡፡ ተከሳሹም ይህ ሰዉ በክሱ ዉስጥ በምስክርነት ያልተመለከተ ሰዉ ስለሆነ ሊመሰክር አይገባም አለ፡፡ ዐቃቤህግ ስለዚህ ሰዉ የማዉቀዉ ነገር የለኝም፣ ስለዚህ የማቀርበዉ ሃሳብ የለም አለ፡፡ ነገር ግን በክሱ ዉስጥ የወንጀሉ ተጠቂ በምስክርነት ያልተቆጠረ መሆኑን አመነ፡፡ የተናጋሪዉን ማንነት በሚገባ ሲያጣሩ በርግጥም የወንጀሉ ተጠቂ መሆኑን አረጋገጡ፡፡

*የሚሰጡትን ትዕዛዝ ይጻፉት*

ፍርድ ቤት በኢትዮጵያ ህግ ሥርዓት ካለዉ ሰፊ ሥልጣን አኳያ በምስክርነት ያልተቆጠረን ሰዉ አስቀርቦ ሊሰማ ይችላል፡፡

አንድ ተጠርጣሪ በቀረበበት የወንጀል ክስ መብቱ አለአግባብ ተገድቦ እንዳይቆይ የተፋጠነ ፍትሕ የማግኘት መብቱ መጠበቅ ያለበትን ያህል በወንጀል ተጎጂ የሆኑ ሰዎችም እንዲሁ ለቀጣይ ሰላማዊ ህይወታቸው ዋስትና ለደረሰባቸው የወንጀል ጥቃት አፋጣኝ ፍትህ ይሻሉ፡፡ ስለዚህ ክሱ በተገቢዉ ፍጥነት ያላግባብ ከሚሰጡ ቀጠሮዎች ነጻ ሆኖ እልባት ማግኘት ይኖርበታል፡፡ ለዚህም ለፍርዱ ሂደት ሊቀርቡ የሚገባቸዉ በፍርድቤት የተፈለጉ ሰዎችና ነገሮች በጊዜ መቅረብ አለባቸዉ፡፡

የምስክር ወይም የተከሳሽ አለመቅረብ ኅብረተሰብና የግል ተበዳይ ወንጀል የሰራን ሰዉ ለፍርድ አቅርቦ እንዲፈረድበት ለማድረግ ያላቸዉን መብት የሚጎዳ ነዉ፡፡ እነዚህ ሰዎች ፍርድቤት

ሳይቀርቡ የሚቀሩት አንዳንድ ጊዜ በህግ አስፈጻሚ አካላት ባልደረቦች ፍላጎት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል የሚጠቁሙ ቅሬታዎች በፍርድቤቶች ሲሰሙ ይስተዋላል፡፡ ስለዚህ ምስክርም ሆነ ተከሳሽ ሳይገኝ ቀርቶ ሳይሆን አንዳንድ ግለሰቦች ስላልፈለጉ የማይቀርቡበት አጋጣሚ ይኖራል ማለት ነዉ፡፡

**መለማመጃ 17**

*ተከሳሹን ፖሊስ እንዲያቀርበዉ ለተደጋጋሚ ጊዜ የቀጠሩበትን መዝገብ ጠርተዉ እያስተናገዱ ነዉ፡፡ ዐቃቤህግ ፖሊስ የጻፈዉ ነዉ ያለዉን ደብዳቤ በመጥቀስ ተከሳሹ ሊገኝ ስላልቻለ በተገኘ ጊዜ ክሱ እንዲቀጥል ታዝዞ እሰከዚያዉ ድረስ ተቋርጦ ይቆይ የሚል ጥያቄ አቀረበ፡፡ ሆኖም አንድ በችሎቱ ዉስጥ ተቀምጠዉ የነበሩ ሴት ተነስተዉ ወንጀሉ የተፈፀመዉ በኔ ላይ ነዉ፣ ተከሳሹን አዉቀዋለሁ የመንደሬ ኗሪ ነዉ፣ ጧት ማታ ስወጣ ስገባ አየዋለሁ፣ የሚኖረዉ ሁሌም በሚኖርበት አድራሻዉ ነዉ፣ በተለያዩ አጋጣሚዎች የፖሊስ ባልደረቦች ወደቤቱ እየመጡ አነጋግረዉት ሲመለሱ አይቻለሁ፣ ሆኖም እስካሁን አልተገኘም እየተባለ መልስ ሲሰጥ እየታዘብኩ ስመለስ ቆይቻለሁ፣ ዛሬ እንዲያዉም ከፖሊሶቹ ጋር እዚሁ ፍርድቤት ግቢ ዉስጥ ቆሞ አይቼዋለሁ፣ ወዲዉም ፖሊሶቹን ተሰናብቶ ሄዷል፣ ስለዚህ ይህን ሰዉ ፖሊስ ጣቢያዉ አስገድዶ እንዲያቀርበዉ ማድረግ ይገባል እንጂ ክሱ ሊቋረጥ አይገባም በማለት ተናገሩ፡፡*

*በዚህ መሰረት የሚሰጡትን ትዕዛዝ ይጻፉ*

*ትዕዛዝዎ የተጠቂዋን በሂደቱ የመሳተፍ ጥቅም ምን ያህል ያስከብራል?*

*ይህን ሁኔታ ከምስክር አለመቅረብ ጋር በማያያዝ ተመሳሳይ ልምምድ ያድርጉ*

በተለምዶ በፍርድቤት የሚፈለጉ ሰዎችን እንዲያቀርብ የሚታዘዘዉ የፖሊስ ተቋሙ ነዉ፡፡ ሆኖም በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 52/2/፣ 125 እና ሰንጠረዥ ሦስት 6ኛና 11ኛ ፎርሞች እንደተመለከተዉ እንዲህ አይነትን ሰዉ አስገድዶ የማቅረብ ስራ እንዲከናወን የሚፈለገዉ ሥሙ ተለይቶ በሚገለጽ የፖሊስ ተቋሙ ባልደረባ ነዉ፡፡

የወንጀል ተጎጂዎችን በምስክርነት መቁጠር ከላይ እንደተመለከተዉ አንዳንድ ጊዜ ችላ የሚባል ቢሆንም በተለምዶ ግን የዘወትር ተግባር ነዉ፡፡ ይህም የፍትህ አስተዳደር ሂደቱን የማገዝ ሚና ይጫወታሉ ማለት ነዉ፡፡ ነገር ግን ይህን የሚያደርገዉ በጉዳዩ የራሱ ጥቅም ስላለ ነዉ ተብሎ የራሱ ጉዳይ ነዉ ሊባል አይገባም፡፡ ምስክር በመሆኑ ከቀደሙት አጥቂዎቹ /ከተጠርጣሪዎች/ የሚሰነዘርበት ተጨማሪ ጥቃት ሊኖር ይችላል፡፡ ከዚህ የመጠበቅ መብት አለዉ፡፡ በዚህ ረገድ የፌዴራል ፍትህ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁ

691/2003 ቁ 16/13/ እንደተደነገገዉ የወንጀል ጠቋሚዎችንና ምስክሮችን ጥበቃ እንዲደረግላቸዉ የማድረግ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ ተጠቂዎች በተጠርጣሪዎች የታወቁ ምስክሮች ስለሚሆኑ በቀላሉ ለተጨማሪ ጥቃት የተጋለጡ ናቸዉ፡፡

ይህ ተጋላጭነት ግን ለምስክርነት ከመቅረብ በፊት ባለዉ ጊዜ ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ ምስክርነት ለመስጠት በቀረቡበት ጊዜም ይህ ችግር ሊደርስባቸዉ ይችላል፡፡ የወንጀል ተጎጂዎች ጥቃታቸውን በአደባባይ ለመግለፅ የሚያጋጥማቸው አእምሮአዊ ጫና እንዲሁም በፍርድ ሂደት ሊያጋጥሟቸው ከሚችሉና መንፈሣቸውን በማቁሰል ለዳግም ተጎጂነት ከሚዳርጓቸው ሁኔታዎችም ጥበቃ ያሻቸዋል፡፡ አንዳንድ የወንጀል ጉዳዮች የሚያሳድሩት የሥነ ልቦና ጫና እጅጉን የከፋ ሊሆን ይችላል፡፡ በእንደነዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ተጎጂዎች በግልፅ ችሎት ቀርበው እንዲመሰክሩ ማድረግ ለተጨማሪ ስነ ልቦናዊ ቀውስ ሊዳርጋቸው የሚችልበትን አጋጣሚ ስለሚፈጥር አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ወቅት ሁሉ ዐቃቤ ሕግ ፍርድ ቤቱ የምሥክርነት ቃላቸውን በዝግ ችሎት እንዲሰማ ማሳሰብ መቻል አለበት፡፡
ከዚህ በተጨማሪ የወንጀል ተጎጂዎች የምሥክርነት ቃላቸውን በሚሰጡበት ወቅት በዋና ጥያቄ፣ በመስቀለኛም ሆነ በማጣሪያ ጥያቄ ሞራላቸውን ሊነኩና የደረሰባቸዉን ጥቃት ደግመዉ ደጋግመዉ እንዲያስታዉሱት ወይም እንዲኖሩት ሊያደርጉ ከሚችሉ ጥያቄዎች እና አስተያየቶች ሊጠበቁ ያሻል፡፡ በዚህ ረገድ ዐቃቤህግ ጥያቄዎቹን በመቃወም፣ ፍርድቤትም እነዚህ ጥያቄዎች እንዳይጠየቁ በማድረግና ራሱም ከንደዚህ አይነት ጥያቄ በመታቀብ የተጎጂዉን ጥቅም መጠበቅ ይኖርባቸዋል፡፡

በቅጣት አወሳሰን ጊዜ አዘዉትሮ እንደሚስተዋለዉ ዐቃቤህግ የወንጀል ሪከርድ ከሌለ ወይም ወንጀሉ ተደራራቢ ካልሆነ በቀር የቅጣት ማክበጃ ክርክር አያቀርብም፡፡ እንዲሁም በህግ ኃላፊነት ቢኖርበትም የቅጣት ማቅለያና ማክበጃ ሲያቀርብ አይስተዋልም፡፡ በዚህ ረገድ የወንጀል ተጎጂዉ የጎላ ሚና ሊኖረዉ ይችላል፡፡ ተጎጂዉን በመስማት የቅጣት አወሳሰኑን ሂደት የተሟላ ማድረግ ይቻላል፡፡ እንዲያዉም በአንዳንድ የወንጀል ጉዳዮች ተከሳሾች በቅጣት አወሳሰን ጊዜ ተበዳዮችን ይዘዉ በመቅረብ ተበዳዩ ወንጀሉን በተመለከተ ለተከሳሹ ይቅርታ ማድረጉን፣ ዕርቅ መዉረዱን፣ ወዘተ እንዲመሰክሩላቸዉ የማድረግ አዝማሚያ በተግባር እየተስተዋለ ነዉ፡፡

## 5.2 የወንጀል ተጠቂዎች የካሳ መብት

ለደረሰባቸው ቁሳዊ፣ ሞራላዊና አካላዉ ጥቃት የወንጀል ተጎጂዎች ካሣ የማግኘት መብት ይህንንም ለማረጋገጥ የህግ ድጋፍ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

የወንጀል ተግባራት ብዙዉን ጊዜ የጉዳት ካሳ ጥያቄ ያስነሳሉ፡፡ በዚህ አይነት ከዉል ዉጭ በሆነ ሁኔታ ጥፋት በሆነ ተግባር ጉዳት ሲደርስ የተጎዳዉ ሰዉ ካሳ የማግኘት መብት አለዉ፡፡ ይህም የፍትሃ ብሄር ነገር በመሆኑ በተለምዶ እና በመደበኛነት ወደፍትሃብሄር ጉዳዮች ፍርድቤት ይቀርባል፡፡

**መለማመጃ 18**

የወንጀል ጉዳይ በሚያዩበት ችሎት በወንጀሉ ተበድያለሁ ያለ ወገን የደረሰበት ጉዳት እንዲካስ የካሳ ጥያቄ አቀረበ፡፡ ተከሳሹና ዐቃቤህግ ጥያቄዉን ተቃወሙ፡፡ የቀረበዉ ክስ ራሱን የቻለ የፍትሃብሄር ክስ ስለሆነና ይህንን ክስ የሚያይ ፍርድቤት ስላለ እዛዉ ያቅርብ እንጂ በወንጀሉ ጉዳይ ላይ መወሳሰብ ስለሚፈጥር ፍርድቤቱ ሊያስተናግደዉ አይገባም አሉ፡፡

*የቀረበዉን የካሳ ጥያቄ በተመለከተ ተገቢ የሚሉትን ትዕዛዝ ይስጡ፡፡*

*ትዕዛዙ የተጠቂዉን የካሳ መብት ምን ያህል የሚያስከብር ነዉ? ይተንትኑ*

ለዚህ ዉሳኔዎ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 154 እና 155 የሚደነግጉትን ይመልከቱ

ጉዳት የደረሰ እንደሆን የዚህን ጉዳት ያህል ካሳ ማግኘት መብት ነዉ፡፡ ይህ ማለት ጉዳት እና ካሳ ተመጣጣኝ ነዉ ማለት ነዉ፡፡ ይህን የካሳ መጠን ለማስከፈል የወንጀሉን ጉዳይ ለሚያየዉ ፍርድቤት ክስ ቀርቦ ሊወሰን ይችላል፡፡ ነገር ግን ይህ ዉሳኔ ተፈጻሚ ላይሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም ተከሳሹ ካሳዉን ለመክፈል አቅም ላይኖረዉ ይችላል፡፡

**መለማመጃ 19**

ከወንጀል ጉዳይ ጋር ተጣምሮ የቀረበለዎትን የካሳ ጥያቄ ተቀብለዉ ካስተናገዱ በኋላ ተከሳሹ ተጠቂዉን ሊክስ እንደሚገባ ስለተገነዘቡ ካሳ እንዲከፍል ወሰኑ፡፡ የካሳዉ መጠን ከደረሰዉ ጉዳት ጋር ሊመጣጠን ስለሚገባዉ የተከሳሹን አቅም ግምት ዉስጥ ሳያስገቡ የወሰኑት የካሳ መጠን ከተከሳሹ አቅም በላይ ሆነ፡፡ ስለዚህ ለማስከፈል የሚቻል አልሆነም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የተጠቂዉ ካሳ የማግኘት መብት አለ፡፡

*ይህን ችግር የሚፈታ ህግ በኢትዮጵያ አለ? ካለ በዚህ ህግ መሰረት ተገቢዉን ትዕዛዝ ይስጡ፡፡*

ከ1923 ዓም የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ጀምሮ በህጋችን ዉስጥ ተካቶ የሚገኝ የካሳን ጉዳይ የሚመለከት ድንጋጌ አለ፡፡ በ1923 ዓም የወንጀል ህግ ቁ/ 18 ስር የተደነገገዉ

> ስለስድብና ስለበትር ስለአካል ጉዳት ለተበዳዩ የሚክሰዉን ለመቀጫ ለዳኝነት የሚከፍለዉ ገንዘብ የሌለዉ ድሃ የሆነ እንደሆነ ዳኛዉ ለመጠባበቂያ ከሚያስቀምጠዉ ከመቀጫዉ ገንዘብ ለተበዳዩ ከፍሎ በደለኛዉን አስሮ ስራ እያሰራ ካሳዉንና መቀጫዉን ያስከፍላል፡፡ ለመጠባበቂያ የተቀመጠ የመቀጫ ገንዘብ ከሌለ ግን መንግሥት መክፈል የለበትም፡፡

የሚል ሲሆን የ1949 ዓም የወ/መ/ህ/ ቁ 101/1/ የሚከተለዉን ደንግጎ ነበር

> ወንጀለኛዉ ወይም ስለርሱ ባለመብቶች የሆኑ በኑሯቸዉ ምክንያት በተበዳዩ ላይ ለደረሰዉ አደጋ ሊክሱ የማይችሉ መሆናቸዉ በተገመተ ጊዜ ከወንጀለኛዉ ላይ ከተያዘዉ ዕቃ ከሚገኘዉ ገንዘብ ዉስጥ፣ ወይም በዋስትናዉ መያዣ ስም ካስያዘዉ ገንዘብ ዉስጥ፣ ወይም በጉልበት ሥራዉ አገልግሎት ከሚገኘዉ የደሞዝ ሂሳብ ዉስጥ፣ ወይም ከንብረቱ ዉርስ ሂሳብ ዉስጥ ለተበዳዩ እንዲከፈል ፍርድቤቱ ለማዘዝ ይችላል፡፡

ይህን ሃሳብ የ1996 ዓም የወንጀል ህግ

> ወንጀለኛዉ ወይም ስለርሱ ተጠያቂ የሆኑት እንደነገሩ ሁኔታና ወይም በኑሯቸዉ ምክንያት በተበዳዩ ላይ ለደረሰዉ ጉዳት ሊክሱ የማይችሉ መሆናቸዉ በታወቀ ጊዜ ከወንጀለኛዉ ላይ ከተያዘዉ ዕቃ ከሚገኘዉ ገንዘብ ዉስጥ ወይም በዋስትና መያዣ ስም ካስያዘዉ ገንዘብ ዉስጥ ወይም ከመቀጮ ዉስጥ ወይም በጉልበት ሥራ ተለዉጦ ከሚያገኘዉ የገቢ ሂሳብ ዉስጥ ወይም ከተወረሰዉ ንብረት ሂሳብ ዉስጥ ለተበዳዩ እንዲከፈል ፍርድቤት ለማዘዝ ይችላል፡፡

በማለት ድንግጎታል፡፡

የወንጀል ተጠቂዎች የካሳ መብታቸዉን ለማስከበር በፍርድቤት ለመከራከር አቅም ላይኖራቸዉ ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ መብታቸዉን ለማስከበር የሚያስችሉ የተለያዩ ህግጋት ሥራ ላይ እንዲዉሉ ማድረግ ተገቢ ነዉ፡፡ የኢፌዴሪ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁ 691/2003 በቁ 16/11/ እንደተደነገገዉ የፍትሃብሄር ክስ ለመመስረትና ካሳ ለመጠየቅ አቅም ለሌላቸዉ ተጎጂዎች በወኪልነት ፍትህ ሚኒስቴር እንዲከራከር ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፡፡ የፌዴራል ፍርድቤቶች ጠበቆች ሥነምግባር ደንብ ቁ 57/1992 በቁ 49 እንደሚደነግገዉ ነጻ አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ መደረግ አለበት፡፡

## ግለ መመዘኛና መወያያ ጥያቄዎች

1. ፀረ ሙስና አዋጅ ቁ.434/97 አንቀጽ 5 እና 6 ላይ የተጠቀሱት ገደቦች የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 19(6) እና 32 ይቃረናሉ ማለት ይቻላል?
2. ለዋስትና በአዋጅ ቁ 434/97 ላይ የተመለከተው የ10 ዓመት መስፈርት መተርጎም ያለበት እንዴት ነው? መነሻ ቅጣቱ ዝቅተኛም ቢሆን ከ10 ዓመት በላይ ሊያስቀጣ ከቻለ በቂ ነው?
3. ydNB m t§lF wNjL MNDnW )
4. l dNB m t§lF g♯Ä×C ?g♯ y t ly |R›T yzrUW lMNDnW)
5. l dNB m t§lF y t z r g♯T y t lÃ† |R›èC MNDÂcW) k m db¾W ywNjL FT? £dT bMN YlÃl♯)
6. ywNjL ?G XÂ ydNB m t§lF ?G DNUg@ãC b t GÆR XNÁT t t Rg♯mW |‰ §Y l!Wl♯ YgÆL)
7. የወጣት አጥፊዎች የፍትህ ሥርዓት ምንድነው?
8. ህጻናት በወንጀል ነገር ገብተው ሲገኙ የተለየ ጥበቃ የሚደረግላቸው ለምንድ ነው?
9. በኢትዮጵያ ህገ መንግስት፣ በህ.መ.ኮ. እና በአ.ሕ.መ.ድ.ቻ. ለወጣት አጥፊዎች ጥበቃ የሚሰጡት ድንጋጌዎች በሀገራችን አሁን ባለው ሁኔታ በወንጀል ህጉ ስነስርዓት አተገባበር ላይ እየተንጸባረቁ ነው ብለዉ ያስባሉ? እንዴት እንደሆነ ይወያዩ
10. እድሜያቸው ከ15 እስከ 18 አመት የሆኑ ህጻናትን እድሜያቸው ከ9 እስከ 15 ዓመት እንደሆኑ ህጻናት በተመሣሣይ ሁኔታ ቢስተናገዱ ምን ጥቅምና ጉዳት ይኖረዋል?
11. በህገ መንግሥቱና በአለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶች ሰነዶች የተደነገጉ የህጻናት መብቶችን ለማክበርና ለማስከበር ከፍትህ አካላት ምን ይጠበቃል?
12. የወጣት ጥፋተኞች የፍትህ ሂደት እንዴት ይተገበራል?

13. ፍ/ቤት የፖሊስን የምርመራ መዝገብ ተመልክቶ ከክስ መሰማት በፊት መዝገቡን ለመዝጋት ያለዉ ሥልጣን ምን ያህል ነዉ?
14. ነገሩ በሚሰማበት ጊዜ ህጻኑን ለመረከብ የሚጠይቅ ሰው የዋስትና ግዴታ መግባት አለበት ወይ?
15. ዓ/ህግ ህጻናትን በተመለከተ በወረዳ ወይም በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሚስተናገዱ ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጡ የወንጀል ጉዳዮች ክስ ካዘጋጀ በኋላ ችሎት ተገኝቶ መከታተል ሊፈቀድለት ይገባል? በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 176 ስር ለከፍተኛ ፍ/ቤት ለሚቀርቡ የወንጀል ጉዳዮች ዐ/ህግ በችሎት ተገኝቶ እንዲከታተል ከተደነገገው አንጻር እንዴት ያዩታል?
16. አንድ ተከሳሽ ጉዳዮ በሌለበት የሚታየው መነሻ ቅጣቱ 12 ዓመት ከሆነ ነው ወይንስ መነሻ ቅጣቱ ዝቅ ያለ ቢሆንም 12 ዓመት ድረስ ካስቀጣ ነው?
17. በሌለበት የተፈረደበት ሰው ያልነበርኩት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው ሲል ጉዳዮ ከአቅም በላይ ነው ለማለት መስፈርቱ ምንድንነው?
18. በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 202 መሰረት ጉዳዩ እንደገና መታየት ካለበት ዐ/ሕግ ስለሁኔታው በክሱ ላይ ገልጾ አዲስ ክስ በሌላ መዝገብ ማቅረብ አለበት ወይስ በዚያው መዝገብ ላይ ጉዳዩ በሌላ አዲስ ዳኛ/ኞች እንዲታይ መደረግ አለበት?
19. ተከሰሹ የፍ/ቤት መጥሪያ ደረሶት ቢቀር እና ታስሮ እንዳይቀርብ ቢሰወር ወይም ጉዳዩን መከታተል ከጀመረ በኋላ ሆነ ብሎ ቢሰወር በጋዜጣ እንዲቀርብ ጥሪ ማድረግ ምን ያህል ተገቢ ነው? ፍ/ቤቱ ስለ ሁኔታው መዝግቦ ጉዳዩን ተከሳሽ በሌለበት በቀጥታ መመልከት አይችልም?

## አራተኛ ጠቅላላ ክፍል

## ከፍርድ በኋላ የወንጀል ህግ ሥነሥርዓት

የወንጀል ሥነሥርዓት ሂደት እስከፍርድ ድረስ ብቻ የሚዘረጋ አይደለም፡፡ ከፍርድ በኋላም የወንጀል ሥነሥርዓት ይቀጥላል፡፡ የተሰጠዉን ፍርድ ያልረካበት ተከራካሪ ወገን እንደገና የሚያስመረምርበት ሂደት ከፍርድ በኋላ የሚጀምር ነዉ፧ የይግባኝ ሂደት፡፡ እንዲሁም በልዩ ሥነሥርዓቶች ክፍል እንደታየዉ አንድ ሰዉ በሌለበት ነገሩ ቢታይና ቢፈረድ ከፍርዱ በኋላ ይህን በሌለበት የተሰጠን ፍርድ የተመለከተ ክርክር

የሚያካሂድበት ዕድል አለዉ፡፡ ፍርዱ ቢሻሻል ወይም ቢጸና የሚፈጸምበት መንገድ በዚህ ከፍርድ በኋላ ባለዉ ደረጃ የሚከናወን ነዉ፡፡ ስለዚህ እነዚህን ሂደቶች አስመልክቶ ለባለሙያዎች ከዚህ ቀጥሎ ያለዉ ሥልጠና ቀርቧል፡፡ በዚህ ክፍል ማለቂያ ላይ ሠልጣኞች

- ስለይግባኝ፣ ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠ ፍርድን ስለማስቀረት እና ስለቅጣት አፈጻጸም የተደነገጉትን ህግጋት ይተነትናሉ
- ስለነዚህ ህግጋት አፈጻጸም የሚነሱ ችግሮችን ይመረምራሉ
- በነዚህ ህግጋት አፈጻጸም ጊዜ የሚከሰቱ ችግሮችን ለማስቀረት የሚችል አሰራር በጉዳዮቹ ላይ የተለያዩ ክርክሮችን በማቅረብና ዉሳኔ በመስጠት ይለማመዳሉ

## 1. ምዕራፍ አንድ

## ስለይግባኝ

ይግባኝ ምን እንደሆነ ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህጉ ላይ አናገኝም፡፡ ዝርዝር ድንጋጌዎቹን በማየት ግን ይግባኝ ማለት አንድ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለትን የወንጀል ክስ በማቋረጥ ተከሳሹን ለጊዜው በመልቀቅ በሰጠው ትዕዛዝ፤ ወይም የቀረበለትን የወንጀል ክርክር ከህጉና ከማስረጃ ጋር አገናዝቦ በሚሰጠው የመጨረሻ ፍርድ ላይ ቅሬታ ያለው ሰው ቅሬታውን ለበላዩ ፍርድ ቤት አቅርቦ የተሰጠውን ትዕዛዝ/ፍርድ ትክክለኛነት የሚያስመረምርበት ሂደት ነው ማለት ይቻላል፡፡

የይግባኝ ስርዓት መኖር የተጀመረን የክርክር ሂደት የሚያረዝም ነው፡፡ ከጊዜና ከወጪ አንፃር ሲታይ ከፍ ያለ ኪሳራን የሚያመጣ፣ የተከሰሰ ሰው የተፋጠነ ፍትህ ማግኘት አለበት ከሚለው መሠረታዊ መርህ ጋር የሚጣረስ ተደርጐ ሊወሰድም የሚችል ነው፡፡ ይሁንና ይግባኝ የማለት መብት በአፈፃፀሙ ልዩነት ሊታይበት ከሚችል በቀር በሁሉም የህግ ሥርዓቶች አለ፡፡ ስለሆነም የይግባኝ ሥርዓትን መዘርጋት ለምን አስፈለገ የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል፡፡ እንዲኖር የተፈለገው ከሞላ ጐደል በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፡፡

### ሀ. ሥህተቶችን ማረም

አንድ የወንጀል ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ ቀርቦለት ፍርድ የሚሰጥ አካል የሚደርስበት መደምደሚያ ከቀረበው ማስረጃና ከህጉ ጋር የሚጣጣም ይሆናል የሚል ግምት አለ፡፡ የተቋሙ ሥራ የሚከናወነው በሰዎች እንደመሆኑ መጠን ግን በማስረጃዎችና በህጉ ላይ ከሚኖረው የግንዛቤ ልዩነት የተነሳ ፍርዶች ሁሉ ቁርጥ ያለ አንድ መደምደሚያ ይኖራቸዋል ማለት ያስቸግራል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ዳኞች በአንድ ፍሬ ነገር ወይም ህግ ላይ ያልተሟላ መረጃን መሰረት በማድረግ ወይም የተሳሳተ ግንዛቤን በመያዝ የሚሰጡት ፍርድ መደምደሚያውምስህተት ሊሆን ይችላል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የሰጡትን ፍርድ ሥህተት ነው ብሎ አፍ ሞልቶ መናገር ባይቻልም ከቀረበው ህግ እና ፍሬ ነገር አንፃር በዳኞች ያልተመረጠው የተለየው አማራጭ የተሻለ ውጤት ያስገኝ ነበር የሚያሰኝ ነገር ሊገኝበት ይችላል፡፡

ስለሆነም የተሻለ የትምህርት ዝግጅት፣ የሥራ ልምድ እና ክህሎት ባላቸው የበላይ ፍርድ ቤት ዳኞች ስህተት አለበት የተባለውን ፍርድ ማሳየት እና ማሳረም አስፈላጊ ይሆናል፡፡ የማይታረም ፍርድ ሊያስከትል የሚችለውን የፍትህ መጓደል ያስቀራል፡፡ በሙግቱ ተሸናፊ ነህ ሊባል የሚችለው ሰው በተሳሳተ ሚዛን፣ ምናልባትም በተንኮል ሊደርስበት ከሚችለው ፍርድ ይጠብቀዋል፡፡ ተከራካሪዎች ፈጣን በሆነ የፍርድ ሂደት ውስጥ እንዲያልፉ የማድረግ ፍላጎት ሊያስከፍል ከሚችለው ዋጋ አንፃር ሲታይ የይግባኝ ሥርዓትን በመፍጠር ሥህተትን ማረም ውጤታማና የበለጠ ጥቅማቸውን የሚያስጠብቅ ይሆናል፡፡ የተከሰሱ ሰዎች መሰረታዊ መብት (due process aspect) አካል ነው የሚባለውም ለዚህ ነው፡፡ ባይሆን ተወዳዳሪ የሆኑ ጥቅሞችን ለምሳሌ በአሁኑ ጉዳይ የተፋጠነ ፍትህ እና መሠረታዊ መብትን (due process) በማጣጣም ተፈላጊውን ውጤት ለማስገኘት የይግባኝ ስርዓቱን በተለያየ ዘዴ መምራት ይገባል፡፡

ሁሉም ቅሬታ ያለው ወገን በተካሄደው በእያንዳንዱ በክርክር ላይ በሚፈጠር ግድፈት ይግባኝ በመጠየቅ ሂደቱ ላይ ጫና እንዳይፈጥር እና ተፈላጊውን ሥልጠትና ውጤታማነት (efficiency and effectiveness) ለማግኘት ይግባኝ የሚባልበትን ጉዳይ ወሰን ማበጀት ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ ሊጓደል ከሚችለው መብት አንፃር እምብዛም ጉዳትን የማያስከትል ሲሆን ይግባኝ እንዳይባልበት በመከልከል፣ ጊዜያዊ በሆኑ ትዕዛዞች ወይም ብይኖች ይግባኝ

እንዳይባል በማድረግ፣ ጊዜው ካለፈ በኋላ በቂ ምክንያት ካልተገኘ በቀር ይግባኝ እንዳይቀርብ፣ በህግ እንጂ በፍሬ ነገር ላይ ይግባኝ እንዳይባል ወይም ከአንድ ደረጃ በላይ ይግባኝ እንዳይኖር በማድረግ በተፋጠነ ፍትህ እና በፍትሀዊነት፣ በውጤታማነት መካከል ያለውን ሚዛን መጠበቅ ሳይሻል አይቀርም፡፡ ይህን ሂደት አልፎ የሚቀርብ ይግባኝ ቢኖር የሚቀርቡትን ጉዳዮች ውጤታማ በሆነ መንገድ ማየት ይቻላል፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ተከራካሪዎች ተፈፀመብን የሚሉትን ሥህተት በማሳረም መብቶቻቸውን የሚያስጠብቁበት መሳሪያ ነው ማለት ይቻላል፡፡

## *ለ. <u>ቁጥጥር ማድረግ (Supervision)</u>*

ፍርድ ቤት አንድን ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ አስተናግዶ የሚሰጠው ፍርድ የመጨረሻ ሲሆን ስህተቶችን የማረም ዕድል አይኖርም፡፡ ዳኛው ሥህተት እንዳይሠራ የሚያተጋው ነገር ያጣል፡፡ የይግባኝ ሥርዓት መኖር ግን ፍርዱ እንዲመረመር ያደርጋል፡፡ ዳኛው ይመዘንበታል፤ ዕድገት ያገኝበታል፤ ወይ ይወቀስበታል፡፡ በዚህ የተነሳ የበላዩን ፍርድ ቤት መልካም ግምት ለማግኘት በተቻለ መጠን ሥህተቶች እንዳይኖሩ ለማድረግ ይጥራል፡፡ ይህ ጥረት በራሱ የተሻሻሉ ውሳኔዎች እንዲታዩ ምክንያት ይሆናል፡፡

የውሳኔዎቹ ጥራት ከፍ ማለትም ህብረተሰቡ በፍትህ ሥርዓቱ ላይ ያለውን መተማመን በማዳበር ይግባኝ የሚባልባቸውን ጉዳዮች ቁጥር የመቀነስ ኃይል ይኖረዋል፡፡ ስለሆነም ይግባኝ የተሰጠ ፍርድን መቆጣጠሪያ መንገድ በመሆን ዳኞችን የሚያተጋ፣ ለፍርዶች መሻሻልና ይግባኝ የሚባልበትን ጉዳይ በመቀነስ ረገድ አስተዋጽኦ የሚያደርግ የቁጥጥር ሥርዓት ነው ማለት ይቻላል፡፡

## 1.1 <u>የይግባኝ መብትና ወሰኑ</u>

"ክርክር በሚታይበት ፍርድ ቤት በተሰጠባቸው ትዕዛዝ ወይም ፍርድ ላይ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አላቸው" በማለት ህገ-መንግስቱ ስለተከሰሱ ሰዎች መብት በአንቀጽ 20(6) ላይ ይናገራል፡፡ ስለሆነም ይግባኝ የማለት መብት ህገ- መንግስታዊ ነው፡፡ ይህ ማለት ፍትህን፣ መሰረታዊ መብትን (due process) ትርጉም ባለው መንገድ ለመተግበር፣ ሥልጠት (efficiency) እና ውጤታማነትን (effectiveness) በማሳደግ የፍትህ ሥርዓቱ በህገ-መንግስቱ ላይ የታሰበውን ተግባር

እንዲወጣ ለማስቻል መብቱ ገደብ አይደረግበትም ማለት አይደለም፡፡ ይህ ገደብ

የሚቀመጠው በዝርዝር ህጐች ላይ ነው፡፡ ለምሳሌ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 184 በትዕዛዝ ላይ ይግባኝ ማለት እንደማይቻል ተደንግጓል፡፡ የአማርኛው ቅጂ "ጊዜያዊ አገልግሎት ያላቸው ትዕዛዛት"

በማለት ፋንታ "ትዕዛዝ" የሚል ቃል ብቻ በመያዙ ነገሩን ያሰፋው ቢመስልም ዞሮ ዞሮ

- በቀጠሮ መስጠት ወይም አለመስጠት፣
- በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 131 መሠረት በክስመቃወሚያዎች ላይ በሚሰጡ ብይኖች፣
- በክርክር ሂደት በሚቀርብ ማስረጃ ወይም በሚሰጥ የምስክርነት ቃል አቀባበልላይ በሚቀርቡ መቃወሚያዎች ላይ የሚሰጡ ብይኖች ይግባኝ አይባልባቸውም

በማለት በይዘቱ ጊዜያዊ አገልግሎት ያላቸውን ትዕዛዛት ለማለት ስለመፈለጉ መረዳት ይቻላል፡፡ እነኚህ ጉዳዮች ዋናው ክርክር እስኪጠናቀቅ ቆይተው በዋናው ፍርድ ላይ ይግባኝ ሲቀርብ ተጠቃለው ሊቀርቡና ሊታዩ የሚችሉ ናቸው፡፡ በነኚህ ብይኖች ምክንያት ተከራካሪዎች ጉዳት ሊደርስባቸው የሚችል ቢሆንም ይግባኝ በመፍቀድ ምክንያት በኢኮኖሚም ሆነ አጠቃላይ በፍትህ ሥርዓቱ

ውጤታማነት ላይ ሊያስከትል ከሚችለው ጫና አንፃር ሊፈቀድ እንደማይገባ ህጉ አቋም ይወስዳል፡፡

በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 185 ላይም ይግባኝ የሚባልባቸው

- በጥፋተኝነትና በቅጣት ውሳኔ፣
- በዕምነት በተሰጠ ፍርድ በቅጣቱ ላይ ብቻ፣
- ለጊዜው በመልቀቅ፣ ነፃ በመልቀቅ እና በቅጣቱ መጠን

ላይ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ስለሆነም ሁሉም ነገር ይግባኝ የሚቀርብበት አይደለም፡፡ ስለሆነም ይግባኝ

የሚቀርብበትንና የማይቀርብበትን ጉዳዮች ወሰን መለየት ጠቃሚ ይሆናል፡፡

## 1.1 <u>የይግባኝ መብት በፌዴራል እና በክልል ፍርድቤቶች</u>

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት መጽሐፍ በ1954 ዓ.ም የወጣ እንደመሆኑ ይግባኝ አቀራረብን በተመለከተ ከቁ 182-183 የተቀመጡት የድሮውን የፍርድ ቤቶች መዋቅርና አደረጃጀት የሚያሣዩ ናቸው በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ያለውን የፌዴራል

ሥርዓት ተከትሎ ፍ/ቤቶችም በፌዴራልና በክልሎች ተደራጅተዋል፡፡ በዚሁ መሠረት በፌዴራል ደረጃ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሲኖሩ በክልሎችም ወረዳ ፍ/ቤት፣ ዞን (ከፍተኛ) ፍ/ቤትና ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች አሉ፡፡

በአዋጅ ቁጥር 25/1988 /በተለያዩ አዋጆች እንደተሻሻለዉ/ መሠረት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተሰጠ ውሣኔ ላይ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይቀርባል፡፡ ውሣኔው በይግባኝ ከፀና ሁለተኛ ጊዜ ይግባኝ ማለት አይቻልም፡፡ ነገር ግን በውሣኔዎቹ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚል አቤቱታ ሲኖር ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ማመልከት እንደሚቻል ተደንግጓል በተመሳሳይ ሁኔታ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ታይቶ በተሰጠ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የሚቀርበው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ነው፡፡ (አንቀጽ 9 እና 13)፡፡

**መለማመጃ 1**

በክልልዎ የፍርድቤቶች አዋጅ ይግባኝን አስመልክቶ በተለይ የተደነገገ ነገር የለም ብለዉ ያስቡ፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድቤት ከወረዳ ፍርድቤት ዉሳኔ ላይ የተነሳዉን ቅሬታ በይግባኝ መርምሮ የወረዳዉን ፍርድቤት ዉሳኔ ሳይለዉጥ በማጽናት ስለወሰነ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 182/2/ መሠረት ከወረዳዉ ቀጥሎ ያለዉ የበላይ ፍርድቤት በይግባኝ ከሰጠዉ ዉሳኔ ይግባኝ ማለት ይቻላል የሚለዉን ተመርኩዞ ይግባኝ ለርስዎ ችሎት /የክልሉ ጠቅላይ ፍርድቤት/ ቀረበ፡፡

*በዚህ ላይ የሚሰጡትን ዉሳኔ ይጻፉት*

*እርስዎ ዐቃቤህጉ እንደሆኑ ያስቡ፡፡ ጠቅላይ ፍርድቤቱ ይግባኙን ያስቀርባል ብሎ ለክርክር ጠራዎት፡፡ በዚህ የፍርድቤቱ ትዕዛዝ ላይ የሚያቀርቡት ክርክር አለ? ይጻፉት*

## 1.1 **ስለትዕዛዝ ይግባኝና ተከሳሽ እንዲከላከል በሚሰጥ ብይን ላይ ይግባኝ ስለማለት**

ይግባኝ ማለት መሠረታዊ መብት ቢሆንም ክርክሩ በሂደት ላይ ባለበት ከፍርድ በፊት በሚሠጡ በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 184 በተዘረዘሩት ትእዛዞች ላይ ይግባኝ ማለት አይቻልም፡፡ ነገር ግን ጉዳዩ ሲወሰን ትእዛዞቹን ጭምር በመቃወም ይግባኝ ማለት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ይግባኝ ሊባል የሚችልባቸዉ ሁኔታዎች በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 185 ተደንግገዋል፡፡ እነሱም የጥፋተኛነት ዉሳኔ፣ የቅጣት ዉሳኔ በዛ ወይም አነሰ በሚል፣ ነጻ የመልቀቅ ወይም ለጊዜዉ የመልቀቅ ዉሳኔ ናቸዉ፡፡ ከነዚህ ሁለት ሁኔታዎች ዉጪ ያሉት ጉዳዮች ይግባኝ ይባልባቸዉ ወይም አይባልባቸዉ እንደሆነ በግልጽ የተደነገገ ነገር የለም፡፡

**መለማመጃ 2**

በፍርድቤቱ በቀረበዉ የወንጀል ክስ ላይ የዐቃቤህግ ማስረጃ ተሰምቶ ፍርድቤቱ ሲመረምረዉ ተከሳሹ ሊከላከል የሚገባዉ ሆኖ ስላገኘዉ ተከሳሹ መከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ አዘዘ፡፡ ተከሳሹ በነጻ ልሰናበት ይገባኛል ብሎ ስላመነ በዚህ ትዕዛዝ ቅር ተሰኝቶ ይግባኝ አቀረበ፡፡

*እርስዎ ይግባኝ ሰሚ ዳኛ ነዎት፡፡ በዚህ ይግባኝ ላይ ምን ይወስናሉ? ይጻፉት*

*ይግባኝ ሰሚዉ ፍርደቤት ይግባኙን ተቀብሎ መልስ ስጥበት ብሎ እርስዎን ዐቃቤህጉን አዘዘ፡፡ ምን ክርክር ያቀርባሉ? ይጻፉት*

## 1.1 <u>ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠ ፍርድና ይግባኝ</u>

ተከሳሽ በሌለበት ነገሩ ታይቶ ሲፈረድ ተከሳሹ ይህን ፍርድ ቀሪ እንዲደረግለት የሚጠይቅበት ሥነሥርዓት አለ፡፡ ይህም ተከሳሹ ነገሩ እርሱ ባለበት የመከላከያ ማስረጃዉን አቅርቦ የቀረበበትን ማስረጃ አግኝቶ መስቀለኛ ጥያቄ አቅርቦ እንዲፈረድ ከፈለገ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት የሚያቀርበዉ ጥያቄ በፍርድቤት ታይቶ ዉድቅ የማድረግ ዉሳኔ ከተሰጠ በዚህ ዉሳኔ ላይ ይግባኝ ማለት አይቻልም /የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 202/3//፡፡

**መለማመጃ 3**

በሌለበት ነገሩ ታይቶ የተፈረደበት ሰዉ ፍርዱ በተሰጠ ማግስት ፖሊስ መኖሪያዉ ድረስ በመሄድ ፍርዱን ለማስፈጸም እንደሚፈልገዉ ገልጾ ይዞት ወደማረሚያቤት ወሰደዉ፡፡ እርሱም በሚቀጥለዉ ቀን ፍርዱ ላይ ይግባኝ እንደሚል በመግለጽ ማመልከቻ ለፈረደዉ ፍርድቤት አቀረበ፡፡ አስከትሎም በዚሁ ቀን ፍርዱ ቀሪ እንዲደረግለት አመለከተ፡፡ ሆኖም ጥያቄዉ ላይ ፍርድቤቱ በቀረበ በሁለተኛዉ ቀን ዐቃቤህግን አስቀርቦ ከሰማ በኋላ ዉድቅ አደረገዉ፡፡

በዚህ ምክንያት ተከሳሹ ከፍርድቤቱ በደረሰዉ የፍርዱ ግልባጭ ላይ ተመስርቶ ዐቃቤህግ በሌለሁበት ያቀረበዉ ማስረጃ ሲመዘን ጥፋተኛ ሊያስብለኝ አይችልም ነበር ስለዚህ የጥፋተኛነት ዉሳኔዉ ይሻርልኝ፣ ይህ የማይሆን ከሆነ ቅጣቱ እኔ የመከላከል መብቴን ሳልሰራበት የተሰጠ ፍርድ እንደመሆኑ ሊቀልል ይገባ ነበር፡፡ ስለዚህ ቅጣቱ ቀልሎ ይወሰንልኝ በማለት ይግባኝ አቀረበ፡፡

*የይግባኝ ሰሚዉ ፍርድቤት ዳኛ እንደሆኑ ያስቡና በዚህ ይግባኝ ተገቢነት ላይ ይወስኑ፣ ይጻፉት*

**1.1 <u>በተከሳሽ ዕምነት መሰረት በተሰጠ የጥፋተኛነት ዉሳኔ ላይ ይግባኝ ስለማለትና የዕምነት ቃልን ስለማሻሻል</u>**

በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 185 ድንጋጌ አንድ ተከሳሽ በእምነት ቃሉ መሠረት የጥፋተኛነት ውሣኔ ከተሰጠበትና ከተቀጣ በቅጣቱ ላይ ካልሆነ በጥፋተኝነት ውሣኔው ላይ ይግባኝ ማለት አይፈቀድም፡፡

የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 134(1) ተከሳሹ በክሱ ማመልከቻ ላይ የተዘረዘረውን ወንጀል ለመሥራቱ በሙሉ ያመነ እንደሆነ ፍ/ቤቱ ተከሳሹ ጥፋተኛ ነኝ ብሏል በማለት እንደሚመዘግብ ያሣያል፡፡ የዚህ እንድምታ ደግሞ ለተከሳሽ ክሱን በዝርዝር እንዲያውቀው ማድረግ እንደሚገባ ነው፡፡ የኢፌዴሪ ሕገመንግስትም በአንቀጽ 20(2) ላይ ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር ለተከሳሽ እንዲነገረውና በጽሑፍም ሊያገኘው መብቱ መሆኑን ያስቀምጣል፡፡ በዚህ መልክ ክሱ ምን እንደሚል በሚገባ ሳይረዳ ተከሳሽ እምነት ክህደት ቢጠየቅና ጥፋተኛ ነኝ ቢል በሕጉ መሠረት ጥፋተኛነቱን አምኗል ለማለት በቂ ነው ማለት አይቻልም፡፡

አንድ ተከሳሽ ጥፋተኛ ነኝ ሲል ፍ/ቤት ጥፋተኛ ነኝ ያለበትን ምክንያት በዝርዝር ሊጠይቀው እና የክሱን ዝርዝር በሙሉ ማመኑን (ወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.134) ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ተከሰሹ በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 134 መሠረት ክሱን በሙሉ እንዳመነ ተቆጥሮ ሊፈረድበት አይገባም፡፡

**መለማመጃ 4**

አንድ በወንጀል የተከሰሰ ሰዉ የፍርድቤቱን የሥራ ቋንቋ ስለማያዉቅ በአስተርጓሚ እየተረዳ ዕምነት ክህደቱን ሲጠየቅ አጥፍቻለሁ በማለት ጸጸት ባዘለ ሁኔታ ለፍርድቤቱ ነገረ፡፡ ፍርድቤቱም ይህንኑ መሰረት አድርጎ ጥፋተኛ ነዉ በማለት ቅጣት ወሰነ፡፡ ሆኖም ተከሳሹ በዉሳኔዉ ላይ ቅሬታ አለኝ በማለት ይግባኝ አቀረበ፡፡ ይዘቱም ጥፋተኛ ተብዬ ሊፈረድብኝ አይገባም ነበር፣ ምክንያም አጥፍቻለሁ በማለት ለፍርድቤቱ የገለጽኩት በባህላችን እኔ የፈጸምኩት ተግባር ጸያፍ ስለሆነ ይህንኑ ለመግለጽ እንጂ አስተርጓሚዉ ለፍርድቤቱ መንገሩን ከፍርዱ እንደተረዳሁት ለወንጀሉ ተጠያቂ ነኝ ማለቴ አልነበረም፡፡ አለመግባባቱ ሊፈጠር የቻለዉ አስተርጓሚዉ የፍርድቤቱንና የእኔን ንግግር ለሌላችን በትክክል ተርጉሞ ባለማስተላለፉ ነዉ፡፡ ፍርዱ በሌላ አስተርጓሚ እየተተረጎመ በሰማሁበት ወቅት እኔ ያላልኳቸዉ ነገሮች እንዳልኳቸዉ ተደርገዉ በፍርዱ ዉስጥ ሲነገሩ ስሰማ በችሎት ተቃዉሜም በፍርድቤቱ ተግሳጽ ደርሶብኛል፣ ቅሬታ ካለኝም በይግባኝ ማቅረብ እንደምችል ተነግሮኛል፡፡ ስለዚህ የጥፋተኛነት ዉሳኔዉ ተሽሮ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል የሚለዉ ተመዝግቦ ማስረጃ ቀርቦ ነገሩ እንደገና ሊሰማ ይገባል የሚል ነዉ፡፡ ዐቃቤህግ በሰጠዉ መልስ በዕምነቱ መሰረት ጥፋተኛ የተባለ ሰዉ በጥፋተኛነቱ ላይ ይግባኝ እንዲል አይፈቀድም፣ ስለዚህ ይግባኙ ወድቅ ተደርጎ የበታች ፍርድቤት ዉሳኔ ይጽናልኝ በማለት ተከራከረ

*ዳኛዉ እርስዎ ቢሆኑ በዚህ የይግባኝ ቅሬታ ላይ ምን ይወስናሉ? ይጻፉት*

## 1.1 <u>በቅጣት ዉሳኔ ላይ ይግባኝ ስለማለት</u>

በቅጣት አወሳሰን ጊዜ ዐቃቤህግ ከፍ ያለ ኃላፊነት አለበት፡፡ ስለቅጣቱ አወሳሰን ዋናዉን ክርክር የሚያቀርበዉ እርሱ ነዉ፡፡ ቅጣት ሊከብድ የሚገባዉ ከሆነ ምክንያቱን የሚያቀርበዉ ዐቃቤህግ ነዉ፡፡ ሊቀልል የሚገባዉ ከሆኑም እንዲሁ፡፡ ስለዚህ ቅጣት አላግባብ ቢከብድም ሆነ ቢቀልል ዉሳኔዉ የዐቃቤህግን ክርክር ያልተከተለ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ዐቃቤህግ በንዲህ አይነት ዉሳኔዎች ላይ ቅሬታ ይኖረዋል ማለት ነዉ፡፡ ዋናዉ የህግ አስፈጻሚ የሥራ ክፍል እንደመሆኑ ስለቅጣት አወሳሰን የተደነገጉ ህግጋትም እንዲሁ በአግባቡ ተፈጻሚ መሆናቸዉን ማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 185 እንደተደነገገዉ ቅጣት አነሰ ብሎ ዐቃቤህግ፣ ቅጣት በዛ ብሎ ተከሳሽ ይግባኝ ሊሉ ይችላሉ፡፡

**መለማመጃ 5**

በክልልዎ ባለ አንድ ፍርድቤት በደንብ መተላለፍ ነገር የተከሰሰ ሰዉ ጥፋተኛ ተብሎ ተፈረደበት። በቅጣት አስተያየት ጊዜ ዐቃቤህግ ተመጣጣኝ ቅጣት እንዲወሰን አመለከተ፣ ተከሳሹ በበኩሉ ቅጣቱ ይቅለልልኝ ብሎ ተከራከረ። ፍርድቤቱም ተከሳሹ በአንድ አመት ተኩል እስራት እንዲቀጣ ፈረደበት። ተከሳሹ በዚህ አካባቢ ቀደም ሲል የነበረዉን የፍርድቤት አሰራር ልማድ ስለሚያዉቅ ይግባኝ አልልም አለ። ምክንያቱ ደግሞ ቀደም ባለ ጊዜ የነበሩ ዳኞች በዚህ አይነት ጉዳይ እስከአምስት ዓመት ድረስ ይፈርዱ እንደነበር ስለሚያዉቅ ይግባኝ ቢል ቅጣቱ አንሷል ተብሎ እንዳይጨመርበት ስጋት አለዉ። ስለዚህ በደንብ መተላለፍ ከሦስት ወር በላይ እንደማይወሰን በህግ የተደነገገ መሆኑ ተነግሮት ይግባኝ እንዲል ቢመከርም ተከሳሹ ፈቃደኛ ሊሆን አልቻለም።

*እርስዎ ዐቃቤህጉ ነዎት እንበል። በዚህ የቅጣት ዉሳኔ ላይ ይግባኝ ይላሉ? ይጻፉት*

*እርስዎ በዚህ አካባቢ ባለ የይግባኝ ሰሚ ፍርድቤት ዳኛ ነዎት። ዐቃቤህግ ከላይ የተመለከተዉን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ይዞ ቀረበ። እንዴት ያስተናግዱታል? ይጻፉት*

## 1.2 ስለይግባኝ ጊዜና ጊዜዉ ስላለፈ ይግባኝ

በተሰጠው ፍርድ ቅር ያለው ወገን ፍርዱ በተሰጠ በአስራ አምስት ቀን ውስጥ ይግባኝ ለማቅረብ የሚፈልግ መሆኑን በመግለጽ ፍርዱን ለሰጠው ፍርድ ቤት የይግባኝ ማስታወቂያ አቤቱታ ማቅረብ አለበት። ይህ ማስታወቂያ የደረሰው ሬጂስትራርም ይግባኝ የተባለበትን ፍርድ አስገልብጦ ለይግባኝ ባዩ፣ ለጠበቃው፣ ተከሳሹ በማረሚያ ቤት የሚገኝ እንደሆነም የፍርድ ቤቱ መዝገብ ሹም ለይግባኝ ባይ እንዲሰጥለት ለወህኒ ቤቱ ሹም ይልካል። ይግባኝ ባይም የፍርዱ ግልባጭ በደረሰው በሰላሳ ቀን ውስጥ ቅሬታውን አዘጋጅቶ ፍርዱን ለሰጠዉ ፍርድ ቤት መዝገብ ሹም ማቅረብ አለበት።

በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 187 ላይ እንደተመለከተው ይግባኝ የሚጠየቀው ፍርድ በተሠጠ በ15 ቀናት ውስጥ ነው። አብዛኛውን ጊዜ የሚፈረድባቸው ተከሳሾች ማረሚያ ቤት ስለሚገቡ በሕጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ይግባኝ መጠየቅ ያለመጠየቃቸውን ማረጋገጥ የሚያስቸግርበትና ጊዜው አልፏል እየተባለ የይግባኝ ማስፈቀጃ ማመልከቻ ለማቅረብ የሚገደዱበት ሁኔታ አለ። ችግሩ በሁለት ምክንያቶች ሊከሰት ይቻላል።

1. ተቀጪው እንደተፈረደበት ይግባኝ ማለቱን ለማስታወቅ በ15 ቀን ውስጥ ማመልከቻውን ጽፎ ሊሆን ይችላል፡፡ እስረኛ በመሆኑ ራሱ ፍርድ ቤት ሊወስደው ስለማይችል የሚሰጠው ለማረሚያ ቤቱ ነው፡፡ ማረሚያ ቤቱ በተለያዩ ምክንያቶች በ15 ቀናት ውስጥ ማመልከቻውን ለፍ/ቤት ሣያስተላለፍ የሚቆይበት አጋጣሚዎች አሉ፡፡
2. የይግባኝ መጠየቂያ ማመልከቻው ፍርዱ በተሰጠ 15 ቀን ውስጥም የተፃፈ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል፡፡ ነገር ግን ለፍ/ቤት ከረጂም ጊዜ በኋላ ይላክና ማረሚያ ቤቱ ማረጋገጫ እንዲሠጥ ሲጠየቅ ታራሚው መቼ ማመልከቻውን እንደሰጠው ማረጋገጥ የማይቻልበት ሁኔታ ይከሰታል፡፡

የመጀመሪያውን በተመለከተ ጥፋቱ የታራሚው ባለመሆኑ ይግባኙን ለመቀበል ብዙ ላያስቸግር ይችላል፡፡ በሁለተኛው ሁኔታ ግን ታራሚው ይግባኝ መጠየቂያ ማመልከቻውን ፍርድ በተሰጠ በ15 ቀን ውስጥ እንደፃፈ በማድረግ ጊዜው ካለፈ በኋላ ለማረሚያ ቤቱ ሊያቀርብ የሚችልበት ሁኔታ ስለሚኖር ፍ/ቤቱ ተጨማሪ ማጣራቶችን ማድረግ ሊያስፈልገው ይችላል፡፡

ይግባኙ በጊዜው መጠየቁ ከተረጋገጠ ሌላው ሊታይ የሚገባው ፍርዱን የሠጠው ፍርድ ቤት የፍርዱን ግልባጭ ለታራሚው በማረሚያ ቤት በኩል የሚያደርስበት ጊዜ እና ታራሚዉ የይግባኝ ማመልከቻዉን ለፍርድቤት በማረሚያቤቱ አስተደደር በኩል የሚያደርስበት ጊዜ ነው፡፡ ታራሚው (ይግባኝ ባይ) የፍርድ ግልባጭ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ የይግባኝ ማመልከቻውን ፍርድ ለሠጠው ፍ/ቤት ማቅረብ ይኖርበታል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 187/2/)፡፡

በዚህ ረገድም ችግሮች ይታያሉ፡፡ ታራሚው የፍርድ ግልባጭ የሚደርሰው በማረሚያ ቤት በኩል እንደመሆኑ መጠን የፍርድ ግልባጩ ደረሰው የሚባለው የመዝገብ ሹሙ (ሬጅስትራሩ) ግልባጩን ለማረሚያ ቤቱ የላከበት ቀን ነው ወይንስ ማረሚያ ቤቱ ለአመልካቹ አስፈርሞ የሚሠጥበት ቀን ነው የሚለው በተግባር ቀላል ሆኖ አይታይም፡፡ ሕጉ የፍርድ ግልባጭ ለማረሚያ ቤቱ የደረሰበትን ቀን እንደ መነሻ የወሰደ ይመስላል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 187(1))፡፡ ይህም ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ ታራሚው የሚገኝበት ማረሚያ ቤት የፍርድ ግልባጩ እንደደረሰው በእለቱ ለአመልካች ይሠጣል በሚል እሳቤ ነው፡፡ አንዳንዴ ግን እውነታው ከዚህ የተለየ ነው፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች የፍርድ

ግልባጭ ለማረሚያ ቤቱ ጽ/ቤት ደርሦም በእለቱ ለታራሚው ሳይሰጥ ሊቆይ ይችላል በዚህ የተነሳም ታራሚው የይግባኝ ማመልከቻውን ፍርድ በደረሰው 30 ቀናት ውስጥ (ለማረሚያ ቤት ከደረሰበት ቀን ጀምሮ እየተቆጠረ ማለት ነው) አላቀረበም የሚባልበት ሁኔታ ካለ ለመዘግየቱ ተጠያቂው ማን መሆኑ ሊጣራ የሚገባው ከመሆኑም በላይ የፍርድ ግልባጭ ለታራሚው ደረሰ ሊባል የሚገባው ለራሱ የደረሰበት እንጂ ለማረሚያ ቤቱ የተላከበት ቀን ሊሆን አይገባውም፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የፍርድ ግልባጭ ለማረሚያ ቤት በደረሰበት ቀን ለታራሚውም ደርሦ ታራሚው የይግባኝ ማመልከቻውን ሠላሣ ቀን ከመሙላቱ በፊት ጽፎ ለማረሚያ ቤቱ ቢያስረክብም ለፍ/ቤት ዘግይቶ የሚደርስበት አጋጣሚም አለ፡፡ በታራሚው በኩል ለመዘግየቱ አስተዋጽኦ እስከሌለ ድረስ ይግባኙ ሊታይ የሚገባው ነው /የሰበር መዝ ቁ 39722፣ ቅጽ 9፣ ገጽ 7/፡፡

> **መለማመጃ 6**
>
> ይግባኝ ባይ የይግባኝ ማመልከቻዉ ለይግባኝ ሰሚዉ ፍርድቤት እንደደረሰ ከማረሚያ ቤት ሆኖ ይግባኙ ታይቶ እስኪወሰን ድረስ ፍርዱ እንዲታገድለት፣ ለዚህም ዋስትና መስጠት ወይም መጥራት እንደሚችል፣ ክሱ በተሰማበት ጊዜ በዋስ ሆኖ ግዴታዉን እያከበረ ይቀርብ እንደነበር፣ ወዘተ. በመዘርዘር አመለከተ፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድቤት ዐቃቤህግን መልስ እንዲሰጥ አዘዘ፡፡
>
> *ዐቃቤህጉ እርስዎ ቢሆኑ ምን ይከራከራሉ?*
>
> *እርስዎ ዳኛዉ እንደሆኑ ያስቡ፡፡ ባልደረባዎን እንደዐቃቤህግ መልስ እንዲሰጥ ካደረጉ በኋላ በጉዳዩ ላይ ዉሳኔ ይስጡ፣ ይጻፉት*

## 1.3 የይግባኝ ክርክር ሂደትና የይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ዉሳኔ

የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 192 የይግባኝ ክርክር ስለሚሰማበት ሁኔታ የሚደነግግ ነው የይግባኝ ክርክር በችሎት የሚሰማ እንደመሆኑ በቃል የሚደረግ ነው፡ የግራ ቀኙም ክርክር በአንድ ቀጠሮ የሚጠናቀቅ ነው ይህን ሕግ ተግባራዊ በማድረግ ረገድ በሕግ ባለሙያ በማይታገዙ ግለሰቦች በኩል ችግር አለ፡፡ በቃል ክርክራችንን ማሰማት አንችልም እያሉ በጽሑፍ መልሳቸውን ያቀርባሉ በግድ በቃል ክርክራችሁን አሰሙ

ማለት መብታቸውን ማጣበብ ይሆናል በሚል መልሳቸውን በጽሑፍ መቀበል የማይታለፍ ይሆናል፡፡ የሌላውን ወገን የመልስ መልስ መስማት አስፈላጊ በሚሆን ጊዜ ቀጠሮ ለመለወጥ ምክንያት ይሆናል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው በሕግ ተለይተው ከተገለፁ ወንጀሎች ውጭ አንድ ተከሳሽ ጉዳዩ በሌለበት አይታይም በይግባኝ ደረጃ ግን ወንጀሉ ምንም ቢሆን መልስ ሰጭ ካልቀረበ ይግባኙ በሌለበት መሰማቱ ይቀጥላል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.193/2/)፡፡ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በዋናነት የሚመረምረው በሥር ፍ/ቤት የቀረቡትን ማስረጃዎች ነው ነገር ግን ተጨማሪ ማስረጃ መስማት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ምክንያቱን ጽፎ ማስረጃውን መቀበል እንደሚችል የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 194 ያሣያል፡፡ ተከራካሪ ወገኖች ይህንን ለፍ/ቤቱ የተሠጠን ሥልጣን ለመጠቀም በመፈለግ በሥር ፍ/ቤት ሊያቀርቡ ሲችሉ ያለፉት ማስረጃ እንዲቀርብላቸው የሚጠይቁበት ጊዜ ስላለ ፍ/ቤቱ ማስረጃውን ከመቀበሉ በፊት የማስረጃውን ወሳኝ መሆን በጥንቃቄ ማገናዘብ ይገባዋል፡፡

**መለማመጃ 7**

የስር ፍርድቤት በከባድ ነፍስ ግድያ ክስ ተከሳሹን በነጻ በማሰናበት በሰጠዉ ፍርድ ላይ ዐቃቤህግ ይግባኝ አቅርቧል፡፡ ባቀረበዉ ይግባኝ በስር ፍርድቤት ያላግባብ ሳይሰሙ የቀሩ ማስረጃዎች አሉኝ፣ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድቤት እነዚህን ማስረጃዎች ሰምቶ ፍርዱን ለዉጦ መልስ ሰጪዉን ጥፋተኛ ብሎ ይፍረድልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ፍርድቤቱም መልስ ሰጪዉን እንዲቀርብ መጥሪያና የይግባኝ ማመልከቻዉን ቅጂ ልኮለታል፡፡ በቀጠሮዉ ቀን መልስ ሰጪዉ ሳይቀርብ ይቀራል፡፡ ምክንያቱም ፖሊስ ሊያገኘዉ አልቻለም፡፡ በዚህ ጊዜ ፍርድቤቱ ዐቃቤህግን ምን እንደሚያመለክት ይጠይቀዋል፡፡

*ዐቃቤህጉ እርስዎ ቢሆኑ ምን ያመለክታሉ?*

*ዳኛዉ እርስዎ ነዎት እንበል፡፡ ባልደረባዎን እንደዐቃቤህግ የሚያመለክተዉን ሰምተዉ ይወስኑ፣ ይጻፉት*

የይግባኝ ክርክር ከተጠናቀቀ በኋላ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሥር ፍ/ቤት የተሰጠን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሠረዝ፣ የጥፋተኝነት ውሣኔ በማጽናት ቅጣት መቀነስ፣ ወይም በሥር ፍ/ቤት በነፃ የተለቀቀን ተከሳሽ ጥፋተኛ በማድረግ መቅጣት ይችላል፡፡ ወይንም ደግሞ ጉዳዩ ወደ ሥር ፍ/ቤት ተመልሶ እንደገና እንዲታይ ማዘዝ ይችላል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 195)፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቅጣት መቀነስ ወይም መጨመር

የሚችል ቢሆንም ቅጣት በዛብኝ ብሎ ይግባኝ በጠየቀ ይግባኝ ባይ ላይ ቅጣት መጨመር ባልተጠየቀ ዳኝነት መፍረድ ስለሚሆን ተገቢ አይደለም፡፡

## 2 ምዕራፍ ሁለት

## ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠን ፍርድ ቀሪ ስለማድረግ

### 2.1 ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠን ፍርድ ቀሪ የማስደረግ ማመልከቻ አቀራረብና አወሳሰን

በሌለበት ጉዳዩ ታይቶ የተፈረደበት ሰው ፍርዱ መሰጠቱን ባወቀ በ30 ቀናት ዉስጥ ፍርዱ ውድቅ እንዲደረግለት ማመልከት ይችላል፡፡ ይህንንም ማመልከት የሚችለዉ ፍርዱን ለሰጠው ፍ/ቤት ነዉ (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 164,197,198)፡፡ ማመልከቻዉ ሲቀርብ ፍርዱ ቀሪ ሊሆን የሚገባበትን ምክንያት መዘርዝር አለበት፡፡

ፍርድቤቱ በዚህ ማመልከቻ ላይ ዉሳኔ ከመስጠቱ በፊት ማመልከቻዉ ለዐቃቤህግ ደርሶ ነገሩን ለመስማ በተያዘዉ ቀጠሮ ዕለት ግራ ቀኙን መስማት አለበት፡፡ በዚህ ዕለት አመልካቹ /ተከሳሽ/ ካልቀረበ ማመልከቻዉ ዉድቅ ይሆናል፡፡ እንዲሁም አመልካቹ ቀርቦም ቢሆን አቤቱታዉን በዉል ካላስረዳ ዉድቅ ይደረግበታል፡፡

### 2.2 ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠን ፍርድ ቀሪ ለማድረግ ተቀባይነት ያላቸዉ ምክንያቶች

ከላይ እንደተመለከተዉ አመልካቹ አቤቱታዉን ካላስረዳ ይህ አቤቱታዉ ዉድቅ ይደረጋል፡፡ ፍርድቤቱ አቤቱታዉን እንዲቀበለዉ ከአመልካቹ ምን እንዲያስረዳ ይጠበቃል? ማመልከቻው ተቀባይነት የሚያገኘው ተከሳሹ ፍ/ቤት ያልቀረበው መጥሪያው ስላልደረሰው ወይም መጥሪያ ቢደርሰዉም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የቀረ መሆኑን ማስረዳት ከቻለ ብቻ ነው፡፡ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ምንድነው የሚለውን የመወሰን ኃላፊነት የፍርድ ቤቱ ነው፡፡

**መለማመጃ 8**

ከዚህ ቀደም በሌለበት ነገሩ እንዲሰማ የወሰኑበትና በሌለበት ነገሩን ሰምተዉ አስራአምስት ዓመት ጽኑ እስራት የፈረዱበት ሰዉ ፍርዱ ቀሪ ሆኖ ክሱ ባለበት እንዲሰማ አመለከተ፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ክሱ መቅረቡን እንደማያዉቅ፣ እንዲቀርብ መጥሪያ ያልተሰጠዉ መሆኑን፣ ፖሊስ አግኝቶት እንደማያዉቅ፣ እንዲሁም በጋዜጣ ስለመጠራቱ ሲጠየቅ ይህንንም እንደማያዉቅ ምክንያቱም በኑሮዉ የተቸገረ ሰዉ በመሆኑ የቀንስራ እየፈለገ በመስራት የሚተዳደር ሰዉ ስለሆነ ጋዜጣ አግኝቶ አንብቦ ስለማያዉቅ መሆኑን፣ በድህነቱ ምክንያት የመገናኛ ብዙሃንን የሚከታተልበት አቅም እንደሌለዉ በመግለጽ ተከራከረ፡፡ መዝገቡን ሲመረምሩ መጀመሪያ ተከሳሽ በተጠራ ጊዜ ፖሊስ ሊያገኘዉ ባለመቻሉ በዐቃቤህግ ጥያቄ መሰረት በጋዜጣ ተጠርቶ ባለመቅረቡ ነገሩ በሌለበት እንዲሰማ የተወሰነ መሆኑን አረጋገጡ፡፡ ሆኖም ክስ የቀረበበት ወንጀል በህጉ ዉስጥ እጅግ ከባድ ከተባሉት ዉስጥ አንዱ በመሆኑ ክሱ ስለመቅረቡ በአንዳንድ ዜና ማሰራጫዎች ክሱ በቀረበበት ዕለት ተነግሯል፡፡

*ይህን ክርክር አስመልክቶ ባልደረባዎን በዐቃቤህግነት ሃሳብ እንዲያቀርቡ ካደረጉ በኋላ አቤቱታዉን ይቀበሉት ወይም አይቀበሉት እንደሆን ዉሳኔ ይስጡ፣ ይጻፉት*

በሌላ በኩል ተከሳሹ በማመልከቻዉ የገለጸዉ ምክንያት የሚከተለዉ ነዉ፡፡ *‹‹ከፍርድቤቱ የተላከዉን መጥሪያ በተቀበልኩ በሳምንቱ በሰፈር በተነሳ ጸብ ምክንያት ብዙ ሰዎች በህይወትና በአካል ስለተጎዱ በአካባቢዉ ከተገኙ ሰዎች ጋር አብሬ ተይዤ ምርመራ ሲደረግ ቆይቶ ክስ ቀርቦ በመታየት ላይ ሲሆን ዋስ ተከልክዬ እስካሁን በእስር ሆኜ እየተከራከርኩ ነኝ፡፡ ለፖሊስ ክፍሉና ለማረሚያ ቤት ነገሩን ባስረዳም ወደፍርድቤት የሚያቀርበኝ አላገኘሁም፡፡ በዚህ ምክንያት ሳልቀርብ የቀረሁ ስለሆነና ይህም ከኔ አቅም በላይ ስለሆነ በሌለሁበት የተሰጠዉ ፍርድ ተነስቶ እንደገና ይሰማልኝ››*

*በዚህ ጉዳይ ፍርድቤቱ አቤቱታዉን የላከልዎ ዐቃቤህግ እንደሆኑ ያስቡ፡፡ ምን ክርክር ያቀርባሉ?*

*ዳኛዉ እርስዎ እንደሆኑ በማሰብ ባልደረባዎን በዚህ አቤቱታ ላይ እንደዐቃቤህግ ሃሳብ እንዲያቀርቡ አድርገዉ በዚሁ መሰረት ዉሳኔ ይስጡ፡፡ ይጻፉት*

## 2.3 ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠ ፍርድ ቀሪ እንዲሆን በሚቀርብ ጥያቄ ላይ የሚሰጠዉ ዉሳኔ የሚያስከትለዉ ዉጤት

አቤቱታዉን ፍርድቤቱ ሊቀበለዉ ወይም ዉድቅ ሊያደርገዉ ይችላል፡፡ እንደፍርድቤቱ ዉሳኔ የሚያስከትለዉ ዉጤት የተለያየ ነዉ፡፡ አቤቱታዉ ተቀባይነት ካገኘ ፍርድቤቱ ነገሩን ለመስማት ሥልጣን ባለዉ ሌላ ፍርድቤት ክሱ እንዲታይ ያዝዛል፡፡ ዐቃቤህግም ክሱን ለዚህ ፍርድቤት ያቀርባል፡፡

አቤቱታዉ ዉድቅ ከተደረገ ግን ስለፍርዱ እና ስለአፈጻጸሙ ተገቢዉን ተጨማሪ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡ ይህ የፍርድቤቱ አቤቱታዉን ዉድቅ የማድረግ ዉሳኔ ይግባኝ አይባልበትም፣ ተከሳሹ ከፈቀደ ግን በአስራ አምስ ቀናት ዉስጥ ቅጣቱን አስመልክቶ ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡

**መለማመጃ 9**

**ቀደም ባለዉ መለማመጃ የተጠቀሰዉ አመልካች ያቀረበዉን አቤቱታ በሚገባ ስላስረዳ መማልከቻዉን ተቀብለዉታል ብለን እናስብ፡፡**

*ከዚህ በኋላ ለጉዳዩ የሚያስፈልጉ ትዕዛዞችን ይስጡ፣ ዐቃቤህግ ምን ሊያደርግ እንደሚገባዉ ለይተዉ ይወስኑ፣ ክስ በሌላ ፍርድቤት የሚቀርበዉ እንደአዲስ ነዉ ወይስ የቀድሞዉን ክስ መዝገብ ወደሌላ ፍርድቤት በማቅረብ ነዉ?*

**በሌላ በኩል ማመልከቻዉን ስላልተቀበሉ ዉድቅ አድርገዉታል፡፡**

*በተመሳሳይ ሁኔታ ትዕዛዝ ይስጡ*

**በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 202/3/ እንደተደነገገዉ ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠዉን ፍርድ ቀሪ ለማስደረግ የሚቀርበዉን ማመልከቻ**

> ***‹‹…ፍርድቤቱ ሳይቀበል ቀርቶ ዉድቅ እንዲሆን በመወሰኑ*** *ይግባኝ ማለት አይቻልም፡፡ ነገር ግን* ስለተፈረደበት ቅጣት ብቻ ማመልከቻዉ ዉድቅ እንዲሆን ከተወሰነበት ቀን እንስቶ በአስራአምስት ቀን ጊዜ ዉስጥ ይግባኝ ቢል አይከለከልም፡፡››

# 3 ምዕራፍ ሦስት

## ስለቅጣት አፈጻጸም

## 3.1 ቅጣት ከመፈጸሙ በፊት ስለሚገደብበትና ስለሚታገድበት ሁኔታ

### 3.1.1 አወሳሰናቸዉ የሚገደቡ ቅጣቶች

አንድ አጥፊ ጥፋተኛ የተባለበት ወንጀል በመቀጮ፣ በግዴታ ሥራ ወይም ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት የሚያስቀጣ ሲሆን ወንጀለኛው ለወደፊቱ ፀባዩን ለማረም የሚችል መሆኑ ሲታመንበት የጥፋተኝነት ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ የፈተና ጊዜ በመስጠት ቅጣት ሣይወሰን ማቆየት ይቻላል (የወ/ህ/ቁ/ 191)፡፡ ወንጀለኛው በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ፀባዩ መልካም ሆኖ ከተገኘ ፍርዱ እንዳልተሰጠ ይቆጠራል፡፡

ስለዚህ እንዲህ አይነት ቅጣት በሚያስከትሉ ወንጀሎች የተከሰሱ ሰዎች ጉዳይ ላይ ፍርድቤቱ ተገቢ ሁኔታዎች መኖራቸዉን ካመነ አስቀድሞ እንደማንኛዉም ጉዳይ ጥፋተኛነትን ይወስናል፡፡ በማስከተልም ለዚህ ጥፋት የሚገባዉን ቅጣት ከመወሰኑ በፊት የተከሳሹን ዓመል መሻሻል በፈተና ለማየት እስከተወሰነ ጊዜ ቅጣቱን ሳይወስን ለማቆየት ይችላል፡፡

### 3.1.2 አፈጻጸማቸዉ የሚገደቡ ቅጣቶች

ቅጣት ከተወሰነ በኋላ እንዳይፈጸም ለፈተና በሚሰጥ ጊዜ ተገድቦ ሊቆይ ይችላል /የወ/ህ/ቁ/ 192 እና ተከታዮቹ/፡፡ ሆኖም በመርህ ደረጃ ቅጣት እንዳይፈጸም መገደብ የሚቻል ቢሆንም ለዚህ ጉዳይ በወ/ሕ/ቁ 194 ላይ ከተደነገገው በተጨማሪ አንዳንድ ሁኔታዎች በቅድሚያ ሊሟሉ ይገባል፡፡ የወንጀለኛው የቀድሞ ታሪኩና ፀባዩ (የወ/ህ/ቁ 196) ሲታይ ገደቡ ጥሩ ውጤት የሚያስገኝ መሆኑ ሲገመት፣ በጥፋቱ ያደረሰውን ጉዳት እንደሚክስ ዋስትና (ማረጋገጫ) ሲሰጥ (የወ/ህ/ቁ 197)፣ ከዚህም ሌላ በገደብ እንዲቆይ ሲወሰን ፍ/ቤቱ ስለተከሳሹ የፀባይ አመራር ደንብ በዝርዝር ሲያስቀምጥና ጥፋተኛው ላይም የጠባቂነት ሥልጣን በተሠጠው አካል ቁጥጥር እንዲደረግበት ሲያዝዝ የቅጣቱ አፈጻጸም በገደብ እንዲቆይ ሊደረግ ይችላል፡፡

በሌለ በኩል በሕግ የተጠቀሱት በገደብ የተለቀቀን ተከሳሽ የሚቆጣጠሩ አካላት ባለመኖራቸው አንድ ሰዉ ለተወሰነ ጊዜ በገደብ መለቀቁን በፍርድ ላይ ከማስፈር ውጭ በሕጉ በዝርዝር በተመለከተው አኳኋን ሲተገበር አይታይም፡፡

***መለማመጃ* 10**

በከባድ ወንጀል የተከሰሰ ሰዉ ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣቱን በተመለከተ ቀልሎ እንዲወሰንለትና የሚወሰነዉም ቅጣት በገደብ እንዲታገድለት አመለከተ፡፡ ፍርድቤቱም ለጥፋቱ ይመጥናል በማለት የማቅለያ ምክንያቶች በመኖራቸዉ ምክንያት ቅጣቱን አቅልሎ በሦስት ዓመት ተኩል ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወሰነ፡፡

*የችሎቱ ዐቃቤህግ እንደሆኑ በማሰብ በዚህ ተከሳሽ የገደብ ጥያቄ ላይ የሚያቀርቡትን ክርክር በጽሁፍ ይግለጹ*

*ዳኛዉ እርስዎ እንደሆኑ ያስቡ፡፡ ዐቃቤህግ ቅጣቱ ሊገደብ አይገባም፣ ከሦስት ዓመት በላይ በሆነ ነጻነትን በሚያሳጣ ቅጣት የተቀጣ በመሆኑ ቅጣቱን ሊፈጽም ይገባል በማለት ያቀረበዉን ክርክር በመያዝ በነገሩ ላይ ተገቢ ነዉ የሚሉትን ዉሳኔ ይስጡ፣ ይጻፉት*

በገደብ የሚታገዱ ቅጣቶች ለገደቡ የተጣሉትን ሁኔታዎችና ግዴታዎች ተቀጪዉ በሚገባ በማሟላት ፈተናዉን ካለፈ ቅጣቱ አይወሰንበትም፣ የተወሰነ ቅጣት ከሆነም አይፈጸምበትም፡፡

## 3.1.3 <u>አፈጻጸማቸዉ ለሌላ ጊዜ የሚተላለፍ /የሚታገድ/ ቅጣቶች</u>

ቅጣትን በገደብ ከማቆየት በተጨማሪ ቅጣት ሳይፈጸም የሚቆይባቸዉ አጋጣሚዎች በህግ ታዉቀዉ ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ የኋለኛዎቹ እንደገደብ የቅጣቱን መቅረት አያስከትሉም፡፡ ቅጣቱ የሚፈጸምበትን ጊዜ ለወደፊት ከማስተላለፍ የዘለለ ዉጤት አይኖራቸዉም፡፡ የሞት ቅጣት የተፈረደባቸዉ ሰዎች ቅጣቱ በርዕሰብሄሩ ከጸደቀ በኋላ በጽኑ ህመም ቢያዙ፣ ወይም ሴት ከሆነች ነፍሰጡር መሆኗ ከታወቀ ቅጣቱ ሳይፈጸም ይቆያል፡፡ ይህም የሚሆነዉ እነዚህ ምክንያቶች እስኪወገዱ ድረስ ነዉ፡፡ ምክንያቶቹ ሲወገዱ ቅጣቱ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**መለማመጃ 11**

ከባድ የነፍስ ግድያ የፈጸመች አንድ ሴት የሞት ፍርድ ተፈርዶባት ቅጣቱ በርዕሰብሄሩ/መስተዳድሩ ጸደቀ፡፡ በዚህ መሰረት ቅጣቱ ሊፈጸም በተቃረበበት ጊዜ የአምስት ወር ጽንስ እንዳላት ተረጋገጠ፡፡ በዚህ ምክንያት ከአንድ ሳምንት በኋላ ሊፈጸም ታስቦ የነበረዉ የሞት ቅጣት አፈጻጸም ሳይፈጸም ቀረ፡፡ ከአራት ወራት በኋላ ተቀጪዋ በሰላም ተገላገለች፡፡ ስለዚህ የሞት ቅጣቱን አፈጻጸም እንዲታገድ ያደረገዉ ምክንያት የተወገደ ስለሆነ ማረሚያቤቱ ቅጣቱን ለማስፈጸም አሰበ፡፡ ሆኖም ከዚያ በፊት የማረሚያቤቱ አስተዳደር ብልህነትን የተላበሰ ሥራ ለመስራት በመፈለጉ ይህን መፈጸም ይችል እንደሁ ምክር ፈለገ፡፡

*ይህን ምክር እንዲሰጡ ነገሩ የተመራልዎ ዐቃቤህግ እንደሆኑ ያስቡ፡፡ ስለሞት ቅጣቱ አፈጻጸም ለማረሚያቤቱ የሚሰጡትን ምክር በጽሁፍ ያስፍሩ፡፡*

በኢትዮጵያ ህግ ታዉቀዉ ነገር ግን በፍርድቤቶች የአሰራር ልማድ ችላ ተብለዉ የሚገኙ የቅጣት አፈጻጸም መመሪያዎች መኖራቸዉ የሚካድ አይደለም፡፡ ከነዚህ ዉስጥ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 206 የተደነገገዉ ትልቅ ምሳሌ ነዉ፡፡ እንደዚህ ድንጋጌ አነጋገር

እንዲያዝ ወይም ከአንድ ዓመት ባልበለጠ ጊዜ በእስራት እንዲቀጣ የተፈረደበት ሰዉ፤

ሀ. ነፍስጡር የሆነች እንደሆነ፤ ወይም

ለ. የቤተሰቡ ደጋፊ ሰዉየዉ ብቻ የሆነ እንደሆነና ይኸዉም ሰዉ ለህዝብ ጸጥታ አስጊ ያልሆነ እንደሆነ ፍርድቤቱ ለመልካም ጠባዩ ዋስ አስጠርቶ ከስድስት ወር ሳልበለጠ ጊዜ ቅጣቱ ከመፈጸሙ እንዲቆይ ሊያስተላልፍለት ይችላል፡፡

**መለማመጃ 12**

አንዲት በከባድ ወንጀል የተከሰሰች ሴት በወንጀሉ ጥፋተኛ ተብላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በመኖራቸዉ፣ በተለይም ጥፋቷን በማመኗና የወንጀሉን ዉጤት እንዳይደርስ ለማድርግ ጥረት በማድረጓ ቅጣቱን በማቅለል በአንድ ዓመት ቀላል እስራት እንድትቀጣ ፍርድቤቱ ወሰነባት፡፡ አፈጻጸሙን ግን ለመገደብ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀረ፡፡ በቅጣት ሃሳብ ጊዜ ተከሳሿ አምስት ህጻናት ተማሪ ልጆቿን ለብቻዋ የምታሳድግ መሆኗን ገልጻ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት የልጆቿን ጉዳይ መልክ ለማስያዝ እንድትችል ወደማረሚያቤት ከመግባቷ በፊት ጊዜ እንዲሰጣት ጠየቀች፡፡

*የችሎቱ ዐቃቤህግ እርስዎ ቢሆኑ በዚህ ጥያቄ ላይ የሚያቀርቡት ክርክር ምንድን ነዉ? ይጻፉት*

*ዳኛዉ እርስዎ ቢሆኑ የሚሰጡትን ዉሳኔ ይጻፉ፡፡*

## 3.2 አመክሮና ሌሎች የቅጣት አፈጻጸም የሚቋረጥባቸዉ ሁኔታዎች

አመክሮ የቅጣት ማስተማሪያነት ከሚገለጽባቸው ሁኔታዎች አንዱ ነው ማለት ይቻላል፡፡ አንድ ተቀጪ ለፈፀመው ወንጀል የተፈረደበትን የእሥራት ጊዜ ሙሉ በሙሉ ከመፈፀሙ በፊት የተወሰነ ጊዜ በመስጠት ቀሪውን የእስር ጊዜ ከእስር ውጪ ሆኖ እንዲያጠናቅቅ የማድረግ ሥርዓት ነው፡፡ አንድ ተቀጪ በአመክሮ ሊፈታ ይችል ዘንድ በወንጀል ሕጉ የተደነገጉት ቅድመ ሁኔታዎች ሊሟሉ ይገባል፡፡

የወ/ሕ/ቁ 201 በተወሰነ ገደብ በአመክሮ መፈታትን አስመልክቶ መርህ አስቀምጧል፡፡ በአመክሮ መፈታት የተቀጪውን ፀባይ ማሻሻያ እና ወደደንበኛው ማህበራዊ ኑሮ መመለሻ ሆኖ መቆጠር እንደሚገባው ይገልፃል፡፡

በአመክሮ ለመፈታት ይቻለው ዘንድ አንድ ተቀጪ ከተፈረደበት ቅጣት 2/3ኛውን መፈፀም ይኖርበታል፡፡ የዕድሜ ልክ ጸኑ እሥራት ፍርደኛ ከሆነም ሃያ አመት ታስሮ ነው ጥያቄውን ማቅረብ የሚችለው፡፡ በአመክሮ የመፈታት ጥያቄ በተቀጪው ወይም “አግባብ ባለው አካል ለፍርድ ቤቱ ይቀርባል” (የወ/ህ/ቁ 202/1/)፡፡ “አግባብ ያለው አካል” ማነው የሚለውን ሕጉ አይመልስም እንደሚታወቀው በወንጀል ጉዳይ ጥፋተኛ ተብሎ እሥራት የተወሰነበት ሰው የሚቆየው በተለየ ተቋም በመሆኑና የአመክሮ ጥያቄንም ለፍ/ቤት የሚያቀርበው በዚሁ ተቋም አማካኝነት በመሆኑ አግባብ ያለው አካል ይኸዉ ተቋም /ማረሚያ ቤት ወይም ወጣት ጥፋተኞች የሚቆዩበት ተቋም/ ሊሆን ይችላል፡፡

አመክሮን በሚመለከትም ማረሚያ ቤት ስለተቀጪው ፀባይ አጣርቶ ለፍ/ቤት ከሚልከው በተጨማሪ ተቀጪው ለደረሰው ጉዳት በተቻለ መጠን ሊከፍል የሚጠበቅበትን በፍርድ ቤት በተወሰነው መሠረት ወይም ከተበዳዩ ጋር በተደረገ ስምምነት መሠረት ካሣ ለመክፈሉ ማረጋገጫ ማቅረብ እንደሚገባ በአንቀጽ 202(1)(ሀ)(ለ) ላይ ተመልክቷል፡፡

***መለማመጃ 13***

*ሆን ብሎ ከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ፈጽመሃል ተብሎ ተከሶ በአራት ዓመት ጽኑ እስራት የተቀጣ ሰዉ የዚህን ቅጣት ሁለት ሶስተኛ ስለፈጸመ በማረሚያቤቱ አማካኝነት ተከሳሹ በአመክሮ እንዲለቀቅ ማመልከቻ ቀረበ፡፡*

*ዳኛዉ እርስዎ ቢሆኑ የአመክሮን አካሄድ የሚመለከቱ ህጎችን ተንተርሰዉ ተቀጪዉንና የቀረበዉን ጥየቄ አስመልክቶ የሚያደርጉትን ምርመራ በዝርዝር ይግለጹ፣ ምን ምን ነገሮችን ማረጋገጥ እንደሚፈልጉና ይህን ለማድረግ የሚያነሷቸዉን ጥያቄዎች ይዘርዝሩ፡፡*

*ይህን ተቀጪ በመረመሩበት ጊዜ ከተበዳዩ ጋር ዕርቅ ለማድረግ ተሞክሮ ያልተሳካ መሆኑን፣ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ተበዳዩ ብዙ ካሳ ስለጠየቀና ተከሳሹ ይህን ያህል ካሳ ይገባዋል ብሎ ስላላመነ ስምምነቱ ሊደረግ ባለመቻሉ መሆኑን፣ ከዚህ የተነሳ በአሁኑ ጊዜ የጉዳት ካሳ ክስ ቀርቦበት በቀጠሮ እንደሚመላለስ፣ ከእስር ቢለቀቅ የሚጠጋበት ዘመድ የሌለዉ መሆኑን፣ የራሱ ስራም ሆነ መኖሪያ የሌለዉ መሆኑን አረጋገጡ፡፡*

*በዚህ ሁኔታ ተከሳሹን በአመክሮ ይፈቱት እንደሆን ይወስኑ፣ ይጻፉት*

ሌላው በሕጉ ላይ የተመለከተውና በፍርድ ቤቶች ግን ሲተገበር የማይስተዋለው ጥፋተኛው ሲፈርድበት ቅጣቱን ከመፈፀሙ በፊት ቀደም ብሎ ሊለቀቅ እንደሚችልና ይህን እድል ለማግኘት ሊፈጽማቸው የሚገቡ ነገሮች እንደሚገለፁለት የተመለከተው ነው፡፡

አመክሮን በተመለከተ በህግ የተካተተ አዲስ *ሥነሥርዓት* አለ፡፡ ይኸዉም ተከሳሹ ልማደኛ ደጋጋሚ አጥፊ መሆኑ ሲረጋገጥ በአመክሮ አይለቀቅም የሚል ነዉ /የወ/ህ/ቁ 202/2//፡፡ ስለዚህ ፍርድቤት ቅጣት በሚወስንበት ጊዜ በአመክሮ ስለመፈታት ለተከሳሹ ሲነግር በእንዲህ አይነቱ አጋጣሚ የአመክሮ ዕድል እንደማይኖረዉ ሊነግረዉ ይገባ እንደሆነ በግልጽ የተባለ ነገር ባለመኖሩ መወያያ ሊሆን ይችላል፡፡

እንደ ገደብ ውሣኔ ሁሉ በአመክሮ የሚለቀቅ ተቀጪም የፈተና ጊዜ ይሠጠዋል ይህም ማለት በተሠጠው የፈተና ጊዜ ውስጥ ፀባዩ ባይሻሻል ወይም ሌላ ወንጀል ሲፈጽም ቢገኝ (የወ/ህ/ቁ 200 እና 206) በአመክሮ እንዲፈታ የተሰጠው ትእዛዝ ተነስቶ ተመልሦ እንዲታሠር ይደረጋል፡፡ በአመክሮ ቀርቶለት የነበረውን ቀሪ ቅጣትና ለአዲሱ ጥፋት የተወሰነበትን ጊዜ ይታሠራል፡፡

የፈተናው ጊዜ እንደወንጀሉ ክብደት እየታየ የሚሠጥ ነው፡፡ በመርህ ደረጃ የፈተና ጊዜ የሚለው ሳይፈፀም የቀረው የእሥራት ጊዜ ማለትም 1/3ኛው የቅጣት ዘመን ነው፡፡

በአመክሮ ተቀጪው እንዲለቀቅ ፍ/ቤት ሲያዝዝ የፈተናው ጊዜ ቢያንስ ሁለት ዓመት ሲሆን ከአምስት ዓመት የማይበልጥ ነው፡፡ በአመክሮ የመፈታት ዕድል ያገኘው ተቀጪ የዕድሜ ልክ እስረኛ ከሆነ ግን የፈተና ጊዜው ከ5 ዓመት ማነስ እና ከ7 ዓመት መብለጥ የለበትም (የወ/ህ/ቁ 204)፡፡

## ግለ መመዘኛና መወያያ ጥያቄዎች

1. ጥፋቱን አምኗል ተብሎ የተቀጣ ይግባኝ ባይ በጥፋተኝነት ውሣኔ ላይም ይግባኝ ቢጠይቅ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መውሰድ ያለበት እርምጃ ምንድነው?

2. በቅጣት ውሳኔ ላይ ቅጣቱ በዝቷል ተብሎ በቀረበ ይግባኝ ዐ/ሕጉ መልስ ሲሰጥ ፍርድ የሰጠው ፍ/ቤት በሕጉ ከተደነገገው ቅጣት አሳንሶ የቀጣው ስለሆነ ቅጣት ሊጨመርበት ይገባል ቢልና ሕጉም ሲታይ እውነትም በሕጉ ከተደነገገው በታች ሆኖ ቢገኝ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ምን ማድረግ አለበት? ለምን?
3. በወንጀል ይግባኝ ጊዜ ያስቀርባል አያስቀርብም የሚል አሰራር ይቻላል ወይ?
4. የጽኑ እስራት ፍርደኛ በተለይ በእስር ላይ እያለ በፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ስለ መብት መሻሩ ሳይጠቀስ ቢዘለል ለምስክርነት መቆጠር ይችላል ወይ?
5. በገደብ ለመለቀቅ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው?
6. ለተበደለ ወገን ካሳ ያልከፈለ ተከሳሽ በወ/ህ/አ 197/2 መሰረት በገደብ ሊለቀቅ ይችላል ወይ?
7. በገደብ ለመለቀቅ በራስ ዋስትና መፈረም በወ/ህ/አ 197/2 መሰረት በቂ ሊሆን ይ ችላል ወይ?
8. በአመክሮ ለመለቀቅ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች ምንድናቸው?

## <u>አጠቃላይ የመወያያ ሃሳቦች</u>

1. በወ/ህ/አንቀጽ 18/2/ ድንጋጌ የተመለከተዉን ወንጀል ይመርምሩ። ይህ ወንጀል በየትኛዉም መንገድ ኢትዮጵያን የሚነካ/የሚመለከት አይደለም። ይህ ከሆነ ከወ/ህ/አንቀጽ 11 ጀምሮ የተዘረዘሩት ወንጀሎች ላይ ኢትዮጵያ ሥልጣን እንዲኖራት የተደረገዉ ወንጀሎቹ በአንድ መልኩ ወይም በሌላ ኢትዮጵያን ስለሚመለከቱ በመሆኑ ይህን ከሃገሪቱ ጋር የሚያገናኘዉ ምንም ነገር የሌለዉን ወንጀል የመዳኘት ሥልጣን በህግ መስጠት ከምን ትንታኔ የሚነሳ ይመስልዎታል?

2. የፌዴራል ፍርድቤቶችን የሚመለከቱ ህጎጋት የፌዴራል ፍርድቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ያላቸዉ በፌዴራል መንግሥት በወጡ ህግጋት መሰረት ወንጀል በሆኑ ጉዳዮች ላይ ነዉ ይላሉ /አዋጅ ቁ 25/1988 ቁ 3 ይመለከቷል/፡፡ከዚህ አንፃር ከፌደራል የዉክልና ስልጣን የሌላቸዉ የክልል ወረዳ ፍርድ ቤቶች እና በአሁኑ ጊዜ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድቤት በተቋቋመባቸዉ አንዳንድ ክልሎች የክልሎቹ ጠቅላይ ፍርድቤቶች የወንጀል ጉዳዮችን የሚያዩበት የህግ መሠረት የላቸዉም፣ ምክንያቱም የወንጀል ህግ የሚወጣዉ በፌዴራል ህግ አዉጪ ነዉ፣ በነዚህ ህጎች መሰረት ሥልጣን ያላቸዉ ደግሞ የፌዴራል ፍርድቤቶች ናቸዉ የሚሉ ወገኖች አሉ። ይህን ክርክር ምን ያህል ይቀበሉታል

3. ነገሩ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን ከሳሽም ተከሳሽም ምስክሮቻቸዉን ይዘዉ እንዲቀርቡ የሚጠይቅ አሰራር ተከሳሹ ቀርቦ ቢያንስ የእምነት ክህደት ቃሉን ባልሰጠበት ሁኔታ ስለሆነ ከተከሳሹ ንጹህ ሆኖ የመገመት መብት አንፃር ያለዉን እንድምታ አንስተዉ ይወያዩ

4. ተከሳሹ ጠበቃ እንደሌለው ገልፆ መንግስት እንዲመድብለት ከጠየቀ ጉዳዩን የያዘዉ ፍርድ ቤት በበኩሉ ተከሳሹ ያለጠበቃ ቢከራከር የፍትህ መጓደል ያጋጥማል ብሎ ካሰበ በመንግስት ወጪ ጠበቃ ይመድብለታል፡፡ በዚህ ረገድ በተለይም ያለጠበቃ መከራከር የፍትህ መጓደል ሊያስከትል የማይችልበት አጋጣሚ አለ ብሎ መከራከር ይቻላል ወይ በሚለዉ ላይ ይወያዩ

5. ክስ ማንሳት በአሁኑ ጊዜ ገደብ ያልተደረገበት በመሆኑ ወይም የነበሩበት ገደቦች የተሻሩለት ሂደት በመሆኑ የክስ ማንሳት ጥያቄ በዐቃቤህግ ሲቀርብ ፍርድቤቶች ሊቀበሉት የሚገባ ይመስላል፡፡ ሆኖም በዚህ ጊዜ የክስ ማንሳቱ ተግባር በተከሰሰዉ ሰዉ ላይ የሚያስከትላቸዉ የመብት ጉዳቶች ይኖሩ እንደሆን ፍርድቤቶች ሊመረምሩ እና የክስ ማንሳት ጉዳይን ሊፈቅዱ ወይም ሊከለክሉ ይችሉ እንደሆነ ይወያዩበት፡፡

6. ዳኞች በምስክር መስማት ጊዜ ጥያቄ የመጠየቅና እዉነቱን የመመርመር ሥልጣን አላቸዉ፡፡ ከሕጉ አነጋገር ተነስተን ዳኞች ምን ዓይነት ጥያቄ ማንሳት እንዳለባቸው ብንመረምር ሕጉ የሚለው "ማናቸውንም" ጥያቄ ነው:: በተግባር ያለው አካሄድ በተለይ ያለጠበቃ የሚከራከሩ ተከሳሾች የዋና ጥያቄ ምንነትና እንዴት እንደሚቀርብ ባለማወቃቸው ወደ ማዘበራረቅ ስለሚገቡ ዳኞች ራሳቸው ዋና ጥያቄ ሳይቀር ሲጠይቁላቸው ይታያል:: ይህ ምን ያህል ተገቢ ነዉ? የገለልተኝነትን መርህ አይጥስም?

7. የፈረደው ፍ/ቤት ወይም ማረሚያ ቤቱ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈው በእነሱ ምክንያት መሆኑን ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ካረጋገጡ የይግባኝ ማስፈቀጃ እንዲቀርብ ማድረግ ብዙም ትርጉም ያለው አይመስልም፡፡ ከዚህ አኳያ በሚከተሉት ላይ ይወያዩ

- *የይግባኝ ማመልከቻዉ መጀመሪያ የሚቀርበዉ ፍርዱን ለሰጠዉ ፍርድቤት እንደመሆኑ ይግባኙን አልቀበልም የሚለዉ ፍርዱን የሰጠዉ ፍርድቤት ነዉ? ስለዚህ ይህ ፍርድቤ ነዉ ይግባኙ በጊዜ አለመቅረቡንና ምክንያቱን መርምሮ ዉሳኔ የሚሰጠዉ ወይስ ሌላ ፍርድቤት? ሥነሥርዓቱስ?*

- *ይግባኙ ተቀባይነት አግኝቶ የሚቀርብ ቢሆን ለመልስ ሰጭዉ መቼ ነዉ ቅጂዉ የሚደርሰዉ? እንደ ሥ/ሥ/ቁ/ 187/4/ ለፈረደዉ ፍርድቤት እንደቀረበ በዚሁ ፍርድቤት የመዝገብ ሹም አማካይነት ወይስ በይግባኝ ሰሚዉ የመዝገብ ሹም?*

8. በወንጀል ይግባኝ ጊዜ ፍርድ ለማገድ ይግባኙ ያስቀርባል አያስቀርብም የሚል ዉሳኔ እስኪሰጥ ድረስ መቆየት የግድ ያስፈልጋልን? የፍትሃብሄር ዉሳኔ የሚታገድበትን ሁኔታ ከሚገዙት የፍትሃብሄር ሥነሥርዓት ህግ ድንጋጌዎች ቁ

332-336 አኳያ ይወያዩበት፡፡ በወንጀል ይግባኝ ያስቀርባል አያስቀርብም የማለት ሂደት አስፈላጊነት ላይም እንዲሁ

9. በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 202/3/ እንደተደነገገዉ ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠዉን ፍርድ ቀሪ ለማስደረግ የሚቀርበዉን ማመልከቻ

*‹‹…ፍርድ ቤቱ ሳይቀበል ቀርቶ ዉድቅ እንዲሆን በመወሰኑ* ይግባኝ ማለት አይቻልም፡፡ ነገር ግን ስለተፈረደበት ቅጣት ብቻ ማመልከቻዉ ዉድቅ እንዲሆን ከተወሰነበት ቀን እንስቶ በአስራአምስት ቀን ጊዜ ዉስጥ ይግባኝ ቢል አይከለከልም፡፡››

የይግባኝ ክልከላዉ ማመልከቻዉን በሚመለከት በተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ብቻ ነዉ ወይስ በዋናዉ ፍርድ ላይ ጭምር ነዉ?